“በበዳይ ተበዳይ ታሪክ”

የተማገረው የኢትዮጵያ ፖለቲካ

የአማራ ህልውና

የኦሮሞ-አማራ ግንኙነት
















ሳልሳዊ ደነቀ ተሰማ

ማውጫ

ማውጫ 1
አጽርዖት 3
ምዕራፍ አንድ፡ መግቢያ 3
ክፍል አንድ፡ ጥቅል ዳሰሳ 3
ክቡር ውሸት (Noble Lie) 9
የተዋረደ ውሸት (Bad lie) 11
ኢትዮጵያ ክቡር ውሸት አላትን? የተዋረደስ? 12
ምዕራፍ ሁለት፡ አማራነት በዘመናዊት ኢትዮጵያ 15
አማራነት 15
አማራ በጣሊያን ወረራ ወቅት 17
አማራ በጣሊያን ወረራ ማግስት 20
“የሶሻሊስታዊ ተራማጅ” ብሄርና የብሄር ጭቆ 21
የደርግ አገዛዝ 26
የህወሃት/ኢህአዴግ የፖለቲካ ካርድና የአማራ የበላይነት ትርክት 29
አበቃቀሉ የተዛነፈ ጽድ 30
የአስተሳሰብ መዛነፉ በመንግታዊ ስርዓት መካተትና የአማራ ህልውና 33
የአማራ የበላይነት ነበረ? የአማራ መንግስትስ? 36
ምዕራፍ ሶስት፡ የአማራ ህዝብ የመደራጀት፣ የውክልናና የማህበረ-ኢኮኖሚ ፈተናዎች 39
ስርዓት ወለድ ማዕቀብ 40
የፕሮፌሰሩ መንገድ 45
የአማራ ማህበረ-ኢኮኖሚ ገጽታ 47
የህዝብ እድገት ምጣኔና የህዝብ ቁጥር 52
የህዝብ ቁጥር ቅነሳ ሳይንሳዊ አመክኖዎችና የአማራ ህዝብ 56
ኢኮኖሚያዊ፡ አማራ በሲቪል ሰርቪስ 59
ስርዓት መራሽ ፍረጃዎችና የእለት ከእለት የአማራ ልጆች ህይወት 62
የአማራ ጉዳይ በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን 65
የአማራ ጉዳይ አይመረመርም 68
ምዕራፍ አራት፡ የአማራ-ኦሮሞ ፖለቲካና የሰለሰችው ካርድ 71
በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የሁለቱ ህዝቦች ታሪክ 75

የበዳይ ተበዳጥ ታሪክ፡ የአማራና የኦሮሞ ህዝቦች ግንኙነት 77
የበዳጥ ተበዳይ ታሪክና የዛሬ ሃውልታችን ፖለቲካዊ አንድምታ 87
“የአማራ-ኦሮሞ ልሂቃን የሚጋጩ አልሞች”? 91
የነገ ሃውልቶቻችን ገጽታና እንድምታ 96
የኢትዮጵያ ስርዓቶችና የወቅቱ የአማራ ህዝብ እምቢተኝነት 98
የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግስት የማነው? 100
የአማራ ህዝባዊ እምቢተኝነት (ቁጣ) እና ወልቃይት 102
የአማራ ህዝባዊ ቁጣ ለምን? 102
የ2008 ዓ.ም. አማራ ህዝባዊ አመጽ በወፍ በረር 103
የአማራ ቁጣና እምቢተኝነት ፋይዳ 109
ወልቃይት፡ የወልቃይት ህዝብ የጥያቄ ይዘትና ታሪካዊ ዳራው 115
የወልቃይት ታሪካዊ ዳራ፡ የታሪክ ማስረጃዎችና ማህበራዊ እሴቶች 120
ስነ-ጥበብ ይናገርል 125
ወልቃይት የትግራይ ነው 127
የወልቃይት የማንነት ጥያቄ ታፍኖ ግጨውና ጎቤ ድርድር ለምን? 130
ከወልቃይት ባሻገር፡ የአማራ መሬት እጣ ፋንታ 132
የወልቃይትና የአካባቢው የአማራ ችግር የመፍትሄ አማራጮች አሉትን? 139
ምዕራፍ አምስት፡ መደምደሚያና ምክረ-ሃሳቦች 143
መደምደሚያ 143
ምክረ ሃሳብ 148
ዋቢ መጻህፍቶች 150

አጽርዖት

ኢትዮጵያዊያን ሳያሰልሱ ዘብ የቆሙላቸው ብዙና ገናና የፊልም ትወና የሚመስሉ ነገር ግን እውነት የሆኑ ታሪኮች ስለመኖራቸው የኢትዮጵያ ታሪካዊ ባላንጣ የሆኑ አካላት ሳይቀሩ ያረጋገጡት ሃቅ ነው። እንዳለመታደል ሆኖ ሃገሪቱ ያልበሰለ የፖለቲካ ስርዓት ሰለባ በመሆኗ ስለታሪኳ መጉደፍ መቆርቆር የሚገባቸው የፖለቲካ መሪዎቿ ተቆርቋሪዎቿን የሚያቆረቁዙ፤ በሚመቻቸው መልኩ የታሪኳን ይዘት፣ መጠን፣ እና ስያሜ በማዛባትና በመለዋወጥ የተጠመዱ ሆነዋል። የአጼዎቹ ስርዓት ታሪክ ጸኃፊዎች የንጉሱንና የንጉሳዊያኑን ቤተሰብ ልዕልናና ገድል የሚያወድሱ ታሪኮችን ይሰሸኑ እንደነበረው ሁሉ በደርግ ዘመን ስለአብዮቱ እንዲተረክና በሶሻሊስት ሃገራዊ ርዕዮት የተቃኘ ታሪክ እንዲጻፍ እንዲሁም ሁሉም ዜጋ ካኪ ለባሽ እንዲሆንና ታሪካችንም የካኪ ለባሾች ታሪክ ሆኖ እንዲቀረጽ ተደርጎ እንደነበር አይካድም። "...ላለፉት ከሁለት አስርት አመታት በላይ ታሪክን መጻፍ ማለት የበደለኝነትን ስሜት ማሸከም ማለት ሆኗል" (በዕውቀቱ፣2008፡9)። ከታሪክ ጸብ ውስጥ የገቡ የትላንትና የዛሬ የሃገር መሪዎች የስኬት ሁሉ ምንጭ ነን በሚል ጥልቅና የተዛባ እምነት (illusion) ውስጥ በመዘፈቅ እና ከልክ በላይ የራሳቸውን ታሪክ የማፍቀር (obssession) ዝንባሌ ስለሚያሳድሩ ያለፈውን ታሪክ የማጣጣል ብሎም በውሸት ትረካ የተጠመዱ ሆነዋል። የሃገርን የግዛት አንድነት የማያናጉ እርመጃዎችን የሚወስዱ፤ የማህበረሰቡን ተቻችሎና ተፋቅሮ የመኖር ታሪክና ብሂል እንዲረሳ ጥቃቅን ልዩነቶችንና የልዩነት ምንጮችን አግዝፎ በማሳየት ስራ ላይ የተጠመዱ ልሂቃን የሚፈለፍል ስርዓት መንስራፋቱ እውነት እንድትደበዝዝ በምትኩ በእውነት የተቀቡ ከፋፋይ የታሪክ መዛግብቶች እንዲበረክቱ አስተዋጽኦ አድርጓልም። የፖለቲካ ቡድኖች ወይም በባሌም በቦሌም በአገሪቱ የአስተዳደር ቁንጮ ላይ የሚገኙ ልሂቃንና የኅበዝ አለቆች የሃገርን ታሪክ አዛብተው ለመተረክ ለሚተጉ ወይም አዛብተው ለሚጽፉ ድጋፍ የሚያደርጉ በመሆኑ ድርጊታቸው ከራሱ ጀርባ መደበቅ እንደሚመኝ የአዕምሮ ታማሚ ወይም በጠራራ ጸሃይ ከራሱ ጥላ ከሚሸሽ ህጻን የሚያመሳስላቸው ሆኗል። ያም ቢሆን አንድ እውነት ብዙ የሃሰት ክምሮችን ታፈርሳለች፤ ታሪክ የህዝብ ነው፤ ህዝብ በምስክርነት አለ። ለጊዜው ህዝብ ለምስክርነት እንዳይበቃ መሰናክሎች ቢበዙም የሃሰት ክምሮችን ማፍረስ የሚያስችሉ የእውነት ተራሮዎች ባለቤት ነው። ለጊዜው በአርማታ ጫካ ውስጥ የሚኖሩ የኅበዝ አለቆች በየደሳሰው ጎጆዎች የሚኖሩ ሚሊዮኖች የሚጠብቋትን እውነት ለመጋፈጥ የሚያስችል የአመክንዮ መስተካከል ስለማይኖራቸው በሚሊዮኖች ላይ ፍራቻን ይነዛሉ፣ ሰይፍም ይመዛሉ። ያም ቢሆን አሁንም እውነት በሚሊዮኖች ጥበቃ ስር ናት፤ ለእውነት ዘብ የሚቆም ትውልድም እየቀጠለ ነው። አዲሱ ትውልድም በደልን አልሸከም ባይነቱ ወኔን አንግቦ እርቅን በመናፈቅ የተሳተውን የእውነት መንገድ መከተል መሻቱን አላቋረጠም።

ምዕራፍ አንድ፡ መግቢያ

ክፍል አንድ፡ ጥቅል ዳሰሳ

የዘመናዊ ኢትዮጵያ ታሪክ ከአጼ-ቴወድሮስ፣ ከአጼ ዮሃንስ አራተኛና ከዳግማዊ ምኒልክ የንግስና ታሪክ ጋር የተያዘነው። የአመሰራረት ሂደቱ ከአጼ-ቴወድሮስ አንድነትና ውህደት ጂማሮ፣ ከአጼ

ዮሃንስ አራተኛ ሂደቱን የማጠናከር ጉዞና ከአጼ ምኒሊክ ውህደትን ከማጠናቀቅ የታሪክ ጉዞ ጋር ትስስር አለው፡፡ ዳግማዊ ምኒልክ ብዙውን የዘመናዊ ኢትዮጵያን አመሰራረት እውን ከማድረጋቸው ጎን ለጎን የኢትዮጵያ ህዝቦች በህብረት ቅኝ ገዢ ወረራን በመመከት ሂደት አድዋ ላይ የደም ቅልቅል እንዲያደርጉ አስችለዋል፡፡ ይች በኢትዮጵያዊን ህብረት የተገነባች ሃገር ከቀድሞው በተሻለ የሃያልነት ቁልፍ ተረክባም ነበር፡፡ ከአድዋ ጦርንት መለስ ኢትዮጵያ የተጎናጸፈችው ክብርና የመደራደር አቅም ብሎም የዘመኑ ንጉስ ‹‹አንጻራዊ የዲፕሎማሲ ልዕልና አንዱን አውሮፓዊ ሃገር ለሌላቸው መመከቻ››[1] በማድረግ ሃገሪቱ በዙሪያዋ ካሉ ቅኝ ገዢ ሃገራት ጋር የድንበር ማካለል ልታደርግ በቅታለች፡፡ ከሞላ ጎደል የዛሬዋን ኢትዮጵያ ለመመስረት እ.ኤ.አ በ1897 ከፈረንሳይ ጋር የኢትዮ-ጂቡቲ ድንበርን፤ በ1902 ከእንግሊዝ ጋር የኢትዮ-ሱዳን ድንበርን፣ በ1907 ኢትዮ-ኬንያ ድንበርንና በ1908 የኢትዮ-ብሪቲሽ ሶማሊላንድ ድንበርን፤ እና ከጣሊያን ጋር በ1908 የኢትዮ-ኤርትራ ድንበርን እንዲሁም የኢትዮጵና ኢጣሊያ-ሶማሊላንድ ድንበርን (በዚህኛው ስምምነት ውል በቃልና በጽሁፍ ሆኖ የማታለል አይት ባህሪ ነበረው) ማካለል ችላለች፡፡ ሆኖም ከእነዚህ ስምምነቶች ኋላ ላይ የ1908ቱ ሰምምነት በሁለት ምክንያቶች (በአለም አቀፍ የስምመነቶች ህግ መሰረት) ተሰርዟል፡፡ ይህም መጀመሪያ “በ1928 ዓ.ም. ስምምነቱን በመጣስ ጣሊያን በኢትዮጵያ ላይ ወረራ በማድረጓ”[2]፤ ሁለተኛ እ.ኤ.አ. በ1952 በተደረገው “የኤርትራ በፌደሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር ለመተዳደር በተደረገው ስምምነት”[3] መሰረት ነው፡፡

ከዳግማዊ ምኒልክ ሞት በኋላ ይህችን አፍሪካዊት ነጻ የህብረብሄር ሃገር ለማስተዳደር የተረከቡት ልጅ እያሱ ሚካኤልና ንግስት ዘውዲቱ ከውጭም ሆነ ከሃገር ውስጥ የጎላ ጫና ሳያስተናግዱ በዲፕሎማሲውም ረገድ በምኒልክ የተሰራችውን ኢትዮጵያ ለአጼ ሃይለስላሴ አስረክበዋል፡፡ አጼውም ስልጣን ተረክበው ብዙ ሳይቆዩ በጣሊያን ወረራ ምክንያት ለአምስት አመታት በውጪ ቆይተው ጣሊያን በመሸነፉ ከተመለሱ በኋላ ረጅሙን የሶለሞናዊ ሰርዎ መንግስትን ስልጣን አስቀጥለው በ1965 ዓ.ም. በደርግ ወታደራዊ መንግስት ከዙፋን በመሰናበታቸው የስርዓቱ ግብዓተ መሬት ሆነ፡፡ አቢዮት ፈነዳ፤ የህዝብ ንቅናቄዎችንና

[1]“Menelik's diplomatic genius is of tencited as a major reason for his strong stature in the eyes of the European powers. More important in this regard was, perhaps, his Adwa victory; that event seems to have enhanced the standing of Menelik and his country in the international arena, frustrated the ambition of the European powers to colonize Ethiopia, and forced them to conclude boundary treaties with him” (ibid, 1993:5).

[2]በሁለትዮሽ ስምምነት አንዱ አንዱ ውል ፈራሚ የስምምነቱን ድንጋጌ የመጣስ ተግባር ከፈጸመ ሌላኛው አባል በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ከውሉ የመውጣትና ውሉ ተፈጻሚ እንዳይሆን የማድረግ ህጋዊ መሰረት ስለሚኖረው (እኤአ የ1969 ቬና ስምምነት፡ የአለም አቀፍ ውሎች ህግ አንጽ 60 (1))፡፡

[3]በጉዳዩ ላይ ሌላ ውል ሲፈጸም የቀድሞው ውል ተግባራዊነት ስለመቋተጡ/ስለመቆመ/(ዝኒ ከማሁ፤አንጽ 59)፡፡

ተቃዎሞዎችን ሁሉ በሃይል በማስተናገድ የተጠመደው የደርግ ስርዓት ከከተማ አስከ ገጠር የገጠሙት ተቃዎሞዎች መባባሱና ይከተለው የነበረው የተዛባ የውጪ ፖሊሲ ታክሎበት በ1983 ዓ.ም. ሃገሪቱ በነጻነት ታጋይነት በተሰለፉ የብሄር ፖለቲካ አራማጆች እጅ እንድትወድቅ አድርጓታል። ወቅቱ የደርግ ስርዓት መጨረሻ የኢትዮጵዊነት (pan-ethiopiansit) አቀንቃኞች- በተለይ ከአማራው ብሄር አብራክ የተገኙ ልሂቃንና ህዝቡ የግፍ ዘመን ከፍታ መጀመሪያ ሆነ። እንሆ ዛሬም በ1983 ዓ.ም. ከወታደራዊ መንግስቱ ስልጣን የተረከበው የነጻነት ታጋዮች ስብስብና ግንባር ሃገሪቱን እያስተዳደረ ሲሆን የዚህ ጽሁፍ ዋነኛ ትኩርትም የዚህኛው ስርዓት ብሄር ተኮር ፖለቲካዊ ሂደትቶች ከአማራ-ኦሮሞ ህዝብ ግንኙነት፣ ከአማራ ህዝበ ማንነትና ህልውና ጋር የሏቸውን መስተጋብሮች ታሪካዊና ወቅታዊ ማስረጃዎችን በማጣቀስ መተንተን ነው።

ከ1983 ዓ.ም. ወዲህ የተደረጉ ለውጦችና አዲሱ ፖለቲካዊ ተክለ-ቁመና በሃገሪቱ ያሉ ብሄር ብሄረሰቦችን ግንኙነት፣ የሃገሪቱን የመደራደር አቅምና የኢኮኖሚ ገጽታን፣ የአካባቢውን ፖለቲካዊ ሁኔታ፤ የዲፕሎማሲያዊ አሰላለፍና ሌሎች መስተጋብሮች እንዲለወጡ ምክንያት ሆኗል። ይህን ለውጥ ተከትሎ የታሪክ ገጽታና ትንታኔያችን ከስርዓቱ ለውጥ ጋር ተያይዞ ሃገሪቱ ያጣቻቸውን ቁሳዊና ስነ-ልቦናዊ ሃብቶች ምንነት ለማሳመን የሚቀርቡ የቀድሞ ታሪኮች እንዲሁም የታሪክ ማስረጃዎች በአዲስ መልክ የመጻፍና የማስተማር ድፍረት ያላቸው ፖለቲከኞች ተደራጅተው እንዲሰማሩ ሁኔታዎች ፈቅደውላቸዋል። ስርዓቱ ከሃቁ የራቁ ትረካዎችም እንደታሪክ እንዲነገሩ መንገድ ከፍቷል። ለማብራራት ያህል የስርዓቱ ለውጥ የወለዳቸው ከእውነታ ያፈነገጡ ማብራሪያዎች እየቀረቡ ስለመሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ለአብነት በጉዳዩ ላይ እውቀት ካላቸው ጸሃፊዎች አንዱ እንደሚሉት የስርዓቱ ቀያሽ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊና መንግስታቸው የሚያቀርቡት የታሪክ ማስረጃና የሚሰነዝሩት ሃሳብ “ሃሰት ወይም ያልነበረን ታሪክን በመፍጠር”[4] ነበር። አቶ መለስ ዜናዊ ኤርትራ በኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ወድቃ ነበር የሚል እምነታቸውን በማራመድ ኤርትራ ከእናት ሃገር

[4] …መዋሸት በራሱ ያስነውራልና ነው! ዘሬ ቅኝ ገዢነቷ ሲተረክላት እየሰማን ነው፤የሚያሳዝነውና የሚያስገርመው ጉዳይ በጭራሽ ያልነበረን ታሪክ እየፈጠሩ የአንድ ሃገርና ህዝብ ብሄራዊ ማንነት፣ ክብረ ህሊናና መልካም ስም እንዲህ ማጉደፍና ጥላሸት መቀባት መቻሉ ነው።… ኢትዮጵያ ቅኝ ገዢ ናት ብሎ የሚያምን ፣ኢትዮጵያን መዳከምና ጤና ማጣት በአይናቸው ለማየት የሚፈልጉትን የውጪ ሃይሎች ህልም ከግብ ለማድረስ ቆርጦ የተነሳ፣ ይህ ሃገር ስለክብሯና አንድነቷ ብርቱ ሆኖ ለኖረችበት ዘመን ሁሉ ቅታት ትቀበል ዘንድ አንገቷን በሰንሰለት አስሮ እጅግ ውድ የሆነውን የስትራቴጂ፣ የኢኮኖሚ፣የታሪክና የክብር ዋጋ እንድትከፍል የባህር በሯን፣ ወደቦቿና ደሴቶቿን፣ ዜጎቿንም ጭምር ለሌላ ባለጊዜ አሳልፋ እንደትሰጥና በየአመቱ ብዙ ቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ ለወደብ ኪራይ እንድትገብር ያደረገ ሰው ምን ተብሎ ይጠራ ይሆን?! (አስራት አብርሃ፣2006 ዓ.ም.፡ ከገጽ 40-41)።

ኢትዮጵያ እንድትገነጠል በማድረጋቸው በኢትዮጵያ ዳር ድንበር ላይ፤ በኢትዮጵያዊን የኢኮኖሚና የመደራደር አቅም ላይ፣ በአካባቢው ጸጥታና በሌሎች ቁልፍ መስተጋብሮች ላይ ለውጥ አምጥተዋል። ለአብነት በመልከዓ-ምድር አቀማመጥ ረገድ አዲስ ጎረቤትና አዋሳኝ ሃገር "ኤርትራ" መፈጠር፣ የግብጽ አዋሳኝ ሀገርነት ማክተም፣ የኢትዮጵያ ወደብ አልባነትና የባህር በር መነፈግ ጉልህ ኩነቶች ሲሆኑ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የኢትዮጵን የኢኮኖሚ ገጽታና የመደራደር አቅም በተለይ ከባህር በር ጋር ተያይዞ ዝቅ ያለበት ሁኔታ ተከስቷል። የጅኦግራፊያዊ ለውጡ ሃገሪቱ በጎረቤት ሃገራት ላይ ጥገኛ ስላደረጋት የወደብም ሆነ የወታደራዊ ስትራቴጂ ባለቤትነቷን ተነጠቀች። የዛሬዎቹ የኢትዮጵያ ልጆች ስለዳህላቅ ደሴቶች ታሪክና እንዳይሰሙ ተደርገዋል።

የአካባቢውን ፖለቲካና የጸጥታ ጉዳይ ስናይ አዲሲቷ ሃገር ኤርትራ ከሱዳን፣ ከየመን፣ ከጂቡቲ የፈጸመችው ግጭትና ትርጉም አልባ የሆነው የኢትዮ-ኤርተራ ጦርነት ብሎም የኢትዮጵያና የኤርትራ መቋጫ ያጣው ፍጥጫ፣ መወነጃጀል ባስ ሲልም የእጅ አዙር ትንኮሳና ጦርነት በ1983 ዓ.ም. በለስ ቀንቶች ስልጣን ከተቆጣጠረው የነጻነት ግንባሮች መንግስት ከመሆናቸው ጋር ቀጥተኛ ትስስር አለው። በሌላ በኩል የስርዓት ለውጡ የኢትዮጵያን ዲፕሎማሲና ትብብር በተመለከተ የራሱ ፋይዳ ያለው ሲሆን የምዕራባዊያን መንግስታት የፖሊሲ ማስተካከያ ውሳኔ እንዲያሳልፉ በማስቻል በልማት አጋርነት፣ በገንዘን ልገሳ፣ በወታደራዊ ዘርፍ ትብበሮችን እንዲተገብሩ አድርጓ። የአረብ ሃገራትም በአፍሪካ ቀንድ አዲስ አጋር እንደያገኙና ተጽኖ ፈጣሪነታቸው እየጎላ እንዲመጣ አስችሏል።

በሃገር ውስጥ ፖለቲካ በብሄረሰቦች ጉዳይና ግንኙነት ላይም ብዙ ለውጦች ተስተውለዋል። በፖለቲካው ዘርፍ የመወዳደር አቅማቸው እምብዛም የሆኑ የብሄር አለቆች የብሄር ፖለቲካውን ስኬት ለመቀዳጀት ዋነኛ ስልት የማድረግ እንቅስቃሴ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ፋሽን ሆኗል። ይህን ጉዳይ በውል የተነተነው በዕውቀቱ ስዩም (2008 ዓ.ም.) "አንባቢን ሆይ የብሄር ፖለቲካ ወፍራም እንጀራ ካላወቅህ ተሸውደሃል፤ በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች የብሄር ፖለቲከኞች ሱቅ ናቸው" ይለናል። የበዕውቀቱ አገላለጽ በማያከራክር መልኩ እውነትነት አለው። ውስን ከህዝብ ፍላጎ የመነጩ የማንነት ጥያቄዎች ቢኖሩም በብሄሩ ልሂቃን ውትወታና ከማህበረሰቡ ፍላጎት ውጭ የሆኑ አካላት የራሳቸውን እንጀራ ለመጋገር የሚቀሰቅሷቸው የማንነት ጥያቄዎች በተለያዩ የሃገሪቱ ክልሎች ተነስተዋል። ገና ከጅማሮው በመንግስት ባለስልጣናትና ወኪሎቻቸው ተከሽነው በሚወጡ የበዳይ ተበዳይ የታሪክ አስተምሮዎች፣ የታሪክ

ሽሚያና የቀድሞ የታሪክ አሻራዎችን የማደብዘዝና የጋራ ማንነትን የማጥላላት ስራዎች ተሰርተዋል። በበዳይ ተበዳይ የታሪክ አስተምሮዎች ቆስቋሽነት የብሄር ግጭቶችና መፈናቀሎች ተስተውለዋል። በዋነኝነት ብሄርን መሰረት ያደረገ የፌደራላዊ ስርዓትም መስፈኑ ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት የለውጡ አንኳር ጉዳይ ነው።

ኢትዮጵያ ከግንቦት ሃያ የግራ ዘመሞች ድል በኋላም የመልካም አስተዳደር እጦት፣ ከፋፍሎ የመግዛትና እርስ በርስ የማናቆር ታክቲክ የመረጡ የፖለቲካ ልሂቃን እንደአሸን የፈሉባት ሃገር ሆናለች። በዋናነት የአማራን ህዝብ "ትምህኪተኛና ነፍጠኛ" የሚል ስም በመስጠት ከሌላው ማህበረሰብ የማናከሱ ስራ ብዙ ተኪዶበታል። የኦሮሞንና የአማራን ልሂቃን የጠላትነት ታሪክ በመስበክ በጎሪጥ እንዲተያዩ በማድረግ ከፋፈሎ የመግዛቱን ታክቲክ ውጤታማ እንዲሆን እየተሰራም ይገኛል (ዛሬ ላይ ውጠየታማነቱ መቀነሱ የሚዘነጋ አይደለም)።

ስለሆነም ይህ መጽሃፍ ከላይ የተገለጹትን የሃሳብ መንደርደሪያዎች መነሻ በማደረግ የተቀረጹ ጥቅልና እርዝር አላማዎች ያሉት ነው። ዋናው የመጽሃፉ አላማ በኢትዮጵያ የተዘረጋው ብሄር ተኮር የፖለቲካ ስርዓት የአማራን ህዝብ እንዴት ያየዋል የሚለውን ጥያቄ በመመለስና የአማራ ብሄር ከሌሎች የሃገሪቱ ብሄረሰቦች በተለይም ከኦሮሞ[5] ብሄረሰብ ጋር በሚኖረውና ባላው ግንኙነት ላይ ስርዓቱ ምን ሚና እንደነበረው/እንዳለው ታሪክ ቀመስ ፖለቲካዊ ትንተና ማድረግ ነው። በዝርዝርም የአማራ ህዝብ በስርዓቱ "የፖለቲካዊ የችግር ትንተና" የተሰጠውን ድርሻ መፈተሽ፣ በፖለቲካው ስርዓቱ መነሻነት በአማራ ህዝብ ላይ አሉታዊ ጫና ያሳደሩ የፖሊሲ አቅጣቻውን መመርምር፣ ችግሮች ካሉ በምን አይነት የፖለቲካ ስልት መቋቋም እንደሚቻል ማመላከት፤ የአማራ ህዝብ መደራጀትን የሚገቱ ወይም የገቱ የስነ-ልቦናና ቁሳዊ ሁኔታዎን ማጥናት፣ እንዲሁም የተዛነፉ የታሪክ አተያዮችን መፈተሽና ጤናማ የፖለቲካ መስመር የሚነደፍበትን አግባብ ማመላከት ነው። በተጨማሪም በስርዓቱ የአማራና የኦሮሞ ህዝብ

[5]በዚህ ጽሁፍ የሁለቱ ብሄሮች (የአማራና ኦሮሞ) ጉዳይ ትኩረት ያገኘበት ምክንያት የሁለቱ ብሄሮች መስተጋብር የላቀ መሆኑና በአብሮነታቸው ላይ የተጋረጠው ስርዓታዊ ችግር ጥልቅና መጠነሰፊ መሆኑ ነው።ሁለት ብሄረሰቦች በሀገሪቱን ህዝብ ከስድሳ አምስት በመቶ በላይ የሚሸፍኑ እንደመሆናቸው የሚያበረክቱት አስተዋጽዖ በዚው ልክ ሰፊ በመሆኑ እንዲሁም በርካታ እሴቶች የሚጋሩ በመሆናቸው እርስበርሳቸው የሚፈጥሩት መስተጋብርም ፈርጀ ብዙ መሆኑንም ልብ ይሏል። የህዝቡ መጎራበት የባህል መወራስን፣ ሃይማኖትና ሌለች ተዛማጀ ሰብአዊ ማንነቶችን ይጋራሉም። ከላይ እንደተገለጸው ከ1983 ዓ.ም. ወዲህ ከተዋቀረው የአማራ ክልል ውጪ ብዙ የአማራ ህዝብ የሚኖረው በኦሮሚያ ክልል ነው። ይህም አዲስ አበባን ሳይጨምር ሁለት ሚሊዮን አማራ በኦሮሚ ክልል ይኖራል። የኦሮሞን ህዝብም ከኦሮሚ ክልል ውጭ በብዛት የሚኖረው በአማራ ክልል ሲሆን በዞን ደራጃ ራሱን እያስተዳደረ መሆኑም ይታወቃል። ይህ መስተጋብር እንዳለ ሆነ ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ ስርዓት ወለድ መቆራቆስና በተለይም በኦሮሚያ አካባቢዎች የአማራ ህዝብን መጨፍጨፍ/ሞት/፣ መፈናቀል፣ መደህየት ያስከተሉ ኩነቶች እየተከሰቱ ቆይተዋል። በመሆኑም የህዝቦችን ግንኙበት መሻከር መንስኤና ለችግሮች የማስተካከያ አቅጣጫን አመላካች ጥናት ማድረጉ አስፈላጊ እንዲሆን ያደረገዋል።

ግንኙነት ምን አይነት ይዘት እንዳለውና ያስከተለው ውጤት ብሎም ለውደፊቱ በሃገሪቱ ፖለቲካ ውስጥ የሁለቱን ህዝቦች የወንድማማችነት መንፈስ ለማጠናከር መሰናክል የሆኑ ፖለቲካዊ ተግዳሮቶችን መዳሰስ፣ የአማራ ህዝብ በማንቱ ላይ የተሰነዘረበት ጥቃት እንዲመክት ምክረ-ሃሳቦችን ማቅረብ የዚህ መጸሃፍ የትኩርት አቅጣጫ ነው።

እንደአጠቀላይ ይህን ጽሁፍ ከላይ የተገለጹትን የፖለቲኮ-ታሪክ መዛባቶችና እያስከተሉት ያለውን የህዝብ ለህዝብ መጠራጠርና በጭቆና ተነጣጥሎ የመገዛት እድልን ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ ግንዛቤ ማያስጨበጥ የሚችል ነው። በዚህ ጽሁፍ ጸረ-ማህበረሰብ ፍረጃዎች ሊስተካከሉ የሚችሉበት ማስረጃዎችን በመቅረብ መሰረተቢስነቱን ከማሳየት በተጨማሪ በአማራ ህዝብና ማንነት ላይ የተፈጸሙና የሚፈጸሙ ዘርፈ ብዙ ግፎችን በወፍ በረር ለማሳየት ይሞከራል። የአማራና የኦሮሞ ህዝቦች ታሪካዊ ወንድማማችነታቸውን መገንባት የሚቻልባቸውን የታሪክ ገመዶችን መጠቆም ታሳቢ ተደርጓል። በተጨማሪው ይህ ጽሁፍ የአማራ ልሂቃን ራሳቸውን አደራጅተው በህዝቡ ህልውና ላይ የተጋረጠውን አደጋ በመመከት ከሌላው የሃገሪቱ ማህበረሰብ ጋር በመተባበር የጋራ ጠላት የሆነውን ጭቆና ጸረ-ኢትዮጵያዊነት የሆነውን ስርዓት በመታገልና የጋራ ታሪካዊ እንድነታቸውን በማጠናከር የተሻሉ ታሪኮችን በማረም ኢትዮጵያን ማጽናት የሚችሉብትን አግባብ አመላካች ነው።

ክፍል ሁለት፡ "የክቡር ውሸት ምንችት ግባ የአፍረሽ ውሸት ጋን ውጣ"

ያች ያፍላጦስ (ፕሌቶ) ሃገር
የፈላስፋ ምናብ
በከበረው ውሸት- አስታርቆ ያነጻት
በነፍስ ክፋይ ተረክ
መሪ አበጅቶ ጠባቂ አቁሞ
ላይጠረቁው መሻት -መንገድ ያጸናባት
ያፍላጦስ ሃገር ውስጥ ሀገሬን ጠየኳት
ውሸትሽ ምነድ ነው?
ኗሪሽ የማያውቀው።
የጸነስሽው ምናብ
ስለኛ በማሰብ።
ና. ሶሎሞን (2008 ዓ.ም.)

የዚች ስንኝ ገጣሚ ናሆም ሶሎሞን ሊነግረን የፈለገው የግሪኩ ፈላስፋ ፕሌቶ በግሪክ ማህበረሰብ የፖለቲካ ስርዓት ስኬታማነት የሚበጅ ውሸት አስፈላጊ ነው ሲል መፈልሰሙን። ውሸቱ ግን የከበረ ውሸት ነው። እናም ገጣሚው በሃገሩ የከበረ ውሸት እንዲኖር በመሻት ሃገሩን የከበረ ውሸት አለሽ ወይ? ሲል ጠይቋል። በመርህ ደረጃ ውሸት ጸያፍ ነው፤ በየትኛውም ማህበረሰብ የሚነቀፍ። ሆኖም ከውሸትም ውሸት አለ፤ አንዱ የከበረ ሌላው ያልከበረ። ያልከበረ ውሸት

ተዋርዶ ያዋርዳል። ውሸት መናገር ስህተትነትም ይኖረዋል፣ ይህም ጸያፍ ውሸት ነው (bad lie)።

ክቡር ውሸት (Noble Lie)

ከላይ ግጥሙ ሊነግረን የፈለገውን የግሪካዊ ፈላስፋ የከበረ/ የተፈቀደ/ ውሸት ምንነት ሲያብራራ ፕሌቶ ዘ-ሪፐብሊክ በተሰኘው ስራው የሚከተለውን ንግግር አድርጓል። "ትርፍ ጊዜያችንን በታሪክ ነጋሪነት እናሳልፍ፣ የምንናገረው ታሪክ ጀግኖቻችንን የሚያሰተምር ይሆናል" በማለት ይጀምራል። ይቀጥላል፡ "ወጣቶች በዚህ ቀረጻ ውስጥ የሚያለፉ ናቸው፤ በቅድሚያ ሙዚቃ ከዚያ የጂምናስቲክ ትምህርት የሚሰጥ ሲሆን ሙዚቃ ስነ-ጸሁፍንም ያካትታል። ስነ-ጽሁፉ እውነትንም ውሸትንም የሚያካትት ነው። ከውሸቱ ብንጀምር፡- የምናስተምራቸው ልብ ወለድ ታሪክ ሙሉ በሙሉ ከእውነት የራቀ አይሆንም። ይህን አይነት ትምህርት የጀምናስቲክ መማሪያ እድሜ ደረጃ ላይ ሲደርሱ የሚሰጥ አይደለም። በትምህርታዊ ቀረጻው ህጻናት የሚነገራቸው ታሪክ በማንኛውም ሰው በየአጋጣሚው የሚተረክ መሆን የለበትም፣ "ሳንሱር ያስፈልገዋል"[6]። "በስነ-ጽሁፍ ለወጣቶች ትምህርት ስናስተላልፍ ትርጉም አልባ እውነቶች አይነገሩም፤ ውሸቶችም የተመጠኑና ሳንሱር የተደረጉ ይሆናሉ"።

"ውሸት" በዚሁ በግሪካዊው ፈላስፋ ስራ ዘ-ሪፐብሊክ (the Republic) "ክቡር ውሸት (Noble lie)" በሚል ስያሜ የፖለቲካዊ ፍልስፍና ተዋስኦ አካል ለመሆን በቅቷል። የፕሌቶ ክቡር ውሸት (Noble Lie) በሪፐብሊኩ (ሪፐብሊክ የሚለውን ሃገራዊ ስርዓት ብለን እንውሰደው) መልካም ግብን ለመምታት ታልሞ ሲዋሽ ነው። በሌላ አገላለጽ መዋሸት የተፈለገው ለቅዱስ አላማ ከሆነና በማንም በምንም ላይ የከፋ አሉታዊ ውጤት የማያስከትል ሲሆን ነው። እንደፕሌቶ የሃገራዊ ስርዓት አካል የሆኑ ሶስት አይነት ማህበራዊ መደቦች ይኖራሉ። ውሸቱ እዚህ ይጀምራል መደቦቹን ከመከፋፈሉ ማለት ነው። መደቦቹ የየራሳቸው መገለጫና ባህሪ ይሰጣቸዋል፣ መደቦቹና የተሰጣቸው መገለጫ ባህሪ በሪፐብሊኩ እንዲሰርጽና እንዲታመንበት ይዋሻል ማለት ነው። መዋሸቱ ያስፈለገም በተተረከው በተጠና አፈታሪክ (myth) መሰረት ዜጎች አምነው ሶስቱም ወሳኝ የሪፐብሊክ አካላት (components) ወይም መደቦች የየራሳቸውን ሚና

[6]"Then the first thing will be to establish a censorship of the writers of fiction, and let the censors receive any tale of fiction which is good, and reject the bad; and we will desire mothers and nurses to tell their children the authorized ones only. Let them fashion the mind with such tales, even more fondly than they mould the body with their hands; but most of those which are now in use must be discarded" (Plato, 1999:53).

እንዲወጡና ለሪፐብሊኩ ስኬታማነት አበርክቶ እንዲኖራቸው ታስቦ ነው። መደቦቹንና መገለጫዎቻቸውን ከታች እንደሚከተለው ይብራራል።

በፕሌቶ ፖለቲካዊ-ፍልስፍና መሰረት ሪፐብሊኩ የምክንታዊነት ስብዕና (Rational soul)፤ የወኔና ጀግንነት ስነ-ልቦና (Spirited Soul[7]) እና የቁሳዊ ፍቅር የመሻት ስነ-ልቦና (appetitive soul[8]) ሲኖር አነዚህ የሪፐብሊኩ ስነ-ልቦናዊ አካላት ከሶስት ማህበራዊ መደቦቹ (social classes)[9] ጋር አብረው የሚሄዱ ናቸው። በሪፐብሊኩ ውስጥ ማህበራዊ መደቦች የሚባሉት የመሪነት ባህሪትን፣ የወታደር ስብዕናና የሰራተኛነት/ አምራችነት/ ተግባራትን የተከፋፈሉ የማህበረሰብ ክፍችን ነው። የምክንታዊና አመክኗዊነትን ስለ-ልቦና በመሪነት የተገለጸው መደብ ባህሪ፣ የወኔና ጀግንነት ስነ-ልቦና የወታደሩ መደብ የሚላበሰው ሲሆን የቁሳዊ መሻት ስነ-ልቦና በሰራተኛነት ከሚታሰብ መደብ ጋር የሚሄድ ነው። ሶስቱም የሪፐብሊኩ ስነ-ልቦናዊ አካል የየራሱን ተግባር የሚፈጽና አንዱ በሌላው ስራ ላይ ጣልቃ የማይገባ ይሆናል። የሶስቱም ሚና እንደሚከተለው ነው።

አመክኗዊ ስነ-ልቦና ያለው የማህበራዊ መደብ ለመማር የሚቋምጥ፣ የመማር ፍቅርን ተላብሶ በእርጋታ ስርዓቱን የሚመራ ነው። ሁለተኛው ወይም የወኔ ስነ-ልቦና (Spirited soul) የሚኖረው ሚና በብልሃትና በምክንያታዊነት የሚወሰኑ የሪፐብሊኩን ስራዎች መፈጸምና የምክንያታዊ ስነ-ልቦና (Rational soul) ከተላበሰው የመሪ መደብ የመተላለፉ ትዕዛዞችን ማክበር ሆኖ ጠቅላላ ስርዓቱን ከውጭ ወረራና ከውስጥ ያለመረጋጋት የመጠበቅ አላፊነትን የሚወጣ ነው። ሶስተኛው የመሻት ስነ-ልቡና ሲሆን ስጋዊ ፍላጎት የሚያስቀድም፣ ሃብትን በመሰብሰብ ደስታን ማግኘት የሚፈልግና በጸታዊ ፍቅር የሚረታ እንዲሁም የንዋይ አፍቃሪነት ስነ-ልቦና የተላበሰ በመሆኑ የአምራችነት ሚናውን ይወጣል። ሶስቱም ተደጋጋፊ ናቸው።

ፈላስፋው ከመደቦች ጋር በማስተሳሰር ባይተነትነውም የሃገር መስራች ወጣቶች ሊማሩት ስለሚገባው የስ-ጽሁፍ ይዘትና ተገቢ የሆኑ ዝርዝር ውሸቶችን ይነግረናል። እውነቶች

[7] The spirited part of the soul yearns for honor; the rational part of the soul desires truth and knowledge. In a just soul, these three parts stand in the correct power relations. The spirited part must enforce the rational part's convictions, and the appetitive part must obey.

[8]The appetitive part of our soul lusts after food, drink, sex, and so on (and after money most of all, since money is the means of satisfying the rest of these desires.

[9] In the specialization os the social classes a man whose nature suits him to farming must farm and do nothing else; a man whose nature best suits him to building objects out of wood must be a carpenter and not bother with any other sort of work. Plato believes that this is the only way to ensure that each job is done as well as possible. The principle of specialization keeps the farmer from carpentering, and the carpenter from farming. It keeps both the farmer and the carpenter from becoming warriors and rulers. The principle of specialization separates society into three classes: the class of producers (including farmers, craftsmen, doctors, etc.), the class of warriors, and the class of rulers.

በምንቀርጻቸው ወጣቶ ላይ የሚያመጡት አሉታዊ ውጤት ካላቸውና ለሃገር ጥቅም የማይሰጡ ከሆኑ "ለወጣቱ ሳይነገሩት ይታለፋሉ፣ ፍጹማዊ አስፈላጊነት ካለ ጥቂቶች ናቸው ሊሰሙት የሚገባው"[10]። በተጨማሪም ወጣቶችን በማስተማር የወደፊቱ ትውልድ ለሃገሩ የቀና/የተሞረድ/ እንዲሆን የሚዋሹ/የሚደበቁ/ ጉዳዮች እንዳሉ ሆነው በሆነ አጋጣሚ ውሸት ጠቃሚና የማይወገዝ መሆኑን "የፕሌቶ ዘ-ሪፐብሊክ"[11] ተዋስዖ ያስረዳል። ይህም ከችግር ለመዳን የሚያስችል የሰዎችን ስነ-ልቦና ለመገንባት ነው።

የተዋረደ ውሸት (Bad lie)

ፕሌቶ ከውሸቶች ሁሉ የከፋ ውሸት የሚል ሃሳብ ይሰነዝራል። ይህንም በምሳሌ ሲያስረዳ ሰአሊ የሆነን ነገር ምስል ሲስል የነገርዮውን አምሳያ ጥላ ሳያሳይ ከቀረ ነው ይላል። ውሸት እንደስሙ የቀለለ ወይም ያልከበረ ውሸት የምንለው በግለሰብም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ የሚነገሩና የሚሰራጩ ትርክቶች የአፍራሽ ሚና ያላቸው ከሆነና የተወሰኑ ቡድኖችን ወይም ገለሰቦችን ፍላጎት ለማስፈጸም ሃሰተኛ መረጃዎችን የማስረጽ ተግባር ከተፈጸመ ነው። የተዋረደ ውሸት በማህበረሰቡ ላይ የሚያደረሰው የቅርብና የሩቅ ዘመን አሉታዊ ውጤት የውርደቱን ደረጃ ከፍ ያደርገዋል።

ከላይ እንዳስተዋልነው ክቡር ውሸት በአላማም በአስተምሮዎም ከአምባገነኖች ቅጥፈት የተለየ ነው። በዘ-ሪፐብሊክ መጽሃፍ 2 ላይ ፕሌቶ ይህን አይነት ውሸት እንደሚከተለው ያብራራዋል። ማንም ሰው ስለ ታላላቅ ሃቆችና ምጥቅ በሆነው አካሉ-መንፈሱ (soul) ሊታለል አይሻም--አይፈቅድም። የሰው ልጅ ምጥቅ በሆነው መንፈሱ ስለታላላቅ ሃቆች እንዳያውቅ /መረጃ እንዳይኖረው/ በመደረጉ ወይም በመታለሉ መንፈሱ በሃሰት ይሞላል፤ ደግሞ ሰውየው ፈጽሞ የሚጠላው ነገር ነው። ከለዚህ የበለጠ የሚጠላው ነገር ያጣል። ይህ በመታለሉ የተነሳ መንፈሱን የሞላው አላዋቂነት እውነተኛ ውሸት (true lie) ተብሎ ሊጠራ ይችላል (ፕሌቶ፣ 2፣

[10] … Even if they were true, ought certainly not to be lightly told to young and thoughtless persons; if possible, they had better be buried in silence. But if there is an absolute necessity for their mention, a chosen few might hear them in a mystery, and they should sacrifice not a common [Eleusinian] pig, but some huge and unprocurable victim; and then the number of the hearers will be very few indeed. Though we know the history of quarrel, it is not to be told for future guardians. If they would only believe us we would tell them that quarrelling is unholy, and that never up to this time has there been any, quarrel between citizens; this is what old men and old women should begin by telling children; and when they grow up, the poets also should be told to compose for them in a similar spirit.

[11] Whereas the lie in words is in certain cases useful and not hateful; in dealing with enemies--that would be an instance; or again, when those whom we call our friends in a fit of madness or illusion are going to do some harm, then it is useful and is a sort of medicine or preventive; also in the tales of mythology, of which we were just now speaking--because we do not know the truth about ancient times, we make falsehood as much like truth as we can, and so turn it to account (ibid, 58).

59)። ስለሆነም እውነተኛ ውሸት በአማልክቶች ብቻ አይደለም፤ በሰው ልጅ የተወገዘና የተጠላ ነው (ዝኒ ካማሁ)። በሰው ልጅ ላይ ከሚደርሰው አልባሌነት በተጨማሪ በዚህ መልኩ የሚከሰት የትውልዱ አላዋቂነት በሪፐብሊኩ ወይም በመንግስት ስርዓቱ ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ውጤት አለ።.

ኢትዮጵያ ክቡር ውሸት አላትን? የተዋረደስ?

ኢትዮጵያ የተከበሩም የተዋረዱም ውሸቶች ባለቤት ናት። በማህበረሰቡ ውስጥ ስር የሰደደ የክቡር ውሸት ስነ-ልቦና ሰርጾ ይገኛል። በተግባር የተፈተነ በጎ አስተዋጽዖ አለው። በተቃራኒው የሃገሪቱን ታሪካዊ ልዕልናና የህዝቦችን ሃገራዊ የጋራ ራዕይ በሚፈታተን መልኩ ተከሽነው በእውነት እየተዋዙ የሚቀርቡ ስርዓታዊ ውሸቶች አሉ። ሁለቱም አይነት ሀገርኛ ውሸቶች እንደሚከተለው ተብራርተዋል።

በአካዳሚዊ ፍልስፍ አይታገዝ እንጂ በኢትዮጵያም ክብር ውሸት ያለና የነበረ ነው። ፈሪሃ-እግዚኣብሄር የማይለያቸው በትህትና የታነጹ አባቶች “ዋሸቶ ማስታረቅ” የሚል የቆየ አስተሳሰብ አላቸው። ይህ አስተሳሰብ በየትኛውም የሃገሪቱ አካባቢ የሰረጸ በተግባርም እየተፈተነ አወንታዊ ውጤት ማሰገኘቱን ኢትዮጵያዊያን ከሊቅ እስከ ደቂቅ የሚያውቁት ጉዳይ ነው። አንዳንድ ሙያዎችም ሰራተኛው የሚያውቀውን ሃቅ እንዳይናገር ወይም እንዲደብቅ ያዛሉ። በቃ አንድ ሰው አይኑ ያየውንና ጆሮው የሰማውን በአጠቃላይ በስሜት ህዋሳቶቹ ታግዞ መገንዘብ የቻለውን እውነታ እንዲገልጽ ሲጠየቅ ያለመናገር መዋሸት ነው። ምክንያቱም ያለመዋሸት አውነቱን ማሳወቅ ነውና። ነገር ግን የውሸት ክብደትና ቅለት እንዳለ ሁሉ የተከበረ ውሸትም አለ ማለት ነው። የመከበሩ ማረጋገጫም በአንድ ፖለቲካዊ ማህበረሰብ ወይም ከዚያ ስፋ ለሚለው የሰው ዘር አወንታዊ ፋይዳ ያለው ሆኖ ሃሰተኛ መረጃው መሰራጨቱ ወይም እውነተኛው ያለመገለጹ በሌው ላይ ምንም አይነት ችግር ያለማስከተሉ ነው። ምሳሌየን ደቃቃ ላድርጋትና አንድ ሰው በአዳማ አዲስ አበባ የፍጠነት መንገድ ላይ እያሽከረከረ አብሮት ያለ ጓደኛው እያሽከረከረ ያለው ሰው እናት እንደሞተች በስልክ ቢነገረው ለጊዜው የእናቱን ሞት እንደሚደብቀው እሙን ነው። አሽከርካሪው ከስልክ ንግግሩ ጥርጣሬ አድሮበት “ችግር አለ ወይ” ብሎ ቢጠይቀው የለም ብሎ እንደሚዋሽ የታወቀ ነው። ክቡር ውሸት። ይህንኑ በማህበረሰብ ደረጃ አስፍቶ በማሰብ ብዙ ስርዓታዊ ክቡር ውሸቶችን ከኢትዮጵያም ነባራዊ የፖለቲካ ሁኔታ ጋር አዛምዶ መገንዘብ ይቻላል።

ከላይ ለመጠቆም እንደተሞከረው እንዳለ ሆኖ ዛሬ በኢትዮጵያ እየታየ ያለው የታሪክና የፖለቲካ ስርዓታዊ ቅጥፈቶችን መዳሰስ ሃገራዊ የተዋረደ ውሸትን ሁኔታ በግልጽ ለመረዳት ያስችል የሚል እምነት አለኝ። በኢትዮጵያ መንግስታዊ ስርዓት የበዳይ ተበዳይ ታሪክን በፈጠራ አጅቦ የመጻፍ፣ የቀድሞ ታሪክን አኮስሶ የማስነገር ተግባራት መጥቀስ የስርዓቱን ቅጥፈት ከክቡር ውሸት ምን ያህል እንደሚርቅ አስረጂ ነው። የኛው ቅጥፈት አላማው የመሪዎችን የስልጣን ዘመን ማራዘምና ሃገሪቱንና የህዝቡን የሚያስተሳሰር ማህበራዊና ታሪካዊ እትብትን የመበጠስ ሚና ያለው ሆኖ ለወደፊት የህዝቡን የግንኙነት መሰረቶች ማመናመን ሆኗል። በጥቅሉ በሃገር የብሄራዊ ጥቅም ላይ ተጻራሪ እርምጃ የመውሰድ ሚና ተሰጠቷቸው በባዕድ አካል የተላኩ ቡድኖች የሚያደርጉት ተግባር ነው። የኢህአዴግ መንግስት የኢትዮጵን ታሪክ ከብዙ ሽህዎች ወደ መቶ ምናምን አውርዶ ይነግረናል። ይህንም ውሸት እንድናምን ኢትዮጵያ የአሁኑን ቅርጽ የያዘችው በመቶ ምናምን አመታት ውስጥ ነው ይለናል። አሜሪካ እ.ኤ.አ. ከ1776 የፒላደልፒያ ኮንፈርንስ በኋላ ስትመሰረት በመጀመሪ ዘጠኝ ስቴቶች ከዚያ 13ና ሌሎችም እየተጨማመሩ ዛሬ ላይ 52 ስቴቶችን የያዘች ሀገር ሆናለች። እንደ ኢህአዴግ የታሪክ አቆጣጠር የአሜሪካ ታሪክ ሊተረክ የሚገባው በቅድሚያ በፌደራል አስተዳደር የተስማሙት ዘጠኝ ከዚያ 13 ስቴቶች ታሪክን ተትቶ 52 ስቴቶች ተሟልተው በፌደራል አወቃቀሩ ውስጥ ከገቡበት በመጀመር ነው። ይህ አይነት ትንሽነት በአሜሪካኖች የሚታሰብም፤ የሚሞከርም አይደለም። የኢትዮጵያ መንግስት ውሸት ሲደጋገም እውነት ይመስላል እንዲሉ በርካታ የመጠላለፊያና የመካከሻ ታሪኮችን በማስተረክ እንዲሁም የመቶ አመት ታሪክን ብቻ ለማስረጽ ብዙ ሃብት አፍስሷል። ብክነት ብለው ይገልጸዋል። ኢህአዴግ የሰው ልጅ ፖለቲካዊ ስርዓት ጀመረ አልጀመረም፣ የኢትዮጵያም ቅርጽ ያሁኑን ይምሰል አይምሰል ማህበረሰቡ ውስጥ ታሪክ እንደሚኖረው መገንዘብ የሚስችል ተክለ-ቁመና የለውም ወይም አስቦበት ችላ ብሎታል። እናም ይህን እንድንዘነጋው ያለ የሌለ አቅሙን አሟጦ በወጣቱ ተውልድ በጭንቅላታችን የውሸት ክምር ለማኖር እየሰራ ነው። እንደ ፕሌቶ አተያይ ይህ ትላላቅ እውነቶችን የማዛባትና የመደበቅ ተግባር በትውልዱ ላይ አላዋቂነትንና አልባሌነትን ማስፈን ነው። ይህን ውሸት ትውልድም ይጠላዋል፤ከዚህም የባሰ የሚጠላው ነገር የለም።

ስርዓቱ የድህረ ሰማንያ ሶስቱ ቡድን ኢትዮጵያ ቅኝ ገዢ ሀገር ነበረች ይለናል። የስርዓቱ መሪዎች የአንዳንዱን ህዝብ በወርቅ ደረጃ ይመድቡታል፣ ነጻ አውጪነት ታሪክ ያጎናጽፉታል፣ ሌላውን የታሪክ ተወቃሽ አድርገው ቅጣት ያውጁበታል። ይህ ሁሉ ውሸት ለምን ሆነ ብሎ የሚጠይቅ አይጠፋም? መለሱ “ደስታ የወለደው ስሜታዊነት ወይም ከጥላቻና ከስልጣን ጥም

የሚመነጭ የአምባገነኖች ቅጥፈት ነው፡፡" ኢትዮጵያም አምባገነን በአምባገነን የመተካት መጥፎ እድል የተጣባት ሃገር በመሆኗ ከ1983 ዓ.ም በፊትም ጭምር ይህ የተዋረደ ውሸት የመንግስታዊ ስርዓቱ መገለጫ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ የማያባራ የገዢ ቡድኖች ውሸት የበላይነት የሰፈነባት መሆኗን የሚከተለው የፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ጽሁፍ በደንብ ይገልጸዋል፡፡

> *ማርክሳዊ-ሌኒናዊ ነን የሚሉ ከሰሜን እስከ ደቡብ ኢትዮጵያ የተውጣጡና የተለያዩ ቡድኖች በአይነደረቅነትና በድንቁርና እርግጠኛነት በመድረክ ላይ እያረገረጉ ለብዙ አመታት ውሸትን በአደባባይ ህዝብን ሲያወናብዱ ከማርክሲስት ሌኒኒስት ፖለቲካ ጋር አፈር በልተዋል፤ ነገር ግን በኢትዮጵያ ውሸት አይሞትም፡፡ ገና የወያኔ ሰራዊት አዲስ አበባ እንደገባ ሁለተኛ አይነት ደረቆችና በድንቁርናቸው የሚተማመኑ ወያኔዎች የታሪክ እውነትን ለማዛባት ራሳቸውን በአሳተማሪነት ሾመው በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩኒቨርሲቲ በራስ መኮንን አዳራሽ መምህርኑን ሰበሰቡ፤ ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል በሚለው ባህላዊ መመሪያ መሰረት ለዩኒቨርሲቲው መምህራን የኢትዮጵን ታሪክ ለማስተማር ደፈሩ፤ ኢትዮጵያ ታሪክ ከአንድ መቶ አመት እንደማይበልጥ ተናገሩ…(መስፍን ወልደማሪያም፣2007 ዓ.ም.21)፡፡*

የፕሮፌሰሩ ጽሁፍ የሚነግረን በህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ዘመን ከ1983 ዓ.ም. ለውጥ ቀደም ሲል ሲፈበረኩ የነበሩ ውሸቶችን በማስቀጠል ታሪክን ለማዛባት ድፍረትን የተጎናጸፉ የጎበዝ አለቆችን እራሳቸውን በአስተማሪነት መሾማቸውን ነው፡፡ ይህ የካድሬዎች በእውቀትም፣ በልምድም ለማይስተካከሏቸው ምሁራን ታሪክንም ፖለቲካንም የማስተማር ድፍረት የማይቋረጥ ልክፍት ሆኗል፡፡ "ታጋዮቹ" ከ1983 ዓ.ም. በፊት የነበሩ ታሪኮች ረብ የለሽ የማስመሰልና የኢትዮጵያ ህዳሴ መነሻ የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ስለመሆኑ ሳይሰለቹ ያስተምራሉም፡፡

በመጨረሻም ከላይ ልገልጽ የሞከርኩትን የአምባገነኖችን የተዋረደ ውሸትን ጸንሰ-ሃሳብ የምንዳራለው ዘውዴ ጽሁፍ ይጠቀልለዋል ብዬ እገምታለሁና እንሆ፡፡ "*Dictators and their retinue are four times removed from truth and reality. The first time they lie to themselves as individuals, the second times they lie to each other as partners, the third times they lie to the people as a group, and the forth time they expect the people to lie to them by acquiescing their lies"* (ምንዳራለው, 2016). በግርድፍ አተረጓጎም አምባገነኖች ከእውነታንና ሃቅን አራት ጊዜ ይሸሻሉ፡፡ እንደግለሰብ ለራሳቸው ይዋሻሉ፣ እርስበርሳቸው እንደባልንጀራ ይወሻሻሉ፣ በቡድን ለህዝቡ ይዋሻሉ በመጨረሻም ህዝቡ የነሱን ውሸት ተቀብሎ እንዲያስተጋባ ይጠብቃሉ፡፡ ዛሬ ላይ እየገጠመን ያለው ችግር ዋነኛ ምክንያት አምባገነኖች የሚፈልጉትን ውሸት የሚያስተጋቡ እንዳሉ ሁሉ ህዝቡ ዘብ የሚቆምለት እውነት ሰርዓታዊ ጥበቃ ያለማገኘቱ ነው፡፡ ለምሳሌ ለብዙ አመታት በአካባቢው

የኖረ ግሰብ በመንግስት የጸጥታ ሃይሎች ተገደለ ተብሎ ከተዘገበ የመንግስት አፈቀላቂዎች ሰውየው በአካባበው ያልነበረና መረጃውም ፈጽሞ ሃሰት ነው በሚል ሲዋሹ ይደመጣሉ፡፡ መረጃውን ይፋ ያደረጉ ሚዲያዎችን በጸረ-ሰላምነት ይወገዛሉ፡፡ ህዝብ ያየውን ያምናልና ለመመስከር አያመነታም፡፡ ጋኑን መልቶ የተትረፈረፈው የተዋረደ ስርዓታዊ ውሸት እንዲወጣ በትንሽ ማሰሮ የምንትሰፈር ክቡር ውሸት አንድትገባ አቅመ የፈቀደውን መስዋዕትነት እየከፈለ ታግሎ እያታገለ የሚኖር ተስፈኛ ትውልድ ግን አለ፡፡ ይህ ከአልባሌነት ወይም መናኛነት ለመላቀቅ የመመኘት ወይም የተዋረደ ውሸት የመጸየፍ ውጤት የሆነው የትውልድ ትግል የድል በር እስኪከፈት የሚቋረጥ አይሆንም፡፡

ምዕራፍ ሁለት፡ አማራነት በዘመናዊት ኢትዮጵያ

ከላይ በመግቢያው ላይ ለመጠቀስ የተሞከሩትን የተለያዩ ኩነቶችን መሰረት በማድረግ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የፖለቲካዊ አቅጣጫና ሂደቶች ከብሄር በብሄረሰቦች ግንኙነቶችንና ቁልፍ የፖለቲካ ገጽታዎችን የሚወስኑ ብሄር ነክ ጉዳዮችን፣ እንዲሁም ዛሬ እየተስተዋለ ያለውን ፖለቲካዊ ሂደት የአማራን ህዝብ አግላይ ከሆነው የብሄር ፖለቲካ ጋር ያለውን መስተጋብር ለመፈተሽ ይሞከራል፡፡

አማራነት

አማራ የሚለውን አሰያየም በተመለከተ ሃይሌ ላሬቦ እንደጻፉት "...ዛሬ የወያኔ መንግሥት ዐማራ ብሎ የሚጠራቸውን እንደነገሯም፣ በጌምድር፣ ሸዋ እንዲሁም የወሎን ከፊሉን አያካትትም፡፡" ሃይሌ ይቀጥላሉ- "የዚህ ክልል ነዋሪዎች አፈታሪክ የሚነግረን፣ "ዐማሮች" ምንጫቸው በቀጥታ ከአክሱም ሲሆን፣ "ዐማራ" የሚለው ቃል ትርጉሙ "ነፃ ሕዝብ " ማለት እንደሆነ ነው፡፡" በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ሌሎችም ሌላና የተለየ አስተያየት ይሰጣሉ፡፡ አማራ ማነው ስል ጎግል አድርጌያለሁ፡፡ በዚህም መሰረት የአማራ አመጣጥና ምንጭ ግልጽ ያለመሆኑን የሚያስረዳ እንዳለ ሁሉ ከየመን ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ የመጡ የሴም ቋንቋ ሂምያሪቶች የአማራ አያቶች ናቸው የሚል መላ ምትም አለ፡፡ በሌላ በኩል አማረኛ ተናጋሪ እንጂ አማራ የሚባል ብሄር የለም የሚሉም እንደሉ የሚታወቅ ሲሆን ፕሮፌሰር ጌታቸው ሃይሌ (እ.ኤ.አ. 2015) ይህን ሃሳብ በመሞገት የአማራ ብሄራዊ ማንነት ስለመኖሩ ለማስረዳት ሞክረዋል፡፡ እንደ ፕሮፌሰሩ ገለጻ አማራ ነኝ የሚሉ በመኖራቸውና ሌላ የብሄር ማንነት ያልተቀበሉ መሆኑን፣ በሌላውም አካል አማራ ናችሁ በሚል መሰየማቸውና ከዚህ ጋር

ተያይዞም ብዙዎች ለጥቃት የተጋለጡ መሆኑን፣ በየዘመኑ የሚደረግ የህዝብ ቆጠራ አማራን እንደአማራ እየቆጠረው መሆኑንና የአማራ ማንነትን የሚያመለክት ቋንቋ መኖሩን በማሳያነት አቅርበዋል።

ሆኖም በዚህ ጽሁፍ ዋናው ትኩረት በኢፌዴሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 39 (5) ላይ ያለውን መስፈርት በሚገባ የሚያሟላውን እንዲሁም በአንቀጽ 47 (1) መሰረት የራሱን ክልል እንዲመሰርት እውቅና የተሰጠው የአማራ ማህበረሰብ ነው። በተጨማሪም በ47 (1) ላይ ከተደነገገው በተጨማሪ በአንቀጽ 39 በተደነገገው መሰረት የጋራ ማንነትቱ እውቅና ያለውና ተመጥናና ተኮርኩማ ከተሰጠችው ክልል ውጪ ተበትኖ የሚኖረውን የአማራ ህዝብም የሚመለከት ነው። በአማራነት ጉዳይ ላይ ብቻ በሚሰጥ ትንተና የአማራ ማህበረሰብ በአህገራቱ ሁሉም አቅጣጫ ተበትኖ ከተለያዩ የሃገራቱ ህዝቦች ጋር በብዙ ሰብአዊ ዘርፎች ተዋህዶ ያለ ማህበረሰብ መሆኑን ችላ ያልተባለ መሆን መገንዘብ ተገቢ ነው። ማለትም አማራ ተበታትኖ በሚኖርባቸው አካባቢዎች ካሉ ለሌሎች ህዝቦች የጎላ የሆነ ልዩ ማንነት የሌለውና በብዙ መልኩ ከሌሎች ኢትዮጵዊን ጋር የሚጋራቸው ማንነቶችም ያሉት ህዝብ ነው። ይህም የዘር ግንድ ቢቆጠር ጭንጨ አማራን ማግኘት ቀላል ያለመሆኑም የሚያስታወሰን ነው።

ስለአማራ ብሄር ስንወያይ ከላይ እንደተገለጸው ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ስለአማራነት ያቀረቡትን ትንታኔ ማስተዋሉ ጠቀሜታ ይኖረዋል። እናም በአንጸራዊነት አማራነት የተሰኘ የጋራ ማንነት አስካለ ድረስ ስለአማራ ታሪካዊ አመጣጥ የሚሰጡ አስተያየቶች መለያየት በዛሬዋ ኢትዮጵያ በጋራ ማንነቱ በሚታወቅ ህዝብ ላይ የሚያመጣው ለውጥ እምብዛም በመሆኑ በዚህ ጽሁፉ የዘመናዊ ኢትዮጵያን የአማራ ህዝብ ፖለቲካዊ መስተጋብርና ተያያዝ ጉዳዮች ላይ በማተኮር ውይይት ለማድረግ ይሞከራል።

ስአማራ የጥንት ታሪክና አመጣጥ የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ሃሳቦችን ይሰነዝራሉ። ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት በአንድ ወቅት በተደረገላቸው የቃለ-መጠይቅ “የጥንት አማራዎች የዮቶር ልጆች” ስለመሆናቸው ያስረዳሉ። እንደፕሮፌሰሩ አባባል ዮቶር የዛሬ 5000 ዓመት በቤጌምድር የሚኖር በግ አርቢ ነበር፤ የዮቶር ልጆች ለንግድና ለተለያዩ ተግባራት ወደ ባህሩ በመጠጋት መንግሥታቸውን መሠረቱ። ይህም የደአማት (ዘ-አማራ) መንግሥት ነው፤የመጀመሪያው ንጉሣቸውም አክናሁስ ይባላል። የግዛታቸው ድንበር እጅግ ሰፊ እየሆነ ሲመጣ የንጉሱ መጠሪያ 'የአገር ሹም ' (አግ ሹም ፣ አክ ሹም በጊዜ ሂደት አክሱም) ይባል ነበር (ዝኒ ከማሁ)። ንጉሱ በዚህ ስም መጠራት የጀመሩት ክርስቶስ ሊወለድ 500 ዓመት

ሲቀረው ነው። ስለዚህ ከሰሜን ቀይ ባሕር እስከ በናዲር (የአሁኑ ሞቃዲሾ) የእነሱ ግዛት እንደነበር የታወቀ ነው (ዝኒ ካማሁ)። ፕሮፌሰሩ ለዚህ የታሪክ ገለጻቸው "ምን ማስረጃ አለዎት" ሲባሉ "ይህ ታሪክ በሳይንሳዊ መንገድ ተጠንቶ የተደረሰበት ነው" ሲሉ መልሰዋል። ፕሮፌሰር ፍቅሬ በቅርቡ በ2008 ዓ.ም. ባሳተሙት የአማራና የኦሮሞ የዘር ግንድን በሚተርከው መጽሃፋቸው አማራ እና ኦሮሞ ከአንድ አባት የሚወለዱ የደሸት ልጆች መሆናቸውንና ደሸት/ደሴት/ አሁኑ ጎጃም ይኖር እንደነበር ጽፈዋል።

አማራ ማነው የሚለውና የታሪክ ሃተታውን እዚህ ላይ አቁመን በዘመናዊ እትዮጵያ የአማራን ህዝብ ፖለቲካዊ ኩነቶችና ሰርዓቶቹ እንዴት ይመለከቱት ነበር በሚለው ጉዳይ ላይ እናተኩራለን። ጉዳዩን መጥኖ ለመመልከት እንዲያመች የአፍሪካ ሃገሮችን የአሁን ገጽታ ለመወሰን እንደአንድ ታሪካዊ መሰረት ተደርጎ ከተወሰደው የቅኝ ገዢዎች አፍሪካን መቀራመትን በይፋ ካወጁበት ዘመን ወዲህ ካለው ታሪክ መጀመሩ ተመራጭ ነው። ይህም ወቅት ተመራጭ የሆነበት ምክንያት ከአማራ ህዝብ ጋር ቁርኝት ያለው የኢትዮጵያ አስተዳደር በተስፈኛ ቅኝ ገዢዋ ጣሊያን የመወረር አደጋ የታቀደበትና የአማራን ህዝብ ለብቻ ነጥሎ የማቆርቆዝ፣ የማጥፋትና የማጽዳት ሴራም፣ ተግባርም የተጀመረበት ወቅት በመሆኑ ነው።

አማራ በጣሊያን ወረራ ወቅት

ቅኝ ገዥዎች የአፍሪካን መሬት ለመቀራመት ሚስጥራዊና ይፋዊ ዲፕሎማሲ ላቅ ወዳለ ደረጃ ከደረሰበት እ.ኤ.አ. 1884ና ከዚያ በኋላ የኢትዮጵያዊያን የስልጣኔ መራቆት ለነጻነት መዋደቃቸውን ሳይገድበው ቅኝ ገዢዎችን በመመከት ሀገራቱን የአፍሪካዊን የነጻነት ተምሳሌት ለማድረግ በቅተዋል። በዚህም ረጂም የትግል ዘመን የአማራ ብሄር እንደሌሎቹ ወንድም ህዝቦች የከፈለው መስዋዕት የላቀ ነው። የቋራው ቴዎድሮስ በስልጣን ዘመኑ አዲስ የሃገር ግንባታ ሂደትን ትልም ለማስፈጸም ባደረገው ውጣ ውረድ የአማራ ህዝብ በሁሉም የህይወት ዘርፍ በመሰማራት የነበረው ሚና የላቀ እውቅና የሚቸረው ነው።

ማህበረሰቡ በአብዛኛው በአንድ ቦታ ሰፍሮ የመኖር ልምድ አለው[12]። የባህላዊ አደረጃጀቱና የሃይማኖታዊ ተቋማቱ የስነ-ዜጋዊ ባህሪ እንዲላበስ አጋዥነት አላቸው። ተሰባስቦ የመኖር ባህሉ የማህበረ-ፖለቲካ ተቋማቱን ተደራሽነት ያረጋግጡለታል። እነዚህ አደረጃጀቶች በስነ-ምግባር የማነጽና የማህበረሰ አደረጃጀት ተዋረዶችን ለመጠበቅ የሚያግዙ አስተምሮዎችን

[12] Unlike some others "…the Amhara are sedentary agriculturalists living mostly on the central plateau" (Paulos Milkias: 2011፡ 82).

የሚያሰርጹ ናቸው። በተለያዩ የነገስታት ዘመን በአካባቢያቸው ያለውን መንግስታዊ ስርዓት በማጽናትና ለንጉሶቻቸው በማገዝ የሀገሪቱ ህልውና በቅኝ ገዢዎች እንዳይደፈር በአስተዳደርና በወታደራዊ አገልግሎት የአማራ ህዝብ ለሀገሪቱ ባለውለታነቱን በዘመኑ ከኢትዮጵያ በተጻራሪ የተሰለፉ ቅኝ ገዢዎች መስክረዋል። በሰባት አመት የመንፈሳዊና የጽሁፍ ትምህርት በቤተክርስቲንና በአዳሪ ትምህርት ቤቶች ይሰጥ ስለነበር ከመንግስታዊ ስርዓቱ ጋር የጠነከረ ግንኙነት ያላቸው አስተማሪ መንፈሳዊ አባቶች ተማሪዎቻቸው የመንግስታዊ ስርዓትንም የሃይማኖታዊ እሴትንም ለማስረጽ እድል ስለሚያገኙ የተማሪዎች ፖለቲካዊ ግንዛቤም የተሻለ በመሆኑ ለዘመናዊ ፖለቲካ እድገት ፈር ቀዳጅ ልሂቃን እንዲፈጠሩ አግዟል። ይህ የግንዛቤ ልህቀት በወታደራዊና በፖለቲካ አመራር ዘርፍ ተመልምለው ሃገራቸውንና የፖለቲካ ስርዓቱን ለመጠበቅ የተሻለ አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ አስቻይ ነበር።

በረጅሙ የሶሎሞን ስርዎ መንግስትና በዛግዌ ስረዎ-መንግስት ብቁ ወታደሮችና አመራሮችን አማራዎች እንዳበረከቱ ይታወቃል። በጎንደር የየጁ ኦሮሞ የስልጣን ዘመንም ተመሳሳይ ሃላፊነት የተወጡ ናቸው። በዮሃንስ አራተኛ ዘመን በሰሜን ጫፍ የአሉላ አባ ነጋን ድንበር ጥበቃን የሚያጠናክር ደጀን የወሎ፣ የበጌምድር፣ የጎጃም አማራ መሆኑን ማስተዋል ያሻል። የሸዋ አማራዎችም ከአዲስ አበባ በስተምዕራብና በስተደቡብ ከሚገኙ ሌሎች ኢትዮጵያዊን ጋር በመሆን በሰሜን፣ በምዕራብና በምስራቅ ለሚደረግ የነጻነጽ ትግል በተለያየ ደረጃ መስዋዕትነት የከፈሉ ናቸው።

የአማራ ህዝብ በአድዋ ጦርነት ከሌሎች ኢትዮጵያውን ጋር በመሆን የአገሪቱ ታሪክ በአፍሪካ ደረጃ የተለየ ክብር እንዲቸረው ያስቻለ ህዝብ ነው። በመንግስታዊ ስርዓቱ ውስጥ የተላመደ ማህበረሰብ በመሆኑና በአብዛኛ ማህበረሰቡ የርግ ገበሮዎች ስብስብ ስለሆነ የጦርንት ነጋሪት ሲጎሰም ፈጥኖ በመደራጀት ፋኖ ታጋይ የመሆን እድል ፈጥሮለታል። ይህ ተጋድሎው በተለያየ ወቅት የቅኝ ገዢዎችና ባንዳዎች የበቀል እርምጃ ሲያውጁበት ተስተውሏል።

በጣሊያን ወረራ ወቅት የአማራ አካባቢ ተብለው በተሰየሙ ቦታዎች ወራሪን በመፋለም የተሰለፉ አርበኞች ቁጥር ከሌላው አካባቢ በእጂጉ የላቀ ነበር። ለአብነት ያህል መስፍን ወልደማሪያም በ2007 ዓ.ም. የአልቤርቶ ስባኪን መጽሃፍ ዋቢ በማድረግ እኤአ ከ1937 እስከ 1938 ባለው ጊዜ በግምት ከ123,350 አርበኞች 5,150 በላስታ፣ 83,200 በጎጃም እና 15,400 በሸዋ፣ በድምሩ በአማራ ምድር 115,550 አርበኞች እንደነበሩ ገልጸዋል። በተመሳሳይ መረጃ መሰረት ሌሎች 7,800 የሚሆኑት በኦሮሚያና በሲዳማ የሚገኙ ናቸው። የሸዋ አርበኞች ሲባል

የሸዋ አማራዎችን፣ ሸዋ ኦሮሞዎን፣ ጉራጌዎችንና በከፊል ሌሎችንም የሚያካትት ቢሆንም የመንዝ-(መንዝ ጌራ) አመጸኛ ዋሻ በመርዝ ደብዛቸው የጠፋ አማሮችን ስናስብ የአማራ መስዋዕትነት አሁንም የገዘፈ መሆኑን እንገነዘባለን። ከላይ ያለው አሀዝ ግምታዊ በመሆኑ ዳግም ጥናት ማድረግ የሚያስፈልግ ቢሆንም የአማራ ምድር ተብለው በሚታወቁ በተለዩት አካባቢዎች አልበገር ባይነቱ የላቀ ስለመሆኑ እልፍ ማስረጃዎች አሉ። በጎጃምና በበጌ ምድር በከበባ ውስጥ ካሉ ጥቂት የጣሊያን ሰራዊት አባላት ውጪ ጣሊያን አካባቢውን እንዳልተቆጣጠረው[13] የጳውሎስ ሚልኪያስ (እ.ኤ.አ፡ 2011) መጽሀፍ ያስረዳል። ከላይ የተገለጹት ሁለቱም መረጃዎች ተመሳሳይ መልዕክት አላቸው። የዛሬዎቹ የጎጃም፣ የበጌምድርና የሸዋ እንዲሁም የላስታ ነዋሪዎች የያኔዎቹ ልጆችና የልጅልጆች ናቸው። በአካባቢው በሰፈራና ስደት ወይም በሌላ ምክንያት የጎላ የማህበረሰብ ማንነት ለውጥ አልታየም። ያኔም ዛሬም በተጠቀሱት አካባቢዎች አማራዎች ይበዛሉ ማለት ነው። በመሆኑም የአማራው ህዝብና ልሂቃኖቹ ትግሉን በማቀጣጠል ብሎም መስዋዕት በመሆን የአንበሳውን ድርሻ ይወስድ እንደነበር መገንዘብ ተገቢ ነው።

በዚህም የተነሳ በአምስት አመታት የወረራ ወቅት ጣሊያን በአማራ ላይ የበቀል እርምጃ ሲወስድም ነበር። አማራውን ለብቻው በመነጠል ለማዳከምና በሌሎች ወንድም ህዝቦች እንደገነር እና በዳይ እንዲታይ በማድረግ የአማራ አርበኞችን የማጥቃቱ ተግባር በሰፊው እንደተሰራበት ይነገራል። በአስተዳደራዊ ክፍፍሉን አማራ በሚል አጥብቦ በመደልደል ብሄር ተኮር ፖለቲካዊ ስርዓት መስርቶም በብዙ የሃገሪቱ አካባቢዎች የብሄሩ ተወላጆች መገለል እንዲደርሰባቸው፣ ለጥቃት እንዲጋለጡ አድረጓል (በጋሻው፣ 2008 ዓ.ም.)። ጣሊያናዊው የታሪክ ተመራማሪ አልቤርቶ ስባኪ እ.ኤ.አ. በ1985 እንደጻፈው ጣሊያኖች የአማራ ሹማምንትን ባለማመናቸውና በማግለላቸው የጣሊያን አስተዳደር በህዝብ ይሁንታ እንዳይቸረው አድረጎት እንደነበርና በተቃዎሞ የተናሳ የአርበኝነት ተጋድሎው ከፍተኛ የወታደራዊ ወጪ በመጠየቁ የቅኝ ግዛት ህልሙ እውን ሳይሆን ቀርቷል። ዋናው ጉዳይ የጣሊያን ወታደራዊ አስተዳደር የአማራን ህዝብና ልሂቃንን በተለየ መነጽር የሚያይና አግላይ ስርዓትን መዘርጋቱ ላይ ነው። ይህ ነጥሎ የማጥቃት ተግባር የአማራን ህዝብ ትግል አላከሰመውም። በአማራ ጀግኖች እና በሌሎች ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያን የተቀጣጠለው ትግል ለጣሊያን ያጎበደዱ እንደነ-ራስ ኃይሉ፣ ራስ ስዩም መንገሻ፣ራስ ጉግሳ፣ ደጃዝማች አያሌው ብሩ፣ሸክ አል-ሆጀሌ ወ.ዘ.ተ.

[13] "In Gojam and Begemider, in particular, there was no Italian presence except at a few isolated fortified spots, where they were virtually surrounded and received food and ammunition by aircraft" (page 57).

እና የባንዳዎች መበርከት እንኳን አላስቆመውም ነበር። አርበኞቹ መስዋዕትነትን በጸጋ የሚቀበሉ ባለታሪኮች ነበሩ።

አማራ በጣሊያን ወረራ ማግስት

የአለም የኃይል ሚዛን ባስከተለው ለውጥና የኢትዮጵያ አርበኞች በከፈሉት መስዋዕትነት የአምስት አመት ሰቆቃ አብቅቶ የንጉሱ መመለስ ሁኔታዎችን መስመር ማስያዝ ችሎ ነበር። አርበኞች ንጉሳቸውን ተቀብለው ቤተ-መንግስት አስገቡ። ከድሉ ፍሬ ለመቋደስ የሚገባቸውን ለማግኘት ግን አልታደሉም። የንጉሱ ስርዓት እንደጠበቁት አርበኞችን የሚያከብር አልሆነም። ይልቁንም ባንዳዎች በስርዓቱ ይሾሙ ነበር። በመሆኑም "ኢትዮጵያ ሃገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ የሞተል ሳለ የገደለሽ በላ" በማለት ብሶታቸውን አሰምተዋል። እየዋል እደር የንጉሱ ስርዓት በቤተሰብ የተተበተበ፣ ከፍጹማዊ ንጉሳዊ አገዛዝ መላቀቅ የተሳነው ሆኖ ድፍን 35 አመት ቆየ። በዚህ መሃል ከስርዓቱ የመነጨ አማራን ነጠሎ የሚያጠቃ አካሄድ ባይኖርም ከስርዓቱ ደካማነት ከሚነሱ ችግሮች የተጎሳቆለ ህይወት እንዲኖር ተፈርዶበት ቆይቷል። እንዲያውም ከአንዳንድ የኢትዮጵያ አካባቢዎች እጅግ በከፋ ችግር ውስጥ ተጎሳቁሎ እንደነበር በርካታ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል። በአብዛኛው የማህበረሰቡ አባላት ኋለ ቀርነት የተንሰራፋ በመሆኑ ስርዓቱ ላይ እንዲተማመን የኃይማኖታዊ ተቋማቱ በሚያደርጉት ሰበካ ተነሳ መንግስትን ከፈጣሪ የተሰጠ አድረጉ የማሰብና ንጉስ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ ሲል መቆየቱ የአደባባይ ሃቅ ነው። በተለያዩ የአማራ አካባቢዎች የመሰረተ-ልማት ባለመዘርጋቱ የመረጃና ትንሽም ብትሆን በከተሞች ትታይ የነበረቸው የለውጥ ጭላንጭል ሳይደርሰው ቆይቷል። ብዙውን የአማራ አካባቢ በየአካባቢው ያሉ ሹማምንት/ የመሬት ባላባቶች/ እንዲሁም ቄሶች ሳይቀሩ በተለያዩ ፖለቲካዊና መንፈሳዊ የመቆጣጠሪያ መንገዶች ተብትበው ስለያዙት በመንግስት ላይ ቅሬታን ለማቅረብና ችግሩን ለማስረዳት የሚችልበት እድልም ጠባብ ነበር። እንደህዝብ በጣሊያን ይደርስበት የነበረውን ሰቆቃ እጅግ የከፋ ስለነበር በንጉሱ አገዛዝ ሃገራዊ ልማት መረሳቱና በአካባቢው ጨቋኞች የሚደርስበትን በደል በወራሪ ሃይ ከሚደርስበት ጋር ማነጻጸሩ ጭቆናን የሚሸከም ጫንቃው እንዲሰፋ አስችሎት ቆይቷል። ኋላ ኋላ ከአብዛኛው የገበሬ ማህበረሰብ የተገኙ የዘመናዊ ትምህርት ቀመስ የአማራ ልሂቃኖች ከሌሎች ኢትዮጵዊን ወገኖቻቸው ጋር በመተባበር የንግሱን ሰርዓት መነቅነቃቸው አሌ የማይባል ሃቅ ነው። በሃገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን መፈንቅለ መንግስት በመሞከር (መንግስቱ ንዋይና ገርማሜ ንዋይ) እና ስለመብት በማቀንቀንና ስርዓቱን በመተቸት የንጉሳዊ ስርዓቱ አይነኬ ተደርጎ

መታሰቡን በመሻር ለቀጣይ ትግል መንገድ በመክፈት ከፍራቻ ነጻ አውጪዎች የነበሩት ዋለልኝ መኮንንና ጥላሁን ግዛው ከአማራ እናት አብራክ የተገኙ ናቸው። ይህን የታሪክ ሃቅ ሊሞግት የሚችል ማንም የለም። በስተመጨረሻም ከሌሎች ወንድሞቻቸው ጋር በመሆን የንጉሱን ስርዓት በማውረድ አቢዮቱን ከግብ በማድረስ በኩልም የአማራ ልሂቃን ባለታሪኮች ናቸው (ሆኖም የአማራ ሰማዕታትን ቁጥር ከማሳደግ ያለፈ አማራን የጠቀመ ስራ ፈይደዋል ለማለት አንዳልሆነ ልገልጽ እወዳለሁ)። በአጠቃላይ በዘመናዊ ኢትዮጵያ ማህበረሰቡ ጭቆናን የሚታገል የልሂቃን ትውልድን በማፍራት በኩል አውራ ነው። የለውጥ ፍሬን ግን ለመዘንቦጥ እድለኛ አይደለም።

ሃቁ እንዲህ ሆኖ ሳለ ከዛሬ አርባ አመት ገደማ ጀምሮ የነበረው የተዛባ አረዳድ የተነሳ ዛሬ ላይ በጦፈው የኢትዮጵያ የብሄር ፖለቲካ ስርዓታዊ ቅርጽ ይዞ የአማራ ህዝብ ያለተወራረዱ እዳዎች እንዳሉበት ተቆጥሮ ለብሄር ፖለቲካው አቀንቃኞች የአማራን ህዝብን/ልሂቃን/ ማወገዝ የተለመደና ሹመት የሚስገኝ ተግባር ሆኗል።

"የሶሻሊስታዊ ተራማጅ" ብሄርና የብሄር ጭቆ

ከ1960ዎቹ ዋዜማው ላይ የንጉሱን ስርዓት ለመለወጥ በተለይም በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና በተለያዩ ስራዎች በተሰማሩ ምሁራን ቅስቀሳ ተደረገ። ስርዓቱ በመሻገቱ ከንጉሳዊ ስርዓቱ ተጠቃሚ ናቸው የሚባሉ ልሂቃን ጭምር የለውጥ እንቅስቃሴው ተሳታፊ ሆኑ። የብሄር ጭቆናን በኢትዮጵያ ስለመንሰራፋቱ አብዝተው ያቀነቀኑት እነዋለልኝ መኮንን ጭቁን ህዝብ ጠብመንጃ ያንሳ የሚሉ ቀስቃሽ ጽሁፎችን በማሳተምና የአማራ ብሄር ጨቋን አስመስሎ በመፈረጅ ጫፍ የረገጠ ተራማጅነት አሳዩ። የወቅቱን ህገ-መንግስት እስካለመቀበል ድረስ በማተት "በታገል ጋዜጣ" ላይ አሳትመው አስነብበዋል። ህገ-መንግስት መናድና ጦረነት ቀስቃሽነት በሚል ግን ያለተከሰሱ መሆኑ ልብ ይሏል። ያኔ ዛረ አይደለማና። በጨቋ ማንነት በኩል ይሰበዘር የነበረው ሃሳብ ከሃቅ ያፈነገጠ ነበር። የብሄር ጭቆና ተንሰራፍቶብናል ለማለት የሚያስደፍር አልነበረም። የዚያን ዘመን ችግር የፊውዳላዊ ስርዓት ጭቆና ተጭኖብናል የሚል አገላለጽ ነበር የሚመጥነው። በተማሳሳይ በዚያን ዘመን አና ዛሬ ላይም "የብሄር ጭቆና ነበር" የሚሉ ቡድኖችን ሃሳብ ብዙ ተከታይ አፍርቶ የነበረ። ነገር ግን መሰረተ-ቢስ የችግር ትንተና መሆኑን ፕሮፌሰር ኃይሌ ላሬቦ እንደሚከተለው ገልጸውታል። "ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የዘውገኝነትና የአለም አቀፍነትን አስተዳደር ርዕዮተ-አለም የሚያራምዱ አንጃዎች ኢትዮጵያ የብሄር ብሄረሰቦች መታጎሪያ እስር ቤት ናት ያእሉ የሚሰብኩት ስብከት ተደማጭነትን

ከማግኘት አልፎ ብዙ ሃገር ወዳዶች ጭምር ሰይቀሩ እያወናበደም፣ እየማረከም ነው፤የሰባኪዎቹ አቋም የግል ጥቅማቸውን የማራመድ እቅድ ካላቸው ይጠቅማቸው ይሆናል እንጂ በኢትዮጵያ ታሪክ በየጊዜውና በተፈጸመ ተጨባጭ የመንግስት ተግባራትና መመሪያዎች አይደገፍም።" ፕሮፌሰሩ እንዳሉት የብሄር ጭቆና ዲስኩር ጥቅም አለው፤ ጨቋኝ ብሄርን በመሰየም የጋራ ጠላት (ጨቋኝ ብሄርን) በማድረግ ለመደራጀት አግዟል።

የብሄር ጭቆና አቀንቃኞች ብቅ ባሉበት ዘመን የካርል ማርክ ሶሻሊዝም በበርካታ የአለም አካባቢዎች አቢዮትን በመስበክ የመንግስትን አላስፈላጊነትን፣ የላብ አደር ገናና ስርዓትን ምስርታ አስፈላጊነትን በመተንተን እና የአለም-አቅፍ ወዛደራዊነት ሰበካ በአለም ላይ ላቅ ባለ ደረጃ ላይ ደርሶ ስለነበር ኢትዮጵዊያንም ለውጥ ፈላጊዎች ይህኑ ፍልስፍና ሳያንጓልሉ መቀበል ችለው ነበር። ፍልስፍው በአንድ የፖለቲካዊ ማህበረሰብ ውስጥ ሶስት መደቦች ስለመኖራችው፣ ከላይ ካፒታሊስቱ/ቡርዥዋው/ ከታች ላብአደሩ ከመሃል በቢሮክራሲው ለመንግስት በአገልጋይነት የተሰለፉ መደብ እንዳሉ በመግለጽ፤ እነዚህ አደራጃጀቶች ለብዙሃኑ ጭቆና ምንጭ ናቸው ብሎናል። ቡርዥዋው የመንግስትን እጅ የሚጠመዝዝና ለራሱ ምቹ ህጎችን የሚያስጸድቅ፣መካከለኛው መደብ ለመንግስት የሚያገለግል በአጠቃላይ መንግስትም ስርዓቱም የቡርዥዋው መጠቀሚያ የብዙሃኑ ላብአደር የስቃይ ምንጨ ናቸው በማለት በሚያሳምን ምልኩ አቅርቧል። የዚህኑ ፍልስፍና በማጣቀስ መፍትሄው የላብአደሮች አቢዮት መሆኑን ለሰፊው ህዝብ በተራማጅ ልሂቃኖች ተቀነቀነ።

ስለሆነም ላብ አደሩ የዚህን አደረጃጀት በአቢዮት በማፍረስ መንግስትንም ላንዱና ለመጨረሻ ጊዜ አሰናብቶ የላብአደር ቢሮክራሲ በመዘርጋት የኢኮኖሚዊ ፍትህ ከሰፈነ፤ ይህ ፍትህ የብዙ ችግሮች መፍትሄ እንደሚሆን በመስበኩ በኢትዮጵያዊያንም ቅቡልነት አገኘ። ነገሩ ግን ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ እጅግ የራቀ በመደብነት የተቀመጡት አደረጃጀቶች ኢትዮጵያን ሳይሆን አውሮፓን የሚመለከቱ ነበሩ። ለምሳሌ ላብ አደር በሚል በአምራች ድርጅት፣ ፋብሪካዎች ጉልበታቸው የሚመዘበሩ ተገቢ ክፍያ የማያገኙ ተብለው በሚወሰዱ ሰዎች ልክ ጭሰኛ ገበሬ ሲኖር በማርክስ እይታ ቡርዥዋ በሚባለው ደግሞ ምንም ታጣ። ምክንያቱም ኢትዮጵያ በበሰበሰ ፊውዳል ስርዓት ውስጥ ነበረችና። ስለዚህ የችግር ትንተናውም መፍትሄውም ለኢትዮጵያ የማይገጠም (unfit) ነበር። ይህ ያለመጣጣም ግራ ያጋባቸው የወቅቱ የማርክስ ፍልስፍና አራማጅ፣ ለውጥ የተጠሙ ልሂቃን ጉዳዩን ወደ ብሂር ወሰዱት። ካፒታሊስት/ቡርዥዋ/ በሚለው ልክ አማራ የሚባል ብሄር እንደተመደበ ሁሉ በአማራ ብሄር

ላይ የፍረጃ ናዳዎች ተስተናገዱ። ከዚህ መሃል የሶሻሊዝም አለም-አቀፋዊ ላባ አድርነት በመፈክር ደረጃ ቢስተጋባም በተግባር በብሄር መደራጀት እና የትግል አቅጣጫውን ከዚሁ ጋር የማያያዝ ስራ ተጠናክሮ ቀጠለ። የዚያህን ዘመን የሶሻሊዝም አቀንቃኞች የነበሩ ልሂቃኖች የአቋም ለውጥ በማድረግ ከአለም አቀፋዊ ብሎም ከብሄራዊ ስሜት ወደታች ዝቅ ብለው በብሄር (ethnic) ፖለቲካ ላይ መጣበቃቸውን በጥልቅ ጥናት ከተደገፈው የፕሮፌሰር መስፍን አገላለጽ መረዳት ይቻላል። ፕሮፌሰሩ አዳፍነ በተሰኘው መጽሃፋቸው በገጽ 17 ላይ "የወቅቱ ተራማጅ ነን ባይ ጥራዝ ነጠቆች መጀመሪያ ላይ የፖለቲካ እምነታቸውን ከብሄራዊ ስሜት አሳልፈው አስተሳሰባቸውን በጣም ሰፊ አድርገው በአለም አቀፋዊ ወዛደርነት ላይ የመሰረቱት ሰዎች አንድ ትወልድ ሳያልፍ የፖለቲካ እምነታቸው ቀኝ ኋላ ዙር ብሎ ጠበበና ከአለም አቀፍ ወዛደራዊነት ወደጎሰኝነት ተለወጠ" ይሉና። እዚህ ላይ ዋናው ጉዳይ የዚያን ዘመን አለም አቀፍ ወዛደርነትን ያቀነቅኑ የነበሩ ተራማጆች ዛሬ ላይ የብሄር ፖለቲካውን ዋነኛ የስልጣናቸው ማቆያ ያደረጉ እና የኢትዮጵያ ችግሮችን ከአማራው ልሂቃን ብሎም ከአማራ ህዝብ ጋር በማስተሳሰር የሚያስነግሩ ከመሆናቸው ላይ ነው። የአማራ ልሂቃን ከአማራ ህዝብ ነጥሎ ማየትም አልተቻለም ነበር።

ላብ አደር ስላልነበረም ጭሰኛ አርሶ አደሩን ላብ አደርን እንዲወክል የማድረግ አዝማሚያ ታየ። ከበውቀቱ ስዩም ጽሁፎች በአንዱ ላይ እንዳነበብኩት ባህር ዳር ላይ ቀድሞ ይርመሰመስ የነበረው አሳ በተለያዩ ምክንያቶች በመጥፋቱ አሳ ያማረው ሰው በጉን ገፍትሮ ከከተተው በኋላ አሳ "ነህ ብየሃለሁ አሳ ነህ" ብሏል አሉ። እንደገናም በመካከለኛው መደብ ልክ የሚታይን የማህበረሰብ ክፍል ለመመደብ ቀላል ስለነበር ተራማጆች ችግር አልገጠማቸውም። የመንግስት ሰራተኛው፣ የሙያ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የጦር ጀነራሎችና ምሁሮች ተመደቡ። እንግዲህ ይህ ለነባሪዊ ሁኔታው የማይመጥን የተውሶ ርዕዮት- አለም የውስጥ ችግርን በሃገር በቀል መፍትሄ የለመፍታትና የሃገራዊ ችግሩን ከምዕራባዊያን ፖለቲካዊ ሁነት ጋር አጋኖ የማነጻጸር ውጤት ነው።

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም የዚህን ዘመን ችግርና ከራስ የመነጨ፣ ስለእራስ ችግር የራስን ግንዛቤ በመያዝ የመፍትሄ አቅጣጫ በመንደፍ ረገድ ያልተሳካልን እንደነበር ለማሳየት የሚከተለውን ሃሳብ ይገልጹታል። ‹‹--- ወሰን የሌለው የሃብታሞች ስርዓት በደርግ ጊዜ ‹‹ሰው በላ›› ስያሜ የተሰጠው ካፒታሊዝም ጸረ-ሰብአዊነት ነው፣ ሰውን ከነነፍሱ ወደሚሸጥ እቃነት ይለውጣል፤ በአሜሪካ ካፒታሊስት ፍልስፍና የሚያራምደው አስተሳሰብ ዋጋው ይለያይ እንጂ ሰው ሁሉ እንደመንኛውም ሸቀጥ ዋጋ አለው የሚል ነው፤ የሰውን ልጅ ከዚህም በታች

ማውረድ አይችልም[14]›› ፕሮፌሰሩ እንደሚሉት ዘመኑ ተውልድ የራሱን ችግር በሰከነ አግባብ መፈተሽ የሚያስችል ምርምር ከማድረግ ይልቅ በሶሻሊት ጸሃፊዎች የተነገሩ የመፈክር ቃላቶችን የሚፈትሽ እንደነበር ይታማል።

ይህ አስተሳሰብ በነገሰበት ወቅት እንኳን የአማራ ህዝብ የመከራ ገፈትን ቀማሽነት አልተረፈም ነበር። የተራማጆች ሶሻሊስታዊ የብሄር ትንተናና ኢትዮጵያ፡ ከጥንስሱ የተራማጁ ወገን ነን የሚሉት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ብሄር ተኮር ትንተናንና የፖለቲካ ጽንፍን ሲይዙ የዋለልኝ መኮንን የአማራን የጨቋነት ሃጢያት የሚያወሱ ጽሁፎች ለንባብ በቁ። ይህን የዋለልኝ መኮንን የብሄር ተኮር ቅስቀሳ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም የብሄር ጭቆና የሚለውን ውሬ "ፍሬ-ቢስነት የሚያሳያው ዋናው ሃዋሪያ ተብሎ የሚጠቀሰው ገና በትምህርትም ሆነ በልምድ ያልተፈተነ [15]ዋለልኝ የሚባል ወጣት ነው፤ ሌላ ቀርቶ በማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍናና በጎሰኝነት መሃከል ያለውን ቅራኔ አልተገነዘበውም ነበር" ይሉታል።›› እንግዲህ ብስለት በጎደለው ሁኔታ በወቅቱ በተፈጠረው የፖለቲካ ግለት ውስጥ የማርክሲዝም፣ ሌኒኒዝምና የስታሊኒዝም ፍልስፍናን ከብሄረተኝነት ጋር በማጣቀስ በአማራ ብሄር ላይ ጣትን የመቀሰሩ አካሄድ እየተንሰራፋ መጣ። ዋለልኝ ሁሉም የለውጥ እንቅስቃሴ ወደ ሶሻሊዝም የሚሻግር እንደሆን ከማሳሰቡ በተጨማሪ እዚህም እዚም የሚታይ የአስተዳደር በደልን የብሄር ጭቆናውን በማስመሰል አግዝፍፎና በቃላት በመከሸን ጽፎ ያስነብብ በነበረ ወቅት ተበድለናል የሚል ስሜት የነበራቸው ብሄሮች ራሳቸው ይህን ያህል ተበድለን ነበር እንዴ? ብለው እንዲጠይቅ የሚያደርግ ገነት እንደነበረበት ጽሁፉን የማንበብ እድል የገጠማው ጽሃፊዎች ይገልጻሉ። ዋለልኝ ግለሰቦችን ከብሄር ጋር በማያዝ ሁሉንም ነገር ከብሄር የበላይነትና የማስተሳሰር አባዜ እንዳለበት ከሚያስገነዝቡ ገለጻዎቹ አንዱ የጀነራል ታደሰ ብሩን የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ የኦሮሞ የበላይነትን ለማንገስ የታለመ ይለው እንደነበርና የገርማሜ ንዋይ እና የመንግስቱ ንዋይን ተመሳሳይ ተግባር ደግሞ የአማራ ጭቆናን ለማስቀጥል የተደረገ ነበር በሚል የሚተነትነው ሃሳብ ነው ውብሸት ሙላት፤ 2007 ዓ.ም.)። ይህ አይነቱ አስተሳሰብ

[14] መስፍን ወልደማሪም። (2004 ዓ.ም.)። አደጋ ያንጎበበበት የአፍሪካ ቀንድ። ገጽ 10።

[15]During the Haile Selassie and Derg period, it was fashionable to thrash Amaras as "chauvinists, Neftegnas, national oppressors", etc and repeating such words was even a mark of distinction that qualified one as a genuine radical revolutionary or progressive. One only needs to refer to the 1969 speech of Wallelign Mekonnen Kassa – a 24 year old young Amara radical student, who by then had hardly any understanding of the social and cultural history of the district of Borana Sayinet, his birth place, much less diagnosing and disentangling the intricate problems of the larger Ethiopian society. The inchoate Wallelign, who was not even drilled in the social history of his birth place, let alone understanding the dynamics of Ethiopian nationalism that eluded many before him, dubbed Ethiopia not a nation but nations (Ibid, 2012:5-6).

እየጎለበተ በመምጣቱ የሻቢያና ወያኔን አይነት ብሄር ተኮር የትጥቅ ትግል የመረጡ ቡድኖች የአማራን ብሄር ጨቋንነት ከማቀንቀን አልፈው ጸረ-ኦርቶዶክስ ክርስትና ብሎም ጸረ-ኢትዮጵያዊነት የፖለቲካዊ ጎዳና መከተል ጀመሩ፡፡ ዋለልኝ የራስን እድል በራስ መወሰንን እና መገንጠልን የሚደግፍ ነበርም፡፡ ነገር ግን መገንጠል ሶሻሊስት ስርዓትን ያሰፈነ የፖለቲካ ማህበረሰብ ለመመስረት በመሆኑ ላይ አስምርበታል፡፡ የዛሬ 25 አመት የተገነጠለችውን ኤርትራ ከተገነጠለች በኋላ ሶሻሊስት ለመሆኗን አይታት ቢሆን ኖሮ አስተሳሰቡ ሁሉ አጉል አጉል መሆኑን ከመረዳት አልፎ የራሱንና ደጋፊዎቹን የብስት ደረጃ መመዘን ይችል ነበር፡፡

ብሄር በሶሻሊዝም ፍልስፍና የሚኖረውን ቦታ ስንመለከት ማርክስ እንደሌኒን ስለብሄር ጉዳይ ባያትትም በተለያዩ ጊዜያት ከጻፋቸው መረዳት የሚቻለው የብሄር ጉዳይ ይመነጫል ብሎ የሚያምነው ከቡርጊዋው ስርዓት መሆኑን ነው፡፡ የቡርጊዋው መደብ የላብ አደሩን ክፍል ንቃተ-ህሊናው እንዳያድግ እንዲሁም እንዳይደራጅ ቀፍድዶ የሚይዝ ማነቆ እንደሆነ በመውሰድ ይህ የቡርዥዋው መደብ በአቢዮት ተደምስሶ ሲለወጥ የብሄር ጥያቄ አብሮ ድምጥማጡ ይጠፋል፡፡[16] በማርክስ ፍልስፈና መሰረት ይህ ካልሆነ የብሄር ጥያቄ የሚቀጥል ሆኖ ከአቢዮት መፈንዳት በኋላ ላብአደሩ ማስተዳደሩን ቦታ ሲረከብ ላብአደሩ በብሄር እንዲደራጅና እንዲያስብ የሚደርገው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚዊና ማህበራዊ ምክንያቶች እንደማይኖሩ እንገነዘባለን፡፡ ኢንግልስም ተመሳሳይ ትንተና የሚያቀርብ ሲሆን ሌኒን በበኩሉ ማንኛውም ሶሻሊስት ሃይል የብሄርም ቢሆን ሶሻሊዝምን ማሳለጥ እስከቻለ ድረስ ለታክቲካዊ (ለስልታዊ) ምክንያት ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል፡፡ በመሆኑም ለነሌኒን ብሄርተኝነትና የማርክሲዝም ጋብቻ /ትስስር/ የብሄር አስተሳሰቡ ትርጉም የሚሰጠው ሶሻሊዝምን አስካመጣ ድረስ ነው፡፡ ይህ በታክቲካዊነት እውቅና የሚሰጠው የብሄር ጉዳይ ሶሻሊስም ሲሰፍን አብሮ ይከስማል በሚል ነው፡፡ ሌኒን አሲምሌሽን (Assimilation) ውህደትን የሚደግፍ ሲሆን የመዋሃዱ አስፈላጊነት የብሄርን መክሰም ስለሚያሰፍን ነው፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ሶሻሊስቶች ለየት ባለመልኩ ስታሊን ብሄሮች በሶሻሊዝም ስርዓት ምስረታ የሚከስሙ ሳይሆን አናሳም ሆነ አልሆኑ የራሳቸው ግዛት እንዲኖራቸው፣ መብታቸው እንዲከበርና እኩል መብት እንዲኖራቸው ጥሯል (ውብሸት ሙላት፣2007 ዓ.ም.)፡፡ እራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር ከቻሉ በከበርቴውና በሌሎች ሰርዓቶች ውስጥ ከሚኖራቸው ግንኙነት በተሻለ መልኩ በመካከላቸው አንድነትና መተባበርን ስለሚያዳብሩ “ሶሻሊስታዊ ብሄሮች” ይሆናሉ፤ከዚም ወደውህደት ሊያመሩ ይችላሉ፣ ሶቪየት

[16] Walker Conner (1994).the national question Marxist Leninist theory and strategy. Princeton: Princeton University press.

ህብረትን እንደየአንድብሄር ሃገር እንድትሆን ይረዳል፤ ውሎ አድሮ አንድ የጋራ ቋንቋና ባህል ያዳብራሉ የሚል ሃሳብ ስታሊን እንደሚያቀርብ ውብሸት ሙላት የሳይመን ጀራርድን (1991 እኤአ) ትንተናን ዋቢ አድርጉ ጽፏል፡፡ ከዛሬዋ ኢትየጵያ ሁኔታ ጋር ስናነጻጽረው የፈደራላዊ ስርዓታችን በስታሊን ፍልስፍና የተቃኘ ስለመሆኑ አስተያየት መስጠት ተገቢነት የሚሆንበት አግባብ አለ፡፡ ስታሊን በራሽያ ይሆናል እንዳለው የስርዓቱ ቆንጮዎች ሃገሪቱ በተለያየ ሁኔታ ትስስር እያዳበረች በመጣች ቁጥር በጠነከረች አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ የፊናቸው በተደራጁ ብሄር ብሄረሰቦችን እንመሰርታለን የሚል አቋም ያንጸባርቃሉ፡፡ ነገር ግን የጋራ ቋንቋና ባህል ያዳብራሉ በሚለው ከስታሊን ጋር የሚጣጣም አተያይ የላቸውም፡፡

ወደኢትዮጵያ ተራማጆች እንመለስና የሶሻሊዝም ርዕየተ-አለም በሃገሪቱ ሰፍኖ በነበረበት ስርዓት ኢትዮጵያ ከነበረችበት ደረጃ ወደኋላ ተንሸራታ ዝቅጠት ውስጥ መግባቷን ሃቅ ነው፡፡ አቢዮትን አቀንቃኝ ተራማጆች ከደርግ ጋር በፈጠሩት የስልጣን እሽቅድድም አንዳንዶቹም በደርግ ውስጥ ተለጥፈው ለውድቀቱ የየራሳቸው ድርሻ ማበርከታቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተለይ ሁሉም ሶሻሊስት ነን ባዮች እርስ በርሳቸው የተጠፋፉ መሆኑን እና ሃገሪቱን ወደለየለት ጦርነት እንደዘፈቋት ከማየት በተጨማሪ በአለም ደረጃ የሶሻሊስት ስርኣት ውድቀት የዚያን ዘመን ተራማጂነት አስተዋይነት የጎደለው፣በስሜታዊነት ይመራ የነበረ መሆኑን እንረዳለን፡፡

ስጠቀልለው ተራነማጆች የነበሩት ኢትዮጵያዊን ሶሻሊዝም ስርዓትን ለማስፈን ያደረጉት ግስጋሴም ስለብሄር ጨቆና አብዝተው ያሰነገሩተና የጻፉት ለአሀኗ ኢትየጵያ ያበረከተው ነገር ቢኖር ውድቀት ነው፡፡ ያኔ ለታክቲክነት ታሰቦ ቢሆን ብሄሮች እንዲዳራጁ፤ ለመደራጀቱ ሃይል እንዲሰጥ አማራን የጋራ ጥላት አድረገው የሶሻሊዝም ጉዞን እንዲፋጠን ያደረጉት ጥረት አስተዋይነት የራቀው በመሆኑ ለዛሬ በአማራ ላይ ለሚፈጸመው በደል አስተዋጾየው የጎላ ነው፡፡

የደርግ አገዛዝ

በጎርጎረሳዊያን አቆጣጠር 1974 አቢዮች ፈነዳ፡፡ ያኔ ወታደሩ በለስ ቀናው ስልጣን ያዘ፡፡ የለውጥ አቀንቃኞችን ስሜት ማዳመጥ ሞከረ፡፡ ብዙውን አስተሳሰባቸውን በፖሊሲው አካተተ፣ የቀድሞውን ስርዓት አመራሮች ገደለ ማህበራዊና የኢኮኖሚ መሰረቶቻቸውን አወደመ፡፡ ሶሻሊዝም ፍልስፍናው ከሚያስቀምጠው መሰረታዊ መርሆች መሚላት ባይችሉም አቢዮች

አደረግን ተባለ፡፡ ይህ ለውጥ አቢዮት በመሆኑ ላይ የአቋም ልዩነት የለኝም ሶሻሊስት አቢዮት ስለመሆኑ ግን እንጥፍጣፊ እምነት የለኝም፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ የአማራ ብሄር የተባለው የገዢ መደብ በሚል ተፈርጆ ስቃዩን መብላት ጀመረ፡፡ አቢዩቱ አማራን ይበላል የሚል መሰለ፡፡ በብሄር የተደራጁ ቡድኖች ይህኑ የአማራን ሀጢዓት አግዝፈው አውሩ፡፡ ችግር የተባለ ነገር ሁሉ አማራ ነው፡፡ ብለም የኦርቶዶክስት ክርስትና ተወቀሰች፡፡ ጉዳዩ የምር የመሰለው የደርግ ወታደራዊ መንግስትም የአማራ ገዢዎች ናቸው ብለው የነገሩትን ወይም በስማበለው በመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) ተራማጆች የተነገረውን በመንተራስ አሳደደ፡፡ ከንጉሱ ስርዓት ጋራ ያልተነካኩትን ጭምር እየለቀመ ገደለ፣ ለስደትም ተዳረጉ፡፡ ይህ ሁሉ ቢደረግም ደርግ በኢትዮጵ አንድነት ያምናልና ለኢትዮጵያ አንድነትና የግዛት ህልውና የቆመ ስለነበረ አማራ ኢትዮጵዊነትን ስለሚያስበልጥ እንደብሄር የተጋረጠበትን አደጋ ለመመከት አልሞከረም ነበር (ጋሻው መርሻ፡ 2008 ዓ.ም)፡፡ በእርግጥም የአማራነትን አርማ ያነገበ ትግልና ድርጅትም አልነበረውም፡፡

አማራ ኢትዮጵያዊነትን ትከሻው እስከሚጎብጥ ተሰክሞ ቆይቷል፡፡ ግን ትረጉም አልባ ትጋት ሆኖበት ኢትዮጵያ ስትጎራብጠው ዛሬ ላይ ደርሰናል፡፡ የአማራ ህዝብ የህዝብ እልቂትና ጥፋት ግንባር ቀደም ኢላማ ሆኖ እንደተጨፈጨፈና በተለይም ይህ የህዝብ እልቂት በሰሜን ሸዋ ላይ ትኩረት ተሰጥቶት በመንዝ በመርድ ብሩና በመስፍን ብሩ መሪነት፣ በመርሃቴ፣አውራጃም በአርሶ አደሩ ግንባር ቀደምትነት የተንቀሳቀሰው አማራ ደርግን በመጀመሪያ የተጋፈጠው ህዝባዊ ሃይል እንደንበረና በዚህም የተነሳ ያለማቋረጥ ሰባት አመት በፈጀው የደርግ የአየር ጭፍጨፋ ያለቀው የሰሜን ሸዋ ህዝብ የሚታወስ መሆኑን ጋሻው መርሻ በ2008 ዓ.ም. ጽፎታል፡፡ በቀይ ሽበር የደብረብርሃን ህዝብ ማለቁ የሚዘነጋ አይደለም፡፡ ጎንደርም በመላኩ ተፈራ ሽዎችን (የአማራ ልጆች) ለቅሶ እንኳን በማይፈቀድበት አኳኋን ቀበረች፡፡ ይህን በጊዜውና በቦታው ሆኖ የታዘበው ባቢሌ ቶላ የትውልድ እልቂት በሚል ርዕስ በ1989 ዓ.ም. ባሳተመው መጽሃፉ ገጽ 172 ላይ በቀይ ሽብር ወቅት በደርግ የተሰነዘረው መጠነ ሰፊ ሽብርና ግድያ በሁሉንም የሃገሪቱን አካባቢዎች ያዳረሰ ቢሆነም “አሰቃቂ ጭፍጨፋ የተካሄደው በአማራው አካባቢ ነው” ብሏል፡፡ ሃቁ እንዲህ ነው፡፡ በአማራ ምድር ልዒቃኑ ተማግኗል፤ ስለሆነም የትውልድ ክፍተት ተፈጥሯል፡፡

ከላይ ያሉት አገላለጾች የኦሮሞ ልጆች በአዲስ አበባ፣ ጂማ፣ አርሲ ወዘተ… ጉራጌው ሲዳማው፣ ትግሬው እና ሌሎችም በተለያዩ አካባቢዎች የስርዓቱ ሰለባ መሆናቸው የታሪካችን

አካል መሆኑን ከመዘንጋት የመነጨ ሳይሆን የጽሁፉ አላማ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ አማራዊነትን በሰፊው በልታው ያልጠገበች መሆኗን በማስረጃ አስደግፎ ማሳየት በመሆኑ ነው፡፡ ምክንቱም አማራ ያልበላውን እዳ እየከፈለና በስርዓቶች ጫና ከነበረበት የማህበረ-ፖለቲካ ደረጃ ከጊዜ ወደጊዜ ዝቅ እያለ በርካታ አስርት አመታት ተቆጥሯል፡፡ በተለይ ካለፈው 50 አመት በፊት ጀምሮ እየተጋፈጠው ያለው ጥቅል ዘር ተኮር አደጋ በሌሎች ብሄረሰቦች እየተከሰተ ካለው የሚልቅ ነው፡፡

ከምንም በላይ አስገራሚው ነገር ትላንትናና ዛሬ የሃይለስላሴ እና የድርግ ስርዓት የአማራን ተጠቃሚነት ለማስቀጠል የሚያግዙ እንደነበሩ በማሰመሰል እንዲሁም አማራ በስርዓቶቹ ተጠቃሚ እንደነበር ለማስመሰል እየተሰራ መሆኑ ነው፡፡ ከላይ በጥቂቱ የጠቀስኩትንና ሌሎች ያልተዘከሩ አስከዛሬም የዘለቁ በደሎች በጥናት ያረጋገጡት ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ በሚከተለው መልኩ ለማስረዳት ሞክረዋል፡፡

> *“አማራው በሶሎሞናዊው ስረዎ-መንግስት ውስጥ ዋና የስልጣን ባለቤት እንደነበረ ተቆጥሮ እስከዛሬ ድረስ ለዘር ጥቃት ሲጋለጥ፣ እየተገለለ ሲፈናቀል፣ ሲሰቃይ እና ሲገደል ኖሯል፡፡ ምንም እንኳን ከነበረው ከማንኛውን ከመንግስት እና ወታደራዊ ስልጣን ከተገለለ አርባ አመታት ያለፉ ቢሆንም አሁንም ስልጣን ላይ እንዳለ እየተቆጠረ የዘር ጥቃት ሆኖ ይገኛል፡፡ በእርግጥ አንዳንድ የጎሳ የፖለቲካና ቡድኖች እርስ በርሳቸው ሙሉ በሙሉ ተጻራሪዎች ሆነው ሳለ ህብረትና አንድነት ለመፍጠርና ስልጣን የመያዝ ፍላጎታቸውን ለማርካት አማራውን እንደ ጋራ ጠላታቸው ቆጥረው ጸረ-አማራነትን የመጠናከሪያና የመሰባሰቢያ ብልሃት አድርገው ሰርተውበታል”* (ፍቅሬ ቶሎሳ፣ 2008ዓ.ም.፡7)፡፡

ይህ አገላለጽ በቀጥታ ከፕሮፌሰር ላሬቦ የጥናት ወጤት ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡ ፕሮፌሰር ፍቅሬ በልምድም ይሁን በሙያዊ ምርምር ካገኙት እውቀት ከ40 አመት በፊት አማራን የሚያስተናግድ ፖለቲካዊ ስርዓት እንዳከተመ አረጋግጠዋል፡፡ ከጽሁፋቸው እንደምንረዳው የአማራ ብሄር በሁለት መልኩ እየተበደለ እንዳለ ነው፡፡ በቅድሚያ ከፖለቲካዊና ወታደራዊ ስልጣን የመገፋትና ህዝቡ እንደህዝብ ስለራሱ የሚወስንበት ውክልና ተነፍጎታል፡፡ ሁለተኛ የጋራ ጠላታችን ብለው አማራን የፈረጁ የጎሳ ቡድኖች አሁንም ጨቋኝ እንደሆነ በማስመሰል የዘር ጥቃት እንዲገጥመውና በዚህም የተነሳ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ጥቅሞት እንዳያገኝ በተለያየ መልኩ ከማድረግ በተጨማሪ ቀድሞ ከነበረበት ደረጃ ቀስ በቀስ እንዲያሽቆለቁል የሚያደርግ ጫና እየተደረገ ስለመሆኑ መረዳትም ይቻላል፡፡

በንጉሱ አገዛዝና በደርግ መንግስት የአማራ ልሂቃን ብሎም ህዝቡ ተደላድለው የኖሩ እንዳለሆኑ ገሃድ የወጣ የታሪክ ሃቅ ነው፡፡ ስርዓቶቹ የአማራ ልሂዋንን የሚያሳድዱም ነበሩ፡፡ ለአብነት

በደርግ ዘመን የአማራ ልጆች የወታደራዊ ስርዓቱን በመቃወም በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ህብረት (ኢዲዩ)፣ በኢትዮጵያ ኢቢዮታዊ ህዝባዊ ፓርቲ (ኢህአፓ)ና በመላው ኢትዮጵያ (መኢሶን) ውስጥ ተሰልፈው የግፍ ጽዋ ተጎንጭተዋል። በደርግ ውስጥም የአማራ ልሂቃን የተሳተፉ በመሆኑ በተቃራኒው የተሰለፉ ቡድኖች የጥቃት ሰላባ አድርገዋቸው ነበር። ስርዓቱ እርስበርሳቸው እንዲተላለቁ በማድረግ የአማራን አንድ ትውልድ በልቶ ሌላኛውን ትውልድ ለሌላ በላተኛ አጋፍጦት ሄዷል። በተጨማሪም አስገንጣዮችንና ገንጣዮችን በመመከት ኢትዮጵያን ለማዳን በተደረገ ከ17 አመታት በላይ በዘለቀ ግብግብ የአማራ ሰማዕታትን መዘንጋት የሚቻል አደለም። ይህ ሁሉ ተደማምሮ በአገር ውስጥ አማራ በትውልድ እልቂትና በልሂቃን ድርቅ ተመታ። ለስደትም የተዳረገውም የትየለሌ ነው። በስደት ያለው ልሂቅ በቁጥርም በአቅምም የተሸለ እንደነበርና አሁንም በተወሰነ መልኩ የዘውግ መስመርን የሚከተሉ እንዳሉ ሁሉ የአንድነት መንገድ (pan-ethiopianist) በማቀንቀን ከተሰለፉ ቡድኖች ተርታ በብዛት እንደሚገኝ ይታወቃል።

የህወሃት/ኢህአዴግ የፖለቲካ ካርድና የአማራ የበላይነት ትርክት

ይህ ድርጅት የቀድሞ ታሪኮቻችን የመጥፎዎች ሁሉ መጥፎ አድርጎ ከሰማንያ ሶስት ወዲህ የተመሰረተው ስርዓት የችግሮቻችን ሁሉ መፍትሄ ተደርጎ ይነገራል። የታሪክ ትምህርት ቤቶችም ቦታቸውን ለስነ-ዜጋና ስነ-ምግባር እየለቀቁ ነው። ስርዓቱ በግድም በውድም ዋሽቶ የሚያስዋሻቸው ዜጎች እየበዙ ነው። እዚህ ላይ ኃይለመለኮት አግዘው የተባለ ጸሃፊ ጥቅምት 19 ቀን 2009 ዓ.ም አዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ የጻፈውን ልጠቅሰው ወደድኩ። እንሆ "አንድን ነገር ነጭ ነው ለማለት አጠገቡ ጥቁር መቀባት ያለበት አይመስለኝም ብሏል። በራሱ ነጭ ነጭ ነው፤ ሳይንሳዊ ትርጓሜ ያለው። እንደዚሁም የዛሬው ስርዓት ለማወደስ የቀድሞውን ማጉደፍ ኣያስፈልግም፤ መልካም ነገር ካለ መልካም ነገር ራሱ በመስክርነት የሚታይ ነው። እያንዳንዱ ዜጋ ላይ እንጥፍጣፊ ስለሚኖረው ተጋሪም አያሻም። አቶ ልደቱ አያሌው በ2009 ዓ.ም. ፋና ባደራጀው ስብሰባ እንደተናገሩት፤ ሚዲያዎች በከንቱ ውዳሴ ስርዓቱን ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ ህዝቡንም በታሪኩና በባህሉ ላይ ጥላቻ እንዲኖረው አድርገዋል"። ገለጻው እውነትንት አለው። እኔ አስከገባኝ ድርስ የስርዓቱ ደቀመዛሙርቶች ታሪካችን ጠልፎ እንዲጥለን ተግተው ሰርተዋል። ይህ አይነት አድርባይነትና ተወናብዶ ማወናበድ የትላንትናው ታሪካችን አካልም እንደነበር የሚታውቅ ነው። ኃይለመለኮት አግዘው (ጥቅምት 19 ቀን 2009) እንደጻፈው "እያንዳንዱ ስርዓት አድርባይ ባንዳ ይቀላቀለዋል" ካሉ በኋላ ጣሊያን ኢትዮጵያን

ለመበታተን እየሰራች በነበረበት ወቅት በመስከረም 13 ቀን 1929 ዓ.ም. ነጋድራስ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ "የቁሳር መንግሥት መልዕክተኛ" በሚባለው ጋዜጣ ላይ ባወጡት ፅሁፍ የንጉስን ስድትና ክብራቸውን አናንቀው የአርበኞችን ትግል አንቋሸው እንደነበር አስታውሶናል።

ሆኖም ጣሊን ባዕድና ወራሪ ነው፤ ችግሩ መሰረታዊና አለደገኛ የሚሆነው ሃገራዊ ስርዓቱን የሚመራው ኢትዮጵያዊ ሃይል በታሪክና በሃገራዊ አንድነት ላይ ባንዳ ሲሆን ነው። ይህም ችግር ስርዓታዊነት ስለተላበሰ ዛሬ ላይ በአርበኝነት የተሰለፉትን እውነት ነጋሪ አባቶችን የሚሰማቸው የመንግስት አካል ጠፍቷል፣ በሰሚ ሰሚ ታሪክ የሚናገሩና የአድር ባዮች ቁጥር በርክቷል። "ኢትዮጵያዊ ማንነትና የጋራ ራዕይ ቅድሚያ ይሰጣቸው" ያሉ ተቆርቋሪዎችም ትምኪተኛ በሚል ተወንጅለዋል፣ ሃሳባቸውም ተገፍቷል።

በዚህ ጽሁፍ የኢትዮጵን ታሪክ ከብዙ ሽህ አመታት በላይ አስመዝግቧል የሚለውን አረዳድ ተቀብየ ለታሪክ ማጣቀሻ ብጠቀምበትም የጽሁፉ ዋነኛ ማጠንጠኛ ዘመናዊ ኢትዮጵያ ናት። ምክንያቱም ለዛሬው ፖለቲካዊ መስተጋብራችን ጉልህ ፋይዳ ያለው ፖለቲካዊ ማንነትታችን በብዛት ከዚያን ዘመን ጋር ንክኪ ያለው በመሆኑ ለሃሳቤ ማስደገፊ የሚሆኑ ታሪኮችን ከዚያው ጀምሬ ልመዝ ወድኛለሁ። ዋና ትኩረቴ ግን የድህረ-ሰማንያ ሶስት የዘውግ ፖለቲካውን ከላይ በተጠቀሱት ተለዋዋጮች በኩል መፈተሽ ነው። በጽሁፉ "ብሄር" የሚለው ገለጻ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ-መንግስት የተሰጠውን አተረጓጎም መውሰድ የጽሁፉን ዋና ጉዳይ ከወቅቱ የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ሁኔታ ጋር ማስተያየት ስለሚያስችል በህግ-መንግስቱ አንቀጽ 39 (5) ላይ ያለው አተረጓጎም እንዳለ ተወስዷል። ብሄር የሚለውን ቃል ዘውግ በሚል ተተክቶ የተጻፈበት ሁኔታም ስላለ ተመሳሳይ ትርጓሜ እንደተሰጣቸው እንገንዘብ።

አበቃቀሉ የተዛነፈ ጽድ

ጥንት በ1967 ዓ.ም. ሕወሓት እንደጠላት የአማራን ህዝብ በመኒፌስቶ ደረጃ ፈርጆት እንደነበር የሚታወስ ነው። የትላንቱ ተስፋችን ይህን አፍራሽ ከውሸት የመነጨ ሃሳብ እርግፍ አድርገው ይጥሉታል ብለን ነበር። ነገር ግን ተስፋችን ምክንያታዊና ትክክል ስለመሆኑ እንድንጠይቅ የሚያስችሉ ክስተቶች በላይ በላ እየተደራረቡ ታዩ። በሌላ አባባል የህወሃት መኒፌስቶው ኋላ ላይ ማንስተካከያ ቢደረግበትም አስተሳሰቡ ከመሪዎቹ ልቡና መፋቁ ላይ መተማመኛ እጠፋና።

ስርዓቱን አብጠርጥረው የሚያውቁት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ከጅማሮው ሰንቀነው ነበረው ተስፋችን ከአላዋቂነት የመነጨ እንደነበር በሚያሳይ አግባብ እንደሚከተለው ጽፈዋል።

“ወያኔዎች በ1983 ዓ.ም. ከጫካ ሲወጡ የያዙትን ሃሳብ ያንኑ በ1967 ዓ.ም. ጫካ ሲገቡ የነበራቸው ነበር” (መስፍን፡ 2007 ዓ.ም.፡ 258)፡፡ በስርዓቱ ሲሰበኩ የምንሰማቸው የበዳይ ተበዳይ ቅስቃዎች የድርጅቱ አቋም ከዱሮው ፈቀቅ ያለማለቱን እንድንገነዘብና የፕሮፌሰሩን ሃሳብ እንድንጋራ የሚገፋፋን ነው፡፡ ሁኔታ አበቃቀሉ የተዛነፈ ጽድ መቃን አይወጣውም ከሚለው አባባል የሚገጥም ነው፡፡ በተለይ የአማራ ልሂቃን በደቡቡ ህዝብና በኦሮሞው ላይ ስለፈጸሙት በደል ማስወራትና አጣፍጦ መጻፍ በትጋት የተሰረበት ጉዳይ ነው፡፡

እንደእውነቱ ከሆነ አማራ ለህወሃት ባለውለታ ነው፡፡ በደርግ ግፍ የተዋለበት ህዝብ መሬቱን ለምሽግ፣ ቅሉን ለውሃ እያዋሰ ሕውሃትን ከግብዓተ መሬት እየታደገ የምኒልክ ቤተ-መንግስት እንዲቀዳጅ ማድረጉ የሚዘነጋ አይደለም፡፡ ትግሉም እንዳለ ሆኖ፡፡ በደርግ ላይ ሰፈነው ጥላቻ የሕወሓት/ኢህአዴግ ጦር በአማራ ክልል እንዲታቀፍና ሊንቀሳቀስና ሊደገፍ ችሏል፡፡ ይህም ከአላዋቂነት ወይም ከየዋህነት የመነጨ ተስፋ ነበር፡፡

ህወሃት አማራን እንዴት ሊጠላ ቻለ? የድርጅቱና አመራሮቹ በአማራ ህዝብ ላይ አሳድሮች ስለነበረው የተዛባ የጠላትነት ስሜት ስረ-መሰረት የታሪክ ሂደቶችን በማጣቀስ ከሚያስረዱ ምሁራኖች አንዱ የሆኑት ደ/ር ጌታቸው ረዳ ጉዳዩን እንደሚከተለው ያስረዱናል፡፡ “የትግራይ ልሂቃን በምኒልክ ላይ ጥላቻቸው የበረታበትን ምክንያቱን እንዲህ ያስረዳሉ፡፡ ዮሐንስ ከሞቱ በሓላ ዘውዱ በምኒልክ ሲተካ፤ ትግሬዎች ከፍተኛ የሆነ “የባዶነት ስሜት” ወይንም ‘emptiness’/ a sense of generalized boredom) ተሰምቷቸዋል”፡፡ የባዶነት ስሜት ለምን ሊሰማቸው ቻለ ለሚለው ጥያቄ? ዶክተሩ ያብራራሉ፡- “የትግሬ ሕዝብ ለዘመናት በራሱ አስተዳዳሪዎች የመገዛት ልምድ ከዘመነ አክሱም ጀምሮ የቆየ እንደሆነ ያስባል፡፡ የካባቢው ሕዝብ ምንም የከፋ ስርዓትና ጨካኝ ገዢ ቢሆንም በአካባቢ ገዢ የመገዛት ፍላጎታቸው የበረታ ነው።” *ለዚህ አስተሳሰብ ልዩ የመነሻ ምክንያት አለውን?* ያብራሩታል፡- “ምክንያቱም ስልጣን የያዘው ሕዝቡ ሳይሆን ገዚዎቹ ቢሆኑም “ስልጣን የያዙ ገዢዎች ትግሬዎች ከሆኑ፤ የትግራዋይነት ጉልበትና የበላይነት ስሜትን በስነ-ልቦናቸው እንዲቀረጽ በማድረግ በሌሎች ጎሳ ገዢ መደቦች ላይም ሆነ በሌሎች ጎሳዎች ላይ የበላይነት ስሜት አንዲያድርባቸው ሆኗል።” ዳግማዊ ምኒልክን በተመለከተስ? የዶክተር መልስ፡- “ትንንሽ ግጭቶች ከግጭትንት አልፈው ስልጣን በያዘው የሽዋ ልሂቃን ላይ ዘመን ተሻጋሪ ጥላቸው እያተረፈ ቆይቶ በምኒልክ ፊታውራሪነት የአድዋ ድል ከተገኘ ማግስትም የስልጣን ተቀማን ስሜትና ጥላቸው አይሎ እንደቆየ ይነገራል፡፡” በተጨማሪም ከአድዋው ድል በፊት በጣሊያን

ቁራሽ ሹመት ተሰጥቷቸው ለጣሊያን ሲያገለግሉ የነበሩ የትግራይ ልሂቃን እንዲሁም ልጆታቸው የምኒልክን ሰልጣን ከአማራነት ጋር በማስተሳሰር በአማራ ልሂቃን ላይ ጥላቻን ሰንቀው እንደቆዩም የጌታቸው ጽሁፍና ሌሎች በርካታ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡

ከለይ አንደምንመለከተው ጌታቸው በጽሁፋቸው "ትግሬዎች" የሚል አጠቃቀም አላቸው፡፡ በእኔ አረዳድ ትግሬ የሚለው ገለጻ የትግራይ ልሂቃንን የሚያመለክት ነው፡፡ በግሌ ከዚህ አረዳድ ውጪ በሆነ መልኩ ትግሬዎች በሚል መደምደም የትግሬ ብሄርን በአንድ ቋት አስገብቶ መፈረጅ አመክኗዊነት ይጎድለዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡ በዛሬዋም ኢትዮጵያን ጭቆና ስንዳስስ በህወሃት ስር የተጠለሉትን ልሂቃን አምባገነንነት ከችግሩ ጋር በማነጻጸር ከማየት ውጪ በህዝብ ደረጃ የሚለካ ችግርን ለመተንተን የሚያስችለን የታሪካዊና ፖለቲካዊ አመክንዮ የለም ባይ ነኝ (ሆኖም የቱንም አይነት ትርጓሜ ያለው ቃል ቢጠቀሙም የዶክተሩን አሳብ እንደማከብር ለመግለጽ እወዳለሁ)፡፡

በተጨማሪም የትግራይ ልሂቃኖቹ በአማራ ልሂቃን ብሎም በህዝቡ ላይ የከረረ የባላጣነት ስሜት እንዲይዙ የረጅም ጊዜ ስራ መሰራቱ የሚካድ አይደለም፡፡ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ በጎርጎረሳዊን አቆጣጠር በ1990 ከፖል ሄንዝ ጋር ያድረገው ቃለ ምልልስ ይህንኑ ሃቅ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በሁለቱ ግለሰቦች ንግግር መሃል መለስ "በግርድፉ የአማራ የበላይነት ከንግዲህ አይኖርም በሚል ሲተነፍስ፤ ሄንዝ ጠየቀ- የአማራ የበላይነት ስትል ምን ለማለት ነው? መለስም ላለፉት መቶ አመታት በአዲስ አበባያ ተንሰራፍቶ የቆየውን የሸዋ አማራ የበላይነትን ነው ሲል መልሷል"[17]፡፡ ይህ ሁሉ በትግል እድሜው ሲያቃዠው የነበረውን ስሜት ነው፡፡

እንግዲህ ከሀገራዊ ስሜት በሚያላቅቅ በማርክስና ሌኒል የአለም አቀፍ ወዛደራዊነት መርህ ተኮትኩቶ ያደገ እንዲሁም አስተሳሰቡን ለሌሎች ጭምር ሲያስርጽ ያደገ መሪ በዘውግ ፖለቲካ ተጠምዶ ስለአማራ፣ ስለሸዋ አማራ ወደታችም ዝቅ ብሎ የዳግማዊ ምኒልክ የዘር ሃረግን ቆጥሮ የጎጠኝነት ሰርዓት ማጠንጠኛ ሲያደርግ መመልከት፣ መስማት ግራ የሚያጋባና ትንግርትም ነው፡፡ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስተር ያደጉበት የፖለቲካ ፍልስፍናቸው ከቃላት ያለፈ ትርጉም ማጣቱን ያመላክታልም፡፡ የፖለቲካ ትርፍ በመሻት የሃገሪቱን መጻኢ እጣፋንታ

[17] We can no longer have Amhara domination" meles Zenawi, said. "What do you mean by Amhara domination?" Puol Henze forwarded question. "When we talk about Amhara domination, we mean the amhara of Shoa, and the habit of shoan supremacy that became established in Addis Ababa during the last hundred years", Meles Zenawi responded.

ማመሳቀል የማይሳናው መሆኑን “ከወደብ/ከባህር በር ባለቤትነት ጋር፣ ከሰንደቅ አላማ ክብር ጋርና ከፖለቲካዊ አመራርነት ሙያዊ ብቃት ጋር የሚያያዙ የአደባባይ ንግግሮቻቸው አስረጂዎች ናቸው።

ይህንኑ ከስልጣን መናፈቅ የማይዘል ስር የሰደደ በሽዋና በምኒልክ ላይ የተጠነሰሰ ተጻራሪ ስሜትን ከክንፉ አብርሃም ጽሁፍ እንደሚከተለው እንረዳለን። “ከአክሱም መንግሥት መዳከም ወዲህ፤ አንዲሁም ድንገተኛውን ወይም ያልተጠበቀውን የአጼ ዮሐንስ አራተኛ ሞት ተከትሎ የመጣው የሸዋ መንበረ መንግሥት ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ “ትግሬዎች በትክክለኛ የፖለቲካ ሥልጣን ሚዛን ላይ አይደለንም፤ ሥልጣናችንና ታሪካችን በሸዋ ገዢ መደቦች ተነጥቀናል” የሚል ስሜት አሳድረዋል (ክንፉ አብርሃም፣ 2001፡223)።

በሌላ በኩል በጣሊያን ማህበረ-ፖለቲካ ስርዓት በፍቅር ከወደቁ ኤርትራዊያንና ኢትዮጵያን ክደው ከጣሊያን ጋር በፍቅር ሲናውዙ ከነበሩ ባንዳዎች አብራክ የተገኙ ታጣቂዎች የመሰረቱት ድርጅት ስለዳግማዊ ምኒልክ መሲህነት፣ ስለኢትዮጵያዊነት፣ ስለብሄራዊ አንድነት ለመስበክ የስነ-ልቦና መነሳሳት ይኖራቸዋል ብሎ መጠበቅ ሞኝነትን የሚያሳብቅ አስተሳሰብ ነው። ለዚህም ነው “አበቃቀሉ የተዛነፉ ጽድ ለመቃን አይበቃም” የሚው አባባል የተመረጠው።

የአስተሳሰብ መዛነፉ በመንግታዊ ስርዓት መካተትና የአማራ ህልውና

ግዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል እንዲሉ በመላው ኢትዮጵያ በተቀጣጠለ ትግል ህዝባዊ መሰረቱ የሰለለው የኮሎኔል መንግስቱ ኀ/ማሪያም መንግስት ሲወገድ በ1983 ዓ.ም. ፖለቲካ ስርዓቱን የተቆጣጠሩት የብሄር የጉጂሌዎች ስብስብ በተለይም ሕወሓት ኢትዮጵዊነትንና ራሱው የመሰረታቸው የዘውግ ብሄረተኞች የአማራ ኢኮኖሚዊ፣ፖለቲካዊና ማህበራዊ መሰረቶችን ለማክሰም የቻሉትን ሁሉ ተግተዋል።

ከላይ ለመጠቆም እንደሞከረው በህወሃት ሞግዚትነት የተመሰረቱና ያደጉት የበዳይነት ትረካው የማረካቸው የተለያዩ የብሄረሰብ ድርጅቶች ያለ ሀይ ባይ በአማራ ህዝብ ላይ ጥቃት ፈጽመዋል፣ አግዘዋል፣ አስተባብረዋልም። ከጅማሮው የኢህአዴግ መሪዎችን በፍቅር አስተሳስሮ ያያዛቸው የጋራ ጠላት የሚሉት የአማራ በዳይነት/የበላይነት/ ነበር። የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ)ና ኢህአዴግም የጥምረት አንዱ ማሰሪያ በአማራ ልሂቃን ላይ ያላቸው ጥላቻ ነበር። አዲስ አበባን በተቆጣጠሩ ማግስት የአማራ የበላይነት የሚባለው ነገር ከድርጀት አስተሳሰብነት አልፎ የመንግስት አቋም ሆነ። የዘውግ ፖለቲከኞች ሌላ የጋራ አላማችን ብለው ያቀነቀኑት

የከፋው ይገንጠል መርህን ኤርትራን አስደስቶ ፋይሉ ተዘጋ። ኦነግ እተገብረዋለሁ ሲል ኢህአዴግ ቃሉን በማጠፉ ጸብ ነገሰ። የአማራ የበላይነትን ለመደቆስ አላማ የሰነቁትና አሸናፊነቱ ያኩራራቸው የግንባሩ(የኦነግ ለማለት ነው) ባለስልጣናት እውነተኛው የህወሃት /ኢህአዴግ የበላይነት ተፈታተናቸው። ለኦነጎች የኦሮሚያ ሪፐብሊክን የመመስረት ምኞት እንደኤርትራ ሪፐብሊክ ምስረታ ቀላል እንደማይሆንምን አመላካች ፖለቲካዊ እንቅስዋሴዎች ተስተዋሉ።

ህወሃት /ኢህአዴግ የምትታለብ ላም የሆነችው ኢትዮጵያ ያለኦሮሚያ ምንም እንዳልሆነች ገና ከጠዋቱ ነው የተገነዘበው። ኦሮሚያ የሌለችበት ኢትዮጵያ ኤርትራ እንደሌለችበት ኢትዮጵያ እንዳለሆነችም ግልጽ ነውና። በትብበራቸው ዘመንና ሁለቱ ቡድኖች አንዱ በአንዱ ላይ የበላይነት ለመቀዳጀት በሚያደርጉት ሽኩቻ አማራን የጥቃት ሰለባ አድረገውታል። ኦነግ አንዳንዴ ነፍጠኞች ጠላት ነው በሚል በአማራ ህዝብ ጦር ይመዝበታል ሌላ ጊዜ ለኢህአዴግ ድጋፍ ሰጥታችኋል በሚል ፍረጃ በአደባባይ ይረሸናል። ኢህአዴግም ኦነግ የጨፈጨፈው አማርኛ ተናጋሪ ህዝብ እያለ የኢትዮጵያ ህዝብ በኦነግ ላይ ጥላቻ እንዲያሳድርና የፖለቲካ ሀይሎች ከጎኑ እንዲሰለፉ ፕሮፓጋንዳ የሚሰራበት ወቅትም ስለነበር በአሰቃቂ ሁኔታ የተጨፈጨፉ የአማራ ብሄር ተወላጆችን ቮዲዮ በማሳየት በኦነግ ላይ የማጠላላት ዘመቻ ያካሂድ ነበር። ከምንም በላይ የሚያሳዝነው አማራ ከለላ የሚሰጠው የመነህግስት አካል ያጣ፣ ነገር ግን ለፖለቲካ ትርፍ ብቻ የዘውግ ፖለቲከኞች የሚጫወቱበት መከረኛ ህዝበ መሆኑ ነው።

“በታጋይ መራሹ ኃይል” ከልካይ የሌለው የማያባራ በደል በአማራ ላይየተሰነዘረባቸው አካባቢዎችን መበራከትና የበደሉ ስፋት የአማራ ህዝብ በስሟ የሚምልላት ኢትዮጵያ ምኑ ናት የሚል ጥያቄን የሚያጭር ነው። ቀደም ባሉት የሰቆቃ ዘመን በደሉን ለሚዲያ የሚያበቃና የሚያሰማለትም አካል እንዳይኖር ተደርጓል። ዛሬ ላይ ለቴክኖሎጂ መስፋፋት ክብር ይስፋውና ያኔ የነበረውን ሰቆቃ በፎቶና በምስል እያጀቡ ተጨባጭ ማስረጃዎች የሚያቀርቡ ድረ-ገጾት በመበርከታቸው “Amhara Genocide, Amhara Massacre, Amhara displacement, Amhara Ethnic cleansing” ብሎ ጎግል ለሚያደርግ የተባዳዮችን የስቃይ ድምጽ መስማትና የስቃይ ገጽታ ማስተዋል የሚቻል ነው። 1982፣ 1983፣ 1984/1985 ዓም. የጭፍጨፋው ሂደት ቅጥ ያጣበት ወቅት ነበር። በሃረርጌ፣ በወለጋ፣ በአርሲ፣ ምስራቅ ሸዋ፣ ምዕራብ ሸዋና በሌሎችም አካባቢዎች የጦፈ ጭፍጨፋ የተከሰተባቸው አካባቢዎች ናቸው። በዚያን የአማራ የስቃይ ዘመን ደርግን ያህል ግዙፍ ወታደራዊ ቡድን ገረሰስኩ የሚለው “ብሶች የወለደው” የህወሓት ሰራዊት የተወለወለ ጠብመንጃውን ከትከሻው እንኳን አላወረደም፤ እንደደገነ ነበር።

ሆኖም በአመራ ላይ የታወጀውን ጭፍጨፋ ለማስቆም የወሰደው ርምጃ ካለመኖሩ በተጨማሪ የኢህአዴግ ግንባር አባላት ቀውሱን የሚያባብሱ ህዝባዊ ንግግሮችንም ሲያደርጉ እንደነበር የጥናት ውጤቶች ያስረዳሉ (የሙሉቀን ተስፋውን የ2009 ዓ.ም. የጥፋት ዘመን የተሰኘ መጽሃፍ ያንብቡ)። የሃረርጌ፣ የበደኖን፣ የአርባጉጉን እልቂት ባስ ብሎ ይታይ እንጂ ችግሩ በሁሉም የሃገሪቱ አካባቢዎች የተንሰራፋ ነው። በአሁኑ ሰዓት የህወሃት ደጋፊዎችና አባላት የኢኮኖሚ ማዕከልነቷ በምትታወቀው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳና ባምባሲ ከተማዎች የአማራ ህዝብ በኦነግ ታጣቂዎች ታጭደዋል። ባምባሲ ላይ የአማራን ተወላጆች አዳራሽ በመሰብሰብ በቦምብ ያጋየበትንና ከሰማንያ ሰው በላይ ሰዎች (እናት ከነልጆቿ ጭምር) ያለቁበትክስት አንገሽጋሽ የትላንት ታሪክ ነው። የአማራን ንብረት ለይቶ መዝረፍ፣ ማቃጠልና ህዝቡ በማህበር የሚያረባቸውን ከብቶች ያለገደብ ማረድ ተራና ከቁብ የማይቆጠር በደል እንደነበር የችግሩ ገፈት ቀማሾች ያስረዳሉ። ከማሽና መተከል ወረዳም (በቤኒሻንጉ) የአማራ ስቃይ ያስተናገደች ናት።

ከኦነግ ውድቀት በኋላም በተለያየ መጠን ከሶማሊና ኦሮሚያ ክልሎች አማራን፣ መጨፍጨፍ ማሳደድ፣ የስራ አድል የማሳጣት የመፈናቀል ተግባራት ተፈጽመዋል። በኦሮሚያ ክልል በ1992/93፣1997ና 1998/99 አመታት አሰቃቂ ግፍ ተፈጽሟል። ከችግሩ ስርዓታዊነት የተነሳ ሊያባራ ባለመቻሉ ኢትዮጵያ ሁለተኛውን ሚሊኒየም ባከበረች ማግስትም የአማራ ህዝብ አባራሪዎች በተደራጀ መልኩ ተንቀሳቅሰዋል። በሽፈራው ሽጉጤ አስተዳደር ከደብቡ ክልል ጉራ ፈርዳ ወረዳ፣ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ቦሎጂጋንፎይ፣ ካማሽና መተከል ወረዳዎች በገፍ እንዲፈናቀሉ ተደረጓል። ከላይ ያለውን ሃሳብ በማጠናከር ዶክተር አሰፋ ነጋሽ በስርዓቱ ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ውሳኔ ከክልሉ ውጭ ያለው የአማራ ህዝብ የመፈናቀል፣ የመደብደብ፣ የሞትና መሰል የኢ-ሰብአዊ አደራጎት አንደተፈጸሙበት በ2008 ዓ.ም. በጻፉት ጽሁፍ ከነማስረጃው ጠቅሰዋል። ስርዓታዊ ፍርድ የተፈረደበት ህዝብ ለመሆኑ በግልጽ በሚያሳይ መልኩ በ2004 ዓ.ም. መለስ ዜናዊ በጉራ ፈርዳ ጉዳይ ላይ ለተወካዮች ምክር ቤት ማብራሪያ ሲሰጡ አማራ ተፈናቀለ እየተባለ መወራቱን ነቅፈው የሰው መሬትና ደን በህገ-ወጥ መልኩ የተቀራመቱ ሰዎች ናቸው በማለት ተፈናቃዮቹን ወንጅለዋል። በተጨማሪም ተፈናቃዮቹ ጥቂት የጎጃም ሰዎች እንደሆኑ ለማስመሰል ሞክረዋልም። የሽፈራው ሽጉጤ ስራ የመለስ ዜናዊን ልብ ስለማረከ ይመስላል በፈደራሉ መንግስት ስልጣን ተሰጠው።

የቤኒሻንጉሉን የአማራ-ጠል የመንግስት ስርዓትና የማፈናቀል ድርጊ ብንመለከት የክልሉ ካቢኔ መክሮበት፣ ተወያይቶበትና ታስቦበት የተፈጸመ ነው። ኢ-የሰብአዊ ድርጊት ሰለባዎቹና ተፈናቃዩቹ በቅድሚያ "ቅንጃ"(ለእርሻ በሬ በማቀናጀት) የሚል ስም ተሰጥቷቸው የማጥላላትና የወራሪ ገጸባህሪን የሚያላብስ የፖለቲካ ስራ ተሰርቶባቸዋል። ኋላ ላይ ችግሩ ፖለቲካዊ ጫና ሲያስገትል የፌደራሉ መንግስት ተግሳጽ ሲሰማ ጥቂት ኪራይ ሰብሳቢዎች የፈጸሙት እንደሆነ ተወራ። ለይስሙላ በአጥፊነት የተከሰሱም ነበሩ። በአማራ ላይ የተሰነዘረው ጥቃት ተጠንስሶ እስኪተገበር ድረስ ዛሬ ላይ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ኮሚሽነር የሆኑት ዶክተር አታክልቲ በክልሉ የአስተዳደር ምክር የፕሬዘዳንት አማካሪ ነበሩ። በአማራን ህልውና ላይ አደጋ የመጣል ተሳትፎ ሹመት ያስገኛል። በመሆኑም በአማራን ህልውና ላይ ያነጣተረው የስርዓቱ እርምጃ ሳይቀለበስ ቆይቶ የዘመን ለውጥ ሆኗል (2010 ዓ.ም.)።

አማራን ለማጥቃትና ስልጣን ለማደላደል የተጠነሰሰውና እስካሁን ሃገራዊ አንድነትን በመናድ ፖለቲካውን በብሄር ጥላቻ ላይ እንዲመሰረት ያደረገ የፖለቲካ መስመር ዛሬ ላይ ለተፈጠረው ውጥንቅት አብቅቶናል። ያልዘሩትን እያጨዱም ነውና ለታሪክ የተዛባ አስተሳሰብ ይዞ በመነሳት አንድን ህዝብ የታሪክ ተወቃሽ አድርጉ የሚፈርጅ ቡድን ዛሬ ላይ ምስቅልቅላችንን ማወጣቱ ያልተጠበቀ ክስተት አይደልም። ምክንያቱም ከጅምሩ የተዛነፈ አስተሳሰብ የመንግስታዊ ስርዓት አካል በመሆኑ ነው።

የአማራ የበላይነት ነበረ? የአማራ መንግስትስ?

አንዳንዴም ከግንዛቤ እጦት ለሌላ ጊዘዜ ደግሞ ከጥላቻ በመነጨ የተወሰኑ የሶሻሊስታዊ ተራማጆችና የብሄር ድርጅቶች ያልተቋረጠ የብሶት ትርክትና ዲስኩር የተበዳይነት አድርገዋል። ለዚህም አንዳንድ "የአማራ ልሂቃንም እውነት እየመሳላቸው ድጋፍም እንዳደረጉ የሚታወቅ ነው። ይህን ሃሳብ በዝርዝ በሚያብራራ መልኩ "ዶር አሰፋ ነጋሽ"[18] ማስረጃዎችን በማጣቀስ የጻፉ ሲሆን የ1960ዎቹ የተማሪዎች እንቅስቃሴም ታሪክም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው።

[18] The Amara Elites Internalize a Negative Identity Imposed by the Enemy:…This is what we call internalization. Internalization in this case is a psychological process whereby the Amara elites and youth have accepted the demonized image of the Amara as being evil-doer, oppressor, bloodsucker, breast-amputator, invader, etc. With the advantage of hindsight, it seems to me that in the whole socialization process and intellectual formation of my generation of youth that participated in the Ethiopian student movement, my generation and the generation before me have tended to internalize the image of the Amaras as rapacious exploiters, blood-suckers, slaver traders, etc. So here we are today, after 21 years of TPLF rule, the Amaras have been reduced to the status of sub-human creatures that have to readily accept any verdict of those ethno-nationalist entrepreneurs of hate who call themselves representatives of the oppressed peoples and feel entitled to bully, trash, bash, uproot, deport and massacre at will innocent Amara peasants (Assefa Negash, 2012:10).

አማራን ከመንግስታዊ ስርዓት ጋር በመያያዝ ሌሎች ኢትዮጵያዊንን ወይም ብሄረሰቦችን የታረኩ አካል እንዳልሆኑ በማስመሰል አሊም የነበራቸውን ሚና ባለመጥቀስ ስልታዊ ዝምታን በመጠቀም አማራን የማውገዙ ስራ መጠነሰፊ ሆኗል። ስርዓታዊ በመሆኑ ብዙዎቻችን አንዳንዴ በመሰላቸትና ሃሳብ ብንሰነዝር ሰሚ አናገኝም በሚል ሌላ ጊዜ ግንዛቤ በማጣት ዝምታን መርጠናል። መናገርና ክርክር መፍጠር የኢኮኖሚና ማህበራዊ ህልውናን የሚያስነጥቅበት ሁኔታም ስላለ ፍራቻች ለዝምታችን መነልበት አጋዥ ሆኗል። የታሪክ መዛግብት ብንፈትሽ ግን ሃቁ አንድ ነው። ማለትም ኢትዮጵያ ከሶስት ሽህ አመታት ባስቆጠረችበት የታሪክ ሂደት ውስጥ የአማራ መንግስት ወይም የአማራ ስርዎ መንግስት ተመስርቶ እንዳለነበረ እንረዳለን። ነግር ግን የአማራ ህዝብ የጋራ ሀገርን በመመስረት ሂደት ትጉህ የነበረ፤ ለመንግስታዊ ስርዓት ምስረታ አስቻይ ማህበራዊ መሰረት ያለው፣ በእምነት የታነጸና ግብረገብ ማህበረሰብን ወይም ትውልድን የመቅረጽ ጸጋን የተላበሰ ነው።

ወደ ሩቁ የኢትዮጵያ የመንግስት ስርዓት ተመልሰን ሰንፈትሽ የፕሮፌሰር ፍቅሬን የታሪክ ትንተና ብንዳስሰው ተገቢ ይመስለኛል። "የአማሮች ህልውና የጀመረው የኢትዮጵ ስርዎ መንግስት ከተመሰረተ ከአራት መቶ አመት በኋላ ነው፤አንዳንዶቹ ንጎሶችና ነገስታት የአማራ ስም ቢይዙም በኢትዮጵያ ስረወ-መንግስትን የሚወክሉ መሪዎች አንዳቸውም አማራ አልነበሩም" (ፍቅሬ ቶሎሳ፡ 2008 ዓ.ም.)። የኢትዮጵ ስርዎ መንግስት እንጂ። "በአራተኛው ክፍለ ዘመን ክርስትና እንዲስፋፋና የመንግስቱም ሃይማኖት እንዲታወጅ በበቃበት ወቅት በአብርሃና አጽብሃ ነግሰው የነበረ ሲሆን የእነዚህ ንጉሶች አባታቸው አጼ ሰይፈ-አርዕድ በናታቸው በኩል የአማራ ደም ነበራቸው፤ይሁንና የአማራ ስርዎ-መንግስት አልመሰረቱም (ዝኒ ከማሁ)። የሶሎሞናዊው ስርዎ መንግስትም እስከተመሰረተበት ጊዜ ድረስ የደሸት ዝርያዎች በስርዎ መንግስታት ውስጥ ተሳታፊ ይሁኑ እንጂ አማሮችን ብቻ የሚመለከት ስልጣን እንዳልነበረም ከፕሮፊሰር ፍቅሬ ጽሁፍ እንደዳለን። የዛግዌ ስርዎ-መንግስትን ከመሰረቱ የአማራ ወታደሮች ከመመልመሉ ባሻገር የአማራ መንግስት እንዳልነበር የታወቀ ነው።

የየጁን ስርዎ መንግስትን ያጸኑ ልሂቃኖች የኦሮሞ ብሄር አባላት ስለመሆናቸው፣ካሳ ሃይሉ (አጼ ቴወድሮስ) አማራነትን ሳይሆን የቋራ ተወላጅነትን አስቀድሞ የመጣና ቅማንቶችን ማንገሱን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል። የወሎው ራስ አሊም የኦሮሞ ተወላጆ ሲሆኑ እርሳቸውም ይሆኑ የየጁ ስርወ-መንግስት ነገስታት አማረኛን የመንግስታቸው ቋንቋ አድርገው መጠቀማቸው ይታወቃል። እነዚህ ስርዓቶች የኦሮሞ መንግስት በሚል የብሄር

አደረጃጀት የተጠናወታቸው አልነበሩም። ዮሃንስ አራተኛም የትግራይ መንግስት በሚል ያልነገሰና አማረኛን የስራ ቋንቋው ያደረገ ነበር። የቀዳማዊ ምንልክም ሆነ የአጼ ኃ/ስላሴ ሰርዓት የሶሎሞናዊ ስርወ-መንግስት ፍሰትን በኢትዮጵያ ሲያስቀጥሉ የነበሩ እንጂ አማራነትን የሚላበስ ብሄር ተኮር ፖለቲካዊ ማንነት አልነበራቸውም። "አንዳንዶች የስርዎ መንግስቱ ንጉሶች የአማራ ስምና ስመ-መንግስት ቢኖራቸውም አንዳቸውም አማራ ነን ብለው አያውቁም፤ ከነዚህ ውስጥ እናቶቻቸው አማሮች መሆን ያለመሆናቸው ባይታወቅም አባቶቻቸው ግን የሶሎሞን ዝርዎች ናቸው" (ዝኪከ ማሁ፡172)።

በተጨማሪም የቀድሞዎቹ ስርዓቶች ዛሬ ላይ ከመሰረትነው አወቃቀር ከብሄር መንግስት በእጂጉ የራቁ ነበሩ። አሁን የብሄር አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) የመሰረተው መንግስት፣የህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ (ሕወሓት) የሚመራው ስርዓት እንዲሁም ሌሎቹ በዘውግ የተደራጁበት መንገድ ነው የብሄር መንግስት ነበር ወይም አለ ለማለት የሚያበቃን። መንግስት የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ ስንገነዘብ የፖለቲካ ርዕዮተ-አለሙን፣ መንግስተ-ህጉን/ፖሊሲውን/፣ የፖለቲካ ፓርቲውን፣ አወቃቀሩንና በድርጅቱ ከአመራር እስከ ምንዝር የተሰባሰቡ ሰዎችን አዳምረን ነው። በመሆኑም በቀድሞው ስርዓቶች የአማራን፣ የትግሬ፣ የኦሮሞን የሚባል መንግስት ያለመመስረቱ፣ ስርዎ-መንግስቱ ኢትዮጵያን የሚመለከት መሆኑና በአባልነት ለመካተት የብሄር ጉዳይ መስፈርት ያለመሆኑ የቀድሞዎቹ ስርዓቶች ከብሄር ጋር የሚያስተሳስራቸው እትብት እንዳልነበራቸው ያስገነዝበናል።

ከላይ እንደተገለጸው ዛሬ ላይ በግልጽ ቋንቋ የኦሮሞ መንግስት፣ የአማራ መንግስት፣ የትገሬ ወዘት... መንግስታት ብሄር አስተዳዳር ስም ተቋቁመዋል። በነዚህ የብሄር መንግስታት የአማራ ህዝብ የበላይ ነበር በሚል ጥላቻ እየተሰበከ መሰቃየቱ ግልጽ ነው። ሆኖም በእነዚህ በብሄር ስም በተደራጁ መንግስታት በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች በመንግስት አነሻስነት በአማራ ህዝብ ላይ ለተፈጸሙ በደሎች የኦሮሞ፣ የሶማሊ ወይም የልላ ህዝብ የታሪክ ተወቃሽ የሚሆንበት የሞራል፣ የህግ አሊያም የፖለቲካ አመክንዮ አይኖርም። በህዝብ መካከል የተደረገ የበዳይ-ተበዳይ ታሪክም አድረጎ መውሰድ የማይቻል በመሆኑ የተጠያቂነት ድርሻውን ስርዓቱ በብቸኝነት ይወስደዋል። ከፋፍሎ የመግዛትን የፖለቲካ አላማ ለማራመድ ካልሆነ በስተቀር የስርዓቱ መሪዎች ከመጡበት ብሄር ጋር በማገናኘት በብሄሮች መካከል የተፈጸ ግፍ አድርጎ መተንተንም የሚቻልበት ህጋዊና ፖለቲካዊ መርህ ባይኖርም በአማራ ላይ ተፈጽሟል። በመሰረቱ የአማራ ህዝብ ለኢትዮጵያ አንድነትና ክብር አበርክቶው እንዳለ ሆኖ ለንጉሳዊያኑ

አገዛዝ መደላድል በሆኑ የእምነትና የባህል ተቋማቱ ተተብትቦ ለከት የሌለውን የስርዓቶች ጫና ተሸክሞ የኖረ ህዝብ ነው። በመሆኑም ዛሬ ላይ ስርዓቱ የአማራ የበላይነትን ታሪክ እንደነበረ ለማላመን የሚያደረገው ቅስቀሳ ከነባራዊው የኢትዮጵያ ታሪክ ያፈነገጠ ና የፖለቲካዊ አላማን ብቻ የማሳኪያ ስልት ነው።

ምዕራፍ ሶስት፡ የአማራ ህዝብ የመደራጀት፣ የውክልናና የማህበረ-ኢኮኖሚ ፈተናዎች

ጫፍ በረገጠ አምባገበባዊነቱ የተነሳ ህዝባዊ መሰረቱ የተናደው የደርግ ስርዓት በግንቦት 20 ቀን 1983 ዓ.ም. በግሃድ አበቃለት። የዘውግ ፖለቲካ አራማጆች የትጥቅ ታጋዮች ደግሞ በለስ ቀናቸው። ወዲያውኑ በሽግግር መንግስቱ ቻርተሩ አንቀጽ 7 መሰረት የተወካዮች ምክር ቤት ከብሄራዊ ነጻነት ንቅናቄዎች፣ ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶችና ከታዋቂ ግለሰቦች ተውጣጥቶ በ87 አባላት ሊመሰረት በቃ። በአዲሱ ህወሃት መራሹ ስርዓት ኢህአዴግን በግንባርነት በመመስረት ኢህዴን ይሰኝ የነበረው ብአዴን ሆኖ ለአማራ ክልል አስተዳዳሪነት ተሰየመ። በምክር ቤቱ የሶስት ድርጅቶች ግንባር ኢህአዴግ 30 ወንበርና ኦነግ በአንጻራዊነት አብላጫውን የምክር ቤት መቀመጫ ማለትም 12 ወንበርና ብሄር ብሄረሰቦችን እንወክላለን ያሉ ቡድኖችና ተዋቂ ሰዎች ቀሪውን ወንበር ተቀራምተውት ነበር። አማራን በአማራ መሬት ላይ ሆነው ደርግን ሲፋለሙ የነበሩ በአብዛኛው አመራሮቹ በብሄር አማራ ያለሆኑ የኢህዴን ታጋዮዎች እንዲወክሉት ተደርጎ ምክር ቤቱም ለአራት አመታት መንግስታዊ ስራን ሲያከናውን ቆየ። በዚህ ድልድል አማራው "እዚህ ግባ የሚባል ተወካይ" እንኳን ሳይኖረው ቁጥር አንድ ተጎጂ ሆኖ ቆይቷል። የቀድመው ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ[19] ለጋዜጠኛ ያደረጉት ንግግር ይህን ሃሳብ የሚያረጋግጥ ነው። ስለሆነም ከሽግግር መንግስቱ ጀምሮ የኢህአፓ ርዝራዦች የሆኑት ኢህዴኖች አስካሁን ዋናውን የክልሉንና ቁልፍ ስልጣንና የፈደራሉ መንግስትም ውክልና በመውሰድ አማራ አማራ የማይሸቱ ውሳኔዎችን በአማራ ህዝብ ላይ በማላለፍ ህወሃት/ኢህአዴግን እያገለገሉ እስከሁንም አሉ።

[19]የአማራን ውክልና ማጣት አስመልክቶ የቀድመው ጠቅላይ ሚኒስተር "አማራን የሚወክል አካል ባለመምጣቱ ወይም አማራን በልዩ ሁኔታ እወክላለሁ ብሎ የመጣ ድርጅት የለም፣ በአማራው ገበሬ ውስጥ ሲታገል የነበረውን ኢህዴን ስለሆነ የአማራ አመለካከትን ይወክላል በልን እናስባለን" በማለት የአማራ በአማራው ያልተወከለበትን አግባብ-አስረድተዋል።
(Prime_minister_Meles_Zenawi_and_Professor_Mesfin_Woldemariam,_About_Amhara__YouTube ላይ ይመልከቱ)።

ከመቼውም በላይ አማራ እንደብሄር ተደራጅቶ የጋራ ችግሩን በህብረት ለመፍታትና የተጋረጠበትን አደጋ ለመታገል ከሚፈታተኑ ዋና ዋና ተግዳሮቶች መካከል በህዝብ ሃብት ጉልበቱ የፈረጠመው የኢህአዴግ ጸረ-አማራ ስርዓት፤ የኢትዮጵዊነት ስሜት ያናወዛቸውና ወደብሄር ፖለቲካዊ (እነሱ እንደሚሉት የጎሳ ፖለቲካ) አደረጃጀት ዝቅ ብሎ መደራደር ያለመፈለግ ስነ-ልቦና የተላበሱ የአማራ ልሂቃን ጫናና አማራ የሚባል ብሄረሰብ የለም የሚል የነፕሮፊሰር መስፍን ወልደማሪያም ተዋስዖ ተጠቃሾች ናቸው። እነዚህንም ስርዓት/ፖለቲካ ወለድ፣ ስነ-ልቡናና የፍልስፈና ተዋስዖ በሚል እከፍላቸዋለሁ። የእነዚህ ፈተናዎች ውጤት በማህበረሰቡ የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ተጠቃሚነትና በማንነቱ ላይ የሚንጸባረቅ ነው።

ስርዓት ወለድ ማዕቀብ

መንግስታዊ ስርዓቱን በመምራት ላይ ያሉት መሰረታቸው ማርክሳዊና ሌኒናዊ ርዐዮተ-አለም የሆኑ የታጣቂ ቡድኖች አመራሮች የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ የሶሻሊዝም ስርዓትን ለማብቃት እንደማያስችል እየተረዱ በመምጣታቸው የብሄር ተኮር ፖለቲካውን እና ምናባዊ የጋራ ጠላት በማበጀት ተዛምዶ በማድረግ የስልጣን አላማ በማሳካቱ በኩል ብዙ ተሳክቶላቸዋል። የእነዚህም ቡድኖች የፖለቲካ አፍ መፍቻቸው "የአማራ የበላይነት መኖሩን በመስበክና" እናሰወግድ በሚል እንደጋራ ጠላት በመቁጠር በአደባባይ የሚማማሉ ሆኑ። የሶሻሊዝም ካባቸውን ለማውለቅ ሲንደረደሩና የምዕራባዊያን ለጋሾችን ቀልብ ለመግዛት የብሄር ጭቆና የችግራችን ሁሉ መነሻ ነው አሉ። የመደብ ጭቆናን ማናቸውም ማናቸውም። የሶሻሊስት አቢዮት ቅዱስነት ሰበካው ተቀዛቅዞ አማራን የጨቆና አውራ አስምሎ የማቀረብ ድርጊት፣ በሻቢያ በኦነግና በኢህአዴግና በአጋር ድርጂቶቹ ሳይቀዛቀዝ ዘለቀ። አንዳንድ ጊዜ ህዝብን መፈረጅ ተገቢ ያለመሆን የሚያስረዳ ትችት ሲገጥማቸው "የሸዋ አማራን ነው ጨቋኝ የምንለው" በሚል ለማጥበብና አማራን ለመከፋፈልም የሚያደርጉት ሙከራ አለ። መንግስታዊ ውክልና ማጣቱ ምንም አይነት ፍረጃና የማጠልሸት እንቅስቃሴ ቢከናወን ሃይ ባይ እንዲያጣ አድርጎታል። ብአዴን አሜን ከማለትና የተቀናጀውን ፍረጃ ከማስተጋባት ውጪ የስራ ድርሻ የሌለው እስኪመስል ድረስ የህወሃት/ኢህአዴግ አገልጋይነቱን አጠናክሯል።

ቀስ በቀስ በቁጥር ላቅ ያለ ድርሻ ያላቸውን ብሄረሰቦች በግልጽም የኦሮሞንና (ሆኖም በኦነግ ጫና ኦሮሞ የአማራን ያህል ውክለና በማጣት አልተጠቃም) የአማራን ፖለቲካዊ ውክልና የማግኘት መብት የሚጋፉ ህግጋትና ግልጽ ተግባራት እየተስተዋሉ ቆይተዋል። የህግጋቱ ውክልና ማሳጣት በተመለከተ ለመወያየት በአማራ ላይ ስናተኩር ለአማራ ህዝብ ተገድባ ከተሰጠችው ክልል ውጪ የተበተነውንና በሁሉም ክልሎች የሚገኝ ማህበረሰብ መሆኑን

ማንሳት ተገቢ ነው። በሚኖርባቸው ክልሎች የቁጥር ልዕልና እንኳን ቢኖረው ስለራሱ ውሳኔ የሚያስተላልፍለት ተወካይ ባለማግኘት ሌሎች ስለአማራ እንዲወስኑ ተደርጓል። የህዝብ የስልጣን ባለቤትነት የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት መርህ ቢሆንም በሚሊዮን የሚቆጠር አማራ በውክልና የስልጣን ባለቤትነት መብትን ሊጠቀሙ አልቻሉም። ኢህአዴግ የቡድን መብቶችና የግለሰብ መብቶች አጣጥሜ አከብራለሁ/አስከብራለሁ የሚል አቋም እንዳለው የሚታወቅ ሲሆን በሌሎች ክልሎች በቡድን እንደአማራ መብቱ ቢነፈግም እንደግለሰብ እንኳን የሚከበሩለት መብቶች እየታጡ መጥተዋል።

ከተለያዩ አካባቢዎች የጠመደውን በሬ እንኳን ሳይፈታ ሀገሬ ብሎ ህይወቱን ካስተሳሰረባት ቅዬ እንዲፈናቀልና በጅምላ እንዲጨፈጨፍ ያበቃው ምንም ፖለቲካዊ ውክልና ያለማግኘቱና ተቆርቋሪ ማጣቱ መሆኑን ብዙ ማሳያዎች አሉ።

በእኩልነት የመወከል መብት ለአማራው ያለመረጋገጡን ለማስረዳት ብዙ ጥልቅ ጥናት የሚያስፈልገው ጉዳይ አይደለም። ይልቁንም በኢፌዴሪ ህገ-መንግስት መሰረት በተደራጀው የፌደራላዊ አመቃቀር ህልውና በተቸራቸው የቤኒሻንጉል ጉሙዝና የሀረሪ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት በክልሎቹ በብዛት ሁለትኛ ደረጃን የሚይዘውን የአማራ ህዝብ እንደብሄር የተሰጠውን ቦታ መፈተሽ ተግዳሮቱን በተግቢ መልኩ ያስረዳናል። እንመልከተው።

<u>*ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት*</u>፡ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የበርታን፣ የጉሙዝን፣ የሽናሻን፣ የማኦን እና የኮሞን ብሄረሰቦች ልአላዊነት በሚደነግገው በ1995 ዓ.ም. በክልሉ ህገ-መንግስት[20] ላይ ዞን የሚለው አወቃቀር ተሰርዞ **የብሄረሰብ ምክር ቤትና የብሄረሰብ አስተዳደር** እንዲመሰረት[21] እውቅና ይሰጣል። በዚህ ክልል አማራና የኦሮሞ ህዝብ በቁጥር ከነባሮቹ ብሄሮች በልጦ እንደሚገኝ መንግስታዊ ተቋም የሆነው የብሄራዊ ስታቲስቲካል ባለስልጣን ምስክር ነው። ሆኖም አሁን በተመሰረተው በብሄረሰብ አስተዳደር ምክር ቤትና ፖለቲካዊ መስመር የአማራና የኦሮሞ ህዝቦች መብት መደፍጠጥ የሚያስችል መደላድል የፈጠረ ነው። ምክንያቱም ሁለቱ ብሄረሰቦች እንደብሄር የሚወከሉበት ህገ-መንግስታዊ መርህ የለምና ነው። ህጉ እየተሰራበት እንዳለም ልብ ይሏል።

---

[20]የክልሉ ባለቤት ብሄረሰቦች፡ በክል የሚኖሩ ሌሎች ህዝቦች የሚወቁ ቢሆም የክልሉ ባለቤት ብሄር ብሄረሰቦች በርታ፣ ጉሙዝ፣ ሽናሻ፣ ማኦና ኮሞ ናቸው (በ1995 ዓም የተሸሻለው የቤ/ጉ/ክ/መ/ ህገ- መንግስት፣ አንቀጽ 2).

[21]ክልሉ በክልል፣ በብሄረሰብ ምክር ቤትና አስተዳደሮች የተዋቀረ ነው (የቤ/ጉ/ክ/መ ህገ-መንግስት፣አንቀጽ 45(1)) *የብሄረሰብ አስተዳደሮች አደረጃጀት፡* የብሄረሰብ አስተዳደር ከክልል ቀጥሎ የሚገኝ የአስተዳደር እርከን ነው (የቤ/ጉ/ክ/መ/ ህግ-መንግስት፣እንቀጽ 74(1))።

የህዝቡን ቁጥር አስመልክቶ የብሄራዊ ስታስቲካል ባለስልጣን ባደረገው በ1999 ዓ.ም.ን የቤትና ህዝብ ቆጠራን ውጤት ዋቢ በማድርግ እንደገለጸው በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል 784,345 ህዝብ የሚኖር ሲሆን 21.7 በመቶ (170,132) የአማራ ህዝብ ነው። ይህም አሃዝ የአማራ ህዝብ በክልሉ ካሉ ብሄረሰቦች በቁጥር ሁለተኛ ያደረገዋል። "የነባር" ብሄረሰቦችን ቁጥር ስናይ በርታ 19,9303፣ ጉሙዝ 163,781፣ ሽናሻ 60,587፣ ማኦ 15,689ና ኮሞ 7,773 እንደሆኑ 1999 ዓ.ም. የቤትና የህዝብ ቆጠራ ውጤት ያረጋግጥልናል። ሌላው በህዝቡ ብዛቱ በእኩልነት ውክልናን እንዳያገኝ የተፈረደበት ኦሮሞ በአራተኛ ደረጃ የሚገኝ ሲሆን 105,275 ይህም ቁጥር የኦሮሞ ብሄረሰብ በክልሉ 13.4 በመቶ ድርሻ እንዲኖረው የሚያስችል ነው። እንግዲህ በተሻሻለው የክልሉ በህገ-መንግስት የብሄረሰብ አስተዳደር እንዲመሰረት(ዞን የሚለው አደረጃጀት ፈርሶ) በህግ ከመደንገጉ በፊት በዞን ደረጃ ተዋቅረው የነበሩትን አካባቢዎች ለነባር ብሄረሰብ" ብቻ ለማከፋፈል የሚያስችል ነው።

የልዩ ወረዳ መፍረስ፡ በፓዊ ወረዳ (80 በመቶ የአማራ ህዝብ ነው) በአሶሳ (አማራው ብዛት በሁለተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል)፣ በመተከል (በሶስተኛ ደረጃ) እና በካማሽ ዞን (በሶስተኛ ደረጃ) የሚኖሩ የአማራ ብሄር ተዋላጆች ተገቢ ውክልናና ራስን የማስተዳደር መብት የተከለከለ ነው። ምክንያቱም በብሄረሰብ አስተዳደር አወቃቀሩ የአማራ ብሄረሰብ እንደብሄር የሚወከሉበት ህገ-መንግስታዊ መርህ ያለመቀመጡ ነው። ምናልባትም በወረዳ ደረጃ በምክትል ሃላፊነት አማራን የመሾም አካሄድ ቢኖርም በሌሎች የፖለቲካ ውሳኔዎች የሚፈጸምና በህገ-መንግስታዊ መሰረት ያልያዘ በመሆኑ ፍር ቢስ ነው። ይህ ሹመት ህገ-መንግስታዊ መሰረት ቢሰጠው እንኳን ውክልና በወረዳ ብቻ የሚወሰንም እንዳልሆነ ማሰብ ተገቢ ነው። ፓዊ ወረዳ ቀደም ሲል ልዩ ወረዳ ሆና አንደነበር የሚታወቅ ሲሆን ልዩ ወረዳ የመሆኗ ጉዳይ የአብዛኛው ነዋሪዋን ወይም የአማራን ህዝብ የሚጠቅም መሆኑ ያላስደሰታቸው የመንግስት አካላት የልዩ ወረዳ አስተዳደሩን በህገ አፍርሰውታል። በመሆኑም የአማራ ህዝብ የሚመለከቱ አሉታዊ ውሳኔዎች ህዝቡ በራሱ ካልተጋፈጣቸው በስተቀር የመንግስት አካላቱ የአማራ ጠል ፖለቲካ አራማጆች እንደሆኑ ህዝቡም በመረዳቱ ከክልሉ መንግስት ጋር ግጭት ውስጥ ገብቶም ነበር።

በክልሉ ከአማራውና ኦሮሞ ውጪ ሌሎች ነባር ያልተሰኙ ብሄረሰቦች ያሉ ሲሆን መጠኑ ይለያይ እንጂ የአማራው አይነት እጣ ፋንታ እንደሚገጥማቸው የሚታወቅ ነው። ከዚህኛው ምድብ የኦሮሞ እና የአገው ብሄረሰቦች የፖለቲካዊ ውክልና ጉዳይ በግንባር ቀደምነት አጠያያቂ እንደሚሆን መገንዘብ ይቻላል። በሌላ በኩል ሌሎቹ ቁጥራቸው ውስን በመሆኑ የቡድን

መብታቸውን ማክበር በማይቻልበት ሁኔታ የግል መብት ጥበቃ መርህን በመከተል የአሰራር ስርዓት ማስፈን ተገቢነት ቢኖረውም እየተሰራበት አይደለም።

ሓረሪ ክልል ብሄራዊ ክልላዊ መንግሰት፡ እንደአጠቃላይ ሃረርና አካባቢዋ የአማራ ስቃዩን ከመላባቸው አካባቢዎች በግንባር ቀደምት ከሚመደቡት ውስጥ ናቸው። ከ1987 ዓም ቆጠራ ጋር ሲተያዋ በ1999 ዓ.ም. አማራ ህዝብ እድገት አናሳ ሆኖ የተገኘበት አካባቢም ነው። የህዝብ ቁጥርንና ውክልናን በተመለከተ ህዝብ በ1999 ዓ.ም. የህዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት መሰረት ከጠቅላላው የሃረሪ ክልል ህዝብ ሶስት ብሄረሰቦች ከ87 በመቶ በላይ ይሸፍናሉ። እነዚህም የኦሮሞ፣ የአማራና የሃረሪ ብሄረሰቦች ናቸው። በ1999 ዓ.ም የመንግስት ቆጠራ ጠቅላላው የክልሉ ህዝን 183,415 ሲሆን ኦሮሞ 103,468 ፣ አማራ 41,768ና የሃረሪ 15,863 ያህሉን ይሸፍናሉ። ይህ አሃዝ እንዳለ ሆኖ በክልሉና በፌደራል መንግስቱ ውክልናቸውን ማረጋገጥ የቻሉት የኦሮሞና የሃረሪ ብሄረሰቦች ብቻ ናቸው። በብዛት በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው የአማራ ብሄረሰብ እንደብሄረሰብ የፖለቲካ ውክልናም ሆነ ራስን የማስተዳደት መብት አልተፈቀደለትም። ገዢው ቡድን አማራ በክልል ስለተወከል በሌሎች ክልሎች የውክልና ቦታ እንደማይገባው ፈርዶበታል። በዚህ ክልሉ ጣሊያን እንኳን ያላደረገውን ነው ኢህአዴግ እያደረገ ያለው። የአልበርቶ ስባኪን ጽሁፍ ዋቢ አድርገው ፕሮፌሰር መስፍን አዳፍኔ በተሰኘው መጽሃፋቸው እንዳሰፈሩት በሃረር ስድስት የሚደርሱ ደመወዝ ተከፋይ የአማራ ሹሞችን[22] ሰይሟል። እንደ ቤኒሽንጉል ጉሙዝ ሁሉ የዚህ ክልል አወቃቀር የጥቂቶች አገዛዝን የሚያሰፍንና ሌሎችን ብሄረሰቦች በአግባቡ የማያሳትፍ ስርዓትን የመሰረተ ነው። ዋነው ጉዳይ አማራን እንዴትም በምን ከውክልና የማራቅ ተግባር ብዙ ርቀት ተኪዶበታል። ቀደም ሲል የሕወሓት ሆነ መሰል የሶሻሊዝም ርዕዮተ-አለም አራማጅ ድርጂቶች መስራች ፋኖዎች አማራ የጋራ ጠላት በማስመሰል መፈረጃቸውን አብራርቻለሁ። ችግሩ "ከሾላ ዛፍ የወይን ፍሬ" ካለመገኘቱ ጋር የሚመሳሰል በመሆኑ አማራን በአፍራሽነት መፈረጁን እንደዘወትር ጸሎት እየተቀባበሉ በማነብነብ የበይ ተመልካች አማራ ትውልድ ለመፍጠር ተችሏል።

እንደ አደጋ የመቆጠር፦ ከላይ ጠገለጹት ህጋዊ ክልከላዎች አንዳሉ ሆነው የአማራ መደራጀት ባልተጻፈ ህግም ይከለከላል። አማራ ሆኖ መደራጀት አሰፈሪ የስርዓቱ አደጋ ተደርጉ ስመወሰዱ ከቅርብ ታሪካችን እንረዳለን። በአማራ ላይ የተሰነዘረ አደገኛ ጥቃት የገባቸው ፕሮፌሰር

[22]ግዛቸው ከተማ (የአማሮች ሹሞች)፣ ኃይሌ ማራኑ (የከምቦልቻ አማራ)፣ ደመቀ ኡበሬ (የሞጆ አማራ)፣ ደስታ ዳምጠው (የግራዋ አማራ)፣ ዝቻታ ወልዳኛ (አማራ ሹም በጭርጨር) እና ሚሊዮን ተድላ (የጨርጨር አማራ ሹም) (መስፊን፣2007 ዓ.ም.:153)።

አስራት አልደየስ የመላው አማራ አንድነት ድርጅትን (መዐሕድ) በመመስረታቸው የአማራ ብሄርን ትኩረት ያደረገ የተደራጀ ቡድን ለመጀመሪያ ጊዜ ይፈ ሆነ። ሆኖም ገዢው ቡድን የአማራን መጠናከርና መደረጀት በፍራቻ ስለሚመለከተው አስራት ወልደየስ ህይወታቸው እስኪያልፍ ድረስ በእስር፣ በማጎሳቆል፣ በማስፋራትና እስከ ጦርነት ቀስቀሽነት ፍረጃ በሚደርስ ስርዓታዊ ግፍ ተፈተኑ። ፓርቲውንም የማጥላትና የማፍረስ ተግባራትም ተከናውነዋል። በተጨማሪም የኢህአዴግ ስርዓት የፕሮፌሰር አስራት ወልደየስን መዐሕድ" ካዳከመ ወዲህ የአማራውን ልሂቃን መደረጀት ለመጨምደድና ገጽታውን ለማጠልሸት የዱሮ ስርዓት ናፋቂዎች፣ ነፍጠኞች፣ ሌላ ጊዜ ትምኪተኞች በማለት ሳይሰለች እስነግሯል። ዶክተር መረራ ጉዲና ይህን ሃሳብ በሚጠናክር መልኩ በ2008 ዓ.ም. ባሳተሙት መጽሃፋቸው "ኢህአዴግ ተቃዋሚዎችን እንደእርዳታ ማግኛ ከመጠቀም ውጪ ለዲሞክራሲዊ ስርዓት ግንባታ አጋር አድርጎ የማይቆጥር፣ሲፈልግ የዱሮ ስርዓት ናፋቂዎች ሲፈልግ ጠባቦች (በተቃዋሚ ጎራ የተሰለፉ የኦሮሞ ልሂቃን የሚመለከት የወል ስያሜ) መሰየምን ስራዬ ብሎ ይዞታል" ይሉናል። እንግዲህ ከላይ እንደገለጽኩት የአማራው ልሂቃን መንግስትን የሚተች የፖለቲካ አጀንዳ ይዘው ቢመጡ የዱሮ ስርዓት ናፋቂና ተመኪተኛ የሚል ስያሜ በጋራ ተችሯቸዋል። በድጋፍ ጎራ ከተሰለፉ ግን ልማታዊ ልሂቃን ይሆናሉ። ሆኖም ልማታዊዎቹ የአመራን ህዝብ እንዲጠቅሙና የፖሊሲ ጫና እንዲያሳድሩ አልተፈቀደላቸውም። ደካማ የአማራ ፓርቲ መሰረትኩ ብለው በየአመቱ የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ በያሚዘጋጀው አጀንዳ ደብተር ላይ ስማቸውን ለማስመዝገብ የሚጣጣሩ የአማራ ፓርቲዎችን ቢኖሩ ስርዓቱ አይጠላም። የቀድሞው "መዐሕድ" ተዳክሞ ዛሬም ድረስ አለሁ በሚለው ሚጢጢው "መዐሕድ" ላይ የኢህአዴግ ስም የማጠልሸት ዘመቻ ቀዝቅዟል።

ዛሬው በየትም ቦታ የአማራ መደረጀትንና የአማራን ጉዳይ የሚያቀነቅን ግለሰብና ቡድን ጠንካራ ሆኖ እንዲደራጅ ህወሃት/ኢህአዴግ አይፈቅድም። ለዚህም ነው የአማራን ጉዳይ ጉዳያቸው አድረገው የሚንቀሳቀሱ ከወልቃይት እስከ መንዝና አዲስ አበባ ያሉ የአማራ ልጆች የአሸባሪነት ወንጀል እየተሰጣቸው የህወሃት እስር ቤቶች የሚሰቃዩት። በአህገሪቱ ካሉ ህዝቦች በአሸባሪነት ወንጀል ከሚከሰሱ ፖለቲከኞች የአማራ ምሁራን፣ ልሂቃንና ታጋዮችና የኦሮሞ ብሄሬተኞች ብዙውን ቁጥር ከሚይዙት ተርታ ናቸው። አንዳንዶቹ ከስም ውጪ የማያውቁትን ግንቦት ሰባት የተባለ ድርጅት አባል ወይም አጋር ናችሁ በሚል ክስ እንደሚመሰረትባቸው የሚታወቅ ነው።

የፕሮፌሰሩ መንገድ

አማራነትን የማንነታቸው አካል ያደረጉ በኢትዮጵያ የፖለቲካና ተያያዥ መስተጋብሮች ላይ እንደሌሎች ህዝቦች ሁሉ ጉልህ ሚና የተጫወቱ ሚሊዮኖች እንደመኖራቸው ሁሉ አማራ እንደብሄር የለም የሚሉ ግለሰቦች መኖራቸውን ጠቋሚ ጽሁፎችን አንብበናል። አማርኛ ተናጋሪ እንጂ አማራ የሚባል ብሄር የለም በሚል አስተሳሰብ የክርክር አጀንዳ ፈጣሪ ጸፊዎች ፊር ቀዳጁ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪም ናቸው። አጼ ኃይለስላሴ የዜጎች መብቶችና ህገ-መንግስቱ በእርሳቸው ችሮታ የሚሰጥ ስለመሆኑ በንጉሳዊ ህገ-መንግስቱ መግቢያ መጠቀሱ የሚታወቅ ነው። ፕሮፌሰር መስፍንን እራሳቸውን የአማራነት ማንነት የመወሰን ሙያዊ ስልጣን እንዳላቸው በማስመሰል የአማራነት ማንነትን የመንፈግ አዝማሚ ያለው ጽሁፍ አስነብበውናል። በ1983/84 ዓ.ም. ኦሮሞ የሚባል የለም ቢሉ ኖሮ ኦነግ የሚወስድባቸው እርምጃ መገመት አይከብድም። የኦሮሞ ህዝብ የጉዲፈቻና የሞጋሳ ባህል በማንሳት "ኦሮሞ የሚባል ብሄር የለም" ብለው ሊያወሩ ያመች ነበር። ግን ዛሬም ቢሆን አይሞክሩትም። የአማራ ተቆርቋሪ የለምና የወደቀ ግንድ... እንዲሉ አማራ ላይ ያሻቸውን ተናገሩ፣ ጻፉም።

ወደዋነው ጉዳይ ስገባ አማራ የለም የሚለውን የአሳተሳሰብ ጭብጥ መሬት ላይ ካለው ሃቅ በእጂጉ የራቀ መሆኑንና ይህን አዲስ አስተሳሰቡ ለማስረጽ መሞከር እንደአማራ ተባብሮ ለመታገል የሚደረገውን ጥረት በማቀጨጭ ከፋፍለው ለሚገዙ ቡድኖች መደላድል ከመፈጠር የተሻለ አላማ እንደሌለው ለማሳየት እሞክራለሁ። ፕሮፌሰሩ ነባራዊ ሃቁን እውቀውት ላለመቀበል አማራ የለም የሚል ክርክራቸውን ቀጥለዋል። ከዚም በላይ አማራ የሚባል ብሄር በእርሳቸው አገላለጽ "ጎሳ" የለም በሚል ጥቂቶችን ለማሳመን ሞክረዋል።

የእኝህ ክቡር ፕሮፌሰር አገላለጸ በደርግ ዘመን አባባል አወናባጅ የሚባል አይነት ነው። በጥናት ሂደት "ገበሬዎችን ጠይቁ በደረስኩበት ድምጋሜ አረጋገጥኩ፣ አማራ የሚባል በሄር የለም " ማለት በራሱ አማራ ነኝ ብሎ እንደማህበረሰብ እየኖረ ያለን ህዝብን እውቅና መንፈግ ከመሆኑም በላይ በሀገሪቱ በብሄር መደራጀትና መብትን በጋራ ለማስከበር ሁሉም በተሰባሰበበት ዘመን አማራ አንድ ሆኖ እንዳይታገል ብሎም ተበታትኖ ለጥቃት እንዲጋለጥ የማድረግ ይፋዊ እንቅስቃሴ ነው። በየትኛውም መለኪያ ህዝባዊ ጥቅም የማይሰጥና ከነባራዊ ሁኔታው የሚጋጭ ነው። ማለትም የፕሮፌሰሩ አቋም በንድፈ- ሃሳብ (theoretically) ደረጃም ይሁን በተግባር ለማመን የሚያስችል ጭብጥ የለውም። ከቀድሞው ጠ/ሚኒስተር ጋር አማራ የሚባል ብሄረሰብ የለም በሚል ሲከራከሩ " አማራነት አሜሪካን ሀገር እየተፈጠረ ነው፣ እሱ እንደማይጋባብን

ተስፋ አደርጋለሁ" ሲሉ ተደምጣዋል። በእርሳቸው ትንተና አሜሪካ ስላለው አማራነት መሰረቱ አሜሪካ ነው አይሉንም። በኢህአዴግ መንግስት አማራ ያለመወከሉ የተቆጨት እውቁ ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ በፓርቲነት አደራጅተው የሕወሓት መንግስትን ሲያስጨንቅና ሲታገል የነበረው ህዝብ የአማሪኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ የህንዶች፣ የቻይናዎች ወይም የኦሮሞዎች ስብስብ ነው የሚል አቋም ይኖራቸዋል ብየ አላስብም። ይልቁንም አንዴ ተናገሬዋለሁ ካፊርኩ አይመልስኝ የሚሉ ነው የመሰለኝ። በጣሊያን የአምስት አመት የወረራ ዘመንም የአማራውን ህዝብ ነጠሎ ለማጥቃት የሚደርግ ዘመቻም እንደነበር የበርካታ የታሪክ ተመራማሪዎችን ጽሁፍም አንብበዋል። የአልቤርቶ ስባኪን መጽሃፍ በአግባቡ እንደተነተኑት መቶ በመቶ እምነቱ ነው። አማራ የለም ሲሉ ተከራካሪያቸው መለስ ዜናዊ ጎንደርንና ጎጃምን ለብቻው፣ ወሎንና መንዝንም እንዲሁ በመከፋፈልና ሰዎች ሲጠየቁ አማራና እስላም የሚል አገላለጽ ያንጸባረቃሉ በሚል አማራ የሚባል ህዝብ የለም ከተባለ ይህ አቋም ለትግራይም (ሽሬ፣ መቀሌ፣ አድዋ በሚል ራሱን ከአካባቢው ጋር በማስተሳሰር የሚጠራ ሰው አስካለ ድርስ) ለኦሮሞም የሚሰራ ነው ሲል መልሷል። እውነታው ይህ ነው።

አማራነትን ከፕሪሞርዲያሊዝም (premordialism) ሆነ ከኮንስትራክቲቪዝም (Social Constructivism) ንድፈ-ሃሳብ አንጻርም ብንመለከተው ያው ብዬር ነው። አማራ እንደህዝብ የተወሰኑ የራሱ የሆኑ የማያሻሙ ቋሚ ማንነቶች የሚያንጸባርቅ ሲሆን አነዚህም የጋራ ቋንቋ፣ ባህልና የጋራ ታሪክ። በታሪክ ሂደት ህዝቦቹ በጋራ አለን ብለው የሚያምኑት እንዲሁም ቀስበቀስ የጋራ ማንነትንም ገንብተዋል። ለምሳሌ የኦርቶዶክስ ክርስትና ተከታይ ያልሆኑ የወሎ አማራዎች መልያ (በሌላው አካባቢ የማይታይ) የኦርቶዶክስንና የእስልምናን እሴቶች በጋራ የማክበር ተግባር አላቸው። የአማራነት ማሰሪያው (ethnic bond) በሃይማኖታቸው አከባበርና በጋራ ተቋማቱን እንዲጠብቁ፣ ሃይማኖት በጋብቻ ለመጣመር ብዙም እንደጉዳይ ላለመቆጠሩና የሃይማኖቱ ልዩነት በማህበራዊ አንድነታቸው ላይ ለውጥ እንዳያመጣ ማስቻሉን ማሰተዋል ተገቢ ይሆናል። ስጠቀልለው የአማራነት ስሜትና ማንነት ከጊዜ በኋላ የመጣም ይሁን ያለና የነበረ በሁለቱም መልኩ አማራ አለ ለሚል ድምዳሜ ከመብቃት ውጪ ሌላ መላምት ለማግኘት አያስችልም።

የወቅቱን የጎንደር፣ የጎጃም፣ የወልቃይት አማራዎች ያለማንም አደራጅነት መንቀሳቀስና የአማራነት ማሰሪያ ክርን በማጠናከር የጋራ ጠላት ባሉት አካል/ስርዓት/ ላይ በእምቢተኝነት እንደተነሱ ፕሮፌሰሩ ከብዙዎቻችን በተሻለ መረጃው አላቸው። እንግዲህ የአማራን እንደብዬር

መኖር ባንፈልገውም ብሎም ከጊዜ በኋላ የተገነባ ማንነትም ይሁን ብቻ አማራ እንደ ብሄር አለ። ለዚያውም ብዙ ሚሊዮን፣ ብዙ ሰርዓት ሰራሽ መከራውችን እየተጋፈጠ ያለ። በመሆኑም ታሪካዊም ሆኑ የወቅቱ ሁኔታውች በአማራ እንደብሄር መኖር ላይ ጥያቄ የሚያስነሳ ክፍተት የላቸውም። በዚህ ረገድ አዲስ አስተሳሰብ በመፍጠር ኢትዮጵያን እታደጋለሁ የሚል መነሻ ቢኖር እንኳን መሬት ላይ ያለው ሁኔታ አይቀበለውም። ጊዜው የአማራን ህዝብ በመታደግ ኢትዮጵያን መታደግ እንደሚቻል የሚያስገነዝብ ነው። ስለሆነም እድሜ ከሰጣቸው ፕሮፌሰሩ ስለአማራነትና የአደረጃጀት ስልትን የሚያመላክት፣ ውሃ የሚቋጥርና ከነባራዊ ሃቁ የማይርቅ ጥናት እንደሚያርጉ ተስፋ አደርጋለሁ።

የአማራ ልሂቃን ፓን-ኢትዮጵያዊነት ጉዞ

ስለማንነት ሲነሳ ብሄራቸውን ባለማስቀደም "ኢትዮጵያዊ ነኝ" የሚሉ ከተሜ አማሮች፣ በተለያዮ የአሃገሪቱ ክልልሎችና በአሁኑ የአማራ ክልል የሚገኙ ሰዎችን ማግኘት ይቻላል። እነዚህ ሰዎች የፖለቲካንና ጠቅላላ ሃገራዊ ስርዓትን በብሄር ደረጃ ዝቅ ማድረግ የማይመቻቸው በመሆኑ ከአማራነት በፊት ኢትዮጵያዊ ሆኖ የግለሰቦች መብቶች መከበር ለማህበረሰብ መብት መከበር መዳረሻ ነው ከሚል መነሻ ነበር። ብዙሃኑ የግለሰቦች ድምር በመሆናቸው በግለሰብ ደረጃ የሃጎስ ወይም የበቀለ ቋንቋ ከተከበረ የብሄረሰባቸው ቋንቋ የማይከበርበት አመክንዮ የለምና። በተጨማሪም ምንም እንኳን በአማራ ህዝብ ላይ እየተደረገ ያለው ሁሉ አቀፍ የማዳከም ተግባር አይነቱና መጠኑ የበረከተ ቢሆንም እስካሁን ህዝቡ በተፈለገው መልኩ የስነ-ልቦና የበታችነት ተጠቂ አልሆነም። ይህም የስነ-ልቦና ልዕልና በሃገር ውስጥ የብሄር ጭቆናውን ችላ ብለው በኢትዮጵያን ዘርፈ ብዙ የስርዓት ለውጦችና ሃገራዊ አንድነት ላይ ትኩረት በማድረግ የሚታገሉ ልሂቃኖቹ ከሌላው ማህበረሰብ የላቀ ቁጥር እንዲኖራቸው አስችሏል። በዚህ ደረጃ መሰለፉ የሚነቀፍ አይደለም ግን የስርዓቱ ይህን አይነቱን አስተሳሰብ የሚገዘግዙ ብዙ ጠላቶችን ያዘጋጀለት በመሆኑ ውጤታማ አልሆነም። በሌላ በኩል ይህ አሰላለፍ የአማራ ብሄረተኝነት እንዳያብብ አንዱ ምክንያትም ነው። በሌላ አገላለጽ አማራዊነትን የሚያንጸባርቅ አደረጃጀትና ውክልላ የተዳከመ እንዲሆን አስተዋጽኦ አደርጓል። የትግሉ ሃይል ይከፋፍላልም።

የአማራ ማህበረ-ኢኮኖሚ ገጽታ

የፖለቲካ ውክልና ያለማግኘት መብት ሌሎች መብቶችን ለማጣት ሁነኛ ምክንያት ስለመሆኑ የሚከራከር ያለ አይመስለኝም። ስልጣን ያለው የመንግስትን ሃብት ያዛል፣ ክፍፍልን ያጸድቃል፣ የትና ምን መደረግ እንዳለበት ይወስናል። በዚች ሃገር የባለስልጣን ደብዳቤ

ስንቅም፣ ትጥቅም ነው። ለምሳሌ ስልጣን ካለ አዲስ አበባበ ወይም ባህር ዳር አሊያም አሶሳ ላይ 10 ሜጋ ዋት በሚሆን ሃይል በኤሌክትሪክ ምጣድ በቀን አንድ ሽህ እንጀራ ጋግሮ እንጀራውን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ፈቃድ የጠየቀን ባለሃብት " የኤሌሪክ ሃይል እጥረት አለብን" በሚል ፈቃድ በመከልከል መተማ ወይም እዚያው አሶሳ 800 ሜጋ ዋት በሚጠይቅ ሃይል የሲሚንቶ ፋብሪካ ለሚከፍት ድርጅት ፈቃድ መስጠት ያስችላል። የትኛው ድርጅት ከፍተኛ ሃይል እንደሚጠይቅ ማብራራት ተገቢነት ያለው አይመስለኝም። በታዳጊ ሃገራት ነባራዊ ሁኔታ የፖለቲካ ስልጣን መቆናጠጥ እንኳን የማህበረ-ኢኮኖሚ ኩነቶችን መቀየር ቀርቶ ሃገራዊ ታሪክንም እንዳልነበረ ማድረግና አዳዲስ ከፖለቲካ ፍላጎት የሚመነጩ የታሪክ መዝገቦች ለመቀመር ያስችላል። የኢትዮጵያም ከዚህ አይነቱ ክሽፈት ነጻ አይደለችም። የስርዓቱ ቁንጮዎች ታሪኩን ሳይሆን ታሪክ እንዲሆንላቸው የሚፈልጉትና የሚጽፉትን ልብወለድ ከጥናትና ምርምር ውጤት በላይ የሚታመንበት ሁኔታም ይታያል።

ዋናውን ጉዳይ ማለትም የአማራን ማህበረ-ኢኮኖሚ ሁኔታን በተመለከተ የብሄረሰቡ አባላት አንገታቸውን እንዲደፉ የሚያስችል የተደራጀ ፍረጃና የችግሮች ሁሉ ባለቤት የማድረጉ ስር የሰደደ ሴራ በእያንዳንዱ ግለሰብ ስነ-ልቦና ላይ የሚፈጥረውን ጫና ወደጎን እንተወውና አማራ እንደብሄረሰብ በአገሪቱ ካሉ ከሁሉም ብሄረሰቦች ያነሰ የህዝብ እድገት መጠን ያስመዘገበ ህዝብ ነው። ከአማራ ህዝብ ቀጥሎ የመራባት መጠኑ ያሽቆለቆለበት አዲስ አበባ ህዝብ ነው። በኢኮኖሚውም ዘርፍ በክልሉ ራስን መቻል አዳጋች የሆነባቸው ዜጎች እጅግ የበዙ ከመሆናቸው የተነሳ አል-ጀዜራ ቴሌቪችርን እ.ኤ.አ. በመስከረም 29 ቀን 2014 በሃገሪቱ የመጨረሻውና የተጎሳቆሉ ዜጎች መኖሪ ሲል በዶክመንተሪ ሃቁን ለአለም አስረድቷል።[23] ይህው ጥናታዊ ፊልም የአማራ ክልል ከኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአለምም የድሃዎች ድሃ አካባቢ ነው ብሎታል። ይህ መረጃ ኢትዮጵያ አስራአንድ በመቶ እድገት አስመዘገብኩ እያለች በነበረችበት ወቅት መሆኑ ሃገራዊ ልማቱና የአማራ ክልል ያለተመጋገቡ መሆኑን ለመገንዘብ የሚያስችል ወይም የልማቱ ጠብታ ለተጠቀሰው ክል ህዝብ ያስገኘው ፋይዳ ወዴት ገባ የሚል ጥያቄ እንዲነሳ ያሚያስችል ነው። ለዚህ ጫፍ የረገጠ ድህነትን በህዝብ ላይ የመጫን ተግባር

[23]Al- Jazeera (29 Sebtember 2014). Al- Jazeera- Amhara Region; not only the poorest in Ethiopia but the world. Available at https://m. www.youtube.com, accessed on 10 Sebtember 2016.

መገለጫውን በማሳየት የአማራ ክልል መንግስትም በ2009 ዓ.ም. እማኝነቱን ሰጥቷል።[24] ክልሉ በህጻናት መቀንጨር በሃገሪቱ ግንባር ቀደም ነው።

<u>በትምህርት</u> ረገድ ክልሉ በዝቅተኛ አፈጻጸም ላይ እንዳለ የሚታወቅ ነው። የአማራ ህዝብ ከአብትና ከቅኔ ትምህርት ጀምሮ ለየትኛውም አዳዲስ እውቀት በሚያስገኝ ተቋም የመሳተፍ፣ እውቀት የመቅሰምና የመመራመር ታሪክ ያለው ነው። ግን ዛሬ ላይ በትምህርት ረገድ "ዝቅተኛ ተሳትፎ ካላቸው አካባቢዎች/ክልሎች/ የሚመደብ ነው (ብርሃኑ ግርማ፣ 2017 እኤአ)። "ውጤታማ ያልሆኑና ፈተናዎችን ማለፍም የሚያዳግታቸው"[25] ተማሪዎች ብዙዎች ናቸው። ለዚህም የአማራ ክልል የመሰረ-ልማት እጦት፣ የጤና ችግር (በኢኮኖሚው ድቀትና በድህነቱ የተናሳ ጤናማ ትውልድን መፍጠር ባለመቻሉ)፣ ቋንቋ ነክ የትምህርት ፖሊሲ፣ በክልሉ የተሻለ የአካዳሚያዊ አቅም ያለውና የተማረ የሰው ሃይል ክልሉን ከማገዝ ይልቅ እንዲሰደድ የሚደረገው ጫና በተለያዩ የሃገሪቱ አካባቢዎች የአማራ ተወላጅ አቅሙን የሚያዳብርበት የትምህርት እድል ላይ የሚደረገው አድሎና ማግለል እንደምክንያት የሚወሰድ ነው። የመሰረተ ልማት ባልተሟላበት ሁኔታም ትምህርት ስኬታማ ስለማይሆን እየደከመው ትምህርት ቤት ደርሶ የሚመለስ የተማሪ ቁጥር ከመመዝገብ ያለፈ ነገር አይጠበቅም። በሌላ አገላለጽ ትምህርት ቤቶች እድሜና ጉልበት መጨረሻ ከመሆን አያልፉም። "በትምህር ተቋማት ስርጭትምና ተደራሽነትም"[26] በኩል ክልሉ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው።

ዜጎች ብዙውን ፈተና አልፈው የተወሰኑ የትምህርት ደረጃዎችን ላጠናቀቁ ምሁራን የትምህርት እድገትና የማሻሻያ ስልጠናዎችን በማግኘት ረገድ ስርዓታዊ አድሎ መኖራቸውም የሚዘነጋ አይደለም። በተለይ በመንግስት በኩል የሚያልፉ የውጪ ሃገር የትምህርት እድሎችን

---

[24] ክልሉ በኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት መቸገሩን፣ በ10 አመት ወስጥ አዲስ የአቅርቦት ዝርጋታ ያለመኖሩን፣ በክልሉ ለልማት አመቺ ሁኔታ አለ ብሎ ለመናገር እንደማይችል እና በሃገር ደረጃ የኢሌትርክ ሃይል አቅርቦት እድገት መኖሩን የክልሉ መንግስት ለፌደራሉ መንግስት አስታውቋል።

[25] In the 2016 academic year, more than 65 percent of Amhara students between the ages of 16 and 20 failed the national 10th grade certificate examination. As to 12th graders, only 35 percent got passing results for university admissions. Apart from purposely producing a large number of Amhara failing students at the 10th and 12thgrades, the ministry of Education makes sure that Amharas illiteracy rate is kept at the maximum. Half of all men in Amhara don't read and write. The Central Statistics Agency of Ethiopia in its 2011 report confirmed that: *"Among regions, the* proportion of females and males with no education … in … Amhara for men ***(47 percent) (*** Abinet Hunegnaw, 2017).

[26] Ajala and Asres (2008) argued further that the current number of higher education preparatory schools in Amhara region run contrary to the present government policy on higher education. The federal government has recently established more universities in the country to increase access to university education in Ethiopia. However, in Amhara region there are 24 higher education preparatory schools, which is a prerequisite to regular university admission. This is quite inadequate for the number of students completing their grade 10, thus it puts the students from Amhara region at disadvantage among the nine regions in Ethiopia. It shows a high level of inaccessibility to education (Girma Berhanu, 2017).

ለማግኘት ብሄርን ወይም የፖለቲካ ታማኝነት መሰረት ተደርጎ አንደሚሰራና በዚህም አማራን ጨምሮ በርካታ የኢትዮጵያ ህዝቦች ከእድሉ ተጠቃሚ እንዳለሆኑ በእኤአ 2017 የታተመውና ብርሃኑ ግርማ የተሰኘ ተመራማሪ ጥናታዊ ጽሁፍ ያስረዳል። በመሆኑም በትምህርት ረገድ በእኩልነት የመታየትና ሙያን የማሳደግ መብት በእኩልንት ላይ ያልተመሰረተ እነዲሆን የሚያደርግ ነው።


<u>ቋንቋና ትምህርት</u>፡ የቋንቋን ጉዳይ ስናነሳ የክልሉ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እስከ 9ኛ ክፍል ድረስ እዲማሩ መደረጉ ይታወቃል። ግን ዘጠነኛ ክፍል ሲደርሱ በእግሊዘኛ እንዲማሩና ከዚያም 10ኛ ክፍል ላይ በእንግሊዘኛ ፈተና እንዲወስዱ ይደረጋሉ። በሃገሪቱ እንግሊዘኛ ሳይችሉ እንግሊዘኛ የሚያስተምሩ መምህራን በበረከቱበት ወቅት በሁለት አመት እንግሊዘኛን የመረዳት አቅም ያዳብራሉ ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነው። ወደፊተና በማስገባትም ጥያቄውን በአግባቡ ተረድተው የሚፈተኑና በእውቀት ተወዳዳሪ ይሆናሉ ለማለት አያስደፍርም። ለምን 7ኛና 8ኛ ክፍል በእንግሊዘኛ አይማሩም? የማያዋጣ መንገድ በመከተል ግትር አቀቋም ባለው መንግስት እየተገዛን እንደሆነ ይሰማኛል። "ኢትዮጵያ ከቻይና እየተወዳደረች ወይም እንደጃፓን አምራት ከሆነ የዩኒቨርሲቲዎቿንም ትምህርት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማድረግ ነው። የተማሪዎቹ የመረዳት ችግር በተግባር እየታየ ነው። ዩኒቨርሲቲ ገብተው እንኳን አብዛኞቹ ሃሳባቸውን መግለጸ እንደማይችሉ የተረጋገጠ ነው። የኦሮሚያና የትግራይም ተማሪዎች የዚህ ችግር ተቋዳሽ ቢሆኑም የአማራና የኦሮሚያ ልጆች የቋንቋ ችግር የባሰ ደረጃ ላይ እንዳለ በሶስት ተከታታይ አመታት የዩኒቨርሲቲ ምልከታየ ማረጋገጥ ችያለሁ። በመሆኑም የትምህርት ሁሉ አቀፍ ተደራሽነት፣ ጥራት፣ በተወዳዳሪነት ውጤታማ መሆን አዳጋች እየሆነ ነው።

<u>መሰረተ ልማት</u>፡ በመሰረተ-ልማት በኩል ምሳሌ ብናነሳ በ2009 ዓ.ም. የክልሉ መንግስት ይፋ ባደረገው መረጃ በክልሉ ባለፉት አስርት አመታት አንድም የኤሌክትሪክ ሃይል ማሰራጫ ሰብ ስቴሽን እንዳልተተከለና አሁን ላይ ያሉ ኢንደስትሪዎች አደጋ ላይ እንደወደቁ ወደፊትም ምንም አዲስ ኢንቨስትመንት ለመጥራ እንደማይቻል ታወቋል። በሃገሪቱ ግን ብዙ የኤሌትሪክ ሃይል የተገነባባት ወቅት እንደሆነ የሚዘነጋ አይደለም። ፍትሃዊ ግን አይደለም። በመንገድ ረገድ አወዛጋቢውን አርማጨሆን ትተነው ሰሜን ሸዋን ብናነሳ ከደብረብርሃን እስከ ታሪካዊው አንኮበር ድረስ ያለው 45 ኪሎ ሜትር መንገድ አንኳን አስፓል መሆን ቀርቶ የተደላደለ ጥርጊያም አይደለም። የመንዝን፣ የደብብን፣ የእንዋሪን፣ የኮላሽን፣ የአጠረትን፣የአህያ-ፈጅን፣

የወረውን ዳገታማና መኪና የሚባል የማይደርስባቸውንና ከደብረብረሃን-መሃልሜዳ ያለውን መንገድ ያስተዋለ በ21ኛው ክፍለ-ዘመን የተራሳ ህዝብ ስለሞሩ ምስክር ነው፡፡

በሌላ በኩል አማራ ክልል የመሰረተ ልማት ችግር ባልተፈታበት ወቅት በ2009 ዓ.ም. ለቀውስ ማርገቢያነት የፌደራሉ መንግስ 10 ቢሊዮን ብር መመደቡ ይታወቃል፡፡ ከዚህ በጀት ክልል ድርሻውን ወስዶ ለማከፋፈል ቢመክር ገንዘቡን ለማምረት አላማ ማዋል የሚያስችል ነባራዊ ሁኔታ የለም ማለት ነው፡፡ ገንዘቡ ለወጣቱ ቢከፋፈል እንኳ ተበዳሪዎቹን ባለእዳ ከማድረግ ያለፈ ፋይዳ የሚሰጥ አይሆንም፡፡

ካርታ 6፡ የመንገድ መሰረተ-ልማት ስርጭተና እድገት የሚያሳይ (Road density and length between 2006 and 2016)



Source: World Bank visualization based on data from various UN agencies (Map taken from World Bank report based on a spatial review of Ethiopian road density within 10 years (2006-2016))

የህዝብ እድገት ምጣኔና የህዝብ ቁጥር

የኢፌዴሪ ማዕከላዊ ስታቲስቲካል ባለስልጣን የ1999 ዓ.ም. የህዝብና ቤት ቆጠራን ውጤት መሰረት በማድረግ ይፋ ባደረገው መረጃ መሰረት የአማራ ክልል የወሊድ መጠን 1.4 ሆኖ ጠቅላላ የክልል ህዝብ ብዛት 17,221,976 ነው፡፡ ከዚህ አሃዝ 15,752,992 የሚሆን ነው የአማራ ብሄረሰብ ነው፡፡ በሃገሪቱ እንደ ብሄር ጠቅላላው የአማራ ህዝብ መጠን 19,878,199 እንደሆነ ይህው መንግስታዊ መረጃ ይፋ አድርጓል፡፡ የሃገሪቱ የወሊድ መጠን በመቶኛ 2.7 እንደሆ ሃይለማሪም ተክሉና ሌሎች (እኤአ 2013) ጸኃፊዎች የማዕከላዊ ስታስቲካል ባለስልጣንን ዋቢ በማድረግ ጽፈዋል፡፡ ይህመ ከአማራ ህዝብ የእድገት ምጣኔ በ1.3 የሚበልጥ ነው፡፡ በዚሁ በ1999 ዓ.ም. የህዝብ ቆጠራ የአደስ አበባ ህዝብም አነስተኛ የእድገት ምጣኔ የተመዘገበበትና የህዝብ ቁጥሩም ከሚታሰበው በታች ያሽቆለቆለ ነበር (ከታች በሰፊው ይዳሰሳል)፡፡

የአማራና የአዲስ አበባ ህዝብ ቁጥር ማነስ በፌደራሉ ምክር ቤት የመወያያ አጀንዳ ሆኖም ነበር፡፡ በመሆኑም በተወካዮች ምክር ቤት የተለያዩ አስተያየቶች ተሰጥተዋል፡፡ አቶ ይልማ የተባሉ የተወካዮች ምክር ቤት አባል “በሃገሪቱ ያልተዛባ፣ ወጥ የሆነ ስታስቲክስ እንዲኖር እፈልጋለሁ፣ አሁን ግን የተዘበራረቀ ስታስቲክስ ነው ያለው፣ በተለይም ደግሞ በአማራው ላይና በአዲስ አበባ መሆኑ ቅር አሰኝቶኛል፤ ምክንያቱም ይህ ጉዳይ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚዊና ማህበራዊ እንድምታ ስላለው ነው” በሚል ስሜታቸውን አንጸባርቀዋል፡፡ አዲስ አበባን ህዝብ ቁጥር አስመልክቶ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ አስተያየት ሲሰጡ “የሀገሪቱ የህዝብ እድገት መጠን 2.7 ሆኖ ሳለ የአዲስ አበባ ህዝብ ቁጥር ከቀድሞው ያነሰ በመሆኑ የአሁኑን የቆጠራ ውጤት ማንም ሊያምን አይችልም” ብለዋል፡፡ አዲስ አበባብ ነጥለን ብናይ ይህ አይነት መዛባት በጥያቄ ብቻ የሚታለፍ እንዳይሆን ከሚያደርገው ዋነኛው ጉዳይ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት በጨመረበት ወቅት መሆኑ ነው፡፡

በወቅቱ በተወካዮች ምክር ቤት አባላት ለተጠየቁ ጥያቄዎች መብራሪያ ለመስጠት መድረኩን የተረከቡት አቶ አዲሱ ለገሰ “ችግሩ ጎልቶ የታየው በአማራ ክልል ላይ ነው፤በምክር ቤት በጸደቀው የቴክኒካል መለኪያ መሰረት የክልሉ ህዝብ በተግባር ተቆጥሮ በማዕከላዊ የስታቲስቲካል ባለስልጣን የተገለጸው ውጤት ይፋ እንደሆነ የታየው መፋለስ እንዳስተዋልን ወደኋላ መፈተሽ ጀመርን፡፡ በፍተሻውም የ1987 ዓ.ም. የአማራ ህዝብ የእድገት መጠን ባልሳሳት 1.83 ሆኖ አገኘነው” አሉ፡፡ ቀጥለውም “ይህም የእድገት መጠን ጥያቄ የሚያስነሳ ሆኖ አግኝተነዋል፤ ወጣ ያለና የማያሳምን ጉዳይ አለው፤አማራው ከሌላው የገጠር ማህበረሰብ የተለየ ገጽታ እንደሌለውም ተገንዝበናል” በማለት የሚፈጥረውን/የፈጠረውን/ ግራ መጋባት አውስተዋል፡፡ በተመሳሳይ መድረክ ወይዘሮ ሳሚያ ዘካሪም (የህዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን አባልና ጸሃፊ) በአማራ ህዝብ ላይ ስርዓታዊ (systematic) መቀነስ ነው የታየው በማለት ስርዓት የተዘረጋለት አማራን የመቀነስ አሰራር መስፈኑን ጠቁመዋል፡፡

ጉዳዩን በዝርዝር እንየው፡፡ የ1987 ዓ.ም. የአማራ ህዝብ የእድገት መጠን መጠኑ እንዴት ሊሆን ቻለ በሚል አቶ አዲሱ ለገሰ ጥያቄ አንስተናል ሲሉ በፓርላማ ተናግረዋል፡፡ መጠየቃቸው መልካም ቢሆንም መልሱም ከእርሳቸው ከነባሩ ታጋይና ጓዶቻቸው ዘንድ እንዳለ እገምታለሁ፡፡ ለታየው ቅናሽ ምክንያት ሊሆን የሚችለው አንደኛ አውነትም ህዝቡ ባለመራባቱ የተገለጸው ውጤት ትክክል በመሆኑ፤ ሁለተኛ ተገቢ ቆጠራ ባለመደረጉና ሶስተኛ በቆጠራው የተገኘው ውጤት ታስቦበት ወይም በስህተት ተቀንሶ ከተገለጸ ነው፡፡ ከአሀገሪቱ አማካኝ በእጂጉ

የወረደ የእድገት መጠን በ1987 ዓ.ም. (ማለትም 1.83) ሲታይና ተመዝግቦ ሲቆይ በወቅቱ ጥያቄው ያለመነሳቱ በራሱ በወቅቱ ስለአማራን ህዝብ ጉዳይ በአግባቡ የሚመክር፣ የሚጠይቅ ተወካይ ያለመኖሩን የሚያሳይ ነው። እንደሚታወቀው የብሄር ፖለቲካው ከሚነገረው በላይ የጦዘ ስለነበርና የአማራን ህዝብ ጥያቄ በጎሪጥ በማየት ጸረ-አማራ አደረጃጀት በመጎልበቱ ስለአማራ ቁጥር ማነስና የወሊድ መጠን ማሽቆልቆል የሚቆረቆር መፈለግ አላዋቂነትን የሚያሳብቅ ነው። አዲሱ ለገሰም በዚያን ዘመን የስርዓቱ አካል ነበሩ፤ ለዚያውም ከላይኛው እርከን ላይ። ዛሬ ግን የአማራ ጉዳይ ያገባናል ያሉና ወደ ህሊናቸው የተመለሱ የተወካዮች ምክር ቤት አባላት ጥያቄውን ሲያነሱት አቶ አዲሱም እንደአዲስ ለምን ሆነ ብለን ጠየቅን ብለዋል። ያኔ 1987 ዓ.ም. ተቀንሶ የተቀመጠው የአማራ ህዝብ እድገት መጠን ለአሁኑ ማሽቆልቆል ማረጋገጫና መንደርደሪያ እንዲሆን ከማስቻል ውጪ ታዓማኝነት ያንሰዋል። የችግሩን መንስኤ ቁልጭ አድረጎ የሚያሳየን መረጃ ከወይዘሮ ሰሚያ ዘካሪያ የተሰጠው ነው። ስርዓታዊ (systematic) ነው ብለዋል። ስርዓታዊ ስንል የፖሊሲ አቅጣጫ የተዘጋጀልት በጀትን ጨምሮ፣ ግብአቶች የተሟሉለት፣ መንግስታዊ ይዘት የያለው ይፋ ወይም ህቡዕ አሰራር፣ ወ.ዘ.ተ. ይመልከታል።

ይህንኑ የሳሚያን ገለጻ የሚያጠናክርልን የምርምር ውጤት በሙሉቀን ተስፋው የቀረበ ሲሆን ዝርዝር ምክንያቶቹን በማካት የአሃዝ ማስረጃዎችን በማካተት የአቀናነስ ታሪካዊ ሂደቱንም አሳይቷል። የአማራ ህዝብ ባለንብት የሰለጠነ ዘመን በህይወት የመኖር ተፈጥሯዊ መብቱ የተነፈገ ህዝብ መሆኑን እንደሚከተለው ያስረዳል።

> *በአማራ ህዝብ ላይ የተከፈቱ ዘመቻዎች ሁሉ አቀፍና የተቀናጁ ሆነው እናገኛቸዋለን። አንድ ቦታ ላይ ሲፈናቀል ሌላ ቦታ ላይ በጅምላ በጥይት ይገደላል፤በሌላ ቦታ ከነ ህይወቱ ገደል ይጣላል፤በሌላ አቅጣጫ በቤተሰብ ምጣኔ ሰበብ የመራባት መብቱ ይገደባል፤በተናጠልም የሚገደልበት ቦታ አለ፤አንዱ ቦታ ላይ በጅምላ ይሰደዳል/ይፈናቀላል/፣ ሁሉም ቦታዎች ላይ በህብረት ይደኸያል፣በህብረት የስኑልቦና ጥቃት ሰለባ ይሆናል (ሙሉቀን ተስፋውን፣2008 ዓም.)*

ከላይ የተገለጸው እንዳለ ሆኖ ጸኃፊው በአማራ ህዝብ ላይ የተሰነዘረውን ጥቃት ስርዓታዊነት ከጣሊያን ወረራ እስከ አሁኑ መንግስት ያለውን የታሪክ መስረጃ በማጣቀስ አስረድቷል። በጠቅላላው እኤአ ከ1974 ወዲህ የታየውን የአማራ ህዝብ ቁጥር አንጻራዊ ማሽቆልቆል ከዚህ ቀጥሎ ቀረበው ሰንጠረዝ ያስረዳል።

ሰንጠረዥ 1፡ የአማራ ህዝብ ከሌሎች ህዝቦች በተለየ የአቀናነስ ሂደት

ብሄረሰብ	1974	1984	1994	2007
አማራ	10 ሚሊዮን	12,055,250	16,007,933	19,878,199
ኦሮሞ	7 ሚሊዮን	12,387,664	17,080,318	25,363,756
ትግሬ		-	3,284568	4,486,513
ሌሎች		-	16,759460	24,022,464
ድምር		42,616,876	53,132,279	73,750,932

ምንጭ፡ ከሙሉቀን ተስፋው የተወሰደ ገጽ 27 (የ2007 እኤአ የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታስቲስቲካል ሌጀንሲን ዋቢ አድርጎ እንዳቀረበው)

ከላይ በሰንጠረዡ እንደሚታየው በአጠቃላይ በሃገሪቱ ከ1974 ቆጠራ ወዲህ ያለው ዘመን የአማራን ህዝብ ቁጥር የሚያመናምን ነበር (የሙሉቀን ተስፋውን ከገጽ 38 እስከ 166 ያንብቡ)፡፡ በተለይም በከ1994 እስከ 2007 ድረስ ከክልልሉ ውጭ 84,0449 ባሉ አካባቢዎች አማራ ከሳይንሳዊ አመክኗውነት ውጪ ጠፍቷል (ዝኒ ከማሁ ገጽ 28)፡፡ በአማራ ክልልና በአዲስ አበባ ደግሞ በርካታ ሚሊዮን ህዝብ የት እንደደረሰ አይታወቅም ወይም መኖር የሚገባው ህዝብ የለም፡፡

<u>አማራ በአዲስ አበባ</u>፡ የአዲስ አበባን ህዝብ በተናጠል ስናየው በ1999 ዓ.ም. በመንግስት በተከናወነው የህዝብ ቆጠራ መሰረት ከጠቅላላው 2,739,551 ህዝብ ውስጥ 1,288,895 የሚሆነው አማራ ሲሆን 534,547 ኦሮሞ፣ 447,777 ጉራጌና 169,182 ትግሬዎች ናቸው፡፡ ቀሪውን ቁጥር የተለያዩ ብሄረሰቦች ይሸፍኑታል፡፡ በዚህ ዳታ መሰረት ከተማው ነዋሪ 47 በመቶ የሚሆነው የአማራ ህዝብ ነው፡፡ይህም የሚያሳየው በአዲስ አበባ ህዝብ ቁጥር በተዛባ መልኩ መቅረብና ወይም እንዲቀንስ ማድረግ የፖለቲካዊ ውክልናና የሃብት ክፍፍል ይህንኑ መረጃ መሰረት አድርጎ መደልደሉና በእርግጥም የህዝቡ ቁጥር ቀንሶ/እድገቱ ተቋርጦ ወይም ዘገምተኛ ሆኖ/ ከሆነ የእድገት ማሽቆልቆል ዋነኛው ገፈት ቀማሽ አማራ ይሆናል ማለት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ካአዲስ አበባ ነዋሪዎች ወደ ሃምሳ በመቶ የሚጠጋው ህዝብ የአማራ ህዝብ በመሆኑ በአማራ ክልልም ሆነ በአዲስ አበባ የሚደረጉ የነዋሪ ቁጥር አሳንሶ ማቅረብ ወይም የህዝቡ ቁጥር እንዲያንስ ስርዓታዊታ ታክቲክ ቀይሶ መንቀሳቀስ በአማራ ህዝብ ላይ አደጋ መጣል መሆኑን መረዳት የሚያዳግት አይሆንም፡፡

ጉዳዩን በዝርዝር ለማየት ስንሞክር በ1999 ዓ.ም. ቆጠራ ከሁሉም ክልሎችና አካባቢዎች ያነሰ አማካኝ የህዝብ እድገት ምጣኔ ያለው የአማራ ህዝብ በብዛት የሚኖርባቸው አካባቢ ነው፡፡ የሁሉንም ክልሎች የእድገት መጠን በሚከተለው ሰንጠረዥ እንመልከት፡፡

ሰንጠረዥ 2፡ የኢትዮጵያ ህዝብ አድገት (growth rate) **በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች ተነጣጥሎ ሲታይ**

ተ. ቁ.	ክልሎች	እድገት መጠን	ምርመራ
1	ትግራይ	2.5	
2	አፋር	2.2	
3	አማራ	1.7	ዝቅተኛ የህዝብ እድገት መጠን ያስመዘገበ ክልል
4	ኦሮምያ	2.9	
5	ሶማሊ	2.6	
6	ቤኒሻንጉል ጉሙዝ	3.0	
7	ደቡብ ህዝቦች	2.9	
8	ጋምቤላ	4.1	ከፍተኛ የህዝብ እድገት መጠን ያለው ክልል
9	ሃረሪ	2.6	
10	አዲስ አበባ	2.1	በሁለተኛ ደረጃ አነስተኛ እድገት ያስመዘገበ የከተማ አስተዳደር
11	ድሬድዋ	2.5	
12	ሃገራዊ የህዝብ እድገት	2.6	

ምንጭ፡ Annual Population Growth Rate by Region between 1994-2007 (Summary and Statistical Report of the 2007 (እኤአ) Population and Housing Census Results)

የህዝብ ቁጥር ቅነሳ ሳይንሳዊ አመክኖዎችና የአማራ ህዝብ

የአንድ ህዝብ የእድገት መጠኑ ሊያሽቆለቁል የሚችለው በስድስት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው፡፡ በመጀመሪያ በስዎች እልቂት የታጀበ ጦርንት ሲኖር፣ ሁለተኛ ከፍተኛ በሽታ ሲኖርና በሽታው የመዋለድ እድልን የሚገታ ወይም እልቂትን ያስከተለ ከሆነ፤ ሶስተኛ ማህበረሰቡ የስልጣኔ ደረጃው ከፍ እያለ በመጣ ቁጥር በቴክኖሎጂ በመታገዝ ወሊድን መቆጣጠር ሲጀምር፤ አራተኛ ስደትና መፈናቀል ሲከሰትና የማህበራዊ ኑሮን ማዛባት ሲችል፣ አምስኛ መንግስት ውልደት ገዳቢ (የአንታይ-ናታል) ፖሊሲ በመከተሉ የወሊድ መጠንን በመቀነስ የሚገኝ የገንዘብ ማበረታቻ ሲሰጥና ህዝብ ሲቀበለው፤ ስድስተኛ በሆነ ቡድን ወይም መንግስት ከዜጎች አውቅና ውጪ የወሊድ መጠንን የሚቀንስ ስልታዊ እርምጃ ሲወሰድ ነው፡፡

በሌላ በኩል አንድ ብሄር ቁጥሩ ሊቀንስ የሚችለው የመዳቀል (Assimilation) በሰፊው ካለና በዚያ ብሄር ማንነት የሚጠሩ ግለሰቦች ሲቀንሱ ነው፡፡ በተጨማሪ ሃብተማሪያም፣ አሉላና ተስፋይ (እኤአ 2013) ባሳተሙት የውልደት መጠንን ተለዋዋጮችን በሚተነትን ጽሁፍ የውልደት መጠን ከአገር ሃገር የሚለያይ ሲሆን ይህም በባህል፣ኢኮኖሚያዊና የጤና ሁኔታዎች ለለዩነቱ እንምክንያት ሊታሰቡ የሚችሉ ናቸው ይሉናል፡፡ እነዚሁ ጽሃፊዎች ከላይ የተጠቀሰውን ሃሳብና የይሆናል አማራጮች በሚደግፍ ወይም በሚያጠናክር መልኩ፣

የማህበረሰብ አሴትና ሌሌች ተያያዥ ማህበራዊ ጉዳዮች የውልደት መጠንን በአወንታዊና በአሉታዊ መልኩ እንደሚወስኑ ያብራራሉ[27]።

በዚህ ጽሁፍ ዋና ጉዳያችን የወሊድ ምጣኔን በአሉታዊነት የሚወስኑ ጉዳዮች በመሆናቸው የአማራን ህዝብ ከሌሎቹ ብሄሮች ባነሰ የወሊድ መጠን ማስመዝገብ፣ የህዝብ ቁጥሩ የተለያዩ የአለም አቀፍ ድርጅቶች ከተነበዩት በእጅጉ አንሶ መገኘት ከላይ ከተጠቀሱት ይሆናሎች (scenarios) በአንዱ፣ በተወሰኑት ወይም በሁሉም ምክንያቶች እንደሚሆን መገመት አይከብድም። የአማራን ህዝብ ቁጥርና የወሊድ መጠን በይሆናል መነጽር ብንመለከተው ከላይ የተዘረዘሩት ብዙዎች ሁኔታዎች ያልገጠሙት መሆኑ ግልጽ ነው። እንደሚከተለው ላብራራው። በአማራ ክልል በእልቂት የታጀበ የጦርነት እንደሌለ፣ የህዝብ አድገት መጠንን የሚያዛባ ከፍተና በሽታ ባለፉት 25 አመታት ውስጥ ከሌላው አካባቢ በተለየ ሁኔታ ያለመከሰቱ፤ በክልሉ ከሌላው አካባቢ የተለየ የስልጣኔ ደረጃው ያለመኖሩ፣ መንግስት ውልደት ገዳቢ (የአንቲ-ናታል) ፖሊሲና ውልደት ቀናሽ ማበረታቻ የሌለው መሆኑ ይታወቃል። በሌላው ክልል አማራ እየተገፋ በመሆኑና ሃገር አቀፍ ሰፊራ በመቆሙ ወደሌሎች ክልሎች የሚደረግ ስደትና መፈናቀል መቀነሱም እሙን ነው። በአጠቃላይ የህዝብ ቁጥጥር በዚህ ደረጃ ሊቀንስ የሚያስችሉና በአማራ ህዝብ ላይ ብቻ የተከሰቱ ነገር ግን በሌሎች አካባቢ ያልነበሩ ተፈጥሯዊ ክስተቶች እንዳልነበሩ ሚሊዮኖች የምናውቀው ጉዳይ ነው።

ስድስተኛውን መላምት ማለትም በሆነ ቡድን ወይም መንግስት ከዜጎች አውቅና ውጪ የወሊድ መጠንን የሚቀንስ ስልታዊ እርምጃ ሲወሰድ ይችላል የሚለውን መላምት የሚያረጋግጡ የማህበራዊ ሚዲያዎች የጥቃት ሰለባ የሆኑ ግለሰቦችን ጭምር በማቅረብ መረጃ የሚሰጡበት ሁኔታ ቢኖርም በማስረጃነት የሚቀርብ በገለልተኛና ወገን የተረጋገጠ መረጃ ለማግኘት ጊዜ የሚጠይቅ ነው። በሌላ በኩል የህዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጸሃፊዋ ሳሚያ ዘካሪያ የአማራ ህዝብ ስርዓታዊ (Systematic) ቅነሳ ነው የታየበት ያሉትም ተቀብሎ ስርዓታዊ ቅነሳው ምን አይነት ዝርዝር ተግባራትን ሊካትት እንደሚችል መላምቶች ማስቀመጥ ይቻላል። የአማራ ህዝብ ከሌላው የገጠሩ ማህበረሰብ የተለየ ነገር ያልገጠመው መሆኑንና ጉዳዩ አወዛጋቢ መሆኑን ወ/ሮ ሳሚያም አቶ አዲሱ ለገሰም ገልጸዋል።

[27] Factors such as the value the society gives to children, preferences relating to the sex of a child and family size, the social position and role of women in a society, economic needs and old age security schemes, and the prevalence of sexually transmitted diseases affect fertility (H/mariam Teklu, Alula Sebhatu and Tesfayi G/selassie (2013).

ስርዓታዊ (Systematic) ቅነሳ ተደርጓል ሲሉ በቅነሳው የመንግስት እጅ መኖሩን መቀበልን የሚያሳይ ነው። ስርዓታዊ ቅነሳ ሲባል ለቅነሰው ገቢራዊነት አጋዥ ግብዓትን የቅነሳ ሂደትን እና ውጤትን የሚመለከት ነው። ስርዓታዊ የሚለው ገለጻ የሚያመላክተው በአጋጣሚ ያልሆነ፣በስሌት የተፈጸመ፣ ሰፊና ወጥነት ያለውና ወጥነቱን የሚስፈጽም ባለቤት ያለው መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው። ስለሆነም በስርዓታዊ ቅነሳ ውስጥ- ጥቃቅን በሽታዎች ገዳይ እንዲሆኖ የመድሃኒትና የመሰረተ-ልማት እጥረትን መፈጥር፣ በታቀደ መልኩ በህዙዕ መካንነትን የሚያስከትሉ ክትባቶችን መስጠት፣ህዝቡን በኢኮኖሚ መደቆስ ማለትም በጀት አመዳደብን ጨምሮ በልማት ሰበብ ባልተመጣጠኝ ክፍያ ማፈናቀል ብሎም ማህበረሰቡ በእኩልነት በኢኮኖሚው እንዳይሳተፍ ስልታዊ ተግባራትን ማከናወን፣ ማዳቀል (Assimilation) እና ማንነት እንዲለውጥ ማድረግ፣ ስደት (ከሃገር ወጪ)፣ ኑሯቸው የተጎሳቆለው ምሁራኖች ተስፋ በመቁረጥና ራስን በመጣል ጋብቻን እንዳይመኙ ማድረግን መጥቀስ ይቻላል። “የወደሊድ መቆያጣጠሪያም”[28] በክልሉ በስፋት ጥቅም ላይ ውሏል። ይህ አነቱ አድራጎት የአማራን ህዝብ ቁጥር ለመቀነሱ ምክንያት የማይሆንበትን አግባብ ለመተንተን የሚያስችል ሃቅ የማግኘት እድላችን ጠባብ ነው።

በክልሉ ውስጥ ያለው ሁኔታ ከላይ በተገለጸው መልኩ ሲሆን ከተለያዩ ክልሎች የማፈናቀል፣ የጅምላ ግድያ፣ ማህበራዊ መሰረቶችን መንጠቅና የአማራን ኢኮኖሚ ማንነትን የማሳጣት ተግባራት ተከታታይነት ለአማራ ህዝብ ቁጥር መቀነስ እንደምክንያት የሚወሰድ ነው። ከመፈናቀል የተረፉ በመፈላቀሉ ሂደትና የአማራ ማህበረሰብ ማንነትን እንዲለውጥ የማድረግ ሂደትንም እንዳለ ከሁለት አስርት አመታት በላይ ሲብላላ ቆይቶ ዛሬ ላይ የፈነዳው የወልቃይት የማንነት ጥያቄ በጠጣር ማስረጃነት የሚቀርብ ነው። የሃገር ውስጥ ስደት ብዙም አንዳልታየ ከሳሚያ ማብራሪያ መረዳት ቢቻልም የአማራ እንስቶች ለሴተኛ አዳሪነት፣ ለአረብ ሃገር ስደት መዳረጋቸው እንዲሁ ልዒቃኖቹ ምን ያህሉ ባገኙት አጋጣሚ እየተሰደዱ መሆኑ በጥናት ባይረጋገጥም በመሬት ላይ ያሉ ተጨባጭ ማሳያዎች ግን አሉ። የመንግስት ባለስልጣናትና ስርዓቱ በአሜሪካ፣ በአውሮፓ፣በደቡብ አፍሪካና በአስራኤል የሚገጥማቸው ተቃዎሞ መበራከቱ ስርዓቱ ከዚህ እያባረረ ለስደት የዳረጋት ኢትዮጵያዊን በተለይም የአማራው ልዒቃን መበርከታቸውን የሚያሳይ ነው። ዋናው ጉዳይ ከላይ የተገለጹት ጫናዎች ለአማራው ህዝብ

[28] According to a September 2004 USAID survey: *“Health institutions (hospitals, health stations, and health posts) were reported as main sources of contraceptive supplies to about two-third of the users in Tigray, and SNRP, 84% in Amhara and 70% in Oromia.”*

ቁጥሩ መቀነስ አስተዋጽዖ እንዳላቸው መረዳቱ ላይ ነው። ውጤቱ በግልጽ የሚታይ በመሆኑ ከላይ የተዘረዘሩ የስርዓታዊ ቅነሳው አካል የሆኑ ተግባራት ለማስፈጸምና ለመፈጸም በህቡዕ የተደራጀ ወይም ግልጽ የተቀመጡ ተቋማት ሽፋን በማድረግ የሚንቀሳቀሱ አካላት ስለመኖራቸው ግምት ማሳድርም የመላምቱ አካል ነው።

ኢኮኖሚያዊ፡ አማራ በሲቪል ሰርቪስ

በአማራ ላይ የሚደረጉ አግላይ ስርዓታዊ ተግባራት ከሁሉም መንግስታዊ ስራ በላይ ትኩረት የተሰጣቸው የሚመስልበት ሁኔታ አለ። የአማራን ብሄር ከሌላው የሃገሪቱ ብሄረሰቦች ነጥሎ በጨቋኝነት ማስቀመጥና የኢህአዴግ መንገስት ከመምጣቱ በፊት ከሹመት እስከሙያ ስራዎች ያሉ የሲቪል ሰርቪሱን ቦታዎች ተቆጣጥሮ እንደነበር የማስረጽ ተልኮ በፌደራል መንግስት እና ክልል መንግስታት እስከታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ ያሉ ባላስልጣናት እንዲካኑት ተደርጎ ብዙ ተሰርቶበታል። መንግስት በተለይ በከተማው ቅቡልነቱ ሲያሽቆለቁልብት የአማራን የበላይነት ለማስተካከል ስንሞክር ነፍጠኛው ተደራጅብን በሚል ሰበካ የሌሎች ብሄረሰቦችን ቀልብ ለመግዛት የምታስችል የተለመደች ትግሉ ቁልፉን ሲያወዛውዝ 25 አመት አልፎታል።

በግል በምስክርነት የተገኘሁበት የ1997 ዓ.ም. የኢህአዴግ ውይይት አማራን የማወገዣ መድረክ እንደነበር አስታውሳለሁ። በሌላ አገላለጽ ይህ መድረክ ስርዓቱ አማራን ከሲቪል ሰርቪሱ የማጸዳም ስራውን ለማሳደግ መቋመጡን በሚያሳብቅ አኳኋን የተቀረጸ ነበር። እንደሚታወቀው በ1997 ዓ.ም. ምርጫ ቅንጅት በከተሞች የበላይነቱን ይዞ ገዢው ፓርቲ እና ምርጫ ቦርድ ባመኑት መሰረት 109 መቀመጫ አሸንፎ በነበረ ማግስት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በየክልሉ በሚገኙ ዩኒቨርሲዎቶች እና አዳራሾች የአቢዮታዊ ዲሞክራሲን እና ሌሎች ተከታታይ ሞጆሎችን ለማሰልጠን ለሳምንታት ስብሰባዎች ተደረጉ። በዚህ ስብሰባ በአጋጣሚ አቶ ተፈራ ዋልዋ በርካታውን ቀናት እና በረከት ስምዖን ለሁት ቀናት በፕላዝማ በሃዋሳ ታቦር ትምህርት ቤት ግቢ ውስ ሲያሰለጠኑ ተካፋይ ነበርኩ። በዚህ ስልጠና ኢሕአዴግ የመንግስት ስልጣን ሲረከብ “የሃገሪቱ የሲቪል ሰርቪስ መስሪያ ቤቶች 50 በመቶ አማራ እና 10 በመቶ ኢትዮጵያዊ ነኝ” የሚሉ ሰዎችን አገኘ ሲሉ አቶ ተፈራ አብራርዋል። አክለውም “10 በመቶ ያህል የትምህኪት ቡድኖት ወይም ከአማራ ብሄር የሚገኙ ናቸው” አሉ። ስለሆነም 60 በመቶ የሚሆነው የሲቪል ሰርቪስ ሰራ በአማራው ብሄር የተያዘ ነው የሚል ድምዳሜን ለማስረጽ ሞከረዋል። ከተወሰኑ ብሄረሰቦች የተወጣጡ ተሳታፊዎች በአማራ በዳይነት ላይ አቋም ይዘው በንዴት ሲንቀለቀሉ በማየቱ ሰበካው ጊዜታዊ ስኬት እንዳመጣ ተገንዝቤ ነበር። አቶ ተፈራ

መንግስት ይህንን የአማራን የበላይነት ለመቀነስ በማመጣጠን ስራ ላይ እንደተጠመደ ነግረውናል። አሁንም፣ በ1997 ዓ.ም.ን ለማለት ነው፣ በከተሞች ነፍጠኛው እና ጥገኛው መበርከታቸውን እና የኢሕአዴግ በከተሞች ለመሸነፉ ዋነኛው ምክንያት ነፍጠኛው፤የዱሮ ስርዓት ናፋቂ ነው ብለዋል። በወቅቱ ጥገኛ በሚል በማሰልጠኛው ማኑዋል የተገለጸው ጉራጌ የሚወክል በመሆኑ የጉራጌ ዞን ተማሪዎች በመቃዎማችን ጉራጌ ለብቻው ተጨማሪ አቢዮታዊ ዲሞክራሲ ጥምቀት በመኩሪያ ሃይሌ እና የጉራጌ ተወላጅ የመንግስት ሹማምንቶች ለአምስት ቀናት በሲዳማ ባህል አዳራሽ ተሰጠ። በመሃል ጫፍ የወጣ ክርክር ሲያደርጉ የነበሩ ተማሪዎች በፖሊስ የተያዙበት ሁኔታ ስለነበር ነገሩ ፍራቻን እያጫረ መጥቶ ኋላ ላይ ተሰብሳቢው ዝምታን መርጦ መታደም ሲጀምር የኢህአዴግ ካድሬዎች ነፍጠኛ ተብሎ በተፈረጀው አማራ ላይ የማውገዝ ነጻነትን ተቀዳጅተው ሰነበቱ።

በተጨማሪም የውስጥ አዋቂው ኤርምሚያስ ለገሰ ባለቤት አልባ ከተሞች በሚል ርዕስ ባሳተመው መጽሃፉ አማራን እና ጉራጌን ከአዲስ አበባ አስተዳደር ሲቪል ስርቪስ የመቀሸብ ስራን እንደሚከተለው ጽፏል።

> "አርከበ በከንቲባነት ዘመኑ የለውጥ ኮሚቴ አዋቀረ፣ በሂደትም ኮሚቴው ወደሚያስፈራ ሀይል ተቀየረ። መሬት መስጠት በታገደበት ሁኔታ የሞቱ ፉይሎችን ህይወት እየዘሩ የከተማዋን መሬት ተቆራመቱ። ወትሮ በዘር ስልቻ ውስጥ ራሱን ከቶ የማያውቀው የከተማው ሲቪል ሰርቪስ በለውጥ ኮሚቴዎቹ ወሬ ምክንያት ዘሩን መቁጠር ጀመረ። አማራነት፣ ጉራጌነት የሚያስጠቃ ሆነ። ከዘር ጋር በተያያዘ በኮሚቴው አባላት የተነዙት ወሬዎች ከእውነት የራቁ አልነበሩም። አርከበ በውስጠ ድርጅት ስብሰባ ላይ" ከአዲሳባ ቢሮክራሲ ውስጥ 65% አማራ በመሆኑ የትምክህት ጫካ ነው። ይህንንም መስበር ይኖርብናል" በማለት በተደጋጋሚ ሲገልጽ ነበር። የእሱን ንግግር ተከትሎ በአቅም ግንባታ ቢሮ በተዘጋጀው የስልጠና ሰነድ ላይ 65% ያህሉ ሲቪል ሰርቪስ አማራ መሆኑ ፍትሀዊ እንዳልሆነና በተራዘመ ጊዜያቶች ቢሮው የማመጣጠን ስራ እንደሚሰራ አስታወቋል። ከጉራጌ ተወላጆች ጋር ተያይዞ የተወሰነው በተቻለ መጠን ወደ ቢሮክራሲውም ሆነ ፓርቲ አመራር እንዳይመጡ መከላከል ነበር። በዚህ ጉዳይ የመጀመሪያው ተጠያቂ አቶ መለስ ሲሆን አርከበ የማስፈፀም ሚና ብቻ ነበረው። የአርከበ ግልጽ ዘረኝነት ከተገለጸባቸው ቦታዎች አንዱ ትምህርት ቢሮ ነበር። ይህ በታሪክ ተወቃሽ የሚያደርግ ስራ የተመራው ከበደ ብሩና ገ/ኪዳን (ክቤና ገሬ) በሚባሉ የአርከበ ቀኝ እጅ የህወሀት ካድሬዎች ነበር። እነዚህ ካድሬዎች ከከተማ እስከ ትምህርት ቤት ያሉትን የለውጥ ኮሚቴዎች በህወሀቶች ጠቀጠቁት። የትምህርት ቢሮ የዝቅጠኝ ግምገማውን አጠናቆ ውጤቱ ይፉ ሲደረግ ያልደነገጠ አልነበረም። ቢሮው የለውጥ ሀይል አይደሉም ብሎ ካባረራቸው 80% የአማራ ተወላጆች ነበሩ።

ኤርሚያስ ራሱም የነበረበት ስርዓት ልቅ የሆነ ጸረ-አማራ ዘመቻ በተገቢው ሁኔታ ገልጾታል። ካላይ ያለው ጽሁፍ ስርዓቱ በአማራ ላይ ጫፍ የረገጠው ጥላቻውን ያለምንም መሸፈኛ ተግባራዊ እንዳደረገው ያስረዳናል። ስርዓቱ ለሰብአዊነትም ርህራሄ ያጣ እንደሆነ ማስተዋል ይቻላል። የተባረረው ሰራተኛ በሱ ላይ ጥገኛ የሆነ ሰዎችን ለረሃብ እንደሚዳርግ፣ ጎዳናም እንደሚያደር የመንግስት ባለስልጣናት አሳምረው ያውቁታል። ዛሬን አያድረገውና ገና ጎፈሬያቸውን ሳይከረክሙ በአዲስ አበባ ኑሮ ፈታኝ መሆኑንም ተምረው አላፈዋል። እናም

ከስራ መባረረ ሰለባውንም በዙሪው ያሉ ሰዎችን ሰቆቃ እንደሚያበዛው ግልጽ ነው። የአርከበን ስራ የአዲስ አበባ ካድሬዎች "የደስታ በሽታ" ብለውት እንደነበርም ኤርሚያስ ጽፏል። የጉራጌ ማህበረሰብም እንደአማራው ሁሉ የዚህ የደስታ በሽታ ዋነኛ ሰለባ ነበር።

በሌላ በኩል አማራን ከሲቪል ሰርቪስ የመቀነስ በመንግስት አጠራር የማመጣጠን ስራ በጂጉ እንደተሰራበት ከበርካታ መረጃዎችን መገንዘብ ይቻላል። በ2008 ዓ.ም. በታተመ የፕሮፌሰር አስራት ቅንጨብ የታሪክ መጽሃፍ "በ1984 ዓ.ም. ከአዲስ አበበ ዩኒቨርሲቲ ከተባረሩ 41 ፕሮፌሰሮች 95 በመቶ የአማራ ምሁራኖች እንደሆኑ ተጠቅሷል" (ጋሻው፣2008 ዓ.ም. ፡182)። ይህን አሃዝ የአሜሪካ መንግስት መንጭ አሳንሶ የገለጸው ሲሆን ከ41 ተሰናባቾች 21 የአማራ ተዋላጆችት እንደሆኑ ያስረዳል። በጎርጎረሳዊን አቆጣጠር 1996 የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር እዝ ውስጥ በተቋቋመ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ከሚቴ ውሳኔ 3961 ጊዜያቸው ሳይደርስ በጡረታ፣ 6397 በሴፍት-ኔት ፕሮጀክት በማቀፍ፣ 4114 በጥቅሉ 14471 ሰራተኞች ከመንግስት ስራ ተቀንሰዋል[29]። የማመታጠን በሚል ሰበብ አማራን ማመናመን የመንግስት አቋም ነውና በዚህ እና ከአለም ባንክ እና በአለም የገንዘብ ድርጂት ፕሮግራም (SAP) መሰረት ብድር ለማሰባሰብ ከተቀነሱ ሰራተኞች አማራው በቀዳሚነት ተሸኝቷል ማለት ነው።

የአማራ ተወላጆች በከተሞችና በፌደራል መስሪያ ቤቶች በርክተው የሚታዩበትን አስመልክቶ ሁለት እውነት አለ። <u>አንደኛ</u>፡ ከ1983 ዓ.ም. ወዲህ የተዘረጋው ቋንቋ ተኮር አሰራር የአማራ ምሁራን አግላይ በመሆኑ ከየክልሉ ገጠራማ አካባቢ እየፈለሱ በከተማ ስራ የመፈለግ ሁኔታ አለ። ገና ከጅምሩ በኦነግ እና ሻቢያ ጥቃት ይሰነዘረብት ስለነበር ወደ አዲስ አበባ እና ወደ ትላልቅ ከተሞች የሚፈልስበት አስገዳጅ ሁኔታም ተፈጥሮ ነበር። ኢህአዴግም ለአማራ ጉዳይ ጆሮ ዳባ ልበስ ከማለቱ በተጨማሪ ጸረ-አማራ ፍረጃውን በማጠናከር ለሞትና ስደት እያመቻቸ ሲሰጠው እንደቆየ የሚሸሸግ አይደለም። ስለሆነም የተሳካለት አዲስ አበባ እና ሌሎች ከተሞች ተቀበሉት የቀድሞ ማህበረ-ኢኮኖሚውን አፍርሶ አዲስ ሲመሰርት በከተሞች በቁጥር የመላቅ እድል የሚያገኝበትም ሁኔታ ተፈጠረ። በብሄር ድልድል ባልተደረገባቸው የሲቪል ሰርቪስ መስሪያ ቤቶችም መታወቂያቸው አማራ የሚል ሰዎች በብዛት ሊገኙ በቁ።

<u>ሁለተኛ</u>፡ ከላይ በጠቀስኳቸውና በሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች መፈናቀልን ጨምሮ የአማራ የኢኮኖሚ መሰረቱ መናጋት ትውልዱ በመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ ከእጅጉ ወደ አፍ ኑሮ ለመግፋት የሚመርጥበት ሁኔታ አለ። በከተሞች የሚገኙ የማህበረሰቡ አባላት የኦኮኖሚ

[29] Paulos Chanie (2001).The Challenges of the Civil Service Reform in Ethiopia: Initial observations.

አቅማቸው ልጆቻቸውን በጥሩ ሁኔታ የማስተማር አድል ስለማይፈቅድላቸው ከ8ኛ ክፍል፣ 10ኛ እና 12ኛ ክፍል እንዲሁም ከዩኒቨርሲቲም ተሰናባቾች እንዲበዙ አስተዋጽዖ ያደርጋል፡፡ እነዚህ ዜጎች በመንግስት መሰሪያ ቤቶች በሲቪል ሰርቫንት ስም በጽዳት፣ አትክልተኝነት፣ተላላኪነት፣ ዘበኝነት የመቀጠር እድላቸው የሰፋበት ሁኔታ አለ፡፡ እንግዲ የጽዳት፣ አትክልተኛ፣ተላላኪ፣ የጥበቃ ስራተኛ መበራከት አማራ የሲቪል ሰርቪሱን ሞላው በሚል መንግስት ለሚያስነግረው ወሬ አስቻይ የቁጥር ማስረጃ ማቅረብ ያስችለዋል፡፡ ሃቁ ግን ብዙዎች የማይመርጡትን ዝቅተኛ ክፍያ የሚያስገኝ ስራ ላይ የተሰማሩ የአማራ ልጆች መብዛታቸውና የተሻ ክፍያ በሚስገኝ የሃላፊነትና የሙ ስራ ላይ የሚሰማሩ የአማራ ወጣቶች በቁጥር አናሳ መሆን ነው፡፡ በማስረጃ ሳሰደግፍ በአንዱ የፊደራል ዩኒቨርሲቲ(አሶሳ ዩኒቨርሲቲ) ከሚገኙ ሰራተኞች በተለይ በአስተማሪነት መደብ የአማራ ብሄር ካለው የህዝብ ቁጥር አንጻር እጅግ አናሳ ሲሆን በጥበቃ፣ ጽዳት፣ አትክልተኛና በተመሳሳይ የጉልበት ስራ ላይ የተሰመሩ የብሄሩ ተዋላጆች በንጽጽ ከሌላው ብሄር የላቀ ቁትር አላቸው፡፡

ከአስረኛ ክፍል በላይ የዘለቁትና ለዩኒቨርሲቲ ትምህርት ለበቁ የአማራ ወጣቶች በመከላከያ ሰራዊት፣ ፖሊስ እና መሰል ልዩ ሙያ በማይጠይቁ መስሪ ቤቶች ለመቀጠር ይገፋፋሉ፡፡ በተለይ ከአማራ ክልል ውጪ የሚኖሩት በሚኖሩበት አማራዎች አካባቢ ከሌላው እኩል ኢኮኖሚ ድጋፍ ስለማያገኙ አደነዚህ መስሪያ ቤቶች የተቀላቀሉበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህን አገላለጽ በማስረጃ ለማገዝ የሚቻል ሲሆን በ2005 ዓ.ም. መንግስት ባወጣው ሪፖርት መሰረት በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ አማራው ከሌሎች ብሄረሰቦች የበለጠ ቁጥር ነበረው፡፡ ማለትም ሰራዊቱ 27% ከአማራ፣ 23% ከኦሮሞ እና 25% ከደቡብ ህዝቦች የተውጣጣ ነው፡፡ እግዲህ የእግረኛ ተዋጊ የሆኑ በትምህርት ረገድ ብዙም ያልተጓዙ የአማራ ልጆች ይበዛሉ፡፡ መስመራዊ መኮንን ለመድረስና መጠነኛ ለውጥ ለማግኘት እንደኳን ፈተናው የትየለሌ ነው፡፡ መሬት ላይ ካለው ሃቅ ብንነሳ በሰራዊቱ ውስጥ ወጣቱ ከ5-7 ያህል እድሜውን ምንም የኔ የሚለው ነገር ሳይኖረው አዛገቦቹን ፈቃድ ሲፈጽም ይኖራል፡፡ በሃገርና በመንግስት መካከል ያለውን ልዩነት እንዳይገነዘብ ከመረጃና ከትምህርት እየራቀ ሀገሩን ጠባቂ መሆኑ እየቀረ የአለቆቹን ንብረትና ስልጣን ጠባቂነት ሚና እየተወጣ እድሜውን የሚጨርስበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡

ስርዓት መራሽ ፍረጃዎችና የእለት ከእለት የአማራ ልጆች ህይወት

በሲቪል ሰርቪስ ስርዓቱ የአማራ ብሄር ነው ብሎ የተገመተ ማንኛውም ሰው ለትምክሒተኝነት፣ ለነፍጠኝነት እንዲሁም በበላይነት ስሜት ሌሎችን በመናቅ ፍረጃ የተጋለጠ ነው፡፡ በብሄር

ብሄረሰቦች ሃገር ኢትዮጵያ ቀድሞውኑ በአማራ ላይ የተሰራው አግላይ ፖለቲካዊ ሰበካ ሌሎች ቤሄሮች በመጠራጠር እንዲያዩት የተበረገደ በር አለው። አንድ ገጠመኝ ላስታውስ። በግንቦት አንድ ቀን 2008 ዓ.ም. እንድ ስሙ አማራነትን የሚያሳብቅ የየትኛውም ፖለቲካ ድርጅት አባል ያልነበረ አስተማሪ ከአንድ የኢህዴግ ግንባር ፓርቲ አመራር ከሆነ አለቃው በጥቅማጥቅም ግጭት ውስጥ ይገቡና ጥቅሜ ተነካብኝ በሚል ሃላፊው በዲፓርትመንቱ መሀተም በመጠቀም እስተማሪዎችን በመናቅ፣ በትምኪተኝነት፡ የመሪዎችን ስም በከንቱ በማንሳት የእነገሌ ዘር ነንኝ በመለት ይኩራራል... እና ሌሎችን በወቅቱ ፖለቲካ ትኩረት የሚሰጣቸውን ጉዳዮች በክሱ አካቶ ከሰሰው። በዚህ የተነሳ መምህሩ አቤቶታ አቅርቦ ማስራጀዎች በከሚቴ ተሰብስበው እና በዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ ሃለፊዎች ግልጽ ግምገማ ተደርጉ መመህራንን ይንቃል ስለመባሉ አንድ ምስክር በሰጡት ቃል ሲሰጥ "የማህበራዊ ሳይንስ አስተማሪዎችን እናውቃቸዋለን ብሏል የጥናት ቢጋር ለግምገማ ቢቀርብም የሚፈጠር ነገር የለም ሲል ምን ማለትህ ነው ስለው መምህራኖቹ የኛው አባላት ብሎም የምንተዋወቅ በመሆናችን የተለየ ነገር አይፈጠርም ገንቢ አሳብ ጨምረውልን ቢጋሩ ይጸድቃል ነው ያልኩት ሌለ ነገር ልታነካካኝ ከሆነ ...." ብሎኛል ሲል መሰከረ። ለሁለተኛው ክስ ተከሳሹን ጨምሮ ሌሎችም "እኛ የአባ ጂፋር ዘር፣ የአጼ ምኒልክ ልጆት፣ የዮሃንስ ልጆች..." የሚል ንግግር አድረጉ ነበር በሚል ማስረጃ ቀረበ። ይህን ማስረጃ መሰረት በማድረግ የዩኒቨርሲቲው አመራር በአቤቱታ አቅራቢው ላይ "ሃገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ብዝሃነተን ለአንድነት መጠቀም ሲገባን የራሶን ብሄር ስም በማንሳት ያለአግባብ በመኩራራትዎ እና የሌሎቹን ብሄር ተማሳሳይ ክብር ባለመስጠቶ" የሚሉ ሃሳቦችን በማካተት ማስጠንቀቂያ ተጻፈለት።

እንገዲህ በግምገማው እንደተረጋገጠው፣ "እኛ የአባ ጂፋር ልጆች፣ የምኒሊክ ልጆች፣ የዮሃንስ ዘር፣... ነን" በሚል አቤቱታ አቅራቢው የተናገረው ፖለቲካዊ ትርጉም በመስጠት ለግምገማ ከመቅረቡ ውጪ "ብሄር" የሚባል ነገር በክሱ ላይ አልተገለጸም፤ ግምገማውም ብሄር የሚል ገለጻ አልተሰነዘረም። የተጠቀሱት መሪዎችም የተለያዩ ብሄረሰብ አባላት እንጂ በራሳቸው ብሄር አይደሉም፤ስማቸውን ያነሳቸው መሪዎች የግለሰቡን ብሄር አባላት ከፍ በሚያደርግ አኳን ሳይሆን የሃገሪቱን ብዝሃነት በሚያከብር መልኩ በሃገሪቱ ታሪክ ጉልህ ቦታ የነበራቸውን ከተለያዩ ብሄሮች የተገኙ መሪዎችን ነበር። በማስጠንቀቂው ላይ ያለው ገለጻ ግን መሪዎችን መጥቀስ አንድ ብሄርን እንደንቆለጳጳስ ተደርጎ ተጸፏል። ሰውየው አማራ ነው፣ ምንም ይበል እሱ የተናገረው ትምክህት ነው፣ ሌሎቸችን የሚንቅ ነው የሚል ድምዳሜ በስርዓት የሚውለበለብ ባንዲራ መሆኑን የሚያሳብቅ ነው። መምህራንንም የመናቁም ጉዳይ በቃ አማራ

እንደዚያው ነው። በአማራ ሰቆቃ፣ ውንጀላና ክስ፣ በማሸማቀቅ ላይ ኢትዮጵያ መሰረቷን እንድትጥል የመበየነ ይመስላለ።

የገዚው ፓርቲ አባል ሳይኮን አማራ ሆኖ ኤርትራ ብሎ መጥራት ማለት እና ሌላ ብሄር ሆኖ በተመሳሳይ መናገር እኩል ትርጉም አይሰጠውም። አማራ ኤርትራ ካለ የዱሮ ስርዓት ናፋቂ ሊሆን ይችላል፣ ኤርትራ የኛ ናት በማለት የብሄረሰቦች የራሰን እድል የመወሰንን መብት ይቃወማል፣ የኤርትራን ወደብ በሃይል እናስመልስ የሚል እንድምታ ያለው ነው ወዘተ ትርጉም ሊሰጠው በሚችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል።

ከላይያለውን ሃሳብ የሚያስረግጥልኝን የታሪክ ኩነት ላንሳ። ጉዳዩ አንዲህ ነው፡- በታህስስ 11 ቀን 1985 ዓ.ም. መንግስት ፕሮፌሰር አስራት ወልየስ በደብረብርሃን ህዝብ ሰብስባ ኢትዮጵያን ገናና ታሪክ፣ የዛሬዋን ኢትዮጵያ አንድነት መናጋት፣ በጣሊያን፣ በደርግ እና የሽግግር መንግስቱ በአማራን ህዝብ ላይ ያደረሱትን በደል፣ የአማራ ህዝብ ተጠናክሮ ሰላማዊ ትግል ማድረግ የሚገባው መሆኑን እንዲሁም የአማራው ህዝብ እንዳይደራጅ የአማረው ልሂቃን እንቅፋት መሆናቸውን ሆኖም በመቻቻልና በትግስት የገጠመንን ችግር እንጋፈጥ የሚሉ ሃሳቦች ለህዝቡ አስረድተው ነበር። ይህን ከተናገሩ በኋላ አስራት ጦርነት ቀስቃሽ የሚል ፍረጃ ተጎናጸፉ። ንግግሩ ለፍረጃው ማስረጃነት የማይውልበት ሁኔታ ቢኖርም ፕሮፌሰሩ የኤርትራን መገንጠል በመቃወማቸው እንደወንጀለኛ መቆጠራቸው እሙን ነው። ፓርቲያቸው ጦረኛ፣ መሪውን ጦርነት ቀስቃሽ በሚል ፍረጃው ተጧጡፎ በአንዳንድ የትግራይ ክተሞች አስራትን የሚቃወሙ ሰልፎም ተደራጅተው ነበር። ሊበሏት ያስቧን... እንዲሉ በታህሳስ 11 ቀን 1985 ዓ.ም. ንግግር ሲያደርጉ ጦርነት ያልቀሰቀሱ በመሆኑና ህዝቡም ስለሰማ፣ ህዝቡን ለማሳመን ስለማያመች ሌላ አደናጋሪ ዘዴ መዘየዱ ይነገራል። ጋሻው መርሻ የፕሮፌሰሩን ሃሳብ ዋቢ አድርጉ እንደጻፈው "በታህሳስ 22 ቀን 1985 ዓም. በተደረገ የደብረብርሃን ስብሰባ ጦርነት ቀስቃሽ መግለጫ በፕሮፌሰሩ እንደተሰጠ በክልል 14 አስተዳደር መግለጫ በማውጣት በቀታይ በፕሮፌሰሩ ላይ ለሚደረግ ወከባ የማዘጋጀት ስራውን መሰረት ጣለ። ሆኖም በታህሳስ 22 ቀን 1985 ዓ.ም. በደብረብርሃን ስብሳባ እንዳልተደረገም ጸሃፊው አስረድቷል። አማራን አድራጅተዋል፣ መገንጠልን ይቃወማሉ፣ የኢትዮጵን አንድነት ያቀነቅናሉ። ስለሆነም ሰውየው ቀድሞውኑ ተፈርጀዋል። ዋናው ጉዳይ ምን ያህል የእስር ዘመን እንደሚበየንባቸው መስማማት ነበር። ቀጠሎም 92 ጊዜ ፍርድ ቤት ቀርበው ከዚም እስር ተበይኖቻቸዋል። ካለው ሁኔታ አንጻር እሳቸው አብዘተውታል። በገሃድ የመላው አማራ ህዝብ ድርጅት ብለው ፓርቲ

መስርተው የሽግግሩን መንግስት አቋም ተቃውመዋል። አማራ መሆንና ትንሽ መጻፍ አሊያም መተንፈስ ለወቀሳ፣ ለክስ በቂ ነው። ፕሮፌሰሩ ቀድሞውኑ ከሲቪል ሰርቪሱ ተባረዋል። ይህ አይነቱ አሁንው ተግዳሮት አሁንም ቀጥሏል።

ዛሬ በጦፈው የኢትዮጵያ የብሄር ፖለቲካ የአማራ ህዝብ ያልተወራረዱ እዳዎች እንዳሉበት ተቆጥሮ የብሄር ፖለቲካው አቀንቃኞ የስብሰባ መክፈቻ ሃሳብ ማጠናከሪያቸው ሆኗል። በአማራ ተወላጅ የኢህአዴግ ካድሬዎች የአማራን ህዝብ ከነፍጠኝነትና ከትምክህተኝነት ጋር በማያያዝ ማጣቀስ የተለመደና ሹመት የሚስገኝ ተግባር ሆኗል። በዚህ ቅጥ ባጣ ፍረጃ የአማራ ልሂቃንን ከሹመት የማራቅ፣ በሰበብ አስባብ ስራቸውን እንዲጠሉ አስቻይ ነባሪዊ ኩነቶች በተግባር ይታያሉ።

የአማራ ጉዳይ በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን

የበአምባሳደር ጥሩነህ ዜና የኮሚሽንርነት ዘመን በአዲስ አደረጃጀት ኢትትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ስምንት ዳይሬክረቶችን ሲያዋቅር በዋና ዋና ክፍልልነት የሰብአዊ መብት ምርመራ ዳይሬክቶሬት፣ የጥበቃና ክትትል ዳይሬክቶሬት፣ የግንዛቤ መስጫ ዳይሬክቶሬት እና በዋና መስሪያ ቤት ብቻ የሚገኝ የጥናትና ምርምር እና የሪሶርስ ማዕከል ሆነው ተደራጀተዋል። እስከ 2007/08 ዓ.ም. ድረስ የነበረውን አደረጃጀት ለማለት ነው።

በእረሳቸው ዘመን የኮሚሽኑ ጥበቃና ክትትል ዳይሬክቶሬት የተሻ መስራቱም እገነዘባለሁ። በማረሚያ ቤቶች እና በፖሊስ ማቆያና ማረፊያ ቤቶች ክትትል ያደርጋል። ከፖለቲካ ተጠርናፊዎች ውጪ ያሉትን ተጠርጣሪዎች እና ታራሚዎችን መብት ለማስከበር የሚያደርገው ጥረት እውቅና የሚገባው ነው። ቀደም ሲል በቀን ለአንድ ታራሚ ይመደብ የነበረው ዘጠኝ ብር ወደ አስራ አንድ ብር እንዲያድግ ኮሚሽኑ ያደረገው ግፊት የሚናቅ አልነበረም። በክትትል ወቅት ከገጠሙኝ የማረሚያ ቤት ኮማንደሮች ብዙዎቹ ለሰበአዊ መብት ኮሚሽን በአጋርነትም፣ በዲሞክራሲያዊ መብት ድርጂትነትም የሚሰጡት ክብር የሚወደስ ነበር። አንዳንዶች ግን የኮሚሽኑ ክትትሎች ሲመጡ ሌባና ፖሊስ እንደሚጫወቱ ተገንዝቤያለሁ። ሰብአዊ መብት ኮሚሽን የእነሱን ወንድም ወይም በቅርብ የሚያውቁትን ሰው በተገቢው መልኩ እንዲያዝ የሚሰራ ተቋም መሆኑን የማይረዱም ነበሩ።

ውጤታማ ናቸው ለማለት ባይቻልም ኮሚሽነሩ (አምባሳደር ጥሩነህ ዜናን ለማለት ነው) መስሪ ቤቱ ጥርስ የሌለው አንበሳ እንዳይሆን ሙከራ ያደርጉ ነበር። ፖለቲካ ነክ ባልሆኑ ጉዳዮች ላይ በመስራት በሰብአዊ መብቶች ጥበቃ ላይ አስተዋጽዖ ማድረግም እንደሚቻል ያምኑም ስነበር

የተለያዩ ተግባራትን ፈጽመዋል። ሆኖም በመጨረሻ የስልጣን ዘመናቸው ትልቅ የነበሩት ሰው በሁለት ነገር አንሰውብኛል። አንደኛ- በየአራት አመቱ በሚደረግ በተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ጉባኤ ግምገማ (Universal Periodic review) "ኢትዮጵያ የቢ (B) ደረጃ ያገኘችው ወሳኝ የድርጁቱን ባለስልጣን በቅድሚያ ጋብገፎ ስላግባባሁት ነው" ብለው መናገራቸውን አብረዋቸው ይሰሩ የነበሩ የበታች ባለስልጣናት በአደባባይ ያረጋገጡ እለት ነው። ነገሩም ሃቅነት አለው። በድለላ ካልሆነ በስተቀር የሰብአዊ መብትን በማስጠበቅ ኢትዮጵያ የቢ (B) ደረጃ የሚገባት ሃገር ያለመሆነዋን የውስጥ አዋቂ መሆንን አይጠይቅም። ጉዳዩ ግልብ ነው፤ ኮሚሽኑ ብዙና ከሌላው መስሪያ ቤት በተሻ ብቃት ያላቸው ዳኞች የነበሩ፣ አቃቤያን ህግጋት የነበሩ፣ የዩኒቨርሲቲ አስተማሪዎች የነበሩ ባለሙያዎችን ያቀፈ ቢሆንም የፖለቲካው ጣልቃገብነት ውጤታማ ስራን ለመስራት በሚያስችለው አቅም ላይ እንዳይቆም አስድርጎታል። *ሁለተኛ*፡ ኮሚሽኑ በ2007 ዓ.ም. ምርጫን ለመታዘብ ከ200 የሚበልጡ ሙያተኞችን በማሰማራት መረጃ ሰብስቦ ሲያበቃ ኮሚስነሩ የሰጡት መግለጫ ካሴት ጎርሰው የተናገሩ ነው የመሰለኝ። እኔ በአንዱ የአማራ ክልል ዞን የታዛቢ ቡድኑ አስተባባሪ ስለነበርኩ የተፎካካሪ ፓርቲዎችን እጩዎችን ከምርጫ በፊት ይርስባቸው የነበረውን ጫና እርሳቸው እንዲሰሙ አድርጌያለሁ። መኢአድ የሚባል ፓርቲን በመወከሉ ምክንያት ቤት የተቃጠለበትና ንብረት የወደመበት ሰው ንግርና ሌሎች አቤቱታዎችን ሲሰሙ ያዘኑ መስለውኝ ነበር። በሌሎች አካባቢዎች በተለይ በአምቦ አካባቢ ገለልተኛ የምርጫ ታዛቢዎች እንዲወጡ ተደርጎ ድምጽ መቆጠሩን አስተባባሪዎች መረጃ አጠናቅረው አቅርበውላቸው ነበር። በሶማሊ ክልል በርካታ የድምጽ መስጫ ካርድ የያዘ ወጣት በታዛቢዎች ተይዞ ሲጠየቅ "ዘመዴን እንድመርጥ በቅድሚያ የተሰጠኝ ካርድ ነው" ሲል መመለሱን የኮሚሽኑ ታዛቢ ቡድን አሳውቋል። ነገር ግን በመግለጫቸው ምርጫው ሰላማዊ፣ ነጻ፣ዴሞክራሲዊ እና እንከን የለሽ መሆኑን አበሰሩ። ህሊናቸው ያውቀዋል።

የ2007 ዓ.ም. ምርጫ ሰላማዊ ነበር። ሰላማዊነቱም ምክንያት ጥርነፋ ነበር። በገጠሩም በከተማውም ህዝቡ የፊጥኝ እንደተያዘ የተረጋገጠ ነው። በግሌ ካናገርኳቸው እናቶች ሁሉም አንድ ለአምስቱ አደረጃጀቱ (አንዳንዶች የልማት ቡድን ይሉታል) እስከ ጓዳቸው ገብቶ የተፎካሪ ፓርቲዎችን የህዝብ ጠላት አድርገው እንዲፈረጁ አድረጓቸዋል። በአንድ የወረዳ ከተማ ያወያየኋቸው ሰዎች "ሰማያዊ የሚባል ፓርቲ የእስላም ፓርቲ" ነው የሚል ግንዛቤ እንደጨበጡ ከአንድ-ለአምስት ጠርናፊያቸው እንደተነገራቸው እና ክርስትናችንን ያጠፋል በሚል እንደጠሉት ተረዳሁ። እነዚህና ሌሎች መረጃዎች ምርጫ የተቀሸበው በቅድመ ምርጫ

ወቅት መሆኑን አስረጂ ናቸው። ገዢው ፓርቲ ድህነቱና ኋላቀርነት ተጠቅሞ የገጠሩን ህዝብ የማስተዋል ነጻነት እንደገፈፈው ግልጸ ነው። ከድህነት የሚተረፍ ፖለቲካዊ ጥቅም። የሰብአዊ መብት ኮሚሽን የቅድመ ምርጫውን ብሎም ድህረ-ምርጫውን አልታዘበም ነገር ግን መበግለጫው "ከሞላ ጎደል ነጻና ዴሞክራሲዊ ነበር" ለማለት እንኳን አልደፈረም። የምርጫን ስኬታማነት ለመናገር ደግሞ ቅድመ ምርጫ፤ እለተ-ምርጫ እና ድህረ-ምርጫን መመርመር ተገቢ ነው። በሌላ በኩል ምርጫው እንከኖች ነበሩበት በሚል ይፋ የሆነውን የአፍሪካ ህብረት መግለጫን እንኳን ማየት አልተፈለገም። ሆኖም ይህ ጭፍን ሙገሳ ኮሚሽነሩ በሌሎች ኮሚሽነሮች ከተተኩ በኋላ ኒዮ-ሊበራል ነበሩ በሚል መብጠልጠል አልቀረላቸውም።

የ2007 ዓ.ም. ምርጫ በአማራ አካባቢ፡ እኔ በአስተባባሪነት በተመደብኩበት የአማራ አካባቢ በምርጫው እለት የሚስተዋለው የመራጮች ፍርህት የሚያነግሱ ተግባራት የምርጫውን ነጻ ያለመሆን ለመገንዘብ ያስችሉ ነበር። በዘጠኝ ጣቢያዎች ራሴ በመገኘት እንዳየሁት፣ በሌሎች ስድስት ጣቢያዎች አባላቶቼ እንዳስተዋሉት የተፎካካሪ ፓርቲዎች ታዛቢዎች አልነበሩም። የገዢው ፓርቲ ታዛቢዎችና በአስተባባሪነት የተመደቡ በመራጩ ስነልቦና ላይ ጫና በሚያሳድር አኳን ይንቀሳቀሱ ነበር። አስተባባሪዎች የሚያውቁትን ሰው አቅፈው እስከ ኮረጆው የማድረስና የመጥቅስ ተግባር ሲፈጽሙ ይታዩ ነበር። እናቶችን "ያው እንደሚወቀው ነው በማለት" ያናግሯቸው እንደነበር ታዝቤያለሁ። ከመራጮችም በኩል ፍራቻው የወለደው ድርጊት ይመስለኛል ኮሮጆ ወደሚገኝበት ድንኳን ውስጥ ሳይገባ "ይህው እናንተን ነው" ብሎ የድምጽ መስጫ ወረቀቱን ከፍ አድረጎ አሲያሳይ አስተውያለሁ። በወቅቱ ታዛቢ እንጂ የምርጫ ክትትል ማለመሆኔ ምንም የእርምት እርምጃ እንድወስድ የሚያስችል ህጋዊ መብት አልነበረኝም። የህዝብ ታዛቢዎች ምርጫው ምንም ትርጉም የማይሰጣቸው በሚመስል መልኩ የሚያንቀላፉ እናቶችን ማስተዋሌን እዚያው ጠቁሜ ማለፌን አልረሳውም። በአማራ አካባቢ ድህነቱ ከሁሉም አካባቢ የከፋ መሆኑን ቀደም ሲል ገልጫለሁ። ይህም ድህነቱ ለጥርነፋው መደላድል የፈጠረ ብሎም የፖለቲካ ትርፍ ያስገኘ ስለመሆኑ የተደበቀ ሚስጥር አይደለም። እንግዲህ በናሙናነት የታዘብኩት የአማራ አካባቢ የምርጫ ሂደት ይህን ይመስል ነበር።

የኮሚሽኑ ጥናትና ምርምር በአማራ ጉዳይ፡ በዚህ ክፍል ከለምገልጸው ጉዳይ ቀጥተኛ ትስስር ያለውን የኮሚሽኑን ክፍል የጥናትና ምርምርና የሪሶርስ መዕከል ነው። ማዕከሉ አዲስ የጠቋቋመ ክፍል እንደመሆኑ አዳዲስ ከፍተኛ ሙያተኞችን ፈትኖ ፈተናውን ሲያልፉ ኮሚሽነሩ በሚገኙበት ቃለ-መጠይቅ ተጣርተው ቅጥር ተፈጽማል። ኮሚሽነር የሚያስቅ ባህሪ አላቸው

ራሳቸው የመሰላቸውን አግባብ ባይሆንም ይፈጸማሉ። ግን ምሁር ናቸው። በእኔ እይታ ለቦታው የሚመጥን ልምድም፣ ይሁን የትምህርት ዝግጅት አላቸው። አንድ ቀን ሰራተኛውን ሰብስበው እኔ የሚያነብ ሰራተኛ እወዳለሁ፣ ሰው ሲቀጠርም ቃለ-መጠይቅ ሳደርግ "የማይረባ" መልስ የሚሰጠ ከሆነ አያሳልፉትም። አንድ ወቅት አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተቋማትን ንገረኝ ስለው ሁዩማን ራይትስ ወች (human rights Watch) ብሎ ስለጀመረ ጥየዋለሁ አሉን። ሁዩማን ራይትስ ወችን (human rights Watch) አይወዱትም። በሪፖርታቸውና እሳቸው ባቀረቡት ንግግር በማረሚያና በማረፊያ ቤቶች ግርፊያ የለም ሲሉ የተጠቀሰው ድርጂት ተቃራኒ የሆነ መግለጫ ያወጣል። አንዳንዴም አፍንጫቸው ስር ያሉ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ቀድሞ በማስረጃ በማስረገጥ ያጋልጣል። ይበሽቃሉ፣ በየስብሰባው የነጮች ወኪልም ይሉታል። ስለሆነም ለቅጥር የመጣ ከፍተኛ ባለሙያ ለቃለ-መጠይቁ መልስ የዚህን ተቋም ስም ጠራባቸው ናቁት፣ ለእሳቸው እውቅት አልባ ነው። እንግዲህ የጥናትማ ምርምር ሊያደርጉ የሚሰማሩ ባለሙያዎች የመጠቀሙት የመረጃ ምንጨም የተመረጠ ሊሆን ይገባል። ሃላፊዎች የማይወዱት ተቋም ሪፖርት እቅን ያዘለ ቢሆንም ተመራጭ የማይሆንበት አግባብ እንዳለ ይታወቃል።

የአማራ ጉዳይ አይመረመርም

ስለ ጠቅላላ የኮሚሽኑ የዚያን ወቅት ሁኔታዎችና ስለጥናትና ምርምር ማዕከሉ ለመግቢያ ያህል ከላይ የተገለጸው በቂ ስሆነ ወደ አማራ ተኮር የኮሚሽኑን ስራ እንመልከት። በማራ ህዝብ ላይ የመግደል፣ ንብረት የማውደም፣ የማፈናቀል እና ዘርፈ ብዙ የሰብአዊ መብት ረገጣ በመንግስት ባለስልጣናት አስተባባሪነትና በእጅ አዙር ሳያቀቋርጥ ተከናወኗል። ይህን ሃይ ባይ ያጣ ግፍ በርካታ ሪፖርቶት የመላከቱ ቢሆንም "ሙሉቀን ተስፋው በ2008 ዓ.ም.)"[30] ያሳተመው ጥናታዊ መጽሃፍ ጠጣር ማስረጃዎችን በማጣቀስ የችግሩን ቀጣይነት ለማሳየት ያቀረበውን ትንተና አንባቢያን አንብበው እንዲማሩበት በመጋበዝ የዚህ ጽሁፍ ትኩረት ወደሆነው ነጥብ እሻገራለሁ።

የዚህ ጽሁፍ አላማ በአማራ ላይ የታወጀውን ጥፋት ከፌደራሉ መንግስት ውሳኔዎች ጋር ያለውን ፖለቲካዊ ተዛምዶ በሚያሳይ መልኩ በ2007 ዓ.ም. ከሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የምርምርና ማዕከል የገጠመውን ተግዳሮት ከታች የተቀመጡትን ናሙናዎች በመፈተሽ ።

[30] "የጥፋት ዘመን፡ ከ1983 እስከ 2007 ዓ.ም. በአማራ ህዝብ ላይ የተፈጸመ የዘር ማጽዳት" አዲስ አበባ። በተለይ ከገጽ 104 እስከ 150 ያለውን ይመልከቱ።

በ2003/04 ዓ.ም. እና 2005 ዓ.ም. ከደቡብ ክልል ቤንች ማጂ ዞን ጉራፈርዳ ወረዳ እና ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከማሽ፣መተከልና አሶሳ ዞን በመንግስት ባለስልጣናት ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ተሳትፎ የአማራ ብሄር ተወላጆች የማፈናቀል ተግባር መጠናከሩን የተለያዩ ምንጮች ያራግቡት ነበር፡፡ ከዚያም አልፎ የተበዳዮች አቤቱታ እና የኢሰመጎ ሪፖርት ለኮሚሽኑ ይደርሰው ነበር፡፡ በአዲስ አበባ በመቶዎች የሚቆጠሩ የጉራፈርዳ ተፈናቃዮች በመ.ኢ.አ.ድ. ቢሮ አካባቢና በየጎዳናዎች ተጎሳቁለው ይታዩም ነበር፡፡ ከጥናትና ምርምርና የሪሶርስ ማዕከል ምስረታም በኋላ በጉራፈርዳ ተመሳሳይ በደል መከሰቱ የሚያስረዱ አቤቱታዎች ለተለያዩ ተቋማት የሰብአዊ መብት ኮሚሽንን ጨምሮ ይቀርብም ነበር፡፡ በኦሮሚያ ክልል አማራን ማፈናቀልና መገድል ረጅም ታሪክ የለው መሆኑ ይታወቃል፡፡ በ2007 ዓ.ም. ከአምቦ ከተማ 30 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኝ ቀበሌ ከ1986 ዓ.ም. ከሚገኙ የአማራ ብሄር ተወላጆች ያቀረቡት ቅሬታ እንደሚያስረዳው መሬታቸውን ለወጣቱ ለማከፋፈል ይወሰዳል በሚል በእነሱ ላይ ብቻ የሚፈጸም የእርሻ መሬት ቅነሳ ትዕዛዝ ሲተላለፍ ይህ አይነት እርምጃ በሁሉም የአካባቢው ገበሬ ላይ ሊተገበር የሚገባና በአማራ ላይ ብቻ ለምን ሲሉ ጸብ በመነሳቱ በገበያ የያዙትን ንብረት እየተነጠቁ ድብደባ ተፈጽሞባቸው ነበር፡፡ መሬት ቀንሶ የማከፋፈሉ ጥያቄ ለነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች በቀረበበት ወቅት በክልሉ ምንም መሬት የማከፋፈል ፖሊሲ ተግባራዊ ለመሆኑም ጉዳዩን በተወሰነ የማህበረሰብ ክፍል ላይ ብቻ ተግባራዊ እንዲሆን የታለመ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ከሌላው ማህረሰብ በተለየ ዱላ እንኳን እዳይዙ በታጣቂዎች ይከለከሉ እንደነበርም መረጃ አለ፡፡ በተመሳሳይ አመት (2007 ዓ.ም.) በምዕራብ ሸዋ ዞን ኖኖ ወረዳም የተደራጀ ጸረ-አማራ የማፈናቀል፣ ድብደባ፣ ቤትና ንብረት የማቃጠልና ለፍሬ ያልደረሱ ሰብሎችን የመጨፍጨፍ ድርጊት መፈጸሙን የሚያስረዳ ሪፖርትና ጥቆማ ደርሶታል፡፡

ኮሚሽኑ ከተቋቋመበት አላማ አንጻር የአማራ መፈናቀል ትኩርት የሚገባው በመሆኑ የችግሩ መሰረታዊ መነሻ እና ወቅታዊውን የመባበስ ሁኔታውን በማጥናት ችግር ፈቺ ጥናታዊ ሪፖርት ለማቅረብ የጥናትና ምርምሩ ማዕከሉ ሙያተኞችና ዳይሬክተሩ ቢጋር/ፕሮፖዛል ተዘጋጀቶ በነበረበት ወቅት ከመንግስት የተሰጠ ምለሻ የተቋሙን አላማ የሚጋፋ ነበር፡፡ ጉዳዩ እዲህ ነው፡፡ በተጠቀሰው ቢጋር ላይ የመንግስት ምላሽ ጥናት መከናወን አይችልም የሚል ነበር፡፡ ይህ የሆነው በ2006 ዓ.ም. ነው፡፡ በወቅቱ በቢጋሩ ላይ ኮሚሽነሩም የመሰላቸውን የማስተካከያ ሃሳብ እንዲያካትት የታዘዘውን የጥናት ቡድኑ አባላት በአካል ለማነጋገር ቀጠሮ ያዙ፡፡ የሂደማን ራይትስ ዎችን ሪፖርት በማስረጃነት ተጠቅሶ ስለነበር ትልቅ የx ምልክት ማድረጋቸውን እና የጥናት ውስንነት በሚል የተቀመጠውን ሃሳብ “ጨለምተኛ” ማለታቸውን አስታውሳለሁ፡፡

ሆኖም ችግር ፈቺ ጥናት ልናከናውን ይሁንታ ሰጥተዋል። እናም የኮሚሽነሩ ውሳኔ የደስታችንን ጥግ አሳይቶን ነበር።

በኮሚሽነሩ አስተያየት መሰረት የተስተካክለው ቢጋር/ፕሮፖዛል/ ቢቀርብላቸውም ቀጠሮው ችላ ተባለ። የቀጠሮ ጊዜ አለፈ። ሆኖም "ኮሚሽነሩ ሙያተኛውን አወያይተው ጥናቱን ያላስጀመሩት ስራ ተደራርቦባቸው ነው" የሚል ግምት በተማራማሪ ሙያተኞች ተይዞ ነበር። እኔም ጭምር። ከአንድ ወር በኋላ በፕሮፖዛሉ የቀረበው ሃሳብ እንዲሰራ የፓርላማው ሰዎች እንዳልፈቀዱ በግልጸ ተነገረን። ጉዳዩ የብሄር በመሆኑ ይመሳሰላል ሌላ የብሄር ተኮር ጥናት እንድናደረግ ዝዕዛዝ ተሰጠን። ቡድቡ የብሄር ችግር የማጥናት ያማረው በሚመስል መልኩ የወለኔ ብሄረሰብ እና የቁጫ ብሄረሰብ የማንንት ጥያቄ እንዲሰራ ትዕዛዝ ተሰጠን። ይህን ጊዜ ቀድሞ የለፋንበት ስራ ተስፋ አስቆረጠኝ፣ አዲሱ የጥናት አቅታጫ ሳልደግፍም ቀረሁ። አዲሱን የጥናት ሃሳብ ያለደገፍኩበት ምክንያት የሁለቱ ብሄሮች ችግሮች በጥናት ላይ የተመሰረተ መፍትሄ አያሻቸውም ከሚል መነሻ አይደለም። የወለኔ ወይም የቁጫ ብሄረሰብ ችግር የሰብአዊ መብቶ ጥሰት ያስከተለ እንደሆነ መረጃውም ነበረኝ። ተስፋ ያስቆረጠኝ ጉዳይ ኢትዮጵያ ለህዝቦቿ ችግር እውነተኛ መፍትሄ የማይፈይድ ስርዓት ባለቤት መሆኗ ነው። የወለኔ ወይም የቁጫ ብሄረሰቦ የማንነት ጥያቄ ጥናት ከአማራ መፈናቀል ጋር የሚያመሳስል መሰረት የለውም። እየተፈናቀሉ የነበሩት የአማራ ብሄር አባላት ማንነቱ አልተከበረም የሚል ጥያቄ አላነሱም ነበርና። በሚካልለው የጥናት ውሰንም ቢሆን የተላያዩና የማይተካኩ ናቸው። የወለኔውና የቁጫው ጉዳይ በደቡብ ክልል የተወሰነ ሲሆን የአማራ መፈናቀልንን ለማጥናት የቀረበው ቢጋር የሚሸፍነው የኢትየጵያ ሶማሊ ክልልን፣ የደቡብ ክልልን፣ የኦሮሚያ ክልል እና የቤኒሽንጉል ጉሙዝ ክልልን ነበር።

እንደሚታወቀው የኢህአዴግ መንግስት የሃገሪቱን የብሄር ችግሮች ለመፍታት ሲምልና ሲገዘት የነበረ ስርዓት በኢትዮጵያ ተከስቶ አያውቅም። ግን በአማራ ላይ የሚፈጽም ግፍን ለማስቆም ቀርቶ ለማጥናትም ፈቃደኛ ያለመሆኑ ታወቀ። ኢህአዴግ በአማራ ብሄር ላይ የሚደረገ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች የአዝማችነት ሚናም እንዳለው የነበረኝን ግምት ሚያጠናክር ሆነልኝ። ቀደም ሲል በመንግስት ደረጃ የአማራ መፈናቀልን አቅልሎ የማየትና የማሳየጥ አቅጣጫ እንዳለ አመላካች ክስትት እንደነበር አስታውሳለሁ። "አማራ ተጠራርጎ ከጉራፈርዳ ተፈናቀለ በሚል ወሬ ይናፈሳል የሰው ጫካ የመነጠሩ ጥቂት ህገ-ወጥ ሰዎች...."በማለት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስተር ለመጨረሻ ጊዜ ያደረጉት የሚያዝያ 14 ቀን 2004 ዓ.ም. የማርላማ

ንግግር አስረጂ ነበር፡፡ እንደ መንግስት ህገ-ወጥ ሰፋሪን ማረም ወደ ህጋዊነትን ማስፈንና ማስተካከያ ማድርግ አስፈላጊ መሆኑንን ማንም ይስማማበታል፡፡ ከሃገር ተሰደው አውሮፓ ለገቡ ኢትዮጵያዊያን ኖርዌ ወደ ሃገራቸው ስትመልስ 50000 ኢውር (130000 ብር) እና እስራኤል ደቡብ ሱዳናዊንን ወደ ሃገራቸው ስትመልስ የአውሮፕላን ትኬት ከ1300 ኢውሮ/ 31000 ብር/ እንደሰጡ አንብቤያልሁ፡፡ ከደቡብ ክልል ተፈናቅለው አዲስ አበባ የገቡ ዜጎች ግን በቀበና አካባቢ በቡድን መንገድ ላይ ተኝተው እንደነበርና ጥቂት እድለኞት ደግሞ መ.ኢ.አ.ድ. የተሰኘ የፖለቲካ ፓርቲ መጠለያ እንደሰጣቸው ከጋዜጦች አንብቤያለሁ፡፡ መንግስት ግን አማራን የጠላ ወይም የረሳ መሆኑን የሚያሰብቅብትን ድርጊት እየፈጸመ ዛሬም አለ፡፡

ወደ ኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ጥናት የማቋረጥ ክስተት ልመለስና የአማራ መፈናቀል ጉዳይ እንዳይመረመር፣ አንዳይፈተሸና እንዲዳፈን የፖለቲካ ውሳኔ ያሳለፉ ፓርላማ ሰዎች እነማን እንደሆኑ በግልጽ ባላውቅም በወቅቱ የዴሞክሲ ተቋማትን የማያስተባብር/የመቆጣጠር/ ሃላፊነት የነበረው አፈ ጉባኤ አባ ዱላ ገመዳ እንደነበረ አውቃለሁ፡፡ አባዱላ ገመዳ የቀድሞ አለቃቸውን ራዕይ የማሳካት ሚና እንደሚኖራቸው መጠራጠር የሚያስችል ምንክያት የለም፡፡ ዋናው ጉዳይ የአማራ ግብር ከፋይ በከፈለው ግብር ችግሩን የማካም እድል የማያስገኝ የሰብአዊ መብት ኮሚሽንና ሌሎች ተቋማት አሁንም አሉ፡፡ የአማራን ህዝብ መጎሳቆልና የአማራል ልሂቃል የቁሳዊና የሞራል ውድቅት የሚያደላድል ስርዓትም የፖ.ሊ.ሲ ለውጥ የማደርግ እርምጃን የሚያመላክት ፖለቲካዊ አቅጣጫ አልተዘረጋም፡፡

ምዕራፍ አራት፡ የአማራ-ኦሮሞ ፖለቲካና የሰለለችው ካርድ

መግቢያ

የአማራ እና የኦሮሞ ህዝብ ታሪካዊና ወቅታዊ ትስስር፣ መስተጋብር እና ወንድማማችነት ከመተንተኔ በፊት ፕሮፌሰር ህይሌ ላሬቦ ስለአጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝቦች የጻፉትን በማጣቀስ ወደዋናው ጉዳይ ልንደረደር ፈለግሁ፡፡ እንሆ፡

> *…በኢትዮጵያ ታሪክና በየግዜው በተፈጸሙት ተጨባጭ የመንግስት ተግባራት እና መመሪያዎች ሊይደገፍም፤ ለዘመናት በየግዜው በሚነሱት የርስ በርስ ጦርነቶችና የህዝብ ፍልሰቶች፣ የሃይማኖት መስፋፋትና እነዚህም ድርጊቶች ስከተሏቸው ግጭቶች፣ በተለያየ ጊዜ የማዕከላዊ መንግስት መፍረስና መልሶ መቋቋም በብዙ መልኩ ሀገሪቱን የጎዱ ቢሆኑም በሌላ አኳኋን ደግሞ የኢትዮጵን ህዝብ ከመቀራረብ አልፈው አዋህደውታል፤እነዚህ ክስተቶች ከንግድ፣የእምነት ላዕከላትን ለመሳለም በየጊዜው ከሚደረጉ የምዕመናን ንግደቶችና ከጋብቻ ጋር ሆነው የኢትዮጵን ህዝብ በታሪክ፣ በደም፣ በቋንቋ፣በባህል አስተሳስረው እንደሰርገኛ ጤፍ ስለደበላለቁት በዘር ምንጨ*

ከአንድ ዘውግ የተገኘ ማህበረሰብ በኢትዮጵያ ውስጥ አለ ማለት እንደዘበት መቆጠር ይኖርበታል (ኃይሌ ላሬቦ፡ 2008 ዓም.)፡፡

የፕሮፌሰሩን አገላለጽ እውነትነት ለመረዳት ብዙም መጓዝ ወይም ምርምር ማካሄድ የሚጠይቅ እንደማይሆን የብዙ ኢትዮጵያዊያን የእለት ከዕለት ኑሩና የማህበራዊ መስተጋብሮች አስረጂዎች ናቸው፡፡ ይህንም ቀላል የሚያደርገቀው አጎቱ ወይ እህቱ ከጉራጌ ማህበረሰብ ሚስት ያገባ/ገባች ኦሮሞ ወይም ትግሬ ማግኘት ስለሚቻል፤ወንድሙ/እህቱ ከኦሮሞ ማህበረሰብ ልጆች ያሉት ሚሊዮን አማራ ማግኘት ስለሚቻል ወይም በጋብቻ የተሳሰሩ የከንባታና የወላይታ ህዝቦች በየአካባቢችን ማግኘት ስለምንችል ነው፡፡ የሃይኖት፣ ባህል እና የቋንቋ መወራረስና መዋሃድም ተመሳሳይ ገጽታ ያለው ነው፡፡ የአማራና የኦሮሞ ማህበረሰብን ነጥለን ስናይ የመልከዓ-ምድር መቀራረብ፣ አንዱ ማህበረሰብ በሌላኛው አካባቢ እስከጫፍ ድረስ ተሰራጭቶ መኖር፣ የሁለቱም ህዝብ ከሌሎቹ ህዝቦች በቁጥር ልቆ መገኘት በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የሁለቱን ህዝቦች ማንነት የያዙ ኢትዮጵያዊን እንዲኖሩ አስችሏል፡፡

ውይይቱን ከራሴ ማህበራዊ ማንነት ብጀምር የስጋ ዘሎዶች ለምሳሌነት ልጠቅስ እችላለሁ፡፡ ከሰባት በላይ የኦሮሞ ማንነት ያላቸው የእህቱ ልጆች በምዕራብ ሸዋ ጉደር አካባቢ ይገኛሉ፡፡ አዲስ አበባ ሁለት በአባታቸው ኦሮሞ የሆኑ የእህቱ የልጅ ልጆች፣ ከዘጠኝ በላይ በአባታቸው ኦሮሞ የሆኑ (በንጉሱ እና በደርግ የሰራዊት አባል የነበረ የሰላሌ አካባቢ ኦሮሞ አክስቱ በማግባቷ) የእናቱ የእህት ልጆች በኩየራ እና በአዲስ አበባ ይገናሉ፡፡ ሌላም ትዝ አለኝ ከኦሮሞ አባት እና ከአማራ እናት የተወለደው የእናቱ የእህቷ ልጅ እዚው ኩየራ የትግራይ ልጅ ናት ሚስቱ፡፡ ሌላም ላክል፡፡ ከየም ብሄረሰብ አባል ከሆነ ጉብል ሁለት ልጆችን የወለደች የአክስቱ ልጅ ሰኮሩ ከተማ ትገኛለች፡፡ ልብ በሉልኝ ከእኔ የስጋ ዘመዶች የሻሸመኔዎቹ አማረኛንም ኦሮምኛንም የሚናገሩ ሲሆን በጉደር አካባቢ ገጠር ቀመስ ቀበሌ የሚገኙት የእህቱ ልጆች ግን የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ኦሮምኛ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊያን ውህደት ፈጽመዋል ወይም ሰርገኛ ጤፍ የሚመስል ማንነት አላቸው የሚለው የፕሮፌሰር ኃይሌ ላሬቦ ገለጻ በሃገሩቱ ዛሬም ሆነ ትላንት ያለውንማና የነበረው ነባራዊ ማህበራዊ ሃቅ ለማስገንዘብ የሚመጥን ነው፡፡

የዛሬውን *ፖለቲካ* መራሽ ኩነት ያስተዋል እንደሆነ የሃገሪቱ አስተዳደር ብዜርን ዋነኛ መነሻ በማድረጉ የአማራና የኦሮሞ ህዝቦች ማህበራዊ ትስስራቸውን ማላላት የሚያችልበት ሁኔታ ከግምት በላይ ቢሆንም በሁለቱ ማህበረሰብ መሃል የተዘረጋው ታሪካዊ የትስስር ሰንሰለት (Historic bonds) አሁንም አለ፡፡ ይህም የሆነው የህዝብ ወንድማማችነት እንዳይሻክር ዘብ የሚቆም በፖለቲካው ሰንካላነት ልተበገረ የማህበረሰብ ክፍል በመኖሩ ነው፡፡ በቤኒሽንጉል

ጉሙዝ ክልል፣ በሃረር እና ድሬድዋ በርካታ የአማራና የኦሮሞ ማህበረሰብ በብዛት እንደመገኘታቸው ሁሉ ተስማምተው ይኖራሉ፡፡ ጥንትም ሆነ ዛሬ ልጆቻቸውን ለኦሮሞ ወዳጆቻቸው በመዳር ዝምድቸውን የሚያጎለብቱ አማራዎችም እና ለአማራ ወገናቸው ልጆቻቸውን ድረው መተሳሰር የሚሹ ኦሮሞዎች ከብዙም በላይ ብዙዎች ናቸው፡፡ ጉዳዩ ጥናትና ምርምር የሚያስፈልገው ቢሆንም በአዲስ አበባ፣ ደብረዘይት፣ አዳማ (ናዝሬ) ፍቼ፣ ጎሐጺዮን፣ ጫንጮ፣ ባሌጎባ፣ አሰላ፣ ኩየራ፣ ሻሸመኔ፣ ጫጫ፣ ሸኖ፣ ሃረር፣ ድሬድዋ፣ ደሴ፣ከሚሴ፣ እና ወዘተ ከተሞች ላይ ያለውን ነባሪዊ ሁኔታ ብንመለከት የአማራና የኦሮሞ ቅይት ትውልድ እጅግ ብዙ እንደሚሆን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ብዙዎቻችን የምናውቃቸውን የኦሮሞና የአማራ የዘር ሃረግ ያላቸውና በሃገራቱ ጉልህ ቦታ የሚሰጣቸው ልሂቃኖች እንኳን ብናስታውስ የሁለቱ ህዝቦች እንደሰርገኛ ጤፍ መቀየጣቸውን በመጠኑም ቢሆን አስረጂ ነው፡፡ ስለሆነም አበበ ቢቂላን፣ አጼ ኃ/ይለስላሴን፣ አቡነ ጴጥሮስን (መገርሳ በጣሳ)፣ ራስ አበበ አረጋይን፣ጸጋዬ ገ/መድህንን እና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል፡፡ በሁለቱ ብሄረሰቦች የፖለቲካ ልሂቃን ወይም በነገስታቱም ዝርያ በኩል የፖለቲካ ጋብቻ በማድረግ ስልጣንን ጠንካራ መሰረት ማስያዝም የተለመደ ታሪካችን ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሁለቱ ህዝቦች የመተሳሰር ሁኔታ ሌለው ማህበረሰብ ከሚያደርገው መሰል መስተጋብር እንደሚልቅም መገመት ይቻላል፡፡ ሁለቱ ህዝቦች ኩታ ገጠም ከመሆን፣ በቁጥር ልቆ መገኘት፣እርስ በእርሳቸው የመፈላለግ እና አንዱ በሌላኛው አካባቢ የመኑር ልምድና ታሪክ ለዚህ መተሳሰር አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡

ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ የአማራ ህዝብ ከኦሮሚያ ክልል እንዲወጣና እንዲፈናቀል በስርዓቱ ካድሬዎች የተደረገው መጠነሰፊ ዘመቻ፣ግድያና የማሰቃየት ድርጊቶች ቢኖሩም በኦሮሚያ ክልል ከሁለት ሚሊዮን በላይ የአማራ ህዝብ ተዋልዶና ተዋህዶ ይገኛል፡፡ በተለይ ከ1983 ዓ.ም. ወዲህ በስርዓቱ እየታገዙ በሚወጡ የሁለቱን ብሄሮች አንድነት የሚያናጉ ልብ ወለዶችና በትንሽ የታሪክ እውነቶች በተጌጡ የቅርብ ጊዜ ፈጠራዎች የተነሳ በአማራ ላይ የተከሰቱ መፈናቀልና የዘር ማጽዳት ተግባራትን የፈጠሩት ጫና ቢኖርም በፍቅር አብሮ የመኖራቸውና የሁለቱ ማህበረሰብ አባላት የሚጋሯቸው እሴቶች በርካታ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ ኩነቶች የሚያመላክቱት መፈላለግ እና መከባበር መኖሩን እና የተወሰኑ ችግሮች ቢኖሩም በቀላሉ መሰረቱ የማይሸረሸር ማህበራዊ ዝምድናቸው ለበርካታ አመታት ሲሰበክ የቆየውን የመከፋፈያ

ስልት በማክሸፍ እስከሁን በሁለቱ ህዝቦች መሃል በቀላሉ የማይናጋ ወዳጅነትን ማስጠበቅ መቻሉን ነው።።

ኦሮሞና የአማራ ማህበረሰብ ኩታ ገጠም በመሆን የሚጋሩት የጋራ ማንነት እንደለ ሆኖ በሌላ ክልል በአሁኑ ወቅት በዞን ደረጃ እራሱን ለማስተዳደር እውቃና የተሰጠው የኦሮሞ ማህበረሰብ ብቻ ነው።። ይህም የኦሮሞ ዞን የሚገኘው በአማራ ክልል ሲሆን ሁለቱ ማህበረሰቦች የተለያየ ቋንቋ ከመናገራቸው በተጨማሪ በባህል፣ አኗኗር፣ ሃይማኖት፣ የዘፈንና የዳንስ እንቅስቃሴ ወዘተረፈ የሚጋሯቸው እሴቶች የተየለሌ ናቸው።። በቃ የሁለቱም ብሄረሰብ አባላት የጠበቀና ስር የሰደደ ዝምድናቸው በዘመኑ የብሄር ፖለቲካ የሰከሩ ልሂቃን እንደሚሉት ጡት የሚቆራረጡ፣ በባላንጣነት የሚተያዩ አይደሉ።። ከንጉሱ ዘመን ወዲህ ጀምሮ ያለውን ክፉውን ከፋፋይ ዘመን ተምረውበት ስለሚያልፉ ወደፊትም በፍቅር ሊኖሩ የሚያስችል የጠበቀ መሰረት እንደሚኖራቸው ይታመናል።

ወደኋላም በሶሎሞን ስርዎ መንግስት በተለይ ከ1262 ዓ.ም. ጀምሮ የነገሱ፣ ለቅቡለነት ሲሉ የሶሎሞን ዝርያ እንዳላቸው የሚያውጁ የኦሮሞ እና የአማራ የዘር ግንድ የነበራቸው በርካታ መሪዎች እንደነበሩ ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ በማሰረጃ አረጋግጠውልናል።

በታሪክ መስተጋብሮች ከተፈጠሩ አንድነቶች በተጨማሪ የአማራ-ኦሮሞ የዘር ሃረግ አንድነትም አላቸው የሚሉ ተመራማሪ ጸሃፊዎች ሲኖሩ በዚህ በኩል የፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጽሁፍ ተጠቃሽ ነው።። ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ የዘር ግንድ ታሪኩን ፍሰት በትንተና በ2008 ዓ.ም. ባሳተሙት "የኦሮሞና የአማራ እውነተኛ የዘር ምንጭ" በሚል መጽሃፋቸው አስረድተውናል።። በመጻህፋቸው አማራ የሚባል ብሄር የለም በሚል የሚያቀነቅኑን ምሁራንን ሃሳብ ውድቅ በሚያደርግ መልወኩ ያቀረቡት የታሪክ ፍሰት እና ቀደም ሲል ኦሮሞ ከማዳጋስጋር መጣ" (በአንዳንድ ጸሃፊዎች) ፣ የኦሮሞ ግንድ ባራንቱና ቦረና ነው" በሚል ለብዙ አመታት ሰርጾ የነበረውን የታሪክ ግንዛቤ የሚሸር ትንተና በልዩነት የሚታይ ነው።። በመጽሃፋቸው ገጽ 73 ላይ የሁለቱን ብሄረሰቦች አመጣጥ ሲተርኩ ... "ኦሮሞና የአማራ የዘር ምንጫቸው ነብይ ከነበረው ከደሽት/ደሴት/ እንደሚነሳ አጢነናል።። የሁለቱ ማለትም የኦሮሞም የአማራሞ ወላጅ አባትና አያት ደሽት ነው ብለናል።። የደሽት ቅድመ-አባትም የሳሌም/የኢየሩሳሌም/ ንግስትና የእግዚዓብሄር አብይ ካህን የነበረው የመልከጸዲቅ የባቢሎን ንጉስ እና የባቢሎን ግንብ አሰሪ የነበረው የናምሩድ ተወላጅ ነው።። ናምሩድ የኖህ ዝርያ ሲሆን ኖህም የማቱሳላ፣" ... እያለ የዘር ፍሰቱን እስከ አዳምና ሄዋን ያደርሰዋል።። ከላይ በፕሮፌሰሩ ገለጻ ላይ "ወላጅ አባትና

አያት" የሚለው ሃረግ የአመታጥ ግንዱን ለማሳየት እንጂ ደሴት በአንድ ጊዜ አያትም አባትም ሆኗል እንደማለት አይመስለኝም። በገጽ 11 ላይም ደሸት የተሰኘው የኦሮሞና የአማራ የጋራ አባት ይኖር የነበረው እስከዛሬ ድረስ ደሴት እየተባለ ከሚጠራው ጣና ሃይቅ አካባቢ ነበር ያም ማለት የሁለቱ ህዝቦች ምንጫቸው ጎጃም መሆኑን እንዳረጋገጡ ጽፈዋል። ይህ አይነት አዲስ ግኝት አንባቢንን ግር የሚሰኝ ነው። የታሪክ አስተማሪዎቻችን በነጮች የተጻፉ የታሪክ ማስታዎሻዎችን በማጣቀስ ካሰረጹብን የኦሮሞ እና የአማራ ታሪኮች የተለየ መሆኑ የቀድሞውን ሽረን አዲሱን ግኝት በቀላሉ ለመቀበል እንደምንቸገር እገምታለሁ። ሆኖም ኢትዮጵያ የሰውዝር መገኛ መሆኗ በሳይንስ በመረጋገጡ እንደተቀበልነው የሚታወቅ በመሆኑ የሰው ዘር መገኛነትችንን ምስክሮች ሉሳና አርዲምን እየተንከባከብናቸው እንገኛለን። እናም የሰው ዘር መገኛነታችን ተቀብለን ካመንን፣ ኢትዮጵያዊያን ወይም የኢትዮጵያ ህዝቦች ከማዳጋስካርም፣ ከመካከለኛው አፍሪካ ወይም ከአረብ ምድር መጡ ወደሚል መደምደሚያ የሚወስድ ምክንያት እናጣለን። ኦሮሞውም አማራውም እንዲሁም ሌለው ኢትዮጵያዊ መፍለቂያው ከዚችው የሰው ዘር መገኛ ከሆነችው ኢትዮጵያ ነው የሚለው ሃሳብ ነው ገገር የሚሆነው። የሰው ዘር መገኛ ስንል ኢትዮጵያዊ ብቻ የተገኘባት ማለት ባለመሆኑ በሰፊው እንድናስብ እንገደዳለን። ስለሆነም የኦሮሞና የአማራ ህዝቦች ከአንድ አባት፣ ከኢትዮጵያ ምድር የተገኙ ናቸው የሚለውን ታሪክ እንደወረደ ልንቀበል እንድንችል ምክንያት ይሆናል።

በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የሁለቱ ህዝቦች ታሪክ

የአማራና የኦሮሞ ታሪካዊ በነገስታቶች ደረጃ መንዝረን እንመልከተው። ነገስታቱ መንግስትን ስልጣን በያዙ ማግስት የአማራ ወይም የኦሮሞ መንግስት የመመስረት አዝማሚያ አሳይተው አያውቁም። የኢትዮጵያ መንግስትን የማጽናትና ብዙውን ጊዜ በተለይ የሶሎሞን ስርዎ መንግስት ረጂም ጊዜ በቆየበት ወቅት ማለትም ከ1262 እስከ 1965 ዓ.ም. ከአማራም ሆነ ከኦሮሞ ዝርያ ያላቸው ነገስታት የኦሮሞነትም ሆነ የአማራነት ማንነት ከማንጸባረቅ ይልቅ የሶሎሞን ዝርያ መሆናቸውን በማሰነገርና በማወጅ ቅቡልነትን ያገኙ ነበር። ለአብነት በ1262 ዓ.ም. የነገሰው ይኮኖ አምላክ በእናቱ የኦሮሞ ዝርያ (የኦሮሞ ዝር ያላቸውን ንጉሶች ሚናና ማንነት ለመረዳት የፕሮፌሰር ፍቅርን መጽሃፍ ከገጽ 188 እስከ 199 ያንብቡ) የነበረው ሲሆን የመጨረሻው የሶሎሞን ስርዎ መንግስት የመራው ራስ ተፈሪ መኮንንም የአማራና የኦሮሞ ዝርያ ያለው መሆኑ የሚነገር ሆኖ ሁለቱም መሪዎች ሶሎሞን ዝርያ ስለመሆናቸው ከቤተ ክህነት እስከ ቤተ-መንግስት ከማስነገር ሌላ ብዬር ማንነትን የሚያንጸባርቁ አልነበሩም።

ማለትም ከሁለቱም ብሄሮች የተገኙ ነገስታት የቤተሰቦቻቸውን እና መንግስታቸውን የሚወክሉ እንጂ ሰፊውን የኦሮሞ እና የአማራ ህዝብ የሚወክል አደረጃጀትም ሆነ አስተሳሰብ እንዳልነበራቸው የሚታወቅ ነው።

የኦሮሞ የጦር አበጋዞች ግዛት ለማስፋት በአማራ የጦር አበጋዞች ላይ ጦር ሲመዙባቸው፣ ይዞታቸው ላይ ሲዘምቱባቸው ወይም ተገላቢጦሹ ሲከሰት በአትንኩኝ ባይነት የተፋለመበት ታሪካዊ ሂደት የማይዘነጋ ክስተት ቢሆንም የውጪ ወረራ በተከሰተ ጊዜ አንዱ ሌላውን አሳልፎ በመስጠት ከጠላት የመወገን ታሪክ እምብዛም አልታየም። በሌላ አገላለጽ ከስልጣን ሽኩቻ የመነጨ ተፎካካሪነት በቅኝ ገዢነት አሰፍስፎ ለነበረ አውሮፓዊ ክፈተት የሚሰጥ ጠላትነት አትረፈው የነበረበት ጊዜ አልነበረም። በዳግማዊ ምኒልክ ግዛት ማስፋፊት ሂደትም የአርሲ ኦሮሞዎች የአትንኩኝ ባይነት ፍልሚያ እንዳደረጉና በመጨረሻ ድል እንዳልቀናቸው የሚታወቅ ነው።

በሌላ በኩል ወደኋላም ባለው ታሪካችን በ16ኛው ክፍለ ዘመን የአማራው ፖለቲካዊ መዋቅርና ጉልብቱ በግራኝ መሃመድ ክንድ እንደተደቆሰ የኦሮሞ ተስፋፊ እንቅስቃሴ ወደሰሜን ያደረገው ጉዞ ያማረውን ይዞታ ማስለቀቁ ይታወቃል። ያም ሆነ እስከዛሬ ድረስ የአማራው ልሂቃን በሀገር ግንባታ አንደነት እንዲመጣና የአካባቢያዊ መሬት ተነጠቅሁ ስሜት ባለማንጸባረቅ ቀድሞውኑ ልሂቃኖቹ የስልጣኑን ሽኩቻና በየቀውጢ የሚፈጠሩ ቅራኔዎች ከሃገር ጥቅም አስበልጠው ቦታ የሚሰጡት ጉዳይ ያለመሆኑን እያስመሰከሩ ይገኛል። ከጥንት ጀምሮ በፖለቲካዊ ስርዓቶች የኦሮሞ ጎበዛዝት ስለነበራቸው ሚና ብዙ መጻፍ የሚቻላል ሲሆን በዘመናዊ ኢትዮጵያ ምስረታ ሂደትም የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት በማስጠበቁና በመጠበቁ ሂደት ባለታሪኮች ናቸው። ለማሳያነት እራሱን ለጣሊያን አረመኔዊ ቅጣት በመስጠት ለአርበኞች ስንቅ የሆነ ተጋደሎውን ያሳየ አቡነ ጴጥሮስን (መገርሳ በጣሳ)፣ለሃገር (ኢትዮጵያ) ሉአላዊነትና ክብር ወደር በማይገኝለት ተጋድሎ የሚታወቁትን ጀነራል ጃገማ ኬሎን እና አብዲሳ አጋን ብቻ በማስታወስ የኦሮሞ ጀግኖችን ባለውለታነት ማሳየት ይቻላል። ይህን ስል የትግራይና የደቡብ ኢትዮጵያ ወይም የሌላ አካባቢ ግጅኖች ስለኢትዮጵያ ያደረጉትን ተጋድሎ ችላ በማለት አይደለም።

በፖለቲካዊ ማህበረሰቡን የቋንቋ ጉዳይ እና ቀረብ ያለውን የፖለቲካዊ ታሪካችን ስንመጣ በዙዎቹ ነገስታት ወደስልጣን ሲመጡ የትግራዩን አጼ ዮሃንስን አራተኛ ጨምሮ የአማረኛን ቋንቋ የመንግስታቸው የስራ ቋንቋ የማድረግ ሁኔታ እንደነበረ የመይካድ ሃቅ ነው። በከተሞች

አካባቢ ሃይማኖትን በተመለከተ የነገስታቱ ዝርያና ነገስታቱ የሚከተሉትን በመከተል ቅቡልነትን ማሳደግ የሚፈለግበት ሁኔታ ነበር። ኦሮሞ ነግስታትም የፖለቲካ ስልጣናቸውን በሚያደላድሉበት የታሪክ ሂደት አማረኛን ቋንቋ የስራ ቋንቋ ሲያደርጉ እንደነበር የሚታወቅ ነው። ለዚህም የኦሮሞ የየጁ ስርዎ መንግስትን መጥቀስ ይቻላል።

በዘመናዊ ኢትዮጵያ ኦሮሞ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ በመገኘቱ አንዲሁም የማህበረሰቡ ታሪካዊ አደረጃት በወታደራዊም ሆነ በፖለቲካው መድረክ ለመሳተፍ አስቻይ በመሆኑ የሰሜን-ማዕከላዊ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ልሂቃን በሚደርጉት የግዛት ማስፋፋትም ሂደትና ከቅኝ ገዢዎች ከሚደረግ ትግል ዘመቻ ሚናው የጎላ ነበር። የውጭ ሃይልን በመመከት ሂደት ወደር የመይገኝላቸው ጀነራሎችን፣ ታላላቅ የጦር መሃንዲሶችን (በየትኛውም አለም ላይ በጦር ውስጥ የላቀ ስኬት ማስመዝገብ ከሁሉም ስኬቶች በላይ በነበረበት ዘመን)፣ ሲቪል የላቀ ሙያ ባለቤቶችንና አመራሮችን በማበርከት የዘመናዊ ኢትዮጵን ግንባታ አውን አድርጓል። በዚህ ሂደትም ብዙው የኦሮሞ ተወላጅ ዛሬን አያደረገውና የአማሪኛ ቋንቋን አቀላጥፎ ለሚናገሩና ለመጻፍ የሚችል ብሎም ለቋንቋውም ቀናኢ ነበር።

የዛሬዋ ኢትዮጵያ መስራች የሆኑት አጼ ምኒሊክ ወደቡብ ምዕራብ፣ ምስራቅ፣ እና ምዕራብ ኢትዮጵያ ግዛቱን በሚያስፋፋበት ጊዜ የግዛት ማስፋፋትን (empire building) አላማ አንግበው ሲያስገብሩ የነበሩት አብዛኞቹ ጀነራሎች ከጎንደር፣ ከጎጃም ወይም ከወሎ የተመለመሉ እንዳልነበሩ የታሪክ ምሁራን የሚጋሩት ነው። እንደእውነቱ ከሆነ ንጉሱ በዘመኑ የያዘውን ፖለቲካዊ አላማ ተጋርተው ሃገር በማስተዳደሩና በማስፋፋቱ የተጠመዱ የኦሮሞ ልጆች ጥቂቶች አልነበሩም። የኦሮሞና የአማራ ነገስታት እንዲሁም ሌሎች የፖለቲካ ስልጣንን ለማደላደል በጋብቻ በመተሳሰር ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ዝምድና የማጠናከር ታሪክ እንደነበራቸው ህያው ምስክሮች ያሉን ሲሆን በ19ኛው እና በ20ኛው ክፍለ ዘመን ላይም ተመሳሳይ ፖለቲካዊ ጋብቻ ነበር። ይህ ሁነታ ከፖለቲካዊ ገጽታው በተጨማሪ የሁለቱ ህዝቦች በእኩልነት የሚተያዩ እንደነበሩ፣ የማህበራዊ ተስተካካይነት ያላቸውና የሚፈላለጉ እንደነበሩና የሚያሳይ ሆኖ ዛሬ ላይም በመንግስት የመከፋፈል ሴራ በቀላሉ ተንበራካኪ ላለመሆናቸው ይህው ትስስር አንዱ አገናኝ ክር እንደሆነ የሚያመላክት ነው።

የበዳይ ተበዳጥ ታሪክ፡ የአማራና የኦሮሞ ህዝቦች ግንኙነት

ይሰሙኝ እንደሆን መለስ ልምከርዎ፣
ቀንሶ ማጋጨት ከንግዲህ ይብቃዎ።

ምንጭ፡ ተስፋዬ ገብርዓብ ከጎንደር በዝጉብኝ ቤቶች በቅኔ አዝማሪዎች ሲያቀነቅኑ ሰማሁ ብሎ በጋዜጠኛው ማስታወሻ ከጻፈው የተወሰደ ግጥም፡፡

ዛሬ ላይ የአማራ ህዝብ ከኦሮሞ ቀጥሎ በብዛት ሁለተኛ ሲሆን ሃገሪቱ የምትከበርባቸው አኩሪና ወርቃማ ታሪኮችን እንደሌሎች የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ሁሉ ሰርቶ ያለፈና ዛሬም በስርዓቱ በህልውናው ላይ የተጋረጠበትን አደጋ በሆደ ሰፊነት በመቻል ለሃገሪቱ የበኩሉን አስተዋጽዖ እያበረከተ ቆይቷል፡፡ ከዛሬ አርባ አምስት አመት በፊት ጀምሮ ሲቀነቀን የነበረው አማራን ከጨቋኝነትና ጋር የመያያዝ የብሄረተኞች የተሳሳተ አካኼድ እስከዛረ ድረስ ቆይቶ ማህበረሰቡ የፖለቲካዊ፣ የኢከኖሚያዊና ማህበራዊ መብቶች በአግባቡ እንደይከበሩለት ሆኗል፡፡ ይህ ስር የሰደደ ተጽዕኖ የማህበረሰቡ ጫንቃ ሊሸከመው ከሚችለው በላይ እየሆነ በመምጣቱ ዛሬ እንደየኦሮሞ ህዝብ ህዝባዊ እምቢተኝነት በማወጅ መስዋዕትን እየከፈለ ይገኛል፡፡ በታሪክ ሂደት ከኦሮሞ፣ አገው፣ ከቅማንት፣ ከትግራይ ህዝቦች አና ከሌሎችም የጠበቀ የታሪክ፣ የፖለቲካ እና የማህበራዊ ትስስር ያለው ማህበረሰብ ነው፡፡ በተለይ ከኦሮሞና ከቅማንትና አገው (የአገውና የቅማንት ህዝብ አማናራው ህዝብ ጋር ያለው ትስስር የዚህ ጽሁፍ የትኩረት አቅጣቻ አይደልም) ህዝቦች ጋር የነበረውንና ያለውን የወንድማማችነት መስተጋብር፣ ተዋልዶ የመኖር፣ የጋራ እምነት፣ የባህል መመሳሰልና የቋንቋ መወራረስን ለመመስክር የተለየ ጥናት የሚጠይቅ አይደለም፡፡ በተለይ ከኦሮሞ ህዝብ ጋር የጋራ ታሪካዊ ማንነት፣ ባህልና አኗኗር እንዳለው ከላይ ተብራርቷል ፡፡ በቅርቡም በይበልጥ ስለኦሮሞ ህዝቦች መብቶች በተቆርቋሪነቱ በአለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂነትን ያተረፈውና የመብት ተቀቆርቋሪው ጂዋር ሞሃመድ የኦሮሞና አማራ ህዝብ ብዙ አንድነቶችን የሚጋራ፣ ጠንካራ ህዝባዊ ግንኙነት ያለው በመሆኑ እስከሁን ተከስተው የነበሩ ሁለቱን ህዝቦች መፈቃቀር የሚጎዱ ኩነቶች በሁለቱ ብሄር ልሂቃን/ምሁራን ድርድር የሚፈቱ ናቸው ሲል አስተያየቱን በተለያዩ ሚዲዎች መግለጹ ይታወቃል፡፡ ከዚህም በላይ በሁለቱ ህዝቦች መሃል የተዘረጉ ታሪካዊና ወቅታዊ አንድነት ማጠንከሪያ ሰንሰለቶችን (bonds) መጠቀስ ይቻላል፡፡ ነበራዊ ሃቁ ለወደፊቷ ኢትዮጵያ ጠንካራ መሰረት የሚሆን ህዝባዊ አንድነት በኦሮሞውና በአማራው ህዝብ መሃል ጸንቶ መቆየቱ ቢሆንም ጥቃቅን ከስርዓቶች፣ ከግለሰቦችና አፍረሽ አላማ ከላቸው ቡድኖች እንዲሁም ውስን የፖለቲካ ልሂቃን የፈጸሟቸውን የታሪክ ቁርሾዎች በማጉላት ብሎም የብሄረሰብ ይዘት በመሰጠት የሁለቱ ህዝቦችን ሰላማዊ ጉርብትና፣ ተፈቃቅሮ የመኖር ባህልንና እጣ ፋንታን በማቀጨጭ የፖለቲካ ትርፍ መግኘት ዋነኛ ግባቸው ያደረጉ የፖለቲካ ልሂቃኖች የሃገሪቱን የፖለቲካ ስልጣን ተቆናጠዋል፡፡ አንድነትን የሚንድ አስተሳሰብ ሳይሰለቹ ሲሰብኩ ይሳማል፡፡ ይህ ለህዝብም ሆነ ሃገሪቱ መጻኢ

እድል የማይበጅ አሰላለፍና የህዝቦችን ታሪክ ያላገናዘብ አስተሳሰብ በፖለቲካ ስልጣን በመታገዝና አዳዲስ የልቦለድ ታሪኮች ከእውነተኛው መለየት እስከሚያዳግት እየቀመሩ ጥላቻን ለማንገስ ብዙ ተሰርቷ ነው። ለአብነት ያህል በኢትዮጵያ የሽግግር ምንግስትና ከዚያም በኋላ በኢትዮጵያ ጉያ ተደብቆ "እንደነቡርቃ ዝምታን"፣ "የሚሸፍቶ ቀሪጦች" ያሉ ጸብ አጫሪ ልብወለዶችን በባለስልጣናት እገዛ አሳትሞ በሁሉም የኦሮሚያ ትምህርት ቤቶች እንዲዳረሱ የማድረጉ ተግባር ሲያከናውን የነበረውን ኤርትራዊ ተስፋ የገብረዓብን መጠቀሱ ተገቢ ነው። የነበረከት ስምዖን መንግስትም የጥላቻ አስተሳሰብ ወሳኝ የሆነውን ልብለድ አወዳሽና ስፖንሰር እንደነበር ራሱ ተስፈፋዬ አረጋግጧል። ትላንትናና ዛሬም አንዳንድ የመንግስት አመራሮች የአማራ መንግስት የሚባል ስርዓት መስርቶ የማያውቀውን የአማራ ህዝብ የአማራ የበላይነት በኢትዮጵያ ተንሰራፍቶ እንደነበረ በማስነገር ሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች በተለይ የኦሮሞ ማህበረሰብ የአማራን ህዝብ በጨቋኝነት እንዲመለከት የሚያስችል ቅስቀሳዎች አድርገዋል።

የቀድሞው አገዛዝ የጥፋቶች ሁሉ ተጠያቂዎች የስርዓቱ ባለቤት የሆኑት መላ ኢትየጵያዊን መሆናቸው ቀርቶ ለአማራው ልሂቃን በመስጠት አሁን የተፈጠረው ምቹ ሃገራዊ ሁኔታ "የነፍጠኛው ገዢ መደብ ከመፍረሱ" ጋር የተሳሰረ መሆኑም መተንተን የ1960ዎቹ አቢዮተኞችን ተራማጅነትን የሚያጎናጽ አስተሳሰብ ሆኖ ተቆጠረ። ይህ አስተሳሰብ ሌሎች ኢትዮጵያዊያን በኢትዮጵያ አኩሪም ሆነ ጎስቋላ ታሪክ የነበራቸውን ድርሻና ለአሁኑ እኛነታችን ያበረከቱትን አስተዋጽኦ የሚኮስስ መሆኑም እየተዘነጋም መጥቷል። የሚኒልክ ወደ ደቡብ፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ኢትዮጵያ የመስፋፋት እንዲሁን ወደሰሜን ኢትዮጵያ በመዝመት ቅኝ ገዢዎን በመመከት ዛሬ በጋራ የእኛ እንደሆነች በማሰብ በምንነታረክባት ኢትዮጵያ ላይ የሁሉም ብሄራሰቦች አሻራ እንዳለ አያጠያይቅም። ይህን ሃቅ ለማጣቀሻነት ማቅረብ የበፊቱን ስርዓት በጉ ጎን ያመላክታል በሚል እሳቤ ይመስላል ተዘንቷል። ይህ ታስቦበትም ይሆን በሌላ ምክንት በኢትዮጵያ የቀድሞ ታሪክ ብሄር ብሄረሰቦች የነበራቸውን ሚና በመዘንጋት ጊዜያዊ የፖለቲካ ጥቅም ለማገኘት መጣር ብዙውን ማህበረሰብ ከኢትየጵያ ባለታሪክነት ጋር ያለውን ዝምድና እንደመደበቅ የሚታሰብ እና ይህ አይነት ተግባር ወደፊት ለምትኖረን ኢትዮጵያ አሉታዊ ጫና የሚኖረው ቢሆንም ጆሮ ዳባ ልበስ ተብሏል።

ይህ አስተሳሰብ የዛሬዋን ኢትዮጵያ በሚያስተዳድሩ የግንባት ሃያ ባለድሎችም የፖለቲካ አቅጣጫ ሆኖ በመቀጠሉ የኦሞና የአማራ ህዝብ ግንኙነትም በዚሁ የበዳይ ተበዳይ ታሪክ እንዲቃኝ ተደረገ። የኦሮሞ እና የአማራ ሕዝብ ለሩብ ምእተ ዓመት ያክል ክፍፍል ግጭትና

ጥላቻ በመካከላቸው እንዲኖር ኢሕአዴግ እንደ ሥርዓት ስለመስራቱ ዶክትር ዳኛቸው አሰፋ በ2009 ዓ.ም. በአዲስ አድማስ ጋዜጣ አስፍረዋል። ጊዜያዊ ውጤታማነትም ስለነበረው ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ የኦሮሞ የፖለቲካ ቡድኖች በአማራ ህዝብ ላይ የፈጸሙት ግፍ የማይዘነጋ ነው። እነዚህ ፖለቲከኞች በአማራና ኦሮሞ ልሂቃን ብሎም በህዝብ መሃል በሚኖረው ያለመግባባት በመጠቀም ስልጣንን ለማደላደል የበደል ታሪኮችን በመፈልፈልና አግዝፎ (በልብ ወለድ በማሳመር ወይም የሃሰት አሃዞችን በማስቀመጥ) በማሳየት ተጠምደው ብዙ የውሸት ተራራዎችን ገንብተው በየመድረኩ የሚነገሩ የተዛቡ የታሪክ ትንተናዎችን ለጆሯችን እየከበዱን ዝምታን የመረጥን ብዙዎች ነን። እንደ ዳኛቸው ገለጻ "በኦሮሞ እና በአማራ ሕዝብ መካከል የመከፋፈል ዘይቤ ገቢራዊ ለማድረግ የኢሕአዴግ ሥርዓት በቀዳሚነት ሦስት ዐበይት መንገዶችን ይጠቀማል። እነኚህም፡- ‹ታሪክ›ን፣ ‹ስያሜ›ንና ‹ቅራኔ›ን ማስተጋባት ናቸው"።

"***ታሪክ (እንድናውቃቸው የሚፈለግ ታሪክ)***"፡ በስርዓቱ ሙያን የማዋረድና በማናለብኝነት ታሪክን የማዛባት አካሄድ በብሄር ብሄረሰቦች ግንኙነትም ላይ ጥቁር ነጥብ የመጣል ተልኮ እያዘለ አንዳንዴ በነጭ ውሸት ሌላ ጊዜ በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረት ልቦለድ በማስመሰል ሌላ ጊዜ በድፍረት ደረቅ ውሸት በመቀመር የሚያሰራጭበት ሁኔታ ተስተውሏል (ዝኒ ከማሁ)። ሌሎችም በኢትዮጵያ የተከሰቱ ስርዓቶች ለመከፋፈያ በተለያየ መልኩ እንደሚዘውሩት በማብራራት ከላይ ያለውን ሃሳብ ዶክተር ዳናቸው አሰፋ[31] ሳይጠቅሱ አላለፉም። ለኦሮሞ የተጨቋኝነትን ካባ ማጎናጸፍ ለአማራ ልሂቃን የጨቋኝነትን ታሪክ አላብሶ መጻፍ የሚከለከል አልነበረም። አይደለምም። በተለይ በ1960ዎቹ የተራማጅነት መገለጫም ነበር። ብሄር ተኮር አደረጃጀት ያላቸው የማረክሳዊ-ሌኒናዊ ቡድኖች ፖለቲካዊ ስልትም ነበር። እንደእውነቱ ህዝብ በሃገሪቱ አያት ቀድመ አያቶቹ የታሪክ ባለቤቶች መሆናቸውን ለአሁኑ ትውልድን ያለማሳወቅ ወይም ያለማስተማር ከታሪክ ነጠቃ አሊም ከክህደት የማይተናነስ ነው። ለነገሩ ሕወሓት መራሹ መንግስት ለኢትዮጵያ እውነተኛ ታሪክ የሚጨነቅ እንደላሆነ ለመረዳት የአመሰራረቱን እና የበፊት ታሪኩን ማስታወስ በቂ ነው። የገግሓትን (የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር) ፖለቲካዊ

[31]በየጊዜው የሚመጡ ሥርዓቶች፣ ታሪክን እንደ መሣርያ ለአገዛዝ ይገለገሉበታል የሚል እምነት አለኝ። ይኸውም ይኹነኝ ተብሎ ሰዎች ታሪካቸውን እንዳያውቁ፣ እንዳያስታውሱና እንዳያነሡ፣ ኢታሪካዊ የኾነ የአእምሮ ድባብ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ ነው። አንድ ሕዝብ በእንዲህ ዓይነት ታሪክን የመርሳት መዳፍ ሥር በሚወድቅበት ጊዜ፣ ሥርዓቱ ለፖለቲካው የሚበጀውን ነገር እየጻፈ፣ ያልተደረገን እንደተደረገ፣ የሆነውን ነገርም በጣም እያጋነነና የታሪክን ሒደት እያፋለሰ ሕዝብ እንዲቀበለው ለማድረግ ይሞክራል።በተጨማሪም፣ ለሥርዓቱ ይበጃል በሚል ወደኋላ ተመልሶ ታሪክን በቁንጽል በመምዘዝና በማጣመም በበጎ እንዳይተያዩ በሚፈለጉ ብሔሮች መካከል ቅራኔ እንዲፈጠር ያደርጋል። ለዚኽም ዓላማው፣ ከየወገኑ መርዶ ነጋሪ አለቆችን በማሠልጠን፣ «በዚያን ጊዜ እንዲህ ተደርጋችኋል»፤ «በዚህን ጊዜ እንዲኽ ተደራርጋችኋል» በሚል የሚፈልገውን የቅራኔ ታሪክ በሕዝቡ ዘንድ ለማሥረጽ በብዙ ይታትራል፤ ታሪክን ለሚፈለገው የፖለቲካ ዓላማ እና ግብ ማሳኪያም ያውለዋል።

አስተሳሰብ ስናይ “ትግራይ በኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት ውስጥ የወደቀች ናት” (አስራት አብርሃም፡ 2008 ዓ.ም.)፡፡ ኂላም ሕወሓት የሻቢያን የመገንጠል አላማ ለማስፈጸም የሚጥር፣ ታላቋን ትግራይ ለመመስረት የታገለ እና የኢትዮጵን ሁሉ አቀፍ ጥቅም የተጻረረ መሆኑን አስራት አብርሃም በማስረጃ አስደግፎ ጽፏል፡፡ አሰፋ ጫቦ የአስራትን ሃሳብ በመጋራት የሚከተለውን ጽፈዋል፡፡ “...መለስ ዜናዊና ኢትዮጵያ እንዴት ይተያያሉ የሚለውን ተመራማሪዎች ቢያዩት ጥሩ ይመስለኛል፤ ወያኔዎች የተነሱት ለትግራይ ሪፐብሊክ ነው፤አድሮ ውሎ አሜሪካኖችና ሌሎቹም ደጋፊዎቻቸው “ትልቁ ዳቦ ይቻላል!” ሲሏቸው በተማረኩ ወታደሮች ካምፕ ተሯሩጠው ኢህአዴግ የሚባል ፍጥረት ፈጠሩ፤ያ ማለት እንግዲግ የመለስ ልቡ፣ ቢያንስ ሙሉ ልቡ ኢትዮጵያ አልነበረችም ወደማለት ይወስዳል” (አሰፋ ጫቦ፣2008 ዓ.ም.)፡፡ እንግዲህ ከስረ መሰረቱ የኢትዮጵያን ህልውና የማያስጨንቀው ቡድን እና የጎበዝ አለቆች ስብስብ ስለኢትዮጵያዊን አንድነትና አውነተኛ አስታራቂ ታሪክ ይቆረቆራል ብሎ ማሰብ ያዳግታል፡፡ እናም ከፋፍሎ ለመግዛት የሚስችሉ ብልሃቶችን በአይነት ማስቀመጥም የሚጠበቅ እንዲሆን ያደርገውል፡፡ አስገራሚውና ግራ የሚያጋባው ነገር የነመለስ ዜናዊ ቡድን ኢትዮጵያን እንደፈለጉ በግል ንብረትነት የሚያሸከረክሯት ከሆነች በኂላ የህዝቦችን አንድነት በማሳደግ ጥቅሟን ለማስጠበቅ አዲስ አስተሳሰብ ሃገራዊ ያለመገንባታቸው ነው፡፡ ከ2008 ዓ.ም. ጀምሮ የተከው ሀገር አቀፍ ቀውስም ከዚሁ ፖለቲካዊ ትንሽነት የሚመነጭ ነው፡፡

ዛሬ ላይ ለመከፋፈያ አመችነት ያላቸው የታሪኮች ክስተቶች ሁሌም ከትውስታችን ውስጥ እንዳይጠፉ የማድረጉ ስራ የጎላ ትኩረት ተችሮታል፡፡ ዶ/ር ዳኛቸው እንደሚሉት የኢሕአዴግ ሥርዓት፣ ሕዝቡ ቢያስታውስ የሚበጀውንና የሚፈልገውን ታሪክ ከመንገር ይልቅ ራሱ ሥርዓቱ የመረጠውንና የፈለገውን ታሪክ ብቻ እንድናስታውስ ብዙ ጥሯል፡፡ ይህ ጥረቱ በሹሉም የአገራችን ብሔሮች ላይ ትኩረት ያደረገ ቢሆንም፣ በተለይም በኦሮሞው እና በአማራው መካከል የመለያየ ታሪክ ፍለጋ ጉልበቱን እንደ ጨረሰ እንረዳለን፡፡ በህዝቦች መካከል ሁሌም የፍቅርና የመቻቻል ታሪክ ነበር ለማለት የሚደፍር ጸሃፊ እንደማይኖር ሳልጠቅስ አላልፍም፡፡ የተላያዩ ግጭቶችና ጦርነቶች ተከስተው የነበረበት ወቅት ነበርና፡፡ ሆኖም እርስ በርስ ግጭቱና ያለመግባባቱ ታሪኮችን በብዜረሰብ ደረጃ ማሰቡና አጠቂና ተጠቂ ብዜረሶቦችን አድርጎ መፈረጅ ታሪክንም የኢትዮጵያዊያን አሴቶችንም አረዳድን የተዛባ ያደርገዋል፡፡ የመስፋፋት አላማ ያላቸው ቡድኖች ሲጠናከሩ የሚከሰት የጦርነትም ግንኙነት መኖሩ የሚገርነጋ ይደለም፡፡ ለምሳሌ አንዳርጋቸው ጥሩነህ የተባሉ ጸሀፊ የማዕከላዊ-ሰሜን ኢትዮጵዊን ከሶማሊው፣ ሃረሪው እና ኦሮሞው ዛሬ የኢትዮጵያ በምንለው መሬት የነበራቸውን የጦርንትና

የፖለቲካ መስተጋብር[32] እና አንዱ በአንዱ ላይ የበላይነት ለመያዝ የነበራቸውን ፍትጊያ ጽፏል። እንደጸሃፊው ገለጻ በመስተጋብራቸው ውስጥ ታሪክ አለ፤ አንዱ አንዱን ያሸንፋል፣ የራሱን ታሪክ በኢትዮጵያ ስም ያንጻል፤ እንደገና ሌላኛው ይነሳል፣ መልሶም በሌላው ይተካል። ይብዛም ይነስም ሁሉም የየራሳቸውን ስርዓት ኢትዮጵያ ላይ ዘርግተው አልፈዋል። ያ ስርዓት ግን ኢትዮጵያዊ ገጽታ (የብሄር አደረጃጀት ያልነበረው መሆኑን ማሰብ ተገቢ ነው) የነበረው መሆኑ እና ሁሉላችንም የዚያ ታሪክ ተጋሪ ስለመሆናችን የሚያጠያይቅ አይደለም።

በተጨማሪ በግዛት ማስፋፋት ሂደት የአርሲ ኦሮሞ የትግል ታሪክ ያልገብር ባይነት ትግል ነበር በሚል የሚወሰድ ነው። የምኒልክን ሰራዊት የተፋለመው በራሱ ሲያስተዳድረው የነበረውን አካባቢ በሌላ ሊቀየርብት ካለመፈለጉ የሚመነጭ ያልደፈር ባይነት ማንነቱ ነጸብራቅ ነበርም። ኦሮሞ የጭቆና ትከሻ አልነበረውም፣ ዛሬም የለውም፣ የበዳይ ተበዳይ ታሪክ አርቃቂዎችና ጸሃፊዎቻች እንደሚሉት ኦሮሞ ከሌሎች ኢትዮጵዊን በተለየ የጭቆና ቀንበር ተጭኖበት የኖረ ብቸኛ ህዝብ አልነበረም። ጭቆናው በሁሉም የኢትዮጵያዊን ላይ ነበርና። በብሄር ስልቻችን ውስጥ ሆነን ካሰብነው የምኒልክ ሰራዊ ቀድሞ ያስገበረው ያማራውን አካባቢ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አልገብርም ገብር በሚል ፍትጊያ ምናልባትም ከአንኮበር አካባቢ የተገኙ የንጉሱ ሰራዊት አባላትና የጎጃም የጎንደር የጎዝ አለቆች ብሎም ነገስታት ሰራዊቶች መሞታቸው እሙን ነው። ስለሆነም በግዛት ማስፋፋት ሂደቱ ከሁሉም ቀድሞ የአማራ ልጆች ደም ነው የፈሰሰው። ግን ጉዳይ ታላቅ ሃገር የመሆን ህልም ስለነብር በዚህ ደረጃ የወረደ የሚች ዘር ቆጠራ ለዚን ዘመን ታሪ አይመጥንም። ዛሬ ላይ ግን ተመራጭ ሆኗል።

በነገራችን ላይ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ቡድኖች የበላይነትን ለመቀዳጀት በያሚደርጉት እሽቅድድም በሚከሰቱ ግጭቶች መሃልና በኋላ የመዋሃድና አወንታዊ ግንኙነት የተፈጠረበት የታሪክ አጋጣሚም እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም። ይህም የሚሆነው ዳግም ላለመጋጨት ድርድር ተደርጎ በጋብቻ የመተሳሰር (Poltical marriages) ልምድ ስለነበርም ነው። ይህ የእርቅ መንገድ ዛሬ ላይ ግን ብዙ አይወራለትም። ምክንያቱም ህዝብ ትስትሮችን አጉልቶ ከማሳየት

[32]The political career of the more important of the kingdoms which was ruled by the so-called Solomanic dynasty and which had emerged among the Amhara in the thirteenth century, was marked by having to change its seat constantly in order to tame independently minded regional governors and to ward off increasingly important Islamic encroachments from the strings of Emirates that had come to exist in the eastern highland and Low land areas during the twelfth century. The decline of this kingdom came in the sixteenth century as a result of invasions by one of these emirates (Harar) and by waves of Oromo migrations from the south. Harar, led by Gragn who was probably a Somali, overran the length and breadth of the central and northern highlands from 1529 to1543.

ይልቅ በተወሰነ ብሄር ላይ ሌለው የፈጸመውን በደልን ማስጠናት፣ ጨማምሮ መተንተን፣መዋሸትና ማስዋሸት ተመራጭ መንግስታዊ ፋሽን በመሆኑ ነው።

ልናስታውስና ልናውቀው የማይደረጉ የታሪክ እሴቶች፦ ለዚህ ፍርጃ የሚጋለጡት የበዳይ ተበዳይነት ባህሪ ያልተላበሱ ታሪኮች ናቸው። በቴወድሮስ ራዕይ መሰረት ቅርጽ የያዘችው ሃገር መነሻ አድርገን ብናወራም ከተለያዩ ብሄር የተገኙ ልሂቃን ከማውራት ያለፈ ስለብሄር ትንተና ለመስጠት ታሪካዊ መሰረት ያጥረናል። በዚችናዋ ኢትዮጵያ ምስረታ ይብዛም ይነስም ሁሉም ኢትዮጵዊን ዋጋ ከፍለዋል። በጣሊን ወረራ ወቅት ደጃዝማች በላይ ዘለቀ በበረሃ ወራሪውን ፋታ ሲነሳ ከኦሮሞ ማህጸን የተገኘው አቡነ ጴጥሮስ ኢትዮጵዊን ለባዕድ አገዛዝ እንዳይንበረከኩ ታግለዋል። በላይ ዘለቀ ከድል በኋላ የተመሰረተው ስርዓት ባይደላውም ሃገራቱን ነጻ የማውጣት ግቡን ግን አሳክቷል። አቡኑ ያለማመንታት ለመስወዕተነት በመብቃታቸው ለጀግኖች የመንፈስ ጥንካሬን ለግሰው፣ ለምዕመናን ለፍትህ የተሰው ጠንካራ የመንፈስ አባትነታቸውን አረጋግጠው አልፈዋል። እንደመርሁ የመንፈስ አባት ከድል በኋላ ፖለቲካዊና ቁሳዊ ድሎት የሚመኝ ባለመሆኑ የሚያስቆጫቸው ባይመስለኝም ሃገራቸው ነጻ በመውጣቷ የመንፈስ ደስታን ከአርበኞች ጋር ተቋድሰው ቢሆን እመኝ ነበር። አብደሳ አጋንና ጀነራል ጃገም ኬሎን ጉዳዩ ያው ነው የኦሮሞ ልሂቃን ኢትዮጵያን የመሰረቱ መሆኑን የሚስረዱ። የጥፋት አቅጣጫ ነው ብዬ የማምነው የትየለሌ ከኦሮሞ አብራክ የተገኙ ብዙ የተወራላቸውን ባለደማቅ ታሪክ የኢትዮጵያ ልጆች መኖራቸውንና አበርክቷቸውን ለህዝቡ ያለማስተማርና ሁሉንም የገገርነት ሚና ከጨቋኝነት ፍረጃ ጋር ጠቅልሎ ለአማራው ወይም ለአማራው ልሂቃን የመስጠቱን የዘመናችን አካሄድ ነው። የአማራ ልሂቃንንም ስለኢትዮጵያ መሞትና መዋደቅ መደህየትና መጎሳቆል ብሎም የአኩሪ ታሪክ ባለቤትንትን ከከማሳወቅ ይልቅ የበዳይነትን ጃኖ የማጎናጸፍ አባዜ አለ። በኦሮሞ ብሄር ላይ ብቻ ሳናተኩር በቀድሞው ስርዓት የነበሩና እንዳናውቃቸው የማይፈለጉ ፖለቲካዊ ታሪኮችን ከአሁኑ ስርዓት ጋር በማነጻጸር መስፍን ወልደማሪም እንደሚከተለው ይገልጹታል።

> *በኃይለስላሴም ሆነ በደርግ የአገዛዝ ዘመኖች በመንግስት ከፍተኛ ሹማምንት፣ በአየር ሃይል፣ በጦር ሰራዊትና በባህር ሃይል ሹማምንት፤ በሌሎች የመንገስት መስሪያቤቶች ሁሉ የሚከኙ ኃላፊዎች የነበራቸው የጎሳ ስብጥር ታስቦበት የተደረገ አልነበረም፣መመዘኛው ጎሳ አልነበረም፣ዛሬ ከወላይታ ጠቅላይ ሚኒስተር መሾሙ በአጼ ኃ/ስላሴ እና በደርግ ዘመን የነበረውን ለማውቁ ለብዙ ሰዎች አዲስ ነገር መስሎ ይታያቸ ይሆናል፤ ግን አዲስ አይደለም፤በሁለቱም የቀድሞው አገዛዞች ከፍተኛ የመንግስት አመራሮች ከወላይታ ነበሩ፤የኢትዮጵያ ከፍተኛ የጦር መኮንኖችም ሆኑ ሚኒስትሮች በጎሳ ድርሻ ባይደለደሉም የጎሳ አድሎ ነበር ለማለት ያስቸግራል። ሌላ ቀርቶ አማረኛ*

ማወቅም ወሳኝ ነበር ለማለት አይቻልም፤የአጼ ኃ/ስላሴ ጎሳ መደበቁ ምንን እንደጎዳና ምንን እንደጠቀመ የወደፊት የታሪክ ተመራማሪዎች ይጨነቁበት...(2007 ዓ.ም.፡36)፡፡

ፕሮፌሰሩ ጎሳ የሚሉት በዚህ ጽሁፍ "ብሄር" የተባለውን ሲሆን ሶስቱንም ስርዓቶች ጉድለትና በጎ ገጽታ ለመናገር የሙያዊም ሆነ የልምድ እጥረት የሌለባቸው ናቸው፡፡ በሚዛናዊነትም በኩል ሶስቱንም ስርዓቶች በመተጨት እድሚቸውን ያሳለፉ በመሆኑ አንዱን አድንቀው ሌላውነ አንኳሰው ለመጻፍ የሚጋብዝ ስብዕና የላቸውም፡፡ የጽሁፋቸው ዋና ፍሬ ነገር የቀድሞ ታሪኮችን በደንብ ያልተገነዘብን በመሆኑ ዛሬ ላይ የቀድሞውን የማጣጣልና የአሁኑን ስርዓት የብሄር ጉዳይ እንዳዲስ ነገር የምንመለከት መሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪም ዛሬ ላይ እነዚህን አይነት የብሄር አድሎ የማይታይባቸው አሰራሮችን እንድናውቅ ከተደረገ የዛሬውን ያልተሳካ ነገር ግን ለብሄር ብሄረሰቦች መብቶች ቆመናል በሚል የሚነዛ ዲስኩር ላንቀበለው ስለሚያስችል እንዳናውቀው የሚደረግበት ሆኔታ መኖሩን እገምታለሁ፡፡

በስጠቀልል እንደ "በኢሕአዴግ አተያይ፣ አማራው የጠባይ ጉድለት አለበት ተብሎ እንደታሰበው ሁሉ፤ ወደ ኦሮሞ ሕዝብ ስንመጣ በመሠረቱ የአመለካከት ግድፈት አለው ብሎ ያምናል፤ እንደ ሥርዓቱ እይታ፣ የዚህም የአመለካከት ግድፈት መንሥኤ፣ ከጠባብ ብሔረተኝነት የመነጨ እንደኾነ በተደጋጋሚ ይገለጻል (ዳኛቸው አሰፋ፣2009 ዓ.ም.) ፡፡ ይህ አተያይ ሁለቱን ብሄሮች በተለያየ ጸንፍ ለማስቀመጥና የማይቀራረብ አስተሳሰን ያላቸው እንደሆኑ አድርጎ ለማሳየት የታለመ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በዋናነት የሁለቱ ብሄሮች የሚቀራርቡ ታሪካዊ የጋራ እሴቶችና ለሁሉም ህዝብ ተቃሚ የሆኑ ሃገራዊ የታሪክ ትሩፋቶች እንዳይነገሩና ህዝቡም እንዳይሰማቸው እቀባ የማድረግ ተግባር የአንድነታችን ተግዳሮች ሆኗል፡፡

የመተራረብ ቅራኔ የፖለቲካ ፍጆታነት ፋይዳ፡ የመንግስት ሚና ቀስ በቀስ ከስነ-ምግባርም ሆነ ከህዝብ መከባበር አንጻር ተቀባይነት የሌላቸው እሴቶች እንዲጠፉ ስርዓት መዘርጋት ሆኖ ሳለ የህኛው ብሄር እንዲህ ብሎህ፣ መናናቅን የሚያሳብቅ ሰም ሰጥቶህ በሚል በብሄሮች መካከል መተባበርን የማቀጨጭ ተግባራት በሚዲዎችም ጭምር እየተሰራበት መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ አንዳንድ በግለሰቦች አንዳንዴም ሰፋ ብለውም በማህበረሰብ የሚንጸባረቁ በንግግርም (እንደተረትና አባበል አይነቶች) እና በጽሁፍ የሚተላለፉ የአስተሳሰብ ነጸብራቅ የሆኑ ተቀባይነት የሌላቸው ትረባዎች እንዳሉ መገንዘብ የሚያዳግት አይመስለኝም፡፡ በብሄር ድረጃ ለመተቻቸት የሚያበቁ ባይሆኑም በብዙ አካባቢዎች ይስተዋላሉ፡፡ በብሄር ደረጃ መተቻቸት አያስችሉም የምንለው አንዱ ብሄር ሌላኛውን በንቀት ያየዋል የሚል መደምደሚያ ስለመይኖር ነው፡፡ ምክንያቱም የመናናቅ አዝማሚያዎች በአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች መሃልም ያለ በመሆኑ፡፡

ዘርዘር ሳደረገው በቀልዶቻችን፣ በተረቶቻችን የሆነ ብሄርን ወይም የሆነ አካባቢ ነዋሪን ከሆነ ባህሪ ጋር፣ አነጋገር ዘይቤ ወዘተ ጋር በማገናኝት አንዱ በአንዱ የሚስቅበት ሁኔታ አለ። ለምሳሌ ጮሌነትንና ቆጥቋጣነትን ለጉራጌ፣ ቂላቂልነትን ለመንዜው፣ አጉል መኩራራትን ለጎንደሬ የማላበስ ሁኔታ ሲኖር ይህ አፈራረጅ በአንዱ ብሄር መሃልም (እርስ በእርሱ ለማለት ነው) ጭምር የሚከሰት ነው። እነዚህን አይነት ታሪኮችና ዛሬም ላይ የሚታዩ ግንኙነቶች መሆናቸውን ፕሮፌሰር መስፍን አዳፍኔ በተሰኘው መጽሃፋቸው በገጽ 38 ላይ ጠቅሰዋል። በዚህ ረገድ ችግሩ የሚነሳው ከላይ እንደጠቀስኩት እነዚህን ሁኔታዎች ተጠቅሞ ለፖለቲካዊ አላማ ብሄር ተኮር መናናቅ እንዳለ በማስመሰል የበዳይ ተበዳይ ትረካ ላይ እመተኮሩ ላይ ሲሆን የወቅቱ የፖለቲካ ስርዓት የዚህ በሽታ ተለካፊም ሌሎችን የሚለክፍ ሆኗል። በመሰረታዊነት የሚናናቅ ማህበረሰብ፣ ለጋብቻ አይፈላለግም፣ አይጋባም፣ አይዋለድም፣ የእድር፣ ማህበር ወ.ዘ.ተ. ማህበራዊ ቁርኝት ለመፍጠር አይገፋፉም። በአብዛኛው ኢትዮጵያዊን በይበልጥ የኦሮሞና የአማራ ህዝቦች ከንጉስ እስከ ምንዝር ይፈላለጋሉም ይዋለዳሉም። መተራረቦች ከአፍ ወለምታ የማያልፉምና ከአካባቢዊ ኩለቶችና የስልጣኔ ሁኔታን መሰረት ያደረጉም ነበሩ። በብሄር መሃል የመናናቅ ታሪክ ነበር ባዮች ክሽፈትም እነዚህን ሃቆች አስበውበት ችላ በማለታቸው ወይም የህዝቦችን የጋራ ፖለቲከ-ማህበራዊ እሴቶችን በውል ካለማወቃቸው የሚመነጭ ነው።

<u>ስምና ቋንቋ፡</u> ስምን በተመለከተ ኦሮሞ ስሞችን በአማረኛ በግዕዝ ወይን በመጸሃፍ ቅዱስ ስሞች የመቀየር አዝማሚንና ተግባርን የአማራ ተጸኖ አስመስለው የሚጸፉ ግለሰቦች አሉ።ይህንም ከተጽዕኖ ጋር ያያይዛሉ። የግዕዝን እና የአማረኛ ቋንቋ ስሞችን እንዲሁም ከመጸሃፍ በመውሰድ በከተሞች አካባቢ የመጠቀም ሁኔታ አለ። የነበረም ነው። ካለፉት አርባ አመታት በተለይም ከ1983 ዓ.ም. ወዲህ ከላይ የባህል የተዘረዘሩትን ኩነቶች በማጣቀስ የአማራ ብሄር ገገርና የበላይ የነበረ በመሆኑ ስም ስቀይራል በሚል በአደባባይ የሚነገሩ ልቦለዶች ለብሄር ፖለቲካው ማጣፈጫ ሆነው ግንዛቤው በሌላቸው ውስን የብሄር ፖለቲከኞ ጣት ሲቀሰሩ ቆይቷል። ነገሩ ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ አይነት ነው። ለማብራራት ስሞክር በአዲስ አበባ የአማራ ስም እንዲሰየም ጫና ይደረጋል በሚል ተስፋየ ገብረአብ "**ጫልቱን እንደሄለን**" በሚል ርእስ ስር "*የስተደኛው ማስታወሻ*" በሚል ርዕስ ባሳተመው መጽሃፍ ገጽ 66 ላይ የተለመደውን የአማራና ኦሮሞ ባላንጣነት አቀንቃኝ ተልኮውን ጽፎ አስነብቦናል። ተስፋዬ[33] በአማራና ኦሮሞ ህዝቦች

[33]የመከፋፈልና ህዝብን የማባለት አላማውን ገቢራዊ ለሚደርግ በልብ ወለድ የአማራና የኦሮሞ ገጸ-ባህሪ በማላበስ የሚጣላሉና የሚጠላለፉ "የአለምሽትንና የአራርሳን" መስተጋብር "የቢሸፍቱ ቆሪጦች" በተሰኘ መጽሃፉ፤ የኦሮሞ

መሃል የጥላቻ መርዝ የሚረጩ ልቦለዶ ደራሲ መሆኑን ከላይ ጠቅሻለሁ። ለመሆኑ ጫልቱ ሌለን ብላ ስሟን ብትቀይር **ሌለን** የሚል ቃል አማረኛ ነው ወይም የአማራ ስም ነውን? ተስፋየን እጠይቀዋለሁ። የስም ለውጥ እውነቱ እንዲህ ነው። ወደከተሞች የሚቀላቀሉ ኢትዮጵያዊን ወይም በቤተሰባቸው ፍላጎት ስማቸው አካባቢዊ ከሆነ የሚያሳድረው ጫና አለ። ለምሳሌ ስለራሴ ስም ላንሳ አያቴ ዳምጠው አሉኝ። የሰፈር ልጆች ሰሜን አይወዱትም ነበር፣ በስሜ ያሾፉመ ነበርና እበሳጨም ነበር፤ አንዳንዱም ከሚያላግጡብኝ ልጆች እጣላ ነበር። ስምህን ቀይር የሚሉኝም ሰዎች እጅግ ብዙ ነበር። ለከተማው ያረጀ ያፈጀ ስም ነው የሚሉኝም ነበሩ። የምተዋወቃቸው ሰዎች በተለይ እንስቶች ስምህን ዋሽተኸናል ይሉኝም ነበር። እንግዲህ እኔ የገጠመኝ ጫና እንደጫልቱ የኦሮሞ ስም ስላለኝ አልነበረም። በርግጥ ከየትኛውም ብሄር የተገኘ ሰው ስሙ ለከተማ አይመጥንም የሚል ግምት ያደረባቸው ግለሰቦች ወይም ስማቸው አካባቢያዊ በመሆኑ ምቾት ያልሰጣቸው ከሆነ የሚቀይሩበት ሁኔታ አለ። በተለይ በከተሞች ይህ ተግባር በዙዎች የተለመደ ነው።

ሃይማኖት መቀየር ከንጉሳዊን ቤተሰቦች ጋር በማመሳሰል ቅቡልነትን ለማብዛት እንጂ የአማራ የበላይነት በሚል የተስፋዬ ገብርአብን ጥላቻ ነገር ህትመቶች የማገዝና የማበረታታት ሚና ያለው ስርዓት እንደሚለው ያለመሆኑ ሊሰመረበት ይገባል። በቀድሞዎቹ ስርዓቶች ምናልባት አማረኛ ቋንቋ እንዲስፋፋና ህዝቡ እንዲለምድ ግፊት ይደረግ እንደነበረ የሚታወቅ ሲሆን ይህ አካሄድ አማረኛ ተናጋሪ ባልሆኑ ህዝች ላይ ጫና ሊያሳድር መቻሉን አሌ የሚባል አይደለም። ሆኖም አንድ መንግስታዊ ስርዓት አንድ ፖለቲካዊ ማህበረሰብ ለመፍጥር እንዲያመቸው ይበጃል ያለውን ቋንቋም ሆነ ሌላ ሃገራዊ እሴቶችን ዜጎች እንዲማሩና እንዲላበሱት ያደርጋል። ዋናው ጉዳይ በፍላጎት ላይ የተመሰረተ መሆኑ ላይ ነው። ትችታችንም መመስረት ያለበት የኔንም ቋንቋ ላሳድግ፣ልናገር የሚል ጥያቄ አልተስተናገደም በሚለው ላይ መሆን ይገባዋል። ሆኖም በአጼ ምኒልክና በአጼ ሀይለስላሴ ዘመን ወይም ከነዚህ ነገስታት በፊት ባለው ዘመን ይህ አይነት ቋንቋ ነክ ዴሞክራሲያዊነት በአለም ላይ/በዴሞክራሲ ስርዓት በሚታወቁት ሃገራትም ጭምር/ ያልተለመደ ነበር። ስለሆነም ትችትም ወቅትንና ቦታን ያማከለ መሆን እንደሚገባው

የቀድሞ መሪዎች በምንሊክ ሰራዊት በመሸነፋቸው አንገቱን የደፋው የቡርቃ ወንዝ ዳማም ወደላይ ላይፈስ በመሬት ውስጥ ሰርጎ እንደሚሄድ በማስመሰል "የቡርቃ ዝምታ" በተሰኘ መጽሃፉ እና በመንግስት ወጪ በሚታተሙ መጽሄቶች የአማራንና ኦሮሞን ታሪካዊ ትስስር የሚንዱ ጽሁፎችን ሲያስነብበን የነበረው ተስፋዬ ገብረዓብ ድህረ-ግንቦት ሃያ የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣን እንደነበር የሚካድ አይደለም። ተስፋዬ ከስርዓቱ ከተፋታም በኋላ ከሻቢና በቀድሞው ፓርቲው ኢህአዴግ እንዲሰራ የተሰጠውን የቤት ስራ ባለመርሳት ይመስላል ከላይ እንዳየነው "ጫልቱን እንደሌለን" በሚል ርዕስ በመጻፍ በኦሮሞ ላይ የአማራን ተጽኖ ለማሳየት የጻፈውን ልብ ወለድ የተንኮሉ ቀጣየነት ማሳያ እንደሆነ መረዳትየሚያስችል ነው።

ታሳቢ ማደርግ የእይታችንን ሚዛናዊነት ይጠብቅልናል። ለምሳሌ ዛሬም አሜሪካዊ ዜግነትን ለማግኘት ጥያቄ የሚያቀርብ ስደተኛ እንግሊዘኛ፣ ሲቪክ እና የአሜሪካ ታሪክን እንዲማር ይደረጋል። አሜሪካ ተሳስታለች ማላት ነው? የዚህ ጥያቄ መልስ ቦታንና የሃገሪቱን ሁኔታ ከታሪክ ጋር አዛምዶ በማገናዘብ የሚገኝ ነው።

የበዳጥ ተበዳይ ታሪክና የዛሬ ሃውልታችን ፖለቲካዊ አንድምታ

ዛሬ ሃውልታችን በሚል ርዕስ ልጽፍ የወደድኩት አወዛጋቢ ስለሆነችው ስለአኖሌ ሃውልት ትንሽ ለማለት ነው። ይህም ሃውልቱ በአንድም በሌላም መልኩ ከአማና ኦሮሞ ህዝቦች ጋር ትስስር ያለው እንዲሆን ታልሞ የተሰራ በመሆኑ ነው። የአኖሌ ሃውልት በ2006 ዓ.ም. በመንግስት ተገንበቶ ቆሞ ለጉብኝት በቅቷል። ባህላዊ ሙዚየምንም የያዘ ነው። አኖሌ ሄጦሳ በምትባል የአርሲ አካባቢ ከአሰላ 25 ኪሎ ሜትር በስተሰሜን የሚገኝ ሃውልት ሲሆን ሃውልቱ የተተከለበት ቦታ የምኒልክ ሰራዊት ከአካአካባቢው ኦሮሞዎች ጋር እ.ኤ.አ. 1886 ከፍተኛው ፍልሚያ ያደረገበትና ብዙዎች የተሰውበት ቦታ ነው።

የኢህአዴግ አመራሮች ለህዝብ ያበረከቱት ታሪካዊ ስጦታ መሆኑን በመንግስት ሚዲያዎች ሲያስነገሩ ጉዳዩ ያገባናል የሚሉ የኦሮሞ ምሁራንም በአኖሌ ሃውልት እንድምታና አስፈላጊነት ላይ የተለያየ አቋም በመያዝ ይጽፋሉ። ለምሳሌ የአኖሌ ጡት እና እጅ ቆረጣ (Harma fi Harka Muraa Aannolee) መሆኑንና የአርሲ ኦሮሞ ትግልን የሚያሳይ እንዲሁም የኦሮሞ ሰማዕታት መታሰቢያ መሆኑን ከፕሮፌሰር አባስ ገነሞ ጽሁፍ እንደረዳለን።

በተቃራኒው ሃውልቱ የዘላቂ እርቅና ሰላም መሰረት በመጣል መንግስት አሳካዋለሁ ለሚለው የዘላቂ ልማት ግብ ከማሻግርና ሁሉም ኢትዮጵያዊ ለአንድ አላማ እንዲሰናዳ መደላድል ከመፍጠር ይልቅ ለቁዘማ ብርቱ ማስታወሻ እንደሚሆን የታሪክ ተመራማሪዎችና የፖለቲካ ልሂቃኖች ስጋታቸውን ሲሰነዘሩ ይደመጣሉ። ለአብነት ያህል ጠቅላይ ሚኒስተር ሃይለማሪም ደሳለኝ ከህዳር 2008 ዓ.ም. ጀምር ለጋለውና ፋታ ለነሳቸው የኦሮሚያ ህዝባዊ አመጽ ምሁራኖችን ሰብስበው ሲያወያዩ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ ለመወቃቀስ የታለመ፣ እርቀንና አብሮነትን የማያበስሩ ሃውልት እንደተሰራ በማመልከት የመንግስትን አካሄድ ሊፈተሽ ስለመገባቱ ጠቁመዋል። ፕሮፌሰር መስፍን ሃውልቱ የቂም ማንጸባረቂያና የመክሸፍ መገለጫ መሆኑን አዳፍኔ በተሰኘው መጽሃፋቸው ገጽ 25 ላይ "እኛ ወደ ፊት በመራመድ ፋንታ ወደ ኋላ ሄደን ለቂማችን በሃያ ሚሊዮን ብር ሃውልት እንደሰራለን፤የማህበረሰቡን ሁለንተናዊና ጠቅላላ መክሸፍ ብቻ ሳይሆን ወደፊትም አብረን ለመራመድ የማንችል መሆናችንን

የሚያመላክት ነው፤ወደ እርቅ ለመምጣት መንፈሳዊ ወኔ የለንም…" ሲሉ ገልጸዋል፡፡ ፕሮፌሰሩ ስርዓቱን ለ26 አመታት መርምረውት ተስፋ በመቁረጥ ይህን ሃሳብ ሊሰነዝሩ ተገደዋል፡፡

ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳም የጡት ቆረጣ ትረካን (saga) ከማይቀበሉ ወገን ሆነው ስለ ዳግማዊ ምኒልክ ምህረት አድራጊነት አብዝተው ጽፈዋል፡፡ በጽሁፋቸውም "ምኒልክ ጡት ቆርተዋል/አስቆርጠዋል/ ብሎ መፈረጅ አግባብነት የሌለው ትንሽ የፖለቲካ ጠቀሜታ ለማግኘት የሚነዛ ርካሽ ፕሮፓጋንዳ ነው" ይሉናል፡፡ ስለዚህ ጉዳይ እውነታነው ያሉትን ሲያብራሩ "ምኒልክ ጡት ቆርጠዋል ብለው ለማስጠላት ሃውልት ያቆሙ አካለት በድርጊታቸው ማፈርና ያንን አሳፋሪ ሃውልትም ማፍረስ ይገባቸዋል፤ ምኒልክ በግላቸው እንደዚያ አይነት ተግባር ጨርሶ አይፈጽሙም፤ ከወታደሮቻቸው አንዱ ቀደም ሲል የተፈጸመ በደልን ለመበቀል ፈጽሞ ከሆነ መወቀስ ያለበት ጥፋተኛው ወታደር ነው እምጂ ምኒልክ አይደለም ሲሉ ጽፈዋል፡፡

ፕሮፌሰር ፍቅሬ መጨረሻ ላይ ወታደሩ መጠየቅ ይገባዋል ያሉት ሃሳብ አንድ የመከላከያ ሰራዊት አባል ያጫወተኝን አስታወሰኝ፡፡ ታሪኩ እንዲህ ነው፡- በአንድ ወቅት በኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ግንባር (ኦብነግ) በኢትዮጵያ ሶማሊ ክልል በተሰማራ የመከላከያ ሰራዊት ላይ ተደጋጋሚ ድንገተኛ ጥቃት እየፈጸሙ አለባበሳቸውን በመቀይር ማህበራሰቡ ውስጥ በመደብቅ አስቸገሩ፡፡ ያኔ በሁኔታው የተበሳጨ ወታደሮች መላ ዘጠዱ፡፡ ጫትና ሌሎች ማህበራዊ ስብስቦች ላይ ካገኟው ሰዎች በአንዱ ላይ እርምጃ መውሰድ ሲጀምሩ ከመሃላቸው የተደበቀን የኦብነግ ታጣቂን አጋልጠው መስጠት ጀመሩ፡፡ በዚህ የተነሳ የመከላከያ አዛገሮች ጭመር ሳያውቁ መሰል እርምጃ ለበርካታ ጊዜ እንደተወሰደም ነግሮኛል፡፡ በዚህ መሃል የሰብአዊ መብት ረገጣ ተከናወነ፡፡ በመንግስትም ትዕዛዝ እውቅና የተወሰዱ የሃይል እርምጃዎችን ነበሩ፡፡ ከነዚ በመነሳት የሰብአዊ መብት ረገጣ ተፈጸመ በሚል የተለያዩ የሰብአዊ መብት ተሟጋች የኢትዮጵያን መንግስት መክሰሳቸው ይታወቃል፡፡ ሆኖም ተቋማቱ በመንግስት ስርዓት የማይፈቀድ ተግባር ጭምር በወታደሮች መከናወኑም አውስተዋል፡፡ እንግዲህ መንግስት ይህን መሰል ክስ ከመነሳቱ በፊትም ሆነ በኋላ ጉዳይን ማጣራትና አላስፈላጊ ኢሰብኣዊ ድርጊት ፈጻሚዎች ወታደሮቹን መቅጣት እንዳለበት ይታወቃል፡፡ ይህንን ካላደረገ ስርዓቱ ጭምር ተጠያቂ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ግን ስርዓት ሲቀየር የብሄር ገጽታ ሰጥቶ የጥላቻ ቀስቃሽ ሃውል ሊሰራለት ምንም መሰረት የለም፡፡

በዚሁ ልክ የሚኒልክ ሰራዊት አባላት በደመፍሉነት አሊያም በበቀል በአርሲ ጡትና እጅና ቆርጠው ከሆነ የንጉሱ አስተዳደር እርምጃ ሊወስድባቸው ይገባ ነበር። ይህን ስል አልተወሰደባቸውምን ለማለት አይደለም። የህግ አግባብነትን ለመጠቆም እንጂ። ተወስዶባቸው ይሆን? ይህን ካላደረገ የንጉሱ አስተዳደር የኢሰብኣዊ ድርጊቱ ተባባሪ ተደርጎ መታሰቡ አይቀሬ ነው። ዋናው ጉዳይ ግን በዚያን የመረጃ ልውውጡ እምብዛም በነበረበት ዘመን ንጉስ ስለጡት ቆረጣውና በሰራዊቱ አባላት ስለተደረገችው ዝርዝር ተግባር የማወቅ እድል ነበራውን? ስለጉዳዩ ግንዛቤ ከነበራቸው ምን እርምጃ ወስደው ነበር የሚለውን ጥያቄ? ማንሳቱና በጥናት ማረጋገጡ የድርጊቱን ሰርዓታዊ መሆን ወይም ያለመሆን ለመረዳት ያስችል ነበር።

የሃውልቱ አሰቃቂ ቅርጽ ይዞ መገንባት በጤና ችግር፣ በድህነት፣ በመንገድና ትራንስፖርት እጥረት ለሚሰቃየው የኦሮሞ ህዝብ የሚሰጠው ጥቅምን ሲመዘን ለተራው ህዝብ ከሚኖረው አወንታዊ ፋይዳው ይልቅ በተበደልን ስሜት ጫፍ የረገጠ የብሄረተኝነት አቋም የያዙ ፖለቲከኞችን የሚያፍነከንክ ነው። በተቀናቃኝነት የተሰለፉ ውስን የኦሮሞ-አማራ ልሂቃኖችን ማካረር እና ወጣቱ ትውልድ ቀደም ሲል ሲቀነቀለት የነበረውን የነፍጠኛውን የገዳይነት ታሪክ የጡት ቆራጨነት የጭካኔ ድርጊት እንደአዲስ አውጠንትንልኝ የሚል መልዕክት አለው። ሃውልቱ እንዲቆም ያስቻለው ዋነኛ ምክንያት ከፋፍሎ ለማዳከምና ለመግዛት ብዙ አገልግሎት ስትሰጥ የነበረችው የብሄር ፖለቲካ ቀዝቀዝ እያለች መምጣቷ አይቀሬ መሆኑን የሚያመላክቱ በወጣቱ ትውልድ የሚነሱ ጥያቀዎች መከሰታቸው ነው የሚል ግምት አለኝ። የሃወልቱ መሰራት የተቀዛቀዘውን የመወቃቀስ ስሜት እንደ አዳዲስ በማነሳሳትና ቁጭት በመፍጠር የተደራጀ በሃገራዊ ፍትህ ላይ የሚያተኩር ጥያቄን በማዳከም ፈታ ማገኝት ያስችላል። በሚፈጠረው ቁጭት ምክንያት ዘላቂ እርቅና በመተባበር ለጋራ ፍትህ የመታገሉ ተግባር ለጊዘውም ቢሆን ይዳፈናል። እነዚህንና መሰል ፖለቲካዊ አላማዎች የሚያስፈጽም በመሆኑ ይመስለኛ ፕሮፌሰር ፍቅር አሳፋሪ ነው እንዲሉ ያደፋፈራቸው።

በድሃ ሃገር በተለይም በኢትዮጵያ የታሪክ ምርምሮችን የሚያግዝ ገለልተኛ አካል የማይገኝ ከመሆኑ በተጨማሪ የሙያው ብቃት ባለቤት የሆኑ የታሪክ ተመራማሪዎች በመታጣቱ ጻሀፊያን የህዝብን ሃብት የተቆጣጠሩ ንጉሶችን የሚያስደስት ታሪክ ሲከሽኑ ቆይተዋል። ይህ ነገስታትን የሚያስፈነድቅ ታሪክ የመከሸን አባዜ ጡት እንደተጣባን ዘልቋል። የትላምትናውን በተመለከተ በዕውቀቱ ስዩም (2008 ዓ.ም.) እንደሚለው “አሁን ሳስበው ላለፉት ሁለት አስርት አመታት ታሪክ መጻፍ ማለት የበደለኝነትን ስሜት ማሸከም ማለት ሆኗል”። የሃውልቱ ጉዳይ

ከዚሁ ጋር የሚያያዝበት ሁኔታ አለ፤ ይህም “ያለፈውን ዘመን ተቀብለን ካለፈው ተምረን የተሻለ የጋራ ቤት መስራትን” የጋራ ግብ ካለማድረግ የሚመነጭ ነው። ዛሬ ላይ የተቆረጠ ጡት ምስሉ መገተር የዳግማዊ ምኒልክን ምህረት አድራጊነት፣ የራስ ገዝነትን ስርዓት የማስፈን ታሪክ አደብዝዞ የጨፍጫፊነት ታሪክ ነዝናኝር ስሜት በመፍጠር ቁዘማን የሚቀሰቅስ በመሆኑ ላይ የጋራ መግባባትን ለመገንባት መደላድል የሚፈጥር ስላለመሆኑ ለመናገር የሚስችሉ ብዙ ምክንያቶች አሉ። እንደ አውነቱ ከሆነ አጼ ምኒልክ ደም መፋሰስ እናስቀር ብለው ንጉስ ጦናን መለመናቸውን እና አሻፈረኝ ብሎ ያለ የሌለ ሃይሉን በመጠቀም ተፋለሚቸው ሲያበቃ ተሸንፎ ከተማረከ በኋላ በበቀል ስሜት የማይበገሩት ንጉስ ጦናን መልሰው በዙፋኑ ማስቀመጣቸውን ማስታወስ የንጉስን ልዕልና በወጉ መገንዘብ ያስችላል። ይህ ታሪካዊ ኩነት ጦር በመዘዙ ሌሎች የአካባቢ ንጉሶችም ላይ የተፈጸመ እንደነበረ ከታሪክ እንረዳለን። “ምኒልክ ተበቃይ ያመበሆናቸውን፤ ይቅር ባይ፣ በተጨባጭ እውነታ የተመሰረት ምክንያታዊ አስተሳሰብ የነበራቸው እና እራሳቸውን እንደጥሩ ክርስቲያን የሚያዩ ሰው ነበሩ” በማለት ሙያዊ አስተያየታቸውን ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ በ2008 ዓ.ም. ባሳተሙት መጽሃፍ ገልጸዋል።

በሌላ በኩል ችግሮች እንዳሉ ሆነው የንጉሱን የአስተሳሰብ ነጻ አውጪነት ግን የማይዘነጋ ነው። የነጻ አውጪነት ስብዕናን ስናነሳ የቀድ ጭቆናን መፈተሽ ስለሚስፈልግ ትንሽ ላውራ። የጎማ ኦሮሞ ባላባት አስተዳደር ዘመን ጥፋተኞች እጃቸውን፣ አፍንጫቸውንና ጆሮአቸውን ይቆረጡ እንደነበር እና አይናቸው በጋለ ብረት እንደሚፈርጥ ሃሪስ የተባለ ጸሀፊ “Ethiopian Highlands” በተሰኘ መጽሃፉ የገለጸውን ዋቢ አድርጎ በዕውቀቱ ስዩም ጽፏል። በባሪያ ፍንገላ በኩል ግን ከልካይ ፖሊሲ ባለማውጣቱ የነበረውን የባሪ ፈንጋይ ስርዓት በማሰቀጠሉ ለተወቃሽነትን አትርፏል። በምኒልክ ዘመን አመጸኞችም ሆኑ ሌቦት በቅጣት እጅና እግራቸውን የመቁረጥ ተግባር ልቀረ ቢሆንም ቀድሞ የነበረው የባላቶች የእብሪት ቅጣቶችን ማስቀረቱ የሚያስረዱ መረጃዎች አሉ። ጉዳዩ እንደልምድ የተወሰደ በመሆኑ አዋጁ ስኬታማ ስላለመሆኑ የታሪክ ጸሃፊዎች የሚዘግቡት እንዳለ ሆኖ በኦሮሞ፣በአማራ በትግራይ፣ በከፋ፣በአፋር እና በሌላ አካባቢ ወታደሮች የሚፈጸም የመስለብ ባህል በአዋጅ ከልክሏል። እንገዲህ የመራቢያ አካልን መስለብን በአዋጅ የከለከለን መሪ እጅግ አሰቃቂ የሆነ ጡት ቆረጣ ይፈቅዳል የሚል መነሻ የለም።

ያም ሆነ ይህ የበዳይ ተበዳይ ታሪክ ፍለጋ ላይ ባለማተኮር “ያለፈውን ዘመን ተቀብለን ካለፈው ተምረን የተሻለ የጋራ ቤት መስራት እንችናለን” የሚል አስተሳሰብ ማጎልበቱ ለሁላችንም

የተሸለ አማራጭ ነው። ኢትዮጵያ የጋራ መሆን የምትችለውም የጋራ መድረክ አበጅተን የጋራ አርማና የጋራ ግባችንን የሚያሳልጥ ሃውልት በክብር ስናቆም ነው ከሚል እምነት በመነሳት የነገ ሃውልቶቻችን ገጽታላ እንድምታ አወንታዊ እንዲሆን ማሰብ ይገባናል።

"የአማራ-ኦሮሞ ልዒቃን የሚጋጩ አልሞች"?

ደክተር መሬራ ጉዲና በ2008 ዓ.ም. ባሳተሙት መጽሃፍ የሃገሪቱ የፖለቲካ ሜዳ በዋነኝነት ስልጣን በያዘው በትግራይ ልዒቃን በሚመራው የኢሕአዴግ ቡድን በዋናዎቹ *ተቀናቃኝ የኦሮሞና አማራ ልዒቃን*፤ ከዲሞክራሲ ፍልስፍና ጸጋ ጋር ብዙ ጠብ በሌላቸው ከደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች በወጡ ልዒቃን የተያዘ ነው ይላሉ።

በዚህ ክፍል ትኩረት የተደረገው የአማራና የኦሮሞ ልዒቃንን በሚመለከቱ ነጥቦች ላይ ነው። ጉዳዩ እንዲህ ነው። በተቀናቃኝነት ጎራ የሚፈረጁት የኦሮሞና የአማራ ልዒቃን በሁለት ጎራ የሚከፈሉ ናቸው። እነዚህም በአንድ በኩል እስካሁን ድሰረስ ቅድሚያ ኦሮሞነት (ኦሮሞ ፈርስት) በሚል የሚንቀሳቀሰው የችግሮች ሁሉ መነሻ የኣማራ ልዒቃንን አድርጎ የሚፈርጅ ቡድን በሌላ በኩል ኢትዮጵያዊነት ከኛ በላይ ላሳር የሚሉና በመንግስቱ ሃይለማሪያም ስንብት ዋዜማ ጀምሮ በተለያዩ ክልሎች አማራነት ለጥቃት ይጋልጥ በነበረ ጊዜ በደረሰ መጠነሰ ሰፊ ጸረ- አማራ ጥቃት ሰለባ የነበሩ የአማራ ልዒቃን የሚያራምዱት የገመድ ጉተታ ትንቅንቅ ነው። በሁለተኛ ደረጃ በገዢው ፓርቲ ውስጥ የስልጣን ሽሚያን እና ባለመተማመን ላይ የተመሰረተ መቧደን (የግንባር ምስረታውን ለማለት ነው) ባስከተለው ጣጣ የተቃናቃኝነቱ ኩነት ለወሬ የሚበቃ ሆኖ እናገኘዋለን ነው። ይህ እውነት ወይም የሁለቱ ልዒቃኖች ጽንፍ ለጽንፍ በመሰለፍ ባለመተማመን የተቀናቃኝነት ፖለቲካ ማራመድ የወደፊት የሃገሪቱን ፖለቲካዊ አንድነት የሚጎዳ መሆኑ መረዳት የፖለቲካ እውቀት የሚጠይቅ ጉዳይ አይደለም።

በተቃራነው ለስልጣን የማይስገበገቡ የኦሮሞና የአማራ ልዒቃን ሃገራዊ የፓርቲካ ድርጅቶችን መስርተው የሚሰሩ/የሰሩ/፣ ተቀናቃኝነትን በመተባበር የሚተካ አስተሳሰብ የሚያራምዱ ጥናታዊ ጽሁፎችን የሚያበረክቱ፣ የሁለቱን ብሄረሰቦች ማህበራዊ ትስስር በተግባር የሚያጠናክሩ ከሁለቱም ብሄረሰቦች የተገኙ ልዒቃንን ዘርዝሮ መጨረስ ያለመቻሉም ሌላ ሃቅ ነው። ዋናው ጉዳይ መንግስታዊ ስርዓቱ በሁለቱ ብሄረሰቦች እርቅ ላይ የተመሰረተ የፖለቲካዊ አካሄድን ለማጠናከር የሚያስችል ሁኔታ አለው ወይ? የሚለውን ጥያቄ በመመለስ ላይ ነው።

በተጨማሪም ተመስርቶ ቢገኝ እንኳን በጎሪጥ ከመታየት እና በአፍራሽ ተግባር ከመጎንተል ይድናል ወይ ብሎ ለሚጠይቅ ተቆርቋሪ ዶ/ር መራራ ጉዲናም ሆኑ ሌሎች የሳቸውን አይነት ሃሳብ የሚሰነዝሩ ሊሂቃኖች ሊሰጡ የሚችሉት መልስ ሳይንሳዊ ምርምር የሚጠይቅ አይደለም። ምክንያቱ የትብብር ፖለቲካዊ መንፈስ እንዳይታይ ስርዓቱ በትኩረት አየሰራ መሆኑን የተደበቀ ሚስጥር አይደለምና ነው።

የወደፊቱን ሁኔታ ለመተንበይም የመንግስታዊ መዋቅርና አደረጃጀት እንዲሁም በተግባር እየተከናወኑ ያሉ ተግባራዊ እርምጃዎች ቀጣይነት ያለው እርቅን በሁለቱ ልሂቃን እና ብሄረሰቦች መካከል የሚያሰፍን ነውን ብሎ ለሚጠይቅም መልሱ ቀላል ነው። ይህንና ሌሎች መሰል ጥያቄዎችን ለመመለስ የአዲስ አበባን ጉዳይና የኢሕዴግን ፖለቲካዊ ስልት፣ ኢሕአዴግ በብሄራዊ ፓርቲዎች ሲፈተን የሚከተለውን የፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ እና የአኖሌን ሃውልት ፖለቲካዊ አንድምታ መፈተሽ ብቻ በቂ ይሆናል (ከታች በሰፊው ተዳሷል)።

ኢትዮጵያን ከነባህር በሯ ለመመስረትና ጠብቆ ለማቆየት የአማራና ሌሎች ህዝቦት ፍልሚያ ላይ እያሉ የኦሮሞ ልጆችም የላቀ ድርሻ እንደነበራቸው ሁሉ የዛሬዋን ኢትዮጵያንም በጋራ እንመስርት በማለት ጉትጎታ የሚያቀርቡ የአማራ ልሂቃን ሲኖሩ በተቃራኒው እትዮጵያ ምኔም አይደለችም በሚል የኦሮሞን ሃገር በኦሮሚያ ምድር መመስረትን የፖለቲካ መስመራቸው ማጠንጠኛያ ያደረጉ የኦሮሞ ልሂቃን አሉ። በነዚህኞቹ ልሂቃን (በአማራ-ኦሮሞ ለማለት ነው) መካከል ያለውን ልዩነት ጫፍና መሃል የተቀመጡ ልሂቃኖች መኖርን የሚረጋግጥ እና በሁለት ጽንፍ ላይ የተሰለፉ ልሂቃኖች አሉ የሚለውን አገላለጽ ውሃ የሚቋጥር ያለመሆኑን የሚያሳይ ነው።

በሌላ በኩል ከአንዳንድ የዲያስፖራ የኦሮሞ አክሪቪስቶችና ከሃገር ውስጥ ምሁራን የሁለቱ ብሄሮች ልሂቃን የተራራቀ ህልም በመያዝ የገመድ ጉተታ ፖለቲካ ውስጥ እንደገቡ አስተያየት ሲሰነዝሩ እሰማለሁ። ከዲስፖራው አስተያየት ሰጪዎች ስሙ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ተጽዕኖ ፈጣሪነትና በጨዋታ ቀያሪነቱ (Game Changer) እየተጠቀሰ ያለውን ጆዋር መሃመድን ብንወስድ የአማራና ኦሮሞ ልሂቃን ጫፍ ለጫፍ በመሰለፍና አስታራቂ መንገድ ባለመምረጣቸው በሃገሪቱ የፖለቲካ ሂደቱ እየተበላሸ እንዲመጣና መስፈን የነበረበት የብዙሃን መንግስት ቀርቶ የጥቂቶች አገዛዝ እንዲዘረጋ አስችሏል ሲል ቆይቷል። የኦሮሞ ፈርስት አቀንቃኝነትና የአማራ ልሂቃንን የታሪክ ተወቃሽም የሚያደረጉ ንግግሮች ያደርግም ነበር። ጎላ ላይ ትንሽ የመለዘብ አዝማሚያ በማሳየት በ2008 ዓ.ም. “የአማራና ኦሮሞ ልሂቃንና

ምሁራኖች ራሳችን መታረቅ እንችላለን በማለት"፤ በሃገር ውስጥ የሁለቱ ህዝቦች የጀመሩትን ህብረት (solidarity) እና በጋራ ተናቦ የመታገል እንቅስቃሴ እንደሚደግፍ በኦሮሞ ሚዲያ ኔት-ወርክ መግለጹ እንደለ የሚታወስም ነው።

ከሃገር ውስጥ ተመሳሳይ ሃሳብ ከሚያቀነቅኑ ልሂቃን ዶ/መሬራ ጉዲናና አቶ ቡልቻ ደመቅሳን መጥቀስ ይቻላል። ደ/ር መሬራ ጉዲና በ2008 ዓ.ም. ባሳተሙት "የኢትዮጵያ የታሪክ ፈተናዎች እናየሚጋጩ ህልሞች---" በተሰኘ መጽሃፋቸው በትንተናዊ ማስረጃ አስረግጠውልናል። ከዲያስፖራ የኦሮሞ እና የአማራ ልሂቃል ብሄራዊ/ሃገራዊ/ አስተሳሰብን በሚጻረር አንዳንዱም በሚገነባ መልኩ በሚሰጣቸው አስተያየቶች የሁለቱ ልሂቃን በተራራቀ ጽንፍ ላይ በመሆናቸው አንዱ አንዱን እየወቀሰ ባለመተባበር ሃገሪቱ በጨቋና እንድትቆይ ምክንያት ሆኗል በማለት ሃሳብ ይሰነዝራል። የብሄር ጭቆና መኖሩ በታሪካዊ መስረጃዎች ማስደገፍ የማይቻልበት ሁኔታ እያለ ከልሂቃን "የሚጋጩ ህልሞች" ተዋስዖ ወጣ ባለ መልኩ "አማራ ህዝብ ቀደም ሲል ለተፈጸሙ በደሎች ይቅርታ ቢጠይቅ በሁለቱ ህዝቦች መካከል እርቁ የተሳካ ይሆን ነበር የሚሉ ጥቂት የኦሮሞ ልሂቃን አሉ(ይህኛው ታሪክን ካለመረዳት ችግርና የበዳይ ተበዳይ ትረካ እስረኛ ከመሆን የሚመነጭ ነው)።

እንደሚታወቀው በሃገሪቱ ሃገራዊ የፖለቲካ አደረጃጀት ውስጥ ግንባር ቀደም የሆኑ የኦሮሞ ልሂቃኖች መኖራቸውን የሚዘነጋ ባይሆንም የኦሮሞ ልሂቃን ኢህአዴግ የከፈተውን የብሄር አደረጃጀት ዘው ብለው ከገቡ ልሂቃኖች ግንባር ቀደም ናቸው። ለአብነት በ2007 ዓ.ም. ሃገራዊ ምርጫ ስምንት "የኦሮሞ ፓርቲዎች"[34] ህጋዊ እውቅና አግኝተው በምርጫው ተሳታፊ ሆነዋል። ይህ አሃዝ በውጪ ሃገር ያሉትን የኦሮሞ ፖለቲካዊ ድርጅቶች አያካትትም። በአማራ ልሂቃብ የተደራጀ የፖለቲካ ቡድንን በተመለከተ በሃገር ውስጥ ከገቢው ፓርቲ ውጪ አንድ ፓርቲ ብቻ ነው ያለው (የመላው አማራ ህዝብ ድርጀት የሚሰኝ ፓርቲ)። ይህ ብቻ አይደለም የኦሮሞ ልሂቃን በቢዝነሱም በኩል ኦሮሞነትን የሚያመላክቱ ተቋማትን የመመስረት ዝንባሌና ተጨማጭ ተግባራትን ያከናውናሉ። በቃራኒው ከ1983 ዓ.ም. የኢህአዴግ ስርዓት ለአማራው የሚጎራብጥ በመሆኑ የአማራ ብሄርተኝነት ቡቃያዎች ዛሬ ላይ እየተስተዋለ ቢሆንም በአማራው ልሂቃን በኩል ያለው ጽንፈኝነት የብሄር አደረጃጀትን ያለመቀበልና የብሄር ድርጅቶችን የማጣጣል አቋም ነበር። ካለፉት ሁለት አስርት አመታት በፊት የኦነግ አሰቃቂ

[34]የሃገር ውስጥ የኦሮሞ ፖለቲካዊ ድርጅቶች፡ የኦሮሞ ብሄራዊ ኮንግረስ፤ የኦሮሞ ነጻነት አድነት ግንባር፤ የኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጀት፤ የኦሮሞ አቦ ነጻነት ግንባር፤ የኦሮሚያ ነጻነት ብሄራዊ ፓርቲ፤የመላው ኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲዊ ፓርቲ፤ ገዳ ስርዓት አራማጅ ፓርቲ፤ ኦሮሞ ፌደራላዊ ኮንግረስ...

ግድዎች ሰለባ የነበሩ እና ኦህዴድም በሕወሓት ልሳን እየተናገረ የአማራን ህዝብ የበዳይነት ታሪክ ከቅኝ ገዢዎች ጋር በማመሳሰል የአማራ ህዝብ የጥቃት ኢላማ መሆኑን ያስተዋሉ እንዲሁም ልሂቃኖቹ እንዲሸማቀቁ መጠነሰፊ ፍረጃዎች ሲሰነዘሩ እማኝ የነበሩ የአማራ ልሂቃን የብሄር አደረጃጀት ባላቸው የኦሮሞ ቡድኖች ላይ እምነት ያጡበት ሁኔታ እንዳለ ይነገራል፡፡

የአማራ የኢኮኖሚ ልሂቃንም በብሄር ስም የሚሰየም ኢኮኖሚ ተቋማትን የመመስረት ልምድ የላቸውም፡፡ ከላይ ያስቀመጥኳቸው ማሳያዎች በልሂቃኑ መካከል ያለውን የፍላጎትና አደረጃጀት መስመር ልዩነት ለማመልከት ነው፡፡ በጓዳኝ የሁለቱ ልሂቃን የአደረጃጀት መስመር ልዩነቱ የሀገር ግንባታው መስመር ምን መምሰል እንዳለበት የሚያመላክት መሆኑን ለመጠቆም በማለም ነው፡፡ ልዩነቶቹ ችግር ያላው ናቸው ወይም ባለመጣጣማቸው ሃገራዊ አንድነትን ይጎዳሉ የሚል አቋም ለመያዝ የሚስችሉ አይደሉም፡፡

ለልዩነቶቹ ወይም በመረራ ገለጻ “ለሚጋጩ ህልሞች” መነሻቸው ሁለት አይነት አስተሳሰቦች ናቸው፡፡ አንደኛ ባለፈው የበዳይ ተበዳይ ታሪክ ላይ መጭጭ በማለት ቁዘማን የሚመርጡ ልሂቃን አመለካከት ሲሆን ይህም በዕውቀቱ ስዩም እንደሚለው “ያለፈውን ዘመን ተቀብለን ካለፈው ተምረን የተሻለ የጋራ ቤት መስራት እንችላለን” የሚል አስተሳሰብ ካለመያዛቸው የሚመነጭ ነው፡፡ በዕውቀቱ ስዩም የዚህ አስተሳሰብ ባለቤት የሆኑትን ልሂቃን “ታሪክ ቁርጭምጪሚታቸው ላይ እንደታሰረ አለሎ የሚከብድባቸው የዘመናችን ደረቅ ብሄርተኞች ናቸው” ሲል ይገልጻቸዋል፡፡ እነዚህ አካላት የኤርትራን ፈለግ በመከተል መገንጠልን እንደአማራጭ የሚያቀርቡም ናቸው፡፡ ሁለተኛው አስተሳሰብ ማንናውንም የፖለቲካና የማህበራዊ መስመር ለመዘርጋት የብሄርን ጉዳይ አታንሱብን፣ ስለኢትዮጵያ ብቻ እንጻፍ፣ እናውራ፣ እንደራጅ የሚል ነው፡፡ የዚህ አስተሳሰብ አራማጆች የብሄር ጉዳይን የሚያቀነቅኑ አካለትን የማይቀበሉ፣ በኢትዮጵያ መሬት ላይ ያለውን አውነት ተቀብሎ ባለመዋጥ ሁሉንም ነገር ማጠንጠኛ ኢትዮጵዊነት ነው የሚሉ ናቸው፡፡በመጀመሪያው አስተሳሰብ ምናልባትም የኦሮሞ ልሂቃ በርከት ይበሉእንጂ የሶማሊ፣ ጋምቤላ፣ የቤኒሻንጉልና የሌሎች ብሄሮች ልሂቃኖችም አስተሳሰቡን ይጋሩታል፡፡ ሁለኛው አስተሳሰብ በማራመድ የአማራ ሊሂቃን የአንበሳውን ድረሻ ቢወስዱም የኦሮሞ፣ የአፋር፣ የጉራጌ፣ የትግራይ፣ አገው፣ ወዘተ ልሂቃኖችም ይህንን ሃሳብ ተቀብለው የፖለቲካ አደረጃጀቶችን መመስረታቸው የሚታወቅ ነው፡፡

በታሪክ አጋጣሚ ለተከሰቱ ፖለቲካዊ በደሎች ህዝብን እንደህዝብ በደል ፈጻሚ አድርጎ በይቅርታ ጠያቂምነት ይቅረብ ማለት ከስሜታዊነት የጸዳ አስተሳሰብ ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡

ነገር ግን በደሉን የቀድሞው መንግስታዊ ስርዓት ከፈጸመው ዛሬ ላይ ያለውን የሀገሪቱን መንገስት በጥናት ላይ ተመስርቶ ካሳ እንዲሰጥ መጠየቅ ተገቢነት ይኖረዋል። በዚህ መልኩ የመንገስት ስርዓትን ከአንድ ብሄረሰብ ጋር ያለማመሳሰል አስተሳሰብ ማራመድ በልሂቃቦች መካከል የሉ መሰረታዊ ልዩነቶች እንዲቀንሱ ያግዛል። የብሄር ማንነትንም ሆነ ፖለቲካዊ መስመሩን የማጥላላት አቋም ያላቸው ቡድኖችም ሳይወዱ በግድ መሬት ላይ ያለወን ሃቅ ተቀብለው አስታራቂ የትግል ስልት እንዱነድፉ ሁነተኔታው ይጋብዛቸዋል (ጫፍ ጠረገጠና አግላይ ብሄረተኝነትን ግን መታገል ምክንያታዊነት አለው) ።

የዶክተር መሬራ "የሚጋጩ ህልሞች" ህልም ፈቺው ካላዛባቸውና እንደይጣጣሙ የሚታትር የተደነቀረው ስርዓት ከተስተካከለ በልሂቃኖቹ መሃል ያለው ልዩነተ የሚታረቅና ጫላንጪሎችም እየታዩ ናቸው። እናም ዋናው ነገር ወደ መሃል መምጣት ነው። ከላይ ያለውን ሃሳብ የሚያንጸባርቀው ጽሁፋቸው ለንባብ ከበቃ ከአመትና ኦሮሞ እምቢተኝነት በተፋፋመበት በ2009 ዓ.ም. ዶክተር መረራ ጉዲናም በኦሮሞ ጥናቶች ማህበር (OSA) አሜሪካ ላይ ባቀረቡት ጥናት "ሌሎች የሃገሪቱ ክልሎች እንደኦሮሞ የፖለቲካ ቡድኖች የወጣቱንና ህዝቡን የማነቃነቅ ችሎታ ቢኖራቸው ኖሮ ከኦሮሞን ህዝብ ጋር የትግል አንድነት ማደረግ ብቻ ሳይሆን እራሳቸውም ከወልቃይት እስከ ለሱዳን የተሰጠ መሬታቸውን እስከ ፖለቲካዊ ጫናና የወጣት ስራ አጥነት ድረስ የራሳቸውን ጥያቄ አንግበው ትግሉን መቀላቀል ይችሉ ነበር" ብለዋል። ይህ ንግግር በቀጥታ አማራን ልሂቃንናና ህዝብ የሚመለከት የትግል ጥሪና ምክረ ሃሳብ መሆኑ ግልጽ የነበረ ሲሆን ይህ ንግግር ከቀረበ ወዲህ የአማራ ወጣቶች የኦሮሞን ትግል መቀላቀላቸው የሚታወቅ ነው። ይህም ሁኔታው አስገዳጅ ከመሆኑ ዶክተሩ እንደሚሉት "የአማራና የኦሮሞ ልሂቃን የሚጋጩ ህልሞች" በጋራ ትግል ላይ የሚያሳድረው ጫና እመብዛም መሆኑን አስተምሯል። እንዲያውም የልሂቃኑን የፖለቲካ አቋም የፈተሻ፣አስተሳሰባቸውን እንዲያለዝቡ የሚያደርግ "ደምህ ደሜ ነው" የሚሉ ወጣቶች በአደባባይ መፈክር ይዘው የወጡበት የህዝብ መነቃነቅ ሆኖ ነው የታየው። ሆኖም "በእምቢተኝነቱ ወቅት የታየው ትብብር"[35] ትርጉ ሰጪ ስለመሆኑ ጥያቄ የሚያነሱ አልጣጡም።

በግሌ ጅማሮው ውጤታማ እንዲሆን የማስቀጠሉ አደራ በየትኛውም ጽንፍ ላይ የቆሙ የሁለቱ ልሂቃኖች ድርሻ መሆኑን ላሰምርበት እውዳለሁ። በህዝቡ በኩል የትግል አንድነት እየመጣ

[35] During the protests, Oromo and amhara nationalists displayed signs of **solidarity** in the face of what thet believed to be a common enemy: the TPLF. But, there were always questions about the comaraderies and whether it was meaningful and sustaibable (Al Jazzera, 17 january 2017)

ቢሆንም ቅሉ ልሂቃኑ ተቀራርበው በጋራ ከመስራት አንጻር ብዙ የሚቀራቸው መሆኑ ግልጽ ነው። የፌደራሊዝም ስርዓት (በዘውግ ላይ ብቻ የተቀጠረውን ለማለት አይደለም) ዋና አላማውም የሚጋጩ ህልሞችን ወይም የሚራራቁ ፍለጎቶችን ማስታረቅ ነው። ሁለት አይነት ፍላጎት ባይኖር ኖሮ ፌደራሊዝም (Synthesis)[36] ላያስፈልግ ይችል ነበርና ነው።

የነገ ሃውልቶቻችን ገጽታና እንድምታ

በኢትዮጵያ ታሪክ የአንድ መጎሳ መንግስት ወይም የዘር ግንዱንም ከአንድ ብሄር ብሄር ብቻ የሚመዝ ግለሰብ በመሪነት ሃገራቱን ስለማስተዳደሩ በማስረጃ አረጋግጦ የሚከራከር የሚኖር አይመስለኝም። የዘመናዊ ኢትዮጵያን መሪዎች ብንመለከት አጼ ቴወድሮስን፣አጼ የሃንስ አራተኛ፣ ዳግማዊ ምኒልክ፣ አጼ ኀለይለስላሴ እንዲሁም የመንግስቱ ሃይለማሪምን የዘር ግንድ መቁጥር የሚሞክር ካለ ከአጼ ዮሃንስ አራተኛ ውጪ ሁሉም ከተለያዩ ብሄረሰቦች አብራክ የተገኙ ናቸው። ሃቁ ይህ ሆኖ ሳለ የሸዋ አማራን ከታሪክ ግድፈቶች ጋር በማስተሳሰር እርስ በርሳችን የመወቃቀስን ስራ እንድንገፋበት መደረጉ በራሱ ከተዛባ ታሪካዊ ግንዛቤ የሚነሳ ወይም ፖለቲካዊ ብስለት ካለመላበስ የሚመነጭ አሊያም በጊዜያዊነት ስርዓቱን ለማቆየት (Regime survival) የተፈየደ ዘዴ መሆኑን ብዙ የፖለቲካ ልሂቃኖች የሚጋሩት ጉዳይ ነው።

ታሪክን በማስታወስ እንዳንዴም በትንሽ አውነተኛ ታሪክ ላይ በመንጠላጠል በማህበረሰብ ውስጥ የበዳይ ተበዳይነት ስሜትን አጪረው የሚያነቋቁሩ አሃውልቶችን መገንባት የሚቻልባቸውን ብዙ ታሪካዊ እውነታዎችን መጥቀስ ይቻላል። እንደአናሌ አይነት ለማለት ነው። አንድ እንበል- በአህመድ ግራኝ ሰራዊ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን አማኞችንና መንፈሳዊ አባቶን መጨፍጨፍ፣ የወደሙ መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ሃብቶችን ለማሰብ የሆነ የሰውነት አካላቸው የተቆረጡ መስቀል የያዙ ቀሳውስት መነኩሳት፣ የተቃጠሉ አብያተ-ክርሲያናት የሚያሳይ ሃውልት፣ የአጼ ዮሃንስን ኢ-ሰብአዊነት የሆነ ሃይማኖት የማስለወጥ ታሪክ ለማሰብ ቁርዓን የሚነጥቁ ወይም የሚያቃጥሉ ወታደሮችን እና በተሸናፊነት የተጎሳቆሉ ሸኪዎችን የሚያሳይ ሃውልት አንጾ ማቆም ይቻላል። ሌላም ልጥቀስ- በጣሊያን ወረራ ወቅት በሰሜን ሸዋ መንዝ ቅያ "አመጸኛ ዋሻ" በሚባል ጥልቅ ዋሻ ውስጥ የተሸሸጉ አርበኞችንና ቤተሰቦቻቸውን ለደምሰስም የጣሊያን ሰራዊት ገደሉ ጫፍ ላይ የመርዝ በርሜል አንጠልጥሎ በመድፍ በመደብደብ ዋሻው ውስጥ ያሉ ህጻናትን ጭምር ረሚም ማድረጉንና ከሞት የተረፉትም አካለ ጎደሎ መሆናቸውን

[36]In the prevalence of two groups of interest named unionst, secessionist, and federalism could be a midleground proposed as a solution Federalism is a synthesis which is conciliation between the thesis (unionist) and ant-thesis (secessionists).

የሚያረጋግጡ ህያው መስክሮች አሉ። ይህን የአመጸኛ ዋሻ እልቂትን “ኢትዮጵያ፡ በጣሊያን ፈሽስቶች የወረራ አመታት በሚል በአልቤርቶ ስባኪ በተባለ ተመራማሪ በ1985 የጻፈው መጽሃፉ አሰረጂ ነው። በህይወት ከሚገኙት የዚያን ጊዜ ሰለባዎች አንዷ አሰገደት በለጠ፣ የእኔ አያት ናት። የእግር ጣቶቿ ጎድለዋ። ይህን ሃቅ ተመርኩዘን መርዝ የሚረጨ የጣሊያን ወታደሮችን በአንድ በኩል፣ የተቆራረጡ ጣቶችን በሌላ በኩል፣ የእኔን አያት ጣት የጎደለው አግር እና ሰውነታቸው በመርዝ የተበጣጠሰ ሰማዕታትን አስቃቂ ምስልን.... የሚሳይ ሀውልት ማነጽ ይቻላል። ግን ይህን ከሚመስሉ ሃዎልቶች ማትረፍ የሚቻለው ጥላቻን እና ቁዘማን ነው። ግን አላደረግንም፤ግፍ በወራሪ ባዕድ ሃገር ተፈጽሞም።

ይህ አይነቱ የሃውልት ገጽታ አመራረጥና አቀራረጽ (በተለይ የአንድ ሃገር ህዝቦችን ለማናቆር የሚያስችል) ከለጊዜያዊ የፖለቲካ ትርፍ ያለፈ ሚና የማይኖረው በመሆኑ የወደፊት ሃውልቶቻችን እንድምታ ከስሜት የጸዳ እና የሩቅ አሳቢ መሪዎች ለህዝባቸው አንድነትና መጻኢ አድል ትረጉም ያለው ስጦታ ሊሆን ይደባዋል። ያ ካልሆነ ሃውልቶቹ በአደባባይ የቆሙ ትርጉም አልባ የአርማታ ክምር ከመሆን አያልፉም።

ወደፊት የሚታነጹ ሀውልቶቻችን ለታሪካዊ ኩነቶች እውቅና ለመስጠት በማለም፣ ጊዜያዊ የፖለቲካ ትርፍ ከማግኘነት የጸዳ እና እውነተኛ ተቆርቋሪነትን የሚያሳይ መታሰቢን በማቆም የሃውልቱ ገጽታና እንድምታ ለተበዳዮች መታሰቢና መጽናኛ ሆኑ ለመጪው ትውልድ አብሮነትና የጋራ ግብ አሉታዊ ውጤት እንዲመጣ መደረጉ የመጨረሻው ግብ ሊሆን ያሻል ነው። ከላይ እንደገለጽኩት የሚያሳቅቅና ከመወቃቀስ ያለፈ ትርጉም በማይሰጥ መልኩ ሃውልት ማነጽ በፖለቲካ ፍላጎት ላይ የተንጠለጠለ ስሜታዊነትን የሚያመለክትና በመሆኑ የጠቀኟቸውን ታሪካዊ ክስተቶችን ለማሰብ አሉታዊ ትርጉም የሚሰጥ ነው። ስለሆነም ዛሬ ላይ ማህበረሰቡ የደረሱበትን በደሎች ሊያካክስለት በሚችልና የወደፊቱን የመፈቃቀር መንፈስ የሚያሳልጥ የመሰረ-ተልማት እንዲሁም የሃውልት መታሰቢዎች ማስቀመጥ ከጤነኛ የፖለቲካ ስርዓትና ከበሳል የስርዓቱ አመራሮች የሚጠበው ነውና ሊታሰብብት ግድ ነው። በተጨማሪም ተረስተው ይሁን ታስቦበት ባላውቅም ብቻ በቂ ማስታወሻ ያልተሰራላቸውን የታሪክ ክስተቶች እንዲህ ቢታወሱ የሚል ሃሳብ አቀርባለሁ። በደርግ ጊዜታዊ ወታደራዊ መንግስት የተጨፈጨፉ ስድሳ ለሚሆኑ የንጉሱ ዘመን ከፍተኛ የሲቪልና እና ወታደራዊ ባለስልጣናትን ለማሰብ “የዲፕሎማሲ ማዕከል”፣ አጼ ን/ስላሴ ላበረከቱት በኢትዮጵያ ታሪክ ወደር ላልተገኘለት የዲፕሎማሲዊ ተጽዕኖ “የዲፕሎማሲና የምርምር ማዕከል”፣ በኢት-ሶማሊያ ጦርነት ለተሰው ኢትዮጵያዊን መታሰቢ

የሚሆን “የህክምና ዩኒቨርሲቲ”፣ በሻቢያና ኢህአዴግ ጸብ የተነሳ በተከሰተው የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ለረገፉ ወታደሮች መታሰቢያ የሚሆን እርቅንና ወንድማማችን የሚሰብክ “ድልድይ”፤ በኢትዮጵያ ታሪክ ፈር ቀዳጁ ሃኪም ለሆኑት ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ “የህክምና የምርምር ተቋም” በአርባ ጉጉና በደኖ በአማራነታቸው ብቻ ለተጨፈጨፉና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ (ከማሸና አሶሳ ዞን) እና ከጉራፈርዳ ለማሰብ በሚከብድ መልኩ ሃብትና ንብታቸውን እየተነጠቁ የተፈናቀሉ ኢትዮጵያዊያን የሚያስብና ማካካሻ የሚሆን “የደን ልማት ወይ የመስኖ እርሻ አሊያም ፋብሪካ…” መገንባት ተገቢነትም ህጋዊነትም የሚኖረው ተግባር ነው።

መጪውን ቤታችንን ለማሳመር ሌላም ብዙ ስራ ይጠብቀናል። በድንበር ይገባናል፣ በሪሶርስ ሽሚያ በአፋር እና ሶማሊ፣ በቦረና ኦሮሞና ገሪ ሶማሊ፣ በጉጂና በኦሮሞ መሃል በሚከሰቱ ግጭቶች የሚሞቱ ሰዎችን ለማሰብ እና ችግሩ ዳግም እንዳይከሰት አስታራቂ የሚሆን የጋራ ስሜያ የሚኖረው የመጠጥ ውሃ (ለእንሰሳም ለሰዎችም) ከትላልቅ ወንዞች ጠልፎ የሚቀርብበት ሰው-ሰራሽ ሃይቅ ማዘጋጀት፣የጋራ የግጦሽ ቦታዎችን በመንግስት ወጪ ማልማትና ቀድሞ በግጨት ውስጥ የነበሩ ብሄረሰቦችን/ህዝቦችን ያማከለ ስያሜ እንዲኖረው ማስቻል በህዝቦቿ መሃል መፈቃቅር የሰፈነባት ሃገር ለመመስረት የጎላ ትርጉም ይኖረዋል።

ከ1996 ዓ.ም. አዲስ አበባ የኦሮሚያ እንድትሆን በመሻት “ፊንፊኔ ኬኛ” በሚል በአደባባይ ከመንግስት ሀይሎች ጋር በመላተማቸው ህይወታቸውን ላጡ፣ የአካል ጉዳትም ለደረሰባቸው ኢትዮጵያዊያንም ስለጥያቄያቸው አግባብነት ማረጋገጫ የተገኘ በመሆኑ መታሰቢ እንደሚስፈልጋቸው እና በ1997 ዓ.ም. ምርጫ ዲሞክራሲያዊ ለውጥ ፍለጋ ሂደት ውስጥ መስዋዕት የሆኑ ኢትዮጵያዊያንም ቢታሰቡና ተገቢው ካሳ ቢደረግ መልካም መሆኑን ከሚከራከሩት ወገን ነኝ። የ2008 እና የ2009 ዓ.ም. በኦሮሞ ምቢተኝነትና በአማራ-ወልቃይት የማንነት ጥያቄ ወቅት የተሰው ሰማዕታት መታሰቢ የማቆሙ ጉዳይና ካሳም ከወደፊት እቅዳችን ውስጥ ሊካተት እንደሚገባው አምናለሁ።

የኢትዮጵያ ስርዓቶችና የወቅቱ የአማራ ህዝብ እምቢተኝነት

የትላንትናዋ እና የዛሬዋ ኢትዮጵያ ለህዝቦቿ ሬት እንደሆነች እና እየሆነች የታላን ወዲያ ኢትዮጵያን የሚያውቁ የትላን ወዲን እንዲናፍቁ በዚህኛው ዘመን እና ከኛ ዘመን 15/20 አመት ቀደም ብለው የመጡ ተውልዶች ሌላ ለውጥ እየናፈቅን፤ የለውጡን መሳሪያ ሁሉ እየፈተሽን እንገኛለን። አሁን እኛ ባለንብት ዘመን ያሉ ችግሮችን አሳሳቢነት፣ ዛሬ ከዱሮው በባሰ መልኩ

መክፋቱን እና የእሮሮ መብዛት የስረዳልኛል ብዬ ባሰብኩት በፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ጽሁፍ ዳሰሳዬን ልጀምር፡፡

> <u>ከትናንት ወዲያ፣ ትናንትና ዛሬ፡</u> ዛሬ ላይ ቆሜ ወደኋላ ሳይ የትናንት ወዲያው ይናፍቀኛል፤ ትናንት ወዲያን አይቼዋለሁ፤ አውቀዋለሁ፤ ትናንትንም አይቼዋለሁ፤አውቀዋለሁ፤ ዛሬንም እያየሁትና እያወቅሁት ነው፤ ከትናንት ወዲያ በጃንሆይ ዘመን የአገዛዙ ነቃፊ ነበርሁ፤ የወደፊቱን የማየት ችሎታ ስለሌለኝ የጃንሆይን አገዛዝ ነቃፊ ነበርሁ፤ በትናንት ወዲያ ላይ በጃንሆይ ዘመን ላይ ቆሜ ዛሬን የማየት ችሎታ ቢኖረኝ የጃንሆይን አገዛዝ ነቃፊ አልሆንምነበር ፤ ትናንትን፣ የደርግን ዘመን ከዛሬው ከወያኔ ዘመን በመሠረቱ እምብዛም የማያለይ በመሆኑ አይናፍቀኝም፤ የዛሬው የወያኔ ዘመን አስመረረኝ፤ ምርር ብሎኛል፤ እንዳልሰደድ ቀዳማዊ ምኒልክ ያለውን ተከታይ ነኝ፤ እንዲህ ብሏል፡-- ‹‹እናቴንና አገሬን እተው ዘንድ አይቻለኝም፤›› እናቴ ‹‹በጡቶቿ አምላኛለችና››፡፡ እናትና አባቴ የኢትዮጵያን ምድር ሆነዋል፤ አባቴ በማይጨው ዘምተው በጥይት ቆስለዋል፤ የመርዙንም ጋዝ በትንሹ ሳንባቸውን ሳይጠብሰው አልቀረም፤ ይቺን እናትና አባቴ አፈር የሆኑላትን አገር ትቼ መሰደዱ ስለማይሆንልኝ እየመረረኝ የመድኃኔ ዓለምን ምሕረት እጠብቃለሁ (መስፍን ወልደ ማርያም፣ ነሐሴ 2008)፡፡

እንደ ፕሮፌሰሩ እድሜ የስጣቸው አናቶች እንዲሁም ዛሬን ከዱሮው የማነጻጸሩ ሙያዊ አቅሙ ያላቸው ምሁራንም ይህን ከላይ የተጠቀሰውን ሃሳብ ይጋራሉ፡፡ ፕሮፌሰሩ ከትላንት ወዲያ እንዳሉ፤ በአጼው ዘመን የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በቡድን ተሰባስበው በየዩኒቨርቲያቸው መንግስትን የሚየጻረር ውይይት የማድረግ መብት ነበራቸው ያደረግ ነበር፣ በየካቲቱ አቢዮት ሰላማዊ ሰልፍ በገፍ የተፈቀድ ነበር፣ በሰለፉ ከጸጥታ ሃይሎች ጋር በሚደረግ ግብግብ ህይወታቸውን ያጡ ዜጎች ቢኖሩም ከደረጉ ዘመን እና ከዛሬው ጋር ማነጻጸር የመይቻል አነስተኛ ቁጥር እንደነበር የሚታወቅ ነው፡፡ ትላንትናና እና ዛሬ ግን በዩንቨርሲቲ ተደራጅቶ ስለስርዓቱ መወያየት እና ሰላማዊ ስልፍ ማድረግ አይደለም ሙከራ ማድረግ አዳጋች ነው፡፡ ፈቃጅ ህጎች በከልካይ መመሪያዎች፣ በስርዓቱ ባለስልጣናት ትዕዛዝ፣ በሰርኩላር ደብዳቤዎች እንዲሻሩ ሆኗል፡፡

በኢትዮጵያ የመንግስታዊ ስርዓት የጭቆናው ደረጃ በደርግ ዘመን (ፕሮፌሰር መስፍን ትላንት ብለው የጠሩት) ጣሪያ የነካ ነበር፡፡ ከሽህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ሶስት ጀምሮ (ዛሬ) ባሉት አመታት ከፍና ዝቅ እያለ ዛሬ ላይ ደረስን፡፡ በህዝብ ላይ የሚፈጸመው ጭካኒያዊ የአደባባይ ጭፍጨፋ ከትላንትናው ጋር ሲነጻ የሚኖረውን ልዩነት ለመግለጸ ጥናት ማድረግ ቢጠይቅም ህዝቡን በቀጥታም በህዝቡ ላይ ጫና ማሳደር በሚችለው በሃገሪቱ ብሄራዊ ጥቅም ላይ የተፈጸመው ክህደት የሽህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ሶስት ያስከተለው ጣጣ መሆኑን የኢትዮጵያን መዳከም የሚፈልጉ ቡድኖች እንኳን የሚመሰክሩት ነው፡፡ ስርዓቱ ጣጣ በጣጣ ሆኖ የጭቆና ታሪክ የተጠናወተውን ህዝብንም ጣጣ በጣጣ እያደረገው 27 አመታት ቆይተን ዛሬም ለመሸከም

የሚያዳግት ከጣጣ በላይ ጣጣ ልንጋፈጥ በቅተናል። እንግዲህ የፕሮፌሰሩ ገለጻ የንጉሱን ስርዓት በአንጻረዊነት የሚሻል መሆኑን ያሳብቃል። ሆኖም ትላንትን (የደርግን ስርዓት) እና ዛሬን (የኢህአዴግን ሰርዓት ለማለት ነው) የሚመርጡ ልሂቃኖች መኖራቸው የማይካድ ነው። ለአብነት በሶስቱም ስርዓቶች ንቁ የፖለቲካ ተሳታፊ የነበሩት እንዲሁም በደርግ ዘመን በስርዓቱ ውስጥ በሃላፊነት ጭምር በመስራት ጥልቅ ግንዛቤ የነበራቸው አሰፋ ጫቦ[37] በሪፖርተር ጋዜጣ በ2008 ዓ.ም. እንደጻፉት " ደርግ... የብሄረሰቦችን ጥያቄ በጥናት ለመወሰን የጥናት ተቋም አቋቁሟል!፣አቢዮቱ በአቢዮትነቱ ያመጣው ነበር! እናውቃለን ባዮች ለስልጣን ሲባል የወታደሩን ቃታ የሳብንበት፤ የቀረነውም በሌላው ተጽዕኖ ህዝብ የፈጀንበት፣ ያፋጀንበት ባይኖር ደርግ የኢትዮጵያ ህዝብ መቼም ሊያገኘው የማይችለው አይነት መንግስት ነበር"። በዚህ መሰረት እንግዲህ አቶ አሰፋ ደርግን ምርጫቸው አድርገዋል። የመረጡበት ምክንያት ግን አያሳምንም። እርሳቸው እንዳሉት ህዝብ ፈጅተዋል፣ አፋጅተዋል፣ ጸረ- አቢዮት ባሉት ላይ ሁሉ የወታደሩን ቃታ ስበዋል (ጥይት አዝንበዋል ማለት ነው)። ይህ ሁሉ ከሆነ ምን ቀረ? ህዝቡ በነሱው ተፈጀ፣ የቀረውን እርስ በእረሱ አፋጁ። በዚያ ዘመን ሃገሪቱ ሰው አልባ መሆን ብቻ ነው የቀራት እንጂ በምሁር ድርቅ እንዲመታት ተደርጓል። ስርዓቱ መጡብኝ በሚል የፍርሃት ስሜት ውስጥ ተውጦ ገና ከጅምሩ የተናካሽ ውሻ ባህሪ ተላብሶም ነበር። ሃገር በመምራት ሂደት ህዝብ መፍጀት፣ ማፋጀት የመጨረሻው ዝቅጠትና በመንግስትነት ደረጃ ለመታሰብ የያማበቃ ነው። ባይሆን ኖሮ የሚል መነሻ አይሰራም። ስለሆነም በሳይንሳዊ ስሌት የደርግ ስርዓት በአንጻራዊነት ሊመረጥ ቀርቶ በአማራጭነት ለማስጥቀስም የሚከብድ ነው።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግስት የማነው?

ብዙ ጊዜ የመንግስት አሰራር ለሌላ ሃገር ዜጎችና መንግስታት የሚጨነቅ ሆኖ እናየዋል። ይህ ልክ ያጣ ለሌላ ሃገር ዜጎች መጨነቅና የራስን ዜጋ ችላ ማለት ለምን እንደመጣ ግራ መጋባቴን ለአንድ ባልደረባየ ስጠይቅ። ስቆብኝ ካበቃ በኋላ "መንግስት በሀገር ውስጥ ስላለው ዜጋ ምን አስጨነቀው በ2007 ዓ.ም. ምርጫ መቶ በመቶ ህዝብ መርጦታል፣ ከአለም ዙሪያ ያሉ ህዝቦች ይህንኑ አሸናፊነቱን እንዲያረጋግጡለት እነሱን ለማሳመን በትጋት ማገልገል ይገባዋል እንጂ" ሲል በምጸት መለሰልኝ።

በ2008 ዓም. በጎንደር በኩል መሬታችን ለሱዳን ተሰጠ በሚል ገበሬዎች በሱዳንን ሰራዊት ላይ ጥቃት መሰንዘራቸው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስቴር ወንበዴዎች የሌላ ሃገርን መሬት

37

ለመውረር ጥቃት መሰንዘራቸውንና መንግስታቸው እንደማይታገሳቸው በኢትዮጵያ ቴለቪዥን ነገሩን። ይህን አይነት መግለጫ ከሱዳን መንግስት ነበር የምጠብቀው። መንግስት ዜጎቹ ተደፍርን ብለው የሚወስዱትን እርምጃ እንዲቆሙ ማግባባት፣ ያለመደፈራቸውን ማሳመን ወይም አግባብነት ከነበረው ከጎናቸው መቆም ነው ያለበት። ህገ-ወጥ ተግባር ፈጽመው ከሆነ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ተገቢ ነው። የጠቅላይ ሚኒስተሩ ንግግር ግን ዜጎቹ በሱዳን መንግስትም በኢትዮጵያ መንግስትም ጦር እንዲደመሰሱ የሚያደርግ፤ በዜጎቹ ላይ የታወጀ ጦርነት ነው።

በተመሳሳይ አመት ሚያዝያ ሰባት በገምቤላ ክልል 208 ሰዎችን በጅምላ ጨፍጭፈው፣ ከመቶ በላይ ህጻናትን አግተው፣ በግምት 100 የሚደርሱ አቁስለው እና ከ2000 በላይ ከብቶችን ዘርፈው የተሰወሩ የደቡብ ሱዳን የሙርሌ (Murle) ታጣቂዎችን አስመልክቶ ጠቅላይ ሚኒሰተሩ ገና በጠዋቱ በሰጡት መግለጫ ታጣቂዎቹ ከደቡብ ሱዳን ፖለቲካዊ ሃይሎች ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው መሆኑን ይፋ አደረጉ። እስኪ አስቡት፤ ኢትዮጵያዊን በተደራጀ የሌላ ሃገር ታጣቂዎች ተጨፍጭፈው የሌላውን ሃገር ከወንጀል ነጻ ለማድረግ ምን ያጣድፋል? ደግም የሚገርመው ነገር የሱዳን መንግስት እና አማጺን “አንተ ነህ አንተ ነህ” በሚል እየተወነጃጀሉ ባሉበት ወቅት ነው ኃ/ለማሪም የደቡብ ሱዳንን መንግስታዊ ሃይሎችን ነጻ ያወጧቸው። ታጣቂዎቹ ጥቃቱን የፈጸሙት ለሶስት ተከታታይ ቀናት መሆኑ ይታወቃል። ለመሆኑ መንግስት ከአንድ ቀን በላይ የቆየ የጸጥታ ችግር እንዴት ሊታገስ ቻለ? የመከላከያ ሰራዊት የት ገባ? በአካባቢው ሰራዊት ባይኖር እንኳን በአንድ ቀን ውስጥ ድንበር ዘለል ጥቃትን የሚመክት ሃይል በሄሊኮፕተር/አውሮፕላን ማንጓጠዝ አይቻልመ ነበር ወይ? ያልተመለሱ ጥያቄዎች ብቻ የኢትዮጵዊያን ስቃይ ችላ የተባለበት፣ መንግስት ውጪ-ውጪውን እያየ፣ የኢትዮጵያዊያን ጥቅም ወዳጅ መግጦ የሆነበት ዘመን ላይ እንደደረስን ይሰማኛል። እነዚህ ኩነቶች ለአብነት የቀረቡና የሰሞኑ ትኩሳቶች ናቸው።

ቀደም ሲል ጀምሮ እስከዛሬም የቀጠለ ከኢትዮጵያ ጥቅም ይልቅ ስለሌላ ሃገር ህዝብ የማሰብ ግራ አጋቢ የስርዓቱ ቁንጮዎች አቋምን ስናይ ለምሳሌ መለስ ዜናዊ (የቀድሞው ጠ/ሚኒስተር) እና አቦይ ስብሃት ከኢትዮጵዊን ጉዳይ በላይ የኤርትራዊን ጉዳይ እንደሚያስጨንቃቸው አስራት አብርሃም ከሃገር በስተጀርባ በተሰኘው መጽሃፉ በማስረጃ ነግሮናል። የኢትየጵያ ህዝብ በድህነት አረንቋ ውስጥ እየማቀቀ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስተር የኤርትራ ህዝቦች ኢትዮጵያ ተመልሰው በመምጣት ንብርትና ይዞታቸውን አንዲረከቡ በሚኒስትሮች መ/ቤት ደምብ አጸድቆ

ተግባራዊ መደረጉ ይታወቃል። የኢትየጵያዊያን ሃብትና ንብረት፣ የሃገሪቱ ገንዘብ ያለተደራዳሪ ኤርትራ እንደወሰደችውና ለኤርትራዊያን መጠቀሚያ ሆኖ ሳለ ኤርትራዊያን ድጋሚ የኢትዮጵያዊያንን ሃብት እንዲጋሩ፣ በመሬቱ ላይ ያለልዩነት እንዲሰሩና ያለልዩነት ሃብትም እንዲያፈሩ፣ ከባንክ ገንዘባቸውን እንዲወስዱ ተደርጓል። ኢትዮጵያዊያን ወደብ አልባ ስለመሆናቸው አግባብነት ሲከራከሩ የነበሩትም እኝሁ በኤርትራ አፍቃሪነታቸው የሚነገርላቸው የቀድሞው ጠ/ሚኒስተር ናቸው። ስርዓቱ የጥቂቶች ብሎም የሃገሩቱን ታሪክ፣ልዕልና፣ የመደራደር አቅም፣ የግዛት አንድነት የሚያቆረቁዙ ተግባራትን የፖለቲካ መርህ አድረጎ ስለመስራቱ ብዙ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል።

የሃገር ውስጥ አንድነትን በመናድና በተለይ አማራ-ጠል ፖለቲካ በመገንባት ታከተኝ የማይል መንግስት ሆኗል። የታሪክ እውነታን በማሳት አዳዲስ ትረካዎችን አብዝቶ በማስነገርና እርስ በእርሳችን እንድንጠላለፍና በመጠላለፋችን መሃል በሚፈጠር የትብበር ማጣት ስልጣንን ማደላደል የዛሬዋ ኢትዮጵያ መገለጫ ነው። ስጠቀልለው ስርዓቱ ተመራጭ አይደለም።

ከላይ የተጠቀሱት ዜጎችን ከመጠበቅና ብሄራዊ ጥቅርምን ከማስከበሩ አንጻር የሚታየው ክፍተት እንዳለ ሆኖ ስርዓቱ ራሱ የሚጭናቸው ፖሊሲ ተኮር ጭቆናዎችና በአድሎአዊ አሰራሮች ህዝቡ ተስፋ ቆርቶ በአህዝባዊ እምቢተኝነት በአደባባይ እንየጮኸ ከስናይፐር ጋር እንዲጫወት ተገደደ፣ ለውጥ ናፋቂዎች ሰማዕታቶች ሆኑም። ይህ ህዝባዊ ቁጣ በብዙ የሃገሪቱ አካባቢዎች የተቀሰቀሰ ቢሆንም በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች የተከሰተው በኢትዮጵያ ታሪክ ያልታየና ሁለቱ ክልሎች በወታደራዊ እዝ ስር እንዲወድቁ ያስቻለ ነው። በዚህ ጽሁፍ የሃሳብ መለጠጥን ለመወሰን በአማራ ህዝባዊ እምቢተኝነት ላይ ይተኮራል።

የአማራ ህዝባዊ እምቢተኝነት (ቁጣ) እና ወልቃይት

የአማራ ህዝባዊ ቁጣ ለምን?

በጎንደር በኩል ከ1983 ዓ.ም. ወዲህ በርካታ ቁጥር ያለው የአማራ ህዝብ በትግራይ ክልል ውስጥ ታካሎ እንዲኖር ተደርጓል። የማካለሉ ተግባር ህዝቡን ከነመሬቱ በመሆኑ የማንነት ጥያቄውም ከአካባቢው ጋር አብሮ የሚነሳ በመሆኑ የማካለሉ ስራ ከተከናወነበት እስካሁን ድረስ የአማራ ማንነት ከሚያንጸባርቁ አካባቢዎች ወልቃይት፣ ጸገዴ፣ ጸለምትና አርማጭሆ ግንባር ቀደም ናቸው። በ1999 ዓ.ም. የህዝብና ቤት ቆጠራ በትግራይ ክልለ 70,561 የአማራ ብሄር ተወላጆች እንደሚኖሩ የማዕከላዊ ስታሰቲካል ባለስልጣን ይፋ አድርጓል። ይህ አሃዝ የወልቃይና

ጸገዴን አማራዎች ወይም የጎንደር አማራዎች ነን የሚሉትን ህዝቦች እንደአማራ በመቀበል ቆጠራ ተከናውኖ ይሆን? ብሎ ለሚጠይቅ እርግጠኛ መልስ ሊሰጠን የሚችል አካል ማግኘት አዳጋች ነው። ምክንያቱም የክልሉ መንግስት ለ25 ዓመታት እንዲሁም ዛሬ የአማራ ልጆች በቋንቋቸው እንዳይማሩና እንዳይዳብር፣ ባህላቸው እንዲከስም፣ የአማራነት ስነልቦናቸው እንደሚሰጣቸው እንዲብረከረክ የሚቻለውን ሁሉ እያደረገ ባለበት አግባብ ተአማኝነት ያለው የአማራውን ህዝብ ብዛት የሚገልጽ አሃዝ ተመዝግቦ እንዲቀርብ የሚደረግበት ምክንያት ሊኖር ስለማይችል ነው። በዚሁ የህዝብና ቤት ቆጠራ መሰረት የወልቃይት ጎንቅናቄ በጦፈበት የምዕራብ ትግራይ በሚል በተሰየመው ቃፍታ ሁመራ ወረዳን፣ ወልቃይት ወረዳን፣ ጸገዴ ወረዳንና የሁመራ ከተማ ወረዳን ባቀፍ ዞን ውስጥ ከሚኖሩ 356,598 ህዝቦት 23,093 ብቻ ናቸው የአማራ ብሄር ተወላጆች። በደቡብ ትግራይ 27,131 የአማራ ብሄር ተወላጆች ይገኛሉ። ሆኖም እንደምዕራብ ትግራይ ህዝቦች የማንነት ጥያቄውን በተደራጀ መልኩ አላስኬዱም። በአማራ ህዝባው ቁጣና አመጽ ውስጥም የሚጠቀስ ሚና አልተጫወቱም።

ወደ ዋናው ጉዳይ ስንመለስ የህዝባዊ አመጹ ሂደቶችና ምክንያቶች ለመዳሰስ የመንግስታዊ አማራ-ነክ ፖለቲካና የወልቃይት ጥያቄ ትኩርት የሚደረግባቸው ጉዳዮች ናቸው። መሰረታዊ የህዝባዊ ቁጣውና አመጽ መነሻዎች በርካታና ከስርዓቱ መንሸዋረር በተለይ ከአማራ-ጠል የመንግስት ፖሊሲ የሚነሱ መሆናቸውን ከላይ ለመጥቀስ ተሞክሯል። እነዚህም የህዝብ መፈናቀሉ፣ ብሄራዊ ድህነት፣ ብሄራዊ መገለልና ዘርፈ ብዙ አድሎ፣ የአማራ ህዝብን መሬት ወደሌሎች ክልሎ ማካለል፣ የህዝቡን ማንነት የማስለወጥ እንቅስቃሴ፣ የአማራ ህዝብ ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን ህብረት እንዳይኖረው የበዳይነት ታሪክ የመስጠት፣ የህዝቡን ስነ-ልቦና መደቆስ ወዘተ... ናቸው። በዚህ ክፍል የእምቢተኝነቱ ወቅታዊ መነሻና ማቀጣጠያ የሆኑ ጉዳዮችን፤ ጥቂት የህዝባዊ እምቢተኝነቱ ባህሪትን እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችን ብቻ ለማየት ይሞከራል።

የ2008 ዓ.ም. አማራ ህዝባዊ አመጽ በወፍ በረር

ለአዲሱ የአማራ ህዝብ መነቃቃት ጎንደር ፋና ወጊ ሆነች። የታመቀውን የህዝብ ብሶት በህዝባዊ እምቢተኝነቱ እንዲታጀብ የወልቃይት የማንነት ጥያቄ ኮሚቴ አባል ኮሎኔል ደመቀ ዘውዱ በችቦ ለኳሽነት ታሪክ አስመዘገበ። በሃምሌ አምስት (5) ቀን 2008 ዓ.ም. ኮሎኔሉ ከአሳሪዎች ጋር ያደረገው የተኩስ ልውውጥ የአማራ ህዝብ ትግዕስት የተፈታተነ ሆኖ የጎንደርን ፋና ወጊነት አበሰረ። ጉዳዩን እንዲህ ነው፡ ኮሎኔል ደመቀ ዘውዱን የፌደራል ፖሊስን ዩኒፎርም

የለበሱ የትግራ ክልል የጸጥታ ኃይሎች (የትግራይ ክልል ልዩ ኃይል እንደሆኑ የተጠቆመ) ክል ከቤቱ አፍነው ወደ ትግራይ ሊያሸግሩት ጎንደር በሚገኘው መኖሪያ ቤቱ ተከሰተው ከበባ አደረጉ ሲሉ እማኞች ይገልጻሉ፡፡ ለጸጥታ ሃይሎች እጁን ለመስጠት ባለመፍቀዱም የተኩስ ልውውጥ ተደርጎ የሰው ህይወት አለፈ፡፡ ኮሎኔሉም የአጋቾቹን ህልም ካከሸፈ በኋላ እጁን ለከተማው የህግ አካል ሰጠ፡፡ ሆኖም ይህን ያዳኘ ታዳኝ- የአፋኝ ታፋኝ ፍልሚያ የተመለከተ ህዝብም የትዕግስት ጽዋውን ከንብሎ ለአመጽ ተነስቷል፡፡ ወቅቱ በኦሮሚያ እዝባዊ አመጽ የጦፈበት ነበርና ለጎንደሩ እምቢተኝነት መነሳሳትም የሚፈጥር ነበር፡፡ በአማራ ክልል የሚደረግን ፈር የለቀቀ የአደን ስራ ያለአማራ ክልል መንግስት እውቀና ውጪ እንደሆነም የወልቃይት የማንነት ይያቄ ኮሚቴው ይፋ አድረጓል፡፡ በደመቀ ላይ የተደረገው አደን የክልሉ መንግስት ስልጣን አልባ መሆንና የብአዴን ሰዎች ሎሌነታቸውን ገሃድ ያወጣ ነው፡፡ የክልሉ የጸጥታ ኃይሎች በአመጹ ላይ የተለሳለሰ አቋም ለመያዝ፣ ለብአዴን የመካከለኛው አመራር ለካድሬዎቹም መነቃቃት የሚፈጥር ነው፡፡

ጉዳዩ ለመንግስት ሌላ የስጋት ምዕራፍ ከፈተለት፡፡ የፕሮፌሰር አስራትን “የመላው አማራ አንድነት ድርጅት (መአዐድ)” ታሪክን ብቻ እንኳን ብናስታውስ የአማራ መደራጀትና መነሳሳት የኢትዮጵያ መንግስት ቁጥር አንድ ስጋት መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ በመሆኑም ህዝባዊ እምቢተኝነቱ በተጋጋለበት ወቅት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ጠቅላይ ሚኒስተር ሃይለማሪም ደሳለኝ ከቀድሞው ለየት ያለ መልዕክት አስተላለፉ፡፡ ይህም ችግሩ መኖሩን በማመን የማንነት ጥያቄ መልሰናል (መንግስት ቀደም ሲል የማንንት ጥያቄ በህግ-መንግስቱ ተመልሷል በሚል ኮሚቴዎችን በጸረ-ሰላምንት የሚፈርጁ መግለጫዎችን ሲሰጥ ቆይቶ ነበር) ከሚለው ትንሽ አፈግፍገው የወልቃይትን ጥያቄ “የትግራይና የአማራ ክልል መንግስታት”[38] የሚመልሱት ነው

[38]የትግራይታ የአማራ ክልሎች እኩል ተደራዳሪና ችግሩን ለመፍታቱ ባለወኔ ናቸው ወይ? ገነት አለሙ (ነሃሴ 2008 ዓ.ም.) በሪፖርተር ጋዜጣ ላይ የወልቃይት ጥያቄ አስመልክቶ እንደጻፈችው “...የአከላለል ለውጥን የሚመለከተው የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 48 በመጀመርያው ንዑስ አንቀጽ ላይ “የክልሎችን ወሰን በሚመለከት ጥያቄ የተነሳ እንደሆነ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ክልሎች ስምምነት ይፈጸማል፤” ይልና “የሚመለከታቸው ክልሎች መስማማት ካልቻሉ የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት የሕዝብን አሠፋፈርና ፍላጎት መሠረት በማድረግ እንደሚወስን ይደነግጋል:: ይህ ንዑስ አንቀጽ የሕዝብ ወሳኝነትን መርህ እንደጠበቀ ለመገለጽ፣ የሚመለከታቸውን ክልሎች ስምምነት ከሕዝብ ፍላጎት ጋር እስካልተጋጨ ድረስ ብሎ ማሰር ሲገባው የተገላቢጦሽ የሕዝብን ፍላጎት “ክልሎች መስማማት ካልቻሉ” በሚል ሁኔታ ላይ ተንጠልጣይ ያደርገዋል (ዝኒ ከማሁ):: ጉዳዩ “ክልሎች መስማማት አልቻሉም የሚለው ነው፡፡ እዚህ ላይ የአማረ ክልል የወልቃይትን ጥያቄ በእኩል ከትግራይ ክልል መንግስት ጋር ተደራድሮ ፍትሃዊ ውሳኔ የማሳለፍ ፍላጎም ሆነ ወኔና አቅም አለው ወይ? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ያስፈልጋል፡፡ መልሱ የለውም ነው፡፡ ህዝቡ ነው አማራ ነኝ ያለው፡፡ አማራ ነኝና በአማራ ክልል ልካለል በሚል የብአዴንን እርዳታ ቢጠይቅም ድርጅቱ፡፡ አማራ ተደራዳሪና ተወካይ መንግስት ሳይኖረው ጥያቄውን ሲያፍን ከቆየው ከትግራይ ክልል ፍትሃዊ መልስ ይገኛል ብሎ መጠበቅ ሞኝነት ነው፡፡

ካሉ በኋላ የጉዳዩ መንተትም ጸጥታ እንዲደፈርስ አድርጓል የሚል ሃሳብ ሰነዘሩ። ሳይቃጠል በቅጠል የሚባል ተረት የሰሙ አይመስለኝም፣ ዘግይተዋል። መንግስታቸው ጥያቄውን ሲያድበሰብስ መቆየቱ የህዝብን በደል አብዝቷል፤ የሃገሪቱም ጸጥታ ሳያደፈርስ መፍትሄ መስጠት የሚቻልባቸውን 26 አመታት አባክኗል።

አመጹ ቀጥሏ። የአማራ ችግር ዘርፈ ብዙ ሆኖ ቢቀጥልም መልስ ሰጪ የለምና። ብዙ ልሂቃኖቹ አማራነትን ለኢትዮጵያዊነት ትልቅ አላማ መስዋዕት አንዲያደርግ ማሰቻላቸው በአማራነት ላይ የተቃጣውን የማንንት ጥቃት በሆደ ሰፊነት እንደታገስ የወጣች ጀመበር አዘቀዘቀች። የአማራ ብሄርተኝነት ቡቃያዎች በዝተው ታዩ። ሃምሌ 24 ቀን 2008 ዓ.ም. የጎንደር ህዝብ አደባባይ ወጣ። ከተማዋ በአርማ አልባ ሰንደቅ አላማ ተሞልታ ዋለች። ከዚህ ቀን ወዲህ የተለያዩ አካባቢዎችን እየሸፈነ፣ በተለያየ፣ ስልትና ቅርጽ የወጣቱን የስሜት ጥግ የሚያሳዩ መፈክሮች እየታተሙ ተዘረጉ። የመፈክሮች መደብ በአረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ቀለሞች አሸብርቀው ታዩ።

በዚህ መሃል ኮሎኔሉ የህዝብ ትኩረትን እንደሳበ ነው። ለወጣቱ የግሰቡን ሁኔታ ያለመታከት መከላታል የአመጹ አካል ነበር። ከጎንድር ወጥቶ ለፌደራልም ሆነ ለትግራይ ክልል እንዳይተላለፍ የሚጠበቁ ሽህዎች ነበሩ። ህልማቸውን አሳክተውታልም። በሃምሌ 29 ቀን 2008 ዓ.ም. የኮሎኔል ደመቀን የፍርድ ሂደት ለመታደም ህዝብ ተሰባሰበ። ከችሎት ውጪ በፍርድ ቤት አካባቢ ሰልፍ ሆነ። የህዝቡ ሁኔታ ያሳሰበው ፖሊስ የተሰበሰበ ህዝብ እንዲበተን የአስለቃሽ ጋዝ ረጨ። በፌደራል መንግስት የጸጥታ ሃይሎችና በአካባቢው በተለይም በወጣቱ የማህበረሰብ ክፍል መሃል ተጠንስሶ የነበረው መንግስት-ጠል ስሜት ዳግም አገረሸ። ነውጥ ተጀመረ፤ ወጣቶች ተገደሉ የጸጥታ ሃይሎች ከታጠቁ ገበሬዎች ፍልሚያ ገጠማቸው፣ የመንግስት ደጋፊና የመብት ጥያቄውንና አመጹን የተቃወሙ ባለሃብቶችና ባለስልጣናት ንብረት ለውድመት ተጋለጠ። ጉዳዩ ያስፈራቸው ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ የመንግስት ደጋፊችና የትግራይ ተወላጆች ለጊዜው ሸሽተውም ነበር። ይህም አንዱ ስርዓት ወለድ አሳዛኝ ክስተት ነበር።

አባይ ማዶም (ጎጃም)፡ ጎንደር ቅዳሜ ሃምሌ 30 ቀን 2008 የጸጥታው ጉዳይ በእጂጉ ከአቅም በላይ ሆነ፣ የአጋዚ ሰራዊትና ማህበረሰቡ መታኮስ ቀጠለ፣ የአጋዚ ሰራዊት አልሞ ተኳሾችና ሌሎች የፌደራል የጸጥታ ሃይሎች የሚተላለፉባቸው መንገዶች በህዝቡ እየተዘጉ ሰነበቱ። የሰው ህይወት ግን አሁንም እየተቀጠፈ ቆየ። ነውጡ ከአባይ ማዶ **ተዛመተ፣** በሰራዊቱ ላይም

ጥቃት መሰንዘር ተጀመረ፣ ጎጃም ጎጃሜ ነኝ የሚል ተለምዷዊ አጠራሩን ወደጎን ትቶ አማራ ነኝ አለ። ነሃሴ 1 ቀን 2008 ዓ.ም. የባህርዳር አማራ ሰልፉን አሃዱ ብሎ ጀመረ። የወልቃይት ህዝብ ጥያቄን ለማድበስበስ የሞከሩትን ሃይለማሪያም ደሳለኝና ካሳ ተክለብርሃንን አውጋዥ መፈክሮች (በተለያየ አገላለጽ የተጻፉ) ከፍ ተደርገው ተውለበለቡ። የአማራን እዝብ መጨቆን እንዲሁም የሃገሪቱን ህዝቦት ብሶት የሚያንጸባርቁ መፈክሮች አደበባይ ወጡ። ለአብነት ያህል የሚከተሉትን እንመልከት፡-

ካሳ ተክለብርሃን አማራን አይወክልም! ወልቃይት አማራ ነው!፣ የትግራይ ነጻ አውጪ ኢትዮጵያ ውስጥ ምን ያደርጋል! ወታደሩ የህዝብ ነው! ሕወሃት አማራን መግደል ያቁም!በኮሎኔል ደመቀ አንደራደርም! በቀለ ገርባ መሪያችን እንጂ አሸባሪ አይደለም (የኦሮሞ አክቲቪስትና ፖለቲከኛ) ! አንዱአለም አራጌ መሪያችን እንጂ አሸባሪ አይደለም! ሞት ቢደገስም አንፈራም (በደብረማርቆስ)! በኦሮሚያ የሚፈሰው የእኛ ደም ነው! ወያኔ በአማራ ምድር አምስት ሳንቲም ሆኗል! የሚሉት እና ሌሎች የትየለሌ መፈክሮች በቀለም ህብረት አሸብርቀው በአደባባይ ከቀይ፣ቢጫ፣ አረንጓዴ ሰንደቅ አላማ ጋር በየጎዳናዎች ሲታዩ ሰንብተዋል።

ከመፈክሮቹ መረዳት እንደሚቻለው ህዝባዊ እምቢተኝነቱ የወልቃይት ጥያቄ መነሻ አድርጉ ይቀስቀስ እንጂ በርካታ ፖለቲካዊ ጉዳዮችን የሚዳስ ነበር። ከነዚህም በመንግስት የታሰሩ ፖለቲከኞች እንዲፈቱ የሚጠይቅ፣ በኦሮሞን ህዝብ ላይ የጸጥታ ሃይሎች የሚፈጽሙትን የሃይል እርምጃ የሚቃወም፣ የአማራን ህዝብ ጥያቄ የሚያጣጥሉ አመራሮችን የሚያወግዝ የወታደሩን የህዝብ ልጅነትና ለህዝብ ጥያቄ አብሮ የሚቆም መሆኑን የሚያመላክት ይዘት ያላቸው ነበሩ። በተለይም የትግራይ ነጻ አውጪ ኢትዮጵያ ውስጥ ምን ያደርጋል! የሚለው መፈክር ከፍ ያለ ትርጉም የሚሰጠው ነው። ነጻ አውጪ ነጻ አወጪ ነው፣ ሕወሓት ደግሞ ስሙንም ተግባሩንም መለወጥ የተሳነው ነው። ስሙ አሁንም ነጻ ሊያወጣ የተደራጀ ቡድን እንደሆነ ነው የሚያሳየን። ዱሮ ትግራይ በኢትዮጵያ ተጨቁናለት የሚል መነሻ ይዞ ነበር ዛሬስ? አሁንም ነጻ የትግራይ መንግስት የመመስረት አላመውን አላቆመም? የመሳሰሉ ጥያቀዎችን ያዘለ ነው። ኢትዮጵያ በነጻ አውጪ ድርጅት የመተዳደሯን አግባብ የሚጠይቅ መፈክር ሆኖ እናገኘዋለን።

እንደጎንደሩ ሁሉ በባህርዳር የባለ አርማው ሰንደቅ አላማ ቦታውን ለልሙጥ አረንጓዴ፣ ቢጫ ቀዩ ለቋል። የባህር ዳር ሰልፍ ከፖሊስ በተተኮሱ ጥይቶች በከፊል የተበተነበት ሁኔታ ነበር። በርካታ ሰዎችም ሞተዋል። የጎንደሩ ህዝባዊ እምቢተኝነት ከሌሎቹ ልዩ የሚያደርጉት ባህሪያት

ነበሩት፡፡ የጎንደር ህዝብ ስቃዩ እየተደራረቡ በመጡ ቁጥር በእጁ የነበሩ ያረጁ ያፈጁ መሳሪያዎች ጭምር በመጠቀም የስርዓቱን ዘበ ተፈታትኗል፡፡ በአዘዞ ወታደራዊ ካምፕ የህዝባዊ ቁጣው አካል የሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎች ጥሰው በመግባት የጦር መሳሪያዎችን መዝረፋቸውን የማህበራዊ ሚዲያዎች ይፋ አድርገዋል፡፡ የባህርዳር ለውጥ ናፋቂ የህዝብ ጎርፍ ቁሳዊ ትጥቅ አልነበረውም፡፡ የታጠቀው ሞትን የሚጋፈጥ የእምቢተኝነት ወኔን ነበር፡፡ ህዝባዊ ቁጣው ሳይበድር የባህርዳር ህዝብን ህይወት ቀጣፊ ጥይቶች ከህንጻ ላይ እየተተኮሱ እከቀጣዮቹ የነሃሴ ቀናት 2008 ዓ.ም. ድረስ ቀጥሏል፡፡፡ ቀኑ ሲጨምር የሰማታትም ቁጥር አደገ፡፡ ጎንደር በነሃሴ 2 ቀን 2008 ዓ.ም. አንጸራዊ መረረጋጋት ስታገኝ ባህርዳር ግን እንደተናጠች ውላ በማግሰቱና በተከታታይ ሌሎች አራት ቀናት የነውጥ አውድማ ሆና ሰንብታለች ፡፡

ከባህር ዳር ደብረማረቆስ ከ22 እስከ 24 /12/2008 መንገድ ዝግ የነበረ ሲሆን በዳንግላ ስምንት የመንግስት ሹማምንት ቤቶች ተቃጥለዋልም (የናስ በላይ፡ 2008 ዓ.ም.)፡፡ ደብረማርቆስ ከነሃሴ 16 እስከ18 ቀን 2008 ዓ.ም. በቤት ውስጥ ያለመውጣት ተቃዎሞ ተጠናክሮ የቀጠለ ነበር፡፡

ጎንደር ከነሀሴ 8/12/08 ዓም ጀምሮ አስከ 10/12/08 ዓም ከቤት ያለመውጣት አድማ አድርጓል፡፡ በድጋሚም በ18/12/08 ዓ.ም. ጀምሮ ለተከታታይ አምስት ቀናት ተመሳሳይ አድማ ተደርጓል፡፡ ሆቴሎች ስራ አቁመዋል፡፡ የቤት አከራዮች ተከራዮቻቸውን ለአንድ ወር በነጻ ለማኖር ቃለ መግባታቸው፣የመንግስት ተሽከርካሪዎች ጭምር ማደማቸው፣ከእጅ ወደ አፋ ገቢ ያላቸውና የቀን ሰራተኞች እንዳይራቡ ወጣቶች ዳቦ እያደሉ መሆናቸው በልዩነት ታሪካዊ ክስተት ሊመዘገብ የሚገባው ሆኖ አልፏል፡፡ በ10/12/08 ዓ.ም. የምስራቅ ጎጃሚ ማርቆስም በተመሳሳይ አድማ የስርዓቱን ኢፍ-ትሃዊነትና በዳይነት እንዳወጀችም ይታወቃል፡፡

ቀድሞ በማህበራዊ ሚዲያዎች ነሃሴ 14 “ነጭ የመልበስ ቀን” እንድትሆን ታወጀ፡፡ በዋዜማው በ13/12/ 08 ዓ.ም በትግሉ ለተሰው ሰማዕታት በአደባባይ የሻማ ማብራት ስነስርዓት ለማድረግ ተሞክሮ በጸጥታ ሃይሎች ክልከላ ምክንያት ባለመሳካቱ በሚካዔል ቤተክርሲን እየተከናወነ ሳለ ወታደሮች ገብተው ድብደባ ተፈጽሟል፡፡ ነጭ የመልበስ በቀጠሮው መሰረት በ14/12/08 ዓ.ም. ወጣቱ የተለመደ የትግል ወኔውን እንደታጠቀ በጎንደር ከተማ አደባባይ ወጥቷል፡፡ የሚጠበቅ አዲስ ምላሽ አልነበረም፣ የፌደራል የጸጥታ ሃይሎች ነጭ በለበሱ ሲቪሎች ላይ ተኩስ እንደከፈቱና ንጹሃንም እንደተገደሉ ተነግሯል፡፡ አንድ ወጣት በአልሞ ተኳሽ የመንግስት ወታደሮች የተገደለ መሆኑን በገለልተኛ የመረጃ ምንጮች የተረጋገጠ ሲሆን ከአካባቢው የሚነገሩ መረጃዎች ግን አራት ነጨ ለባሾች መሞታቸውን ይመሰክራሉ፡፡ ነጭ ልብስ በመልበስ

የመሰባሰባቸው ዋና ምክንያት ነሃሴ 14 ቀን የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ መታሰቢያ ቀን በመሆኑ ይህ ዕለት በአማራ ህዝብ ላይ ግፍና ጭቆናን ስርዓታዊ ካደረጉ የፖለቲካ ልሂቃን የአንዱና የዋና የሙት አመት የመታሰቢ ቀንን ለመቃወም ነበር፡፡

ባህር ዳር ከ15/12/08 አስከ 17/12/08 ዓ.ም ድረስ የቆየ የሶስት ቀናት የተሳካ ከቤት ያለመውጣት አድማ አድርጋለች፡፡ በመንግስት በኩል የተለያዩ ማስፈራሪዎችና እርምጃዎች (ከሱቅ ማሸግ እስከ ማስር የሚደርስ ተግባር ተፈጽሟል) ቢሰነዘሩም ከቤት ያለመውጣት ህዝባዊ እምተኝነቱን ሊገታው አልቻለም፡፡

ወርሃ መስከረም መጀመሪያ ለሶስት ቀን የቀጠለ በባህር ዳርና ጎንደር ከቤት ያለመውጣት አድማ ተከናወነ፡፡ ህዝቡ የመንፈስ አንድነቱን የፈተሸበት በቀጣይ የጋራ ራዕይ ለመንደፍና በሃገሪቱ የአማራ ህዝብ ማንንቱና መብቱ ተጠብቆለት አንዲኖር የሚያስችል የተደራጀ ትግል ለማድረግ አመርቂ የስነ-ልቦና መሰረት እንዳለ አመላካች መናበብ ታየ፡፡

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከታወጀም ወዲህ በጎንደር አካባቢዎች በጎበዝ አለቆች የሚመራ የትጥቅ ትግል ከፌደራል መንግስት ሃይሎች ጋር ሲያደረግ እንደነበር ከመንግስት ምነንጮች ተረጋግጧል፡፡ እነዚህን የጎበዝ አለቆች መንግስት ጽረ-ሰላም ሃይሎች በሚል ሰይሞ በአስቸኳይ ጊዜ አማጭ ወቅት መጠነ ሰፊ የኃይል እርምጃ እንደወሰደባቸው የሚያሳብቁ መግለጫዎች ሰጥቷል፡፡ ይህ ሁሉ አልበገር ባይነትና የገበሬ ፍልሚያ በጎንደር ከተማ የተጀመረችው የሰላማዊ የህዝብ እንቀስቃሴ የወለደችው እምተኝነት ውጤት ነው፡፡ ለሰልፉም፣ እልህ ለተቀላቀለበት የአማራ ህዝባዊ መነሳሳ የኮሎኔል ደመቀ ማንንትን የማሰጠበቅ ትግል የማትዘነጋ የታሪክ ክስተት ናት፡፡ በአመጽ ወቅት የአማራ ህዝባዊ እምቢተኝነት ዋና ዋና ማዕከሎች የሚከተሉት ነበሩ፡፡

- ሻውራ (አለፋ ጣቁሳ)
- ጎንደር ከተማ፣ አዘዞ፣
- አዲስ ዘመን (ሊቦ ከምከም)
- ወረታ (ፎገራ)
- ደብረማርቆስ በ7/12/08 ዓም.
- ቻግኒ አገው
- ስማዳ ወረዳ
- ቋሪት ወረዳ
- ዳንግላ
- ደብረ ታቦር
- ቡሬ-ከተማ (ምዕራብ ጎጃም)
- ደምቢያ
- ሶሮቃ፣ ዳንሻ
- ደምበጫ
- ብርሸለቆ
- ፍኖተ-ሰላም
- ባህር ዳር
- እስቴ
- ደባርቅ
- ዱርቤቴ

- ሳንጃ
- ክምር ድንጋይ
- ደምቢያ
- ቆላድባ
- በማቻከል
- ቡሬ
- አምባ-ጊዮርጊስ

የአማራ ቁጣና እምቢተኝነት ፋይዳ

እምቢተኝነቱ አይቀሬ ነገር ግን የእድሜልክ ጫና ፈጣሪው የሆኑት የህወሃት መስራችና የፖለቲ ቢሮ አባል ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ በ2009 ዓ.ም. እንደገለጹት ለመንግስት ያልጠበቀው ዱብ እዳ እንደነበር ተናግረዋል። እንደ ደራሽ ጎርፍ የወጣቱን አልበገር ባይነት፣ የጎበዝ አለቆችን ደጀንነት ፍንትው አድርጎ በማሳየቱ ያስከተለው ስጋትም የጎላ ነበር። ስጋቱን ተከትሎ መንግስት ከቁሶች የሽንገላና ድለላ እስከ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ (በአዋጅ የተሸሞነሞነ የእስርና ግድያ ወቅት) የሚደረሱ ለቁጥር የሚያዳግቱ እርንጃዎችን ወስዷል። የአስቸኳ ጊዜ አዋጅ በይፋ ሳይነግር በፊ የአማራ ህዝብ "በጠቅላይ ሚኒስተር ኃ/ማሪያም"[39] የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ተጥሎበት ነበር። የህዝቡም የተባበረ የኃይል እርምጃ በመውሰድ የኃይል አማራጭ ወስዶ እንደነበር የመንግስት ምንጮች ጭምር አረጋገጠዋል።

አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ተነስቶ የህዝቡ ጥያቄ መልስ ሳያገኝ የጎንደርና የጎጃም የሰማዕታት አመት ሞላው። ወኔው ያልተለየው ህዝቡም በባህር ዳር የሰማዕታትን ቀን ስራ ዘግቶ ዘከረ። የጎንደርም ህዝብም የመስቀል በአልን የአማራነትን መነሳሳት የሚያሳዩ ቲሸርት በመልበስ በቀድሞው አመጽ ሲያውለበልቡት የነበረውን በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሰንደቅ አላማ ህግ የተከለከለውን ልሙጥ ባንደራ ያለፍራቻ ሲያውለበልቡ ተስተውለዋል። የሞቱ ምክንያት የአጋዚ ወተደር ጥይት መሆኑን የሚያሳይ ጽሁፍ በመቅረጽ የሰማዕት መቃብር ያነጹም አሉ። እንግዲህ የ2008 ዓ ም. መነቃነቅና አመጹ ፋይዳ የሚገለጸውና ለወደፊት ስለሚኖረውም ትርጉም መተንተን የሚቻለው እዚህ ላይ ነው። ምክንያቱም አማራ ችላ ብሎት የነበረውን በዘውግ **የመደራጀትንና የመተባበርን ቢያንስ** በታክቲክ ደረጃ አስፈላጊ መሆኑን አመላካች ጅምሮ ነውና። በየትኛውም የፖለቲካ ስሌት የጠነከረ ትብብር ገንብቶ የአማራ ህዝብ ህልውናውን ካላስጠበቀ ያጋደለውን የኢትዮጵያዊነት ጎጆ ከሌሎች ወገኖች በመሆን ሊያቃና የሚችልበት አቅም አይኖረውም። ስርዓቱን ለማስተካከል ወይም ለመቀየር የሚደረገው ንቅናቄም መና የሚቀር ነው የሚሆነው። አማራ ኢትዮጵያዊ ነኝ በሚል ብቸኛ በዘውግ ያልተደራጀ ሃይል ሆኖ መቀጠሉ

[39] "የጸጥታ ሃይሎች አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስዱ አዝዣለሁ ሲሉ" ጠቅላይ ሚኒስተር ኃ/ማሪም ደሳለን በጎንደር ጎጃምና ሌሎች የአማራ ክልል አካባቢዎች ለተሰማራው አግአዚ የማሰር፣ የመደብደብ ብሎም በተግባር እንደተስተዋለው የመግደል ፈቃድ የሰጡበት አግባብ ነበር።

የጥቃት ሰለባ ከመሆን የማያተርፈው እንደሆነ እስከ 2009 ዓ.ም. ድርስ ሲፈጸሙ የነበሩ ግፎች አስረጂ ናቸው።

በነሃሴ አጋማሽና መጨረሻዎቹ የመንግስት ባለስልጣናት በተለያዩ አዳራሾች ጎንደርን ነዋሪዎች፣ የሃይማኖት አባቶችንና ተዋቂ ሰዎችን ባነጋገሩበት ወቅት የአማራ የአባቶች መነሳሳትና ትብብር ፍንትው ብሎ ታይቷል። የአማራ ህዝብ በመንግስት ሰራዊት ተከቦ እየተተኮሰበት የሃይማኖት ወሪዎች ህዝቡን እንዲያረጋጉ ሲጠየቁ፣ መቃዎማቸውና ቅስቀሳ ማደረጋቸው የሚታወቅ ሲሆን አንድ አባት ከሙሴ የኦሪት መጽሃፍ ጠቅሰው "ርስትን የሚፈልስ የተረገመ ነው" በማለት ህዝቡ ከእርስቱ መነቀሉን አመላክተዋል። ሌላ የእስልምና የሃይማኖት አባት አሏህ ሁሌም ከተበዳዮች ጎን ነው የሚቆመው፤ አማራ እጂግ ተበድሏል እናም አሏህ ከኛ ጋር ነው ሲሉ የህዝቡን ብሶት አንጸባርቀዋል። ስብሰባው የተከናወነው በከንቲባ ጽህፈት ቤት በሚገኘው አዳራሽ፤ በሳይንስ አምባ በሚገኘው አዳራሽ (ገዱ አንዳርጋቸው የሚገኙበት) እና በፒያሳ በሚገኘው ሲኒማ አዳራሽ ነበር። በመሆኑም በሁሉም የአማራ ማህበረሰብ የመደራጀትና የመተባበር መንፈስ የሚመጣው ከሁኔታዎች ግፊት በመሆኑ የአማራ አመጽ ተባብሮ ራስን ለመከላከል እንቅስቀሴ ፈር ቀዳጅ ከመሆኑም በላይ የበደል ቀንበርን ላይሸከም የተነሳሳ ወጣት አፍርቷል። እምቢተኝነቱ የአማራን ህዝብ ህልውና የሚጠብቅ ጠንካራና በሳል አስተሳሰብን የተላበሰ ትውልድን በመፍጠር እምቅ የሆነውን የአማራ ህዝብ የአሸናፊነት ኃይል ብኩን እንዳይሆን መሰረት የሚጥልም ነው። ይህን ሲባል አመጹ በራሱ የተደራጀና ጠንካራ፣ ስርዓታዊ የሆነና ቁሳዊ ሃይል የታጀበ ነበር/ነው/ ለማለት እንዳልሆነ የሚሰመርበት ጉዳይ ነው።፤ ሆኖም ንቅናቄው የስነ-ልቦና መናበብን በወጣቱ ውስጥ ያሰረጸ፣ የአማራ ህዝብ ህልውናን ለመታደግ የጋራ አማራዊነት የተላበሰ ትግልን ያነሳሳ፣ አስፈላጊነቱንም ያስገነዘበ ነበር። ስለሆነም በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ኢትየጵያዊነትን የሚቀበል አማራዊነት ለማደራጀት ግፋ ሲልም በወጣቱ ዘንድ እየተቀነቀነ ላለው "ቤተ-አማራ" ወይም "የአማራ መንግስት" እሳቤ አነቃናቂ ክስተት ነው።

የትግል ትብብር ስሜትን ማጫር የቻለ ንቅናቄ መሆኑ፦ የአማራ ህዝብ የሌላውን የኢትዮጵያ ህዝብ በደልና ችግር እንደራሱ ችግር አድርጎ የመውሰድና እስከ መሰዋዕትነት የሚደርስ ታሪክ ያለው ቢሆነም ለመበርካታ አመታት መንግስት መር ታሪክን የማጉደፍ ተግባር ስለተፈጸመበት በጎ ታሪኮቹ እንዲደበቁ ተደርጓ። ይህ በሆነበት ወቅት ማህበረሰብ ጉዳይ የራሱ ጉዳይ አድረጎ የሚያስብ የአማራ ትውልድን የአባቶቹን ትወፊት ስለማስቀጠሉ በትይንተ ህዝቡ ወቅት የተስተዋሉ መፈክሮች ምስክሮች ናቸው። የኦሮሞ ወጣቶችን ሞች የሚያወግዙ፣ የኦሮሞ

ፖለቲከኞችን እስርና እንግልት የሚቃወም መፈክሮችን አንግበው በአደባባዮ ተስተውለዋል። በመንግስት የአማራና የኦሮሞ ትውልድ ጭድና ጫቃ ሆኖ በጋራ ክንድ በመከፋፈል ላይ ህልውናውን ያጸናውን ስርዓት የሚጋፈጡበትን መስመር የተለመ ነው። በትግባርም የዲያስፖራ የኦሮሞ ፖለቲከኞች የሃሳብ ለውጥ በማደረግ ከአማራ ልሂቃን ጋር በደርድር የኢትዮጵያን ህልውና ከከፋፋይ ስርዓት እንታደጋለን የሚል ሃሳብ እንዲሰነዝሩ አስችሏል።

በተጨማሪም የትይንተ-ህዝብ ተሳታፊዎች ለኦሮሞ ህዝብ ትግል አጋርነታቸውን ማሳየታቸው ስርዓቱ የሁለቱ ህዝብ የማይቀራረብ ነው ብሎ ስለሚያምንና ከፋፍሎ ለመግዛት ዋነኛ መሳሪያው ሲያደርገው እንደነበር ለማንኛውም ዜጋ ግልጽ እንዲሆን አድርጎታል። በዚህ ረገድ የመደጋገፉን ዜና የሰሙት የወቅቱ የኢፌዴሪ የኮሚዩኒኬሽን ሚኒስተር አቶ ጌታቸው ረዳ "የኦሮሞውና አማራው ቡድን እሳትና ጭድ ናቸው" በማላት የእሳቸውንና የመንግስታቸውን ሃሳብ ብሎም እንዲሆን የሚፈልጉትን ማለትም ምኞታቸውን በሚዲያ ተናግረዋል። እዚህ ላይ መንግስት ያቀራርባል እንጂ እንዴት እሳትና ጭድ ናቸው እያለ ይለፍፋል የሚል ጥያቀቄ ማንሳት የኢትዮጵያን መንግስት ስነ-ፍጥረትና አድገት ካለማወቅ ወይም ከሞኝነት የሚነሳ ነው። ያም ሆነ ይህ የአማራ ንቅናቄ የስርዓቱን የመጫወቻ ካርድ ያነተበ፣ያሰለለና የባለስልጣናቱን የከፋፋይነት ስሜት ለማንኛውም ዜጋ ያጋለጠ ነበር። በወቅቱ በኦሮሚና በአማራ ክልሎች የተቀሰቀሰው ተቃቆሞ መንግስት በ25 አመታት ውስጥ ከቀጠሙት ሁሉ የላቀ መሆኑን እየተገለጸ መሆኑን ዮናስ አባይ ጠቆሚል። ይህንን ሃሰብ መንግስትም ይጋራዋል። ይህም የአማራ ህዝብ መነቃነቅ የትብብር መንፈስ ከማጎልብት ባሻገር የሁለቱ ህዝቦች የጋራ ትግል ስርዓቱን በቀላሉ መሰረት የሚያሳጣው መሆኑን **በተግባር** ያሳየ ነው።

በሌላ በኩል ሰልፈኞች የትግራይ ህዝብን ከህወሃት ለጥሎ የሚያሳይና የትግራይ ህዝብ እንደህዝብ ከአማራ ህዝብ ጋር ጽብ እንደሌለው፣ እንደማይኖረው ላማሰየት የሞከሩበትም መፈክርና መግለጫም ታይቷልም፤ ተሰምቷልም። ይህኛውም ህወሃት ለትግራይ ህዝብ የመጡበሽ ፖለቲካ ቢነዛም የህዝብ ለህዝብ መልካም ግንኙነት በፖለቲካዊ ድርጅቶች ሴራ የሚሻክር ያለመሆኑም የሚያሳይ ነው።









የአማራን ክልል በሚያሰተዳደረው ብአዴን ላይ ጫና ማሳደሩ፦ እንድርጅት የብአዴን አፈጣጠርና አሁንም ያለብት ሁኔታ የሚያሳየው የአማራን ህዝብ ጥያቄን የዘነጋ ድርጅት መሆኑን ነው፡፡ ድርጅቱ በብዜር አማራ ያልሆኑ የህወሃትን ተልኮ ለማስፈጸም ሹም ሽር ሳይነካቸው የተቀመጡ የበላይ አመራሮች የሚዘውሩት እንደሆነ በስፋት ይነገራል፡፡ ትግባራቶቹም አማራ ድርጅት ስለመሆኑ የሚመሰክሩ አይደለም፡፡ የአማራ ህዝብባዊ አመጽ ከተከሰተ ወዲህ ግን በአማራ ህዝብ ላይ እየተፈጸሙ ያሉ በደሎችን የሚናገሩ የክልሉ አመራሮችን ለማየት ተችሏል፡፡ የክልሉ ምክር ቤት የጦፈ ክርክር የማደረግ እድል እንዲያገኝ፣

ከልማት እስከ ድንበር ይገባኛ ባሉ ጉዳዮች (የአማራ ጥያቄዎች በሆኑት ጉዳዮች) ላይ ሃላፊዎችን የመሞገት ወኔ የተላበሱ የድርጅቱ አመራሮች ብቅ ብቅ እንዲሉና በአባላት መካከል ያለመተማመን እንዲነግስ የራሱ አስተዋጽኦ አበርክቷል። ዛሬ ላይ እንደሚታየው የህዝቡ ጥያቄ እየተድበሰበሰ ሳይመለስ ከቆየ የወጣቱ የመተባበር መንፈስ የተቀጣጠለ በመሆኑም የድርጅቱ አባል አመራሮች የህዝብ ወገንተኝነታቸውን እንዲያጠናክሩ አበረታች ኃይል (Impetus) ይሆናቸዋል።

አማራ ተነጥሎ የጥቃት ሰላባ መሆኑን ለወጣቱ በስፋት የማስገንብ፣ የማሳቅ ሚናው፡ ከመፈክሮቹ ብንነሳ "አማራነት ይከበር! አማራነት ወንጀል አይደለም! የአዲሱ የአማራ ትውልድ ታሪክን የድሳል! የአማራ ህዝብ አሸባሪ አይደለም! አማራነት ወንጀል አይደለም! አማራን መግደል ይቁም! እና የመሳሰሉ በማንነት ላይ ያተኮረ ፖለቲካዊና ይዘት ያለው በደልን የሚያሳዩና የአማራ ብሄረተኝነትን ቀስቃሽ ጽሁፎችን አይተናል። በብዙው የአማራም ሆነ በሌላው ኢትዮጵያዊ ከሚታወቀው ፈር የለቀቀ ከሌሎች ክልሎች ዘር ከማጽዳት ተግባር በተጨማሪ የአማራ ክልል በሚል ተሰፍሮ በተሰጠው መሬት አማራ የጥቃት ሰለባ መሆኑን የሚያመላክት ህዝባዊ ቁጣ ነበር። በመሆኑም የችግሩን ግዝፈት ግንዛቤ ላልነበራቸው ሁሉ በማሳወቅ በህቡ ላይ የተጋረጠውን ችግር በጋራ የመታገሉን አስፈላጊነትና ውጤታማነቱንም አመላካች ነው።






#የአማራ_ተጋድሎ


Free Muslim
Committee


ድቁም!





ወልቃይት፡ የወልቃይት ህዝብ የጥያቄ ይዘትና ታሪካዊ ዳራው

የማንነት ጥያቄው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የአስተዳደር ክልሎች ከተዋቀሩበት በተለይም የወልቃይት፣ ጠለምትና ጸገዴ አካባቢዎች ወደ ትግራይ ከተካለሉበት ጊዜ ጀምሮ የነበረ ነው። እንደሚታወቀው የወልቃይት ህዝብ የማነት ጥያቄ በሚል የሚታወቀው የአማራ ተጋድሎ ችቦ ለኳሽ ንቅናቄ ነው። ጉዳዩ የማንነት ተባለ እንጂ የአማራ ማንነት በመርህ ደረጃ መልስ ካገኘ ቆይቷል። ችግሩ ከማንነት ጋር የሚያያዘው የአማራ ህዝብ በምዕራብ ትግራይ በተካለለው መሬቱ ላይ የአማራ ማንነቱን እንዲሸር፣ እንዲደመስስ፣ በምትኩ የሌላ ማህበረሰብ ማንነት እንዲቀዳ በመገደዱ ነው (የኮሚቴው አባላት መግለጫ 2008 ዓ.ም.)። ከዚህ ጋር ተያይዞ ስርዓታዊና የማያቋርጥ ዘር የመጽዳት ብሎም ከማንነት ጋር ዘርፈ ብዙ ትስስር ካለው መሬቱ ላይ እንዲጠፋ የማጽዳት ተግባር በህዝቡ ላይ እየተከናወነበት በመሆኑ በማንነት ላይ የተጋረጠውን አደጋ ለመመከት የተዘየደው ፖለቲካዊ ትግል የማንነት ጥያቄ በሚል ተሰይሟል። በአጠቃላይ ችግሩ በህግ የተደነገጉ መርሆች ለአማራ ህዝብ የማይሰሩ ከመሆናቸውና ባልተጻፉ የመጨቆኛ ህጎች ትግባራዊነት ጋር ጥብቅ ቁርኝት እንዳለው ባለፉት 26 አመታት ውስጥ በአማራ ህዝብ ላይ የደረሱት በደሎች ማስረጃዎች ናቸው።

በመሆኑም እድሜ ጠገቡ የወልቃይት ህዝብ ጥያቄ ትኩረት አንዳይስብ በመደረጉና የመብት ጠያቂዎቹ ህዝቦች የሃይል ምንጭ በመንጠፉ ተዳፍኖ የቆየ እንደነበርና ለሁለም ጊዜ አለው እንደተባለው በ2007/08 ዓ.ም. በተደራጀ ሁኔታ በመገንፈሉ የሚመለከታቸውን አካላት ያካለሉ

ጥያቄዎችም በማንነት ኮሚቴው አማካኝነት እንዲቀርቡ ተደረጓል፡፡ በቅድሚያ በ2008 ዓ.ም. ኮሚቴውና የአቤቱታ ደብዳቤው እንደሚያስረዳው የማንነት ጥያቄው የትግራይ ክልልን በዋናነት ስለሚመለከት በዚያው ክልል ላሉ ለአራት ተቋማት የቀረበ ሲሆን እነዚህም የትግራይ ክልል ርዕሰ መስተዳደር፤ የትግራይ ክልል የህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ ጽ/ቤት፤ለትግራይ ክልል የኢትዮጵያ የሰብኣዊ መብት ኮሚሽን ቅርንጫፍ ጽ/ቤትና የትግራይ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ናቸው፡፡

ጥያቄውን የወልቃይትን የመልከዓ ምድር አቀማመጥ፣ አዋሰኝ አካባቢዎች፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ መስተጋብር ዝርዝር ሁኔታዎችን የያዘ ነበር፡፡ ሙሉ ሃሳቡ እንደሚከተለው እንደወረደ ቀርቧል፡፡ እንደወረደ በተቀመጠው ደብዳቤ ወስጥ ውስን የቃላትና የፊደል ግድፈቶች ስለነበሩ በማረም የደብዳቤው ይዘት ለአንባቢያን የቀረበ መሆኑን ላስገነዝብ እወዳለሁ፡፡

የትግራይ ክልል ርዕሰ መስተዳደር፤
የትግራይ ክልል የህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ ጽ/ቤት
ለትግራይ ክልል የሰብኣዊ መብት ኮሚሽን
ጽ/ቤት እና የትግራይ ክልል ምክር ቤት
መቀሌ

ጉዳዩ፡- <u>የወልቃይት ህዝብ የአማራ ብሄረተኝነት የማንነት ጥያቄን ይመለከታል</u>

እኛ የወልቃይት ማህበረሰብ በታላቋና ገናናዋ ኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጉልህና አኩሪ ድርሻ ያለን፣ከአያት ቅድመ አያቶቻችን ዘመናት በጀምሮ ማንነታችን፣ ትውልዳዊ እርስታችን ታውቆ፣ ታፍሮና ተከብሮ ኖርን፤ ከትውልድ አስከ ትውልድ በክብር የምንዘምርለትና አኩሪ ኢትዮጵያዊ ማንነት ለን ኩሩ ህዝቦች ነን፡፡

የአካባቢችንን መልከኣ-ምድራዊ አቀማመጥ፣ ባህልና ቋንቋ፣ ሃገራዊ አስተዋጸዖና በመጨረሻም ዛሬ ያለንበትን ነባራዊ ሁኔታና ለለማንነት ጥያቄ ያስገደደንን ህጉ-መንግስታዊ ጥሰት አበይት ምክንቶች ሲሆኑ በተለይ የተፈጸመብንና እየተፈጸመብን የሚገኘውን ግፍና በደል፣ ታሪካዊና ትውልዳዊ ጥያቄያችን በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ምልከዓ-ምድር፡ *ወልቃይት በቀድሞው በዘመነ ኃ/ስላሴ በሰሜን በጌምድር ጠቅላይ ግዛት፣በወገራ አውራጃ፤ በደርግ፡ በጎንደር ክፍለ ሃገር በወገራ አውራጃ የሚገኝ ወረዳ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ከእኛ ህዝብ ፍላጎት ውጪ ማንነታችን ወደማይለጸበት በምዕራብ ትግራይ ዞን የተከለለ ሲሆን ነገር ግን እኛ ከአማራ ህዝብ ጋር በታሪክ፣ በባህል፣ በስነልቦና እና በመልከዓ-ምድር ተሳስረን የኖርን አሁንም የተሳሰርን ህዝቦች ነን፡፡*

አዋሳኞቹ፡ በሰሜን- ተከዜ (ኤርትራ)
በደቡብ- ጠገዴ (በአማራ ክልል በኩል ማለት ነው)

በምስራቅ-- የተከዜ ወንዝ (ትግራይ)
በምዕራብ- አርማጨሆና ሱዳን ናቸው

ባህልና ቋንቋ፡ *የወልቃይት ማህበረሰብ ኢትዮጵዊ አማራ ሲሆን የራሱ የሆነ አማረና ዘይቤና ምልአት ያለው፣ የትግሬና (የድንበርተኛ) ቋንቋዎች፣ አልፎ አልፎም ከሱዳን በሚዋሰኑ አካባቢዎች የሱዳን አረብኛ ይናገራል። ባህላዊ ዘፈኑ፣ ጭፈራውና ዳንኪራው፣ የሃዘን እንጉርጉሮው፣ ቀረርቶውና ሽለላው፣ሃይማኖታዊ ስነ-ሰርዓቱ እንዲሁም ምሳሌያዊ አነጋገሮቹ ሳይቀር በአማረኛ የሚከወኑ ሲሆን የራሱ የሆነው ትግሬኛም ከኤርትራና ከትግራይ ድንበሮች እየራቀ በሄደ ቁጥር እየሞተ (attenuate) ይሄዳል። ይህ በእንዲህ እለ እኛ ወልቃይቶች ከትግራይ ጋር የሚያመሳስለን ነገር ቢኖር ተግሬኛ መናገራችን ሲሆን ይህም የእኛ ትግሬኛና የእነሱ ትግሬና ሰፊ ልዩነት አለው። ከዚህ ውጪ ከትግራይ ጋር በባህል፣ በታሪክ፣ በስነልቦናና በመሳሰሉት የማንነት ዋና ዋና መስፈርቶች አንገናኝም።*

ሃገራዊ አስተዋጽኦ

<u>*በኢኮኖሚ ዘርፍ፡*</u> *የወልቃይት አብዛኛው ህዝብ በግብርና ሙያ የሚተዳደር ሲሆን የወባ በሽታን (ንዳድ)፣ አንበሳና ነብሩን፣ ጊንጥና እባብ ንክሻን ተቋቁሞ መዘጋ፣ ወልቃይትንና ሁመራን መሳሰሉ ገናና የእርሻ ቦታዎችን ለማ ፣በሃገራችን ኢትዮጵያ ታዋቂና ገናና የነበረውን የሜካናይዝድ እርሻን በመጠቀም በአንድ ወቅትም ከ1500 ያላነሱ ትራክተሮችን በመጠቀም ሰሊጥ፣ ጥጥና ማሽላ በገፍ በማምረት አካባቢውን አልምቷል። በነዚህ የልማት ዘመናትም ከልማቱ ኢኮኖሚዊ ጠቀሜታ ከማስገኘት ባሻገር ታላላቅ ሃገራዊ ፋይዳ ያላቸው ቁምነገሮችን አከናውኗል። አሁን ባለንበት የልማት ጎዳና ምንም እንኳን የልማት እድል ባያገኝ በተለያዩ ክልሎች ተሰዶ ዘመናዊ እርሻ እያስተዋወቀ ያለ ህዝብ ነው።*

<u>በፖለቲካው ዘርፍ፡</u> እኛ ወልቃይት ህዝቦች እንደሌላው የሃገራችን እዝቦች ለሃገራችን ማበርከት የነበረብንን ትግል ሁሉ ያካሄድንና በማካሄድ ላይ ያለን ህዝቦች ነን። በተለይ ከደርግ መደምሰስ በፊት አሁም በሃገራችን ለሰፈነው የሰላም የልማት አቢዎታዊ የዲሞክራሲ መድረክ በትጥቅ ትግል፣ ለትግሉ እንደባህር ወደብ ሆነን፣ ትግሉን ከውጪው አለም ጋር እንዲገናኝ ያደረግን፣ የድርጅቱ ቤዝ ሆነን የታገልንና ያታገልን ህዝቦች ነን።

የወልቃይት ህዝብ የአማራ ብሄረተኝነት የማንነት ጥያቄ ምንጭ ወይም መነሻ ሁኔታ

በመሰረቱ የወልቃይት ህዝብ የአማራ ብሄረተኝነት የማንነት ጥያቄ አሁን የተነሳ ጥያቄ ሳይሆን ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ የተነሳና በህገ-መንግስቱ የሰፈሩት ሃሳቦች ታይተው ምላሽ ያልተሰጠው፣ በየጊዜው እየተንከባለለ የመጣና በተደራጀ መንገድ ጥያቄው እንደጥያቄ አሁን ባለንበት የአቢዎታዊ ዲሞክራሲ መስመር ይፈታል ብሎ በአመለካከት ባለመያዙና ይህን ጥያቄ እንደጥያቄ ማንሳት በህግ እንደማያስቀጣና ህገ-መንግስታዊ መብት ነው ብሎ እንደመብት ተደርጎ ባለመወሰዱ የተነሳ ሲንከባለል የቆየ ጥያቄ እንጂ አዲስ ጥያቄ አይደለም።

የወልቀይት አማራ ብሄረተኝነት ጥያቄ እንደጥያቄ ሲነሳ ዋናው መነሻው ህገ-መንግስቱን መሰረት ያደረገ ነው። በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 39፣ ተራ ቁጥር (ንኡስ አንቀጽ 2 እና 5 ለማለት ነው) እንደሚከተለው ያስቀምጠዋል። ተራ ቁጥር 2 (አንቀጽ ሁለትን ለመግለጽ ነው) ፦ "ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰብና ህዝብ ቋንቋውን የማሳደግ ባህሉን የመግለጽ፣

የማዳበር እንዲሁም ታሪኩም የመንከባከብ መብት አለው" ይላል። ከዚህ በተጨማሪ በተራ ቁጥር 5 (አንቀጽ) በዚህ ህገ-መንግስት ውስጥ ብሄር ብሄረሰቦች፣ ህዝቦች ማለት ከዚህ ቀጥሎ የተገለጸውን ባህሪ የሚያሳይ ማህበረሰብ ነው። ሰፋ ያለ የጋራ ባህሪ የሚያንጸባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፤ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው፣ ጋራ ወይም የተዛመደ ህልውና አለን ብለው የሚያምኑ፣ የስነ-ልቦና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተተያያዘ መልከዓ-ምድር የሚኖሩ ናቸው።

በወልቃይት ህዝብ የደረሱ የፖለቲካ ተጽዕኖዎች

- ልጆቻችን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዳይማሩ፣ በግድ በትግሬኛ እንዲማሩ ተደርገዋል፤
- የአማራ ባህል ቀይራችሁ በግድ የትግሬኛ ባህል ተቀበሉ እየተባልን ነው፤
- የአካባቢያችን ጥንታዊ የሃገር፣ የወልና የጋራ ስሞች ማለትም የወረዳ ከተማ፣ መንደር፣ወንዝ ጋራ፣ ሸንተረር፣ምንጭ በትግራይ ስም ተሰይመዋል፤
- በትግራይ ባሉ መስሪ ቤቶች የወልቃይት ተወላጆች 5 በመቶ የትግራይ ተወላጆች 95 በመቶ ሲሆን ያሉትም እኩል መብት እና ስልጣን የላቸውም፤
- ትግራይ ክልል መሆን አንፈልግም ብለው የተቃወሙትን ከ300 በላይ የሚሆኑ የወልቃይት ተወላጆችን ከየቤታቸው በጨለማ ታፍነው ተወስደው ያለፍርድ ጠፍተዋል፤
- ለዚህም አባሪውን መመልከት ይቻላል (አባሪ አያይዘዋል)፤ ለነዚህ ወገኖች በአመለካከታቸው የተነሳ ለመጥፋታቸው ዋነኛው ምክንያት የማንነት ጥያቄ ማንሳታቸው በመሆኑ የወገኖቻችን መጥፋት የህገ-መንግስት ጥሰት ስለሆነና ይህን የፈጸመ የትግራይ ክልል መንግስት መሆኑ፤
- ሴት ልጆቻችን እና እህቶቻችን ባላችው እንዲታሰርና እየተተደረገ በትግራይ ተወላጆች በግድ እየተደፈሩ እንዲወልዱ ተደርገዋል፤ ሴት ተማሪዎች፣ ተደፍረዋል፣ ቤተሰብ አቤት ቢልም ወልቃይት እንዲያወም ይህ በያንሳችሁ ነው የሚል መልስ ተሰጥቷል፤ በማንኛውም መድረክ እንዳንነጋገር ሰብአዊ መብታችንን እንዳንጠቀም ተደርገናል፣ ከተናገርን ደግሞ የዱሮ ስርዓት ድጋፍ ነው ወዘተ...በማለት እንድንታሰር ተደርገናል፤
- ወልቃይት በመወለዳችን በማንነታችን እንድናፍር ተደርገናል።

የወልቃይት ህዝብ በኢኮኖሚ የደረሰብት በደል

- ትግራይ አይደለንም ያሉ በቀጥታ ሃብታቸውን ንብረታቸውን ተወርሰዋል(ዝርዝሩ በአባሪነተረ ተያይዟል)
- መሬታችን ተነጥቆ ለትግራይ ተወላጅ በመሰጠቱ የወልቃይት ተወላጆች ወደ ድህነት እንድንወርድ ተደርጓል፣ በግልባጭ የትግራይ ተወላጆች ያለአግባብ ሃብታም እንዲሆኑ ተደርጓል፤...

...ያለ ይቀጥል። ንብረታቸው የተወሰደባቸውን፣ የተገደሉ የተፈናቀሉ ሰዎችን ዝርዝር በአባሪነት በማያያዝ አቤቱታው በዝርዝር እንዲቀርብ ተደርጓል። ከላይ እንዳለ/እንደወረደ

የተጠቀሰው ደብዳቤ እንዳለ ሆኖ በቅድሚያ የማንነት ኮሚቴው ጥያቄውን ለትግራይ ክልል መንግስት፣ ለአማራ ክልል መንግስት፣ እንዲሁም ለሁለቱም ክልል ገዢ ፓርቲዎች አመልክተው የትግራይ ክልል አስተዳደር ጥያቄውን ከነጠያቂው እንዲከስም እንደሞከረ የኮሚቴው አባለት በመግለጫቸው አስረድተዋል። ለአብነት የዞኑ (የምዕራብ ትግራጥ ዞን) ሃላፊና ሌሎች የትግራይ ክልል መንግስት ሃላፊዎች ጥያቄው ሲቀርብላቸው "ወልቃይት ታግሎ ትግራዊነቱን ያረጋገጠ ስለሆነ አርፋችሁ ተቀመጡ" ስመባለቸውም የኮሚቴው አባላት ማረጋገጫ ስጥተዋል።

ማንም ሰው እንደሚገነዘበው ይህ ጥያቄ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት የቀረበ ቢሆንም ባለስልጣናቱና የመንግስት ቢሮዎች የተለያዩ ጉዳዩን ለማጣጣል ወይም ለማዳፈን የታለመ ምላሾችን ሲሰነዝሩ እንደነበር ነው። ለምሳሌ "ማንነት ጥያቄ መልስ ካገኝ ቆይቷል"፤ "ጥያቄው የህዝብን ፍላጎት አያንጸባርቅም" "የጸረ-ሰላም ሃይሎች ግፊት ነው" ወዘተ.....የሚሉ ይገኙበታል።

ያም ሆኖ ጠያቂዎቹ አቤቱታቸውን አላቋረጡም፣ለፊደራሉ መንግስት በተለይም ጉዳዩ ለሚመለከተው የፌደሬሽን ምክር ቤት ለማቅረብ ወደ አዲስ አበባ ተጓዙ። ግን የህወሃት ጫና አልተቋረጠም። ወደ አዲስ አበባ ባደረጉት ጉዞ ጫንጮ (ኦሮሚያ ክልል) ላይ በጸጥታ ኃይሎች የደረሰባቸው እንግልት (በኦሮሚያ ክልል መንግስት እገዛ ከእገታ በኋላ ሊጓዙ ቢችሉም)፣ አዲስ አበባ ላይ ወከባና እንደከባድ ወንጀልኛ አሻራ እንዲሰጡ የማድረግ ተግባር ተፈጽሟል። ይህ ሁሉ አጀንዳው የህዝባዊ አመጽ መንስኤ ከመሆኑ ቀደም ብሎ የተከናወነ ነው። ከወከባው በኋላ በጥር 25 ቀን 2008 ዓም. እና የካቲት 19 ቀን 2008 ዓ.ም. ለፌደራሉ መንግስት አመልክተው/ጥያቄያቸውን አቅርበው/ አቤቱታው በቀጥታ የሚመለከተው የፌደሬሽን ምክር ቤት ጉዳዩ በትግራይ ክልል በተዋረድ ቀርቦ ሊፈታ የሚገባው ስለሆነ ወደዚያ መርቸዋለሁ ሲል

ደብዳቤ[40] ጽፎላቸው ነበር። የፌደሬሽን ምክር ቤት የጻፈው ደብዳቤ በደል ተፈጸመብን ብለው የከሰሱት የትግራይ ክልል መንግስት ራሱ ዳኛ እንዲሆን ያስቻለ ሆነ። ገለልተኛ አካል ፍትህን እንዲያሰፍን የሚችልበት አኳኋን እንደማይኖር የሚያስገነዝብም ውሳኔ ነበር። "ዱሮ አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ" ይባል ነበር። ይህኛ ጉዳይ ግን ከዚህም የባሰ ነው። "ጠዋት ቀማኛ ማታ ላይ ዳኛ" እንደማለት ነው።

ጥያቄው ከታችኛው የመንግስት መዋር መጀመር እንዳለበት ለማንም ግልጽ ነው። ግን ተሞክሯል። ምናልባትም የትግራይ ክልል ቢሮዎችና ባለስልጣናት በየመድረኮች ጥያቄውን የሚያዳፍንና መልስና ማስፈራሪያ ከመስጠት ያለፉ በሰነድ የተደገፈ መልስ ስለመስጠታቸው እጠራጠራለሁ። በተዋረድ ጉዳዩ የቀረበላቸው የክልሉ የመንግስት አካላት በሰነድ የተደገፈ መልስ ካልሰጡ ኮሚቴው ለፌደሬሽን ምክር ቤት የሚያቀርበው ጉዳዩ ለክልሉ መንግስት እንደቀረበና እምቢተኛ መልስ እንደተሰጠ ሊያሰረዳለት የሚችል ሰነድ አይኖረውም ማለት ነው። በዋናነት በትግራይ ክልል መንግስት መፍትሄ ይሰጠው የሚለውን የፈደሬሽን ምክር ቤትና የኢህአዴግ መንግስትን ውሳኔ ከታች የከተብኳት ሃገርኛ የህዝብ ግጥም ትገልጸዋለች።

ዳኛው ዝንጀሮ ፍርድ ቤቱም ገደል
እምን ላይ ተቁሞ ይነገራል በደል።

የወልቃይት ታሪካዊ ዳራ፡ የታሪክ ማስረጃዎችና ማህበራዊ እሴቶች

ዴሞክራሲያዊና ከተስፋፊ ብሄረተኝነት የጽዳ ሃገራዊ ስርዓት ባለበት ሁኔታ ወልቃይት በአማራ ክልል መካለሉ ወይም በትግራይ ክልል መካተቱ የችግሮች መንስዔ ይሆናል የሚል እምነት ማሳደር አይቻልም። ለመከራከርም የሚያበቃ ጉዳይ አይደለም። ዋናው ነገር በወልቃይት የሚኖረውን ህዝብ ያለአድሎ በፍትሃዊ የሚያስተዳደር የመንግስት ስርዓት መስፍኑና

40

ለትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት (መቀሌ)
ጉዳዩ፡ ለምክር ቤቱ የቀረቡ ጥያቄዎችን ይመለከታል
በትግራይ ብሄራዊ ክልል ውስጥ የሚኖሩ የወልቃይትና የጠገዴ ህዝቦች ተወካዮች ነን በሚል ጥር 25 ቀን 2008 ዓም. እና የካቲት 19 ቀን 2008 ዓ.ም. የተጻፈ አቤቱታ ለምክር ቤታችን አቅርበዋል፡ ፡በአቤቱታቸውም የማንነትና ሌሎች ተያያዥ መብቶች እንዲከበሩልን የሚል ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን የምክር ቤቱ የህገ-መንገስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጉዳዩን ተመልክቶ በቅርቡ በተካሄደው የምክር ቤቱ መደበኛ ጉባኤ ቀርቦ አቅጣጫ መቀመጡ ይታወቃል። በዚሁ መሰረት የፌደሬሽን ምክርቤትን ለማጠናከርና ስልጣንን ተግባርን ለመዘርዘር በወጣው አዋጅ ቁጥር 251/1993 ዓ.ም.አንቀጽ 20 እንደተመለከተው እንዲህ አይነት ጥያቄዎችን አስቀድመው በክልል በሚገኙ የተለያዩ የመስተዳድር እርከኖች ቀርበው መፍትሄ የሚሰጣቸው ሲሆን ቀጥታ ለምክር ቤቱ ሊቀርቡ እንደማይችሉ ግንዛቤ ተይዟል። በመሆኑም በአቤቱታ አቅራቢዎች የቀረበው የማንነትና ሌሎች ተያያዥ የመብት ጥያቄዎች በክልሉ በኩል ቀርበው መፍትሄ እንዲሰጠው ጉዳዩን የመለስን መሆኑን እናሳውቃለን።
ያለው አባተ ረታ፤- የፌደሬሽን መ/ቤት አፈጉባኤ
ግልባጭ፡
ለህገ-መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤
ለፌደሬሽን ም/ቤት ጽ/ቤት፤
ለፌደሬሽን ም/ቤት፤
ለአቤቱታ አቅራቢዎች ወኪሎች
ባሉበት

ያለመስፈኑ ላይ ነው፡፡ የወልቃይትን ነባራዊ ሁኔታ ስንመለከት እንደሚታወቀው ለወልቃይት ህዝቦች የአማራ ማንነት ጥያቄ መነሻው በብሄር ፖለቲካ ላይ በተንጠለጠለው በሃገሪቱ ፌደራላዊ ስርዓት ውስጥ የአማራ ማነንትን ማንጸባረቅ ብሎም አማራ መሆን ለመጨቆን እንደ አንድ ምክንያት መሆኑ ላይ ነው፡፡ በተግባር እያንዳንዱ የአማራ ትውልድ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጫናው እንዲደርሰው የሚያስች የተጻፈም (በተለያዩ ክልሎች አማራ እንዳይወከል የሚያደርጉ ህጎን መጥቀስ ይቻላል) ያልተጻፈም (በተግባር ብቻ የሚገለጹ) ህግጋት አሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተለይም የህወሃት ነባር አመራሮች የአማራን አክርካሬ ሰበራ ስምሪት ሰጪ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በክልሉ አማራ ማንነት በሚያንጸባርቁ ዜጎች ላይ የሚያደረግ አድሎና የፍትህ መጓደል የማንነት ጥያቄ ለማንሳትና ወደአማራ ክልል እንካለል እንዲሉ በቂ ምክንያት ይሆናል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው አማራ ነን በማለት ማንነታቸውን፣ ታሪክንና የዛረውን ነባራዊ ሁኔታ በማስረገጥ የሚከራከሩ ሰዎች እያሉ በትግሬኛ ቋንቋ ካልተማራችሁ የሚል አቋም ማራመድ፤ ጥያቄውን ለማዳፈን ጠያቂዎችን የማሸማቀቅ ብሎም ወልቃይቶች እንደሚሉት የሰዎችን ደብዛ የማጥፋት፣ሃብት ንብረት የመውረስ፣ ማደህየትና የማፈናቀል ተግባር መፈጸሙ ጉዳዩን አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንዲደርስና ከአማራ ህዝብ ጋር የመካለልን ጥያቄ ብቸኛ አማራጭ እንዲሆን ያችለዋል፡፡ አስችሎታልም፡፡ ይህን ሃሳብ በተለያዩ ጊዜ በወልቃይት የማንነት ጠያቂ ኮሚቴ የቀረቡ አቤቱታዎች የሚያጠናክሩት ሲሆን ወደ ነውጥ መየሩም የግፉን ጥግ የሚያሰይ ነው፡፡ ይህን ሃሳብ እዚህ ላይ እናቁምና የዚህ ክፍል ዋና ትኩረት ወደሆነው የወልቃይት አስተዳደራዊ ታሪክ እንሻገር፡፡

ወልቃይት አማራ ነው ወይም የአማራ ማንነት አለው በሚል በአንድ ወገን በሌላ ወገን ወልዋይት የትግራይ ማንነት አለው የሚሉ ተከራካሪዎች አሉ፡፡ የትግራይ ታጋዮችና ደጋፊዎቻቸው ወልቃይት የትግራይ ማንነት ታሪክ ያለው ነው በሚል የመከራከሪያ ሀሳቦችን ሲያቀርቡ በተቀቃራነው ወልቃይት ዛሬ ላይ ያለውን የአከላለል ቅርጽ ይዞ እንደማያውቅ የሚያረጋግጡ የጽሁፍና የሰው ማስረጃዎች አሉ፡፡ የወልቃይት ህዝብ የማንነት ኮሚቴም የሁለተኛውን የታሪክ አተያይ መሰረት አድርጎ የሚንቀሳቀስ ቡድን ነው፡፡ ስለሆነም የማንነት ጥያቄውን መሰረታዊ ጉዳይ በጥልቀት ለመረዳትና የክርክሩን ምክንያታዊነት ለመርመር የቀድሞውን የአስተዳደር አከላለልና የወልቃይት ህዝብን ታሪካዊ ሁኔታ መዳሰሱ አስፈላጊነት ስለሚኖረው በሚከተሉት አንቀጾች የተለያዩ መረጃዎችን በመፈተሽ ትንታኔዎች ይቀርባሉ፡፡

ወልቃይት በትግራይ ተካሎ አያቅው ከሚለው የታሪክ ተዋስዖ ልጀምር። በቀድሞው ስርዓቶች ወልቀይት በበጌ ምድር ክፍለ ሃገር የሚተዳደር እንደንበረ የታሪክ ማስረጃዎችን (ለምሳሌ የታሪክ መዛግብትን፣ የአጼዎቹንና የወታደራዊ መንግስቱን ኣስተዳደራዊ ካርታ) በስፋት ማግኘት እንችላለን። የሚያከራክርም ጉዳይ አይደለም። የህወሃት ተከራካሪዎችም ይህን አይክዱም። ወልቃይት የትግራይ ነው ማለታቸው ግን የማይዛነፍ አቋም ነው።

አቻሜለህ ታምሩ የተባለ ጸሃፊ ከአስራ አምስተኛው ክፍለ-ዘመን እስከ ኢህአዴግ አዲስ አበባን እስከተቆጣጠረ ድረስ ወልቃይት የጎንደር አካል እንደነበር የሰነድና የካርታ ማስረጃውች መኖራቸውን ያወሳል። ሃሳብን ሲያጠናክርም ፕሎውደን[41] የተሰኘ አውሮፓዊ የታሪክ ተመራማሪ እ.ኤ.አ. በ1948 እንደጻፈው የትግራይ አካባቢዎችን ዘርዝሮ በደቡብ ከተከዜ ወንዝ መለስ እንደሆነ መግለጹን ያትታል። ሌላው ሚሽነሪ ጆሴፕ ኢሚሌ ኩልቤክስ[42] የወልቃይት ህዝብ የአማራ ማንነት የተላበሰ መሆኑን ጽፏል። የተከዜ ወንዝ የአማራንና የትግራይን ድንበር በአግባቡ የሚወስን መሆኑን ደግሞ እኤአ በ1968 የተጻፈው የሄነሪ አሮን ስተርን[43] ጽሁፍ ያስረዳናል። እነዚህ መረጃዎች ተከዜ የሁለቱ ህዝቦች የተፈጥሮ ድንበር መሆኑን የሚያረጋገጡ ናቸው።

በሌላ በኩል በቀድሞዎች ስርዓቶች ከኢህዴግ በፊት የነበሩትን ለማለት ነው የብሄር አወቃቀር ስላልነበረ ወልቃይት አማራ ነው ለማለት አያስደፍርም የሚሉ ተከራካሪዎች አሉ። የክርክሩ መነሻ ልክ ነው፣ በነዚህ ዘመናት ብሄርን ዋነኛ መሰረት ያደረገ የአስተዳደር ድልድል ተግባራዊ አልተደረገም ነበር። ሆኖም ግን የትኛው ብሄር በቀደምትነት የትኛው አካባቢ እንደሚኖር የሚታወቅ ነው። ለዚህም ነው በጉዳዩ ላይ የተደረጉ ጥናቶችን መፈተሽ ብሎም ምሁራን፣ አካባቢውን በተሻለ ደረጃ የሚያውቁ የእድሜ ባለጸጎችና ባለስልጣናት ምስክርነታቸውን

[41]Among the nineteenth century notable foreign writers about northern Ethiopia is Walter Chichele Plowden who traveled as a missionary in 1848 and wrote the book "Travels in Abyssinia and the Galla Country: With an Account of a Mission to Ras Ali in 1848". According to Plowden, by then, the region of Tigray consisted of all Christian regions North of the Tekeze River. The sub-divisions were Hamasen, Saraye, Akale guzay, Agame, Tigray proper, Shire, Adiabo, Temben, Inderta, Woggerat, and Silalo. The writer clearly wrote that the river Tekeze is the line separating the Tigray province and Gondar where the people of Wolkait are located (Achamenleh tamiru, 2016).

[42]Another missionary Joseph-Émile Coulbeaux of France wrote a book on the location and identity of Wolkait people as inhabitants of Gondar-Amhara. Joseph-Émile Baeteman (September 29, 1880 – 1938) was a French missionary and religious writer. In 1905 he went to Ethiopia for teaching, but he returned to France during World War I, in which he served at the front.

[43]Henry Aaron Stern wrote a book entitled as "Wanderings among Falashas in Abyssinia: together with a description of the country and its various inhabitants", he pointed out the situation of the Jewish refugees or Falashas and wrote also that the boundaries which, in imitation of the "cities of refugee" the avenger of blood dare not pass with hostile intent are well defined by Tekeze between Tigre and Amhara, the abay between shwa and Gojjam…(Stern, Henry 1868).

እንዲሰጡ የሚያስፈልገው። ከነዚህ መረጃዎች አንጻር የተቃኙትን የሚከተሉትን ታሪክ-ነክ ገለጻዎች እንመልከት።

ከሽህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ሶስት በፊት አካባቢው ብዙም ሰዎች ያልሰፈሩበት እንደነበረና ወልቃይቴዎች ወደ በርሃው እየተጓዙ ሰሊጥ እያመርቱ እንደሚመለሱ የአካባቢው የእድሜ ባለጸጎች ይነገራል። በዚሁ ዘመን የትግራይ ሰዎችም ለቀን ስራ ወደወልቃይት መጥተው በቀን ስራ ተሰማርተው ወደ አካባቢያቸው ይመለሱ እንደነበርና ኋላ ኋል ግን በወልቃይት ሰዎች ፈቃድ እዚያው እንዲቆዩም የተደረጉ እንዳሉ የሚታወቅ ጉዳይ ነው ሲሉ ። በ2008 ዓ.ም. በቀድሞው ስርዓት የትግራይ ጠቅላይ ግዛት አስተዳዳሪ የነበሩት ልዑል ራስ ስዩም መንገሻ[44] ከቪ.ኦ.ዔ. ራዲዮ የአማራኛ ቋንቋ ጋዜጠኛ ጋር ባደረጉት ቃለ-ምልልስ የትግራይ ክልል ከተከዜ አልፎ እንደማያውቅ አረጋግጠዋል። እንደእርሳቸው ገለጻ የትግራይ አዋሳኝ በሰሜን በኩል መረብ ወንዝ ከኤርትራ፣በደቡብ በኩል ከበጌ ምድር ተከዜ ወንዝ ሲሆን ወልቃይት በበጌ ምድር ይተዳደር ነበር። ጋዜጠኛዋ "ከ1943-48 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ነው ወደበጌ ምድር የተካለለው፣ ከዚያ በፊት የትግራይ ክልል አካል ነበር በሚል መረጃ የሰጡን ሰው አሉ ይህንን መረጃ እንዴት ያዩታል" ስትል ላቀረበችላቸው ጥያቄ "ይህን አሁን ነው የምሰማው" ብለዋል። አክለውም ኮሎኔል ታምራት ይገዙ የበጌ ምድር ጠቅላይ ግዛት አስተዳዳሪ በነበሩ ጊዜ በወልቃይት የልማት ስራ በመተጋገዝ ሰርተናል እንጂ ግዛቱ የትግራይ አልነበረም ብለዋል።

ከላይ በጋዜጠኛዋ የተገለጸውን "ከ1943-48 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ነው ወደበጌምድር የተካለለው የሚል መረጃ አለ" የሚለውን ሃሳብ በአትኩሮች ብንመለከተው ልኡሉ መረጃው አዲስ እንደሆነባቸው አመላክተዋል። እንደ እውነቱ ከሆነ ከእርሳቸው (ከልዑል ራስ ስዩም) ያወቀ ላሳር። ከእርሳቸው የተሻለ የሚያስተዳደሩትን ክልል የሚያካልሉ አካባቢዎችን የሚያውቅ የለምና። የትግራይ ተወላጆነታቸው ላይ ጥያቄ ስለማይነሳ ልዑሉ ለአማራ በማዳላት አስተያየት ሰጡ ለማለት የሚደፍርም አይኖርም።

የታሪክ ማስረጃም ብንመረምርም ከልዑሉ የሚቃረን ሃሳብ አናገኝም። እንሆ። በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ በምርምር የተካነው አልቤርቶ ስባኪ ጽፎት በእምሻው አለማየሁ የተተረጎመው መጽሃፍ "በ18ኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያና በ19ኛው አጋማሽ ኢትዮጵያ በበርካታ አነስተኛ ግዛቶች የተከፋፈለች" እንደነበረች ይገልጽና ጎጃም፣ ትግራይ፣ በጌምድር-አማራና ሸዋ ዋና ዋናዎቹ

[44]ልኡል ራስ መንገሻ ስዩም፣ የራስ ስዩም የመንገሻ ልጅ፣ የራስ መንገሻ ዮሀንስ አራተኛ የልጅ-ልጅ (grandson) ፣ የካሳ መርጫ (ዮሃንስ መርጫ አራተኛ) የልጅ ልጅ ልጅ (great grabdson) እና ከ1953 እስከ 1966 ዓ.ም. ለ14 አመታት የትግራይ ጠቅላይ ግዛት አስተዳዳሪ የነበሩ ናቸው።

ናቸው ይለናል። ከዚህ ታሪክ በግልጽ የምንረዳው ምናልባትም ከ1775 እስከ 1850ዎቹ ባሉት አመታት ውስጥ በጌምድር-አማራ አንዱ የኢትዮጵያ ግዛት ነበር የሚለውን ነው። እዚህ ላይ በጌምድር በ1943 ዓ.ም. የተካለለች ግዛት እንዳልሆነች ልብ ይሏል። ትግራይ ለረጅም ጊዜ የራሱ ነገስታት የነበሯት የታፈረች አካባቢና በግልጽም አካባቢው የትግራይ ግዛት ተብሎ ሲሰየም በጌምድር የሚለውን ስም ስናይ ግን አማራ የሚል ቅጽል ተሰጥቶታል። ስለሆነም ከ1943 እስከ 48 ድረስ ያሉት አመታት የ20ኛው ክፍለ-ዘመን በመሆናቸው ከላይ ባለው የታሪክ መስረጃ መሰረት በጌምርድ-አማራ (ወልቃይት የሚገኝበት ግዛት) ከ20ኛው ክፍለ ዘመን በፊትም የአማራ ህዝብ ማንነት የሚንጸባረቅበት እንደሚሆን መረዳት ይቻላል።

በጉዳዩ ላይ የሕወሓት የቀድሞ ሰዎችም ምስክርነት እንደሰጡም ይታወቃል። ገብረመድህን አርዕያ የተባሉ የሕወሓት የቀድሞ ታጋይ እንደጻፉት ከታህሳስ 1969 ዓ.ም. ጀምሮ ድርጅታቸው ከወሎና ከጎንደር የትግራይ መሬት ነው በማለት በኃይል ተነጥቆ የተወሰደ መሬት አለ፤ከጎንደር ክፍለ ሃገር ወልቃይ፣ ጸገዴ ጸለምትና ሁመራ ከወሎ ደግሞ ራያና ቆቦን በካርታ ወደ ትግራይ አካቶ ይዟል (መስፍን ወልደማሪያም፣ 2007 ዓ.ም. ፡61)። በዚያው መሰረት ከ1983 ዓ.ም. ወዲህ በተግባር ተቆጣጥሮሯል። “ከባለቤቱ ያወቀ ላሳር” የሚል ሀገራዊ ተረት አለ። ገብረመድህን ከድርጅቱ ባለቤቶች አንዱ ናቸው፤ በመሆኑም ከስር መሰረቱ የድርጅቱን ጉዳይ ወይም አላማ አብጠርጥረው ያውቁታል። ስለሆነም የውስጥ አዋቂ መረጃ ተብሎ መወሰድ የሚችል ነው። ከሁሉም በላይ አቶ ገብረመድህን የሚያወጧቸውን መረጃዎች ፉርሽ የሚያደርግ አሳማኝ የታሪክ ማስረጃ በሕወሓት መቅረብ ያለቻሉ የውስጥ አዋቂውን ምንጪ በታማኝነት እንድንቀበል የሚያደርገን ነው። ዶክተር ጌታቸው ረዳ (2006 ዓ.ም.) እንደጻፉ ከጎንደርና ከወሎ ተቆርሰው የተወሰዱ መሬቶች (በእሳቸው ገለጻ የመሬት ቅሚያ ይሰኛል) ወደ ትግራይ ክልል መካለላቸውን ገልጸው ይህንም እስራሎች ከፍልስጤም ‘የዌስት ባንክን’ መሬት ቀምተው ለሰፋሪ እስራሎች ከመስጠታቸው ጋር የሚመሳሰል ነው።

የመሬት መሬትና ህዝብ ወደትግራይ ተሻገረ ወደአማራ ክልል ተደመረ ወይም በጌ ምድር ሆኖ ቆየ ትልቅ የፖለቲካ ማጠንጠኛ ይሆናል ብሎ ለማሰብ የማያስችልበት ሁኔታ አለ። ብዙዎቻችን ወደትኛውም ክልል የተካለለ መሬትና ህዝብ የኢትዮጵያ አካል መሆኑን ልናስብ ተገቢም የሚሆንብት አግባብ አለ። ዋናው ጉዳይ የትም የሚኖር ኢትዮጵያዊን እንደሰው መብቱን በመጠበቅና ከሃገሩ ሊያገኘው የሚገባውን ማንኛውንም ተጠቃሚነት ሳይሸራረፍ መረጋገጥ ላይ እና ሁሉንም በእኩልነትና በፍትሃዊነት ነው የሚስተናግድ ስርዓት በዘርጋቱ ላይ ነበር። ግን

አልሆነም፤ ይህ ያለመሆኑም የድርጅቱን ወይም የስርዓርቱን ሰንካላነት የሚያጋልጥ ነውጥ አስከተለ። ወደታሪክ ማፍተሻው ልመለስና ብዙዎቹን የታሪክ መረጃዎች ብንጨምቃቸው ከ1983 ዓ.ም. በፊት ወልቃይት ከትክራይ ክልል ጋር ምንም አይነት ጋብቻ እንዳልነበራት ያመለክቱናል።

በተጨማሪም ከላይ እንደተዘረዘረው በወልቃይት የማንነት አስተባባሪ ኮሚቴ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር፣ ለትግራይ ክልል ርዕሰ መስተዳደር፤ ለትግራይ ክልል የህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ ጽ/ቤት፣ ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የትግራይ ክልል ጽ/ቤትና ለትግራይ ክልል ምክር ቤት የተጻፉ የአቤቱታ ደብዳቤዎች ከታሪክ ማስረጃዎች ጋር የሚዋደድ ወይም የሚጣጣም ይዘት አለው። ለአብነት ያህል ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር የተጻፈው አቤቱታ እስከ ዛሬ ድረስ ያለውን የሕወሓትንና የህዝቡን ግንኙነት የሚያስረዳ ሲሆን እንደሚከተለው በጥቂቱ ተቀንጭቦ ቀርቧል።

> *ወልቃይት ከ1983 ዓ.ም. በፊት በጎንደር ክፍለ ሃገር በወገራ አውራጃ ዳባት ዋና ከተማ ሆኖ ራሱ የቻለ ወረዳ አሰተደዳር የነበረ ሲሆን ይህ አከባቢ በወቅቱ በነበረው በሰተ-ምዕራብ ሱዳን በሰተ-ሰሜን ኤርትራና በምስራቅ ትግራይ ያዋሰነ ሠፊ ለም መሬት የያዘ ነው። በአጠቃላይ መጠሪያቸን "ወልቃይት ጠገዴ ሰሜን አርማጭሆ" ይባላል። ወልቃይት የአፄ ኃ/ሰላሴ አሰተዳደር ተገርስሶ በምትኩ ጊዚያዊ ወታደራዊ መንግስት ከተመሠረተበት ጊዜና የደርግ መንግሰት በህዝቦች ትግል እስከ ተገረሰሰበት ጊዜ ድረስ ደርግን ተቃውሞው ለወጡ ታጋይ ድርጀቶች እንደ ኢድዩ፣ ኢህአፓና ህወሃት ለትግል እስትራቴጂክ አካባቢ ሆኖ አገልግሏል። ህወሃት ወልቃይት ከገባችበት ከ1972 ዓ.ም. ጀምሮ ደርግ እስከሚደመሰስበት በነበረው የትግል ጊዜ አንድም ቀን በሰላም ከህዝቡ ጋር ተዋህዳ ያሳለፈችበት ጊዜ አልነበረም።*

ይህ ገለጻ አካባቢው በትጥቅ ትግል ዘመን የብዙ ነፍጥ ያነገቡ ታጣቂዎች ወሻ እንደነበርና የአካባቢው አማሮችም ስርዓቱን በመቃወም የመደርግ መንግስት አስተዳደራዊ መቅርን እንዳይዘረጋ ከማደረርግና ህወሃትም ያለውን ጸረ-ደርግ የህዝብ አቋም እንደመልካም አጋጣሚ ተጠቅሞ በ1972 ዓ.ም. ወልቃይትን እንደረገጠ የሚያስገነዝብ ነው።

ስነ-ጥበብ ይናገርል

ስነ-ጥበብ የአንድ ማህበረሰብ የጋራ ስነ-ልቦናና የታሪክ ነጸብራቅ ነው። በቃ ስነ-ስነ-ጥበባት የማህበረሰቡ የፖለቲካ ማህበራዊና ጠቅላላ የአኗኗር ገጽታን የሚያንጸባርቁ ስለመሆናቸው ብዙ ማብራሪያ የሚሻ ባለመሆኑ በቀጥታ የተወሰኑ የስነ-ጥበብ ውጤቶችን እንመለከታለን። የወልቃይትም ጉዳይ ከአካባቢው የስነ-ጽሁፍ ትውፊቶች ጋር የተቆራኘ መሆኑን የሚያመላክቱ መረጃዎችን ማግኘት ብዙ ልፋት የሚይቅ አይደለም። ምክንያቱም በሰሜን ጎንደር ወልቃይትን

አሞካሽቶ ማቀንቀን የተለመደ ነው። ደስታውንና ሃዘኑን በእንጉርጉሮና በአዝማሪዎች ጥበብ የማስተጋባት ልምድ ያላለው የጎንደርና የአካባቢው ህዝብ የሙዚቃ ይዘትና ቃና የማህበረሰቡን ስሜት የሚያሳይ መሆኑ ከእውነትም በላይ እውነት ነው። የስነጥበብ ውጤቶችን እንደመረጃ ስንወስድ ጎንደሬ ነን ብለው የሚያስቡ አቀንቃኞች ወልቃይት ጠገዴ ሰሜን አርማጭሆ የሚለውን ገለጻ ያዘወትሩታል። ተስፋዬ ገብርዓብ ከጎንደር በዝገብኝ ቤቶች በቅኔ አዝማሪዎች ሲያቀነቅኑ ሰማሁ ብሎ በጋዜጠኛው ማስታወሻ ከጻፈው የተወሰደ ግጥም እንዲህ ይላል።

“ጎንደር ሃገር ጠፍቶ -ሲፈለግ ሌሊት፣
ቀን ካዲሱ ጋራ ሲሄድ አየሁት
አዲስ አዲሱ ሰው በዝቶ እየተባዛ፣
ከበሰዶ ሜዳ ላይ-ቀረን እንደዋዛ።
በሁመራ ገብተን በመሃሉ ላይ፣
ሰው አገኘን -መሬት መሬት ባይ።
ወልቃይት ጸገዴ -አስተውሉ ላያት፣
ያኔ ወይ ያኔ -ወይን ነት ወይን ናት።”

የተስፋዬ የጎንደር ጉብኝት ከሸህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ሶስት ወዲህ ነው። ግጥሙ የክልሉ መሪዎች የጎንደርን መሬት የሚያስኮበልሉ መሆናቸውን አመላካች ነው። የሁመራን የወልቃይትን መሬት ለምነት ከእነሱ እጅ በመውጣቱ ያላቸውን ቁጭት የተነፈሱበት አንጀት ማራሻቸው ግጥም ናት። “መሬት መሬት ባይ” የሚለው ገለጻም መሬት ነጣቂን የሚመለከት ነው፤ በሁመራ የእነሱን መሬት የመሹና የሚወስዱ መበርከታቸውን አመላካች።

በተጨማሪም የመኢአድ የቀድሞ ፕሬዘዳንት አቶ አበባው መሃሪ “ዱሮ ልጅ ሆኜ ጎንደር ስማር ተዋቂው ድምጻዊ ይርጋ ዱባለ ለምለሚቷ ጎንደር እንኳን ደስ አለሽ የሰሊጥ መሬቷን ሁመራን ይዘሽ እያለ ይዘፍን ነበር፤ ይህ የራሱ ታሪክ አለው፣ የትግራይና የአማራ ልሂቃን በእርጋታ ተቀምጠው ታሪክ መመርመር አለባቸው” በማለት የጎንደር ሰው ጥንትም ጀምሮ ሁመራን እንርስቱ አድረጎ ስለሚያስበ መመኪያው መሆኑን ገልጸል። የአቶ አበባው ንግግር ታሪክ ለጉዳዩ እልባት ስለሚሰጥ ባለጉዳዮች እንዲወያዩበት ምክር ብጤ የሚለግስ ነው።። ሌላም ላክል በቅርብ ሁላችን የምናውቀው የፋሲል ደመወዜ ዘፍን አለ። ፋሲል አረሱት በሚል ርዕስ ባቀነቀነውና በፍቅር በሚወደው የፊጠራ ውጤቱ እንዲህ ይላል። *“...አለ ነገር! ጎንደርና ጎጃም መሬም አለ ነገር! አል-ሸዋም (2)፣ አለ ነገር፣ አለ ነገር 2) ፣ መቼም ታመን ታመን አንገት ደፍተን አንቀር፣ አለ ነገር (3)፤ አረሱት (2) አረሱት ይሉኛል የሁመራን መሬት፣አረሱት (2) ይሉኛል የመተማን መሬት ያርማጨሆን መሬት ያውም የኛን እጣ (2) አረሱት (2) ይሉኛል ያውም*

የኛም መሬት ያውም የኛን እጣ ለነሱ... ለኛ ሰው ሲታጣ... በማለት በማህበረሰቡ ስር የሰደደ ቁጭትና በአቅም ማነስ ምክንያት ህዝቡ ከምንም በላይ የሚወደውን መሬቱን መነጠቁን አመላክቷል።

ትንቢተ-ፋሲል ሊፈጸም ቀረበና 2008 ዓ.ም. ብሶቱ ገንፍሎ ወጣ። መቼም ታመን ታመን አንገት ደፍተን አንቀር ብሎን ነበር። ፈነዳ፤ ፋሲል በዘፈኑ እንደቴወድሮስ ያለ ጀግና በተወለደ በሚል እናቶችንም ተመሃጽኖም ነበር። መንግስት ከሚለው የመልካም አስተዳደር ችግር ከፍ ባለ ደረጃ ከትግራይ ህዝብ የተለየ የአማራነት ማንነት አለን በሚል ወልቃይቶች ወደ አማራ ክልል የመካለል ጥያቄ የቆሰቀሰው የአማራ ወጣት ንቅናቄና ነውጥ "የአንገት ደፍተን አንቀር" ትንቢት ፍጻሜ ጅምሮ ሆነ።

በሌላ በኩል የትግራይ የቀድሞ የስነ-ጥበብ ስራዎች የወልቃይትን፣ ጠለምትን፣ አርመጨሆን፣ ቃብትያን፣ሁመራንና ሰሜንም በማሳት የማቀንቀን ልምድ አይስተዋልም። ይህ አይነት ተግባር ተጀመረው ግፋ ቢል ከ1983 ዓ.ም. ወዲህ እንደሚሆን ሳይታለም የተፈታ ነው። ጉዳዩ የቅርብ ጊዜ መሆኑን የሚያሳብቁና የወልቃይት የማንነት ጥያቄ ጡዘት ላይ በነበረበት ወቅት ወልቃይትን የሚዘክሩ የትግሬኛ ዘፈኖች እንደተቀነቀኑ ማስታወስ ይቻላል። በትግል ጊዜ የሚዘፈኑ ዘፈኖችም የግጥም ይዘት የወልቃይትን ትግራዊነት የሚያሳዩ ስለመሆናቸው ማስረጃም የለም።

ወልቃይት የትግራይ ነው

ከላይ የተዘረዘሩት ጠጣር የታሪክና ህያው ማስረጃዎች እንዳሉ ሁሉ የሕወሓት አመራሮችና የወልቃይት መሬት የትግራይ ክልል መሆኑ የህልውና ጉዳይ አድረገው የሚያስቡ ሰዎች ወልቃይት የተግራይ አካል ስለመሆኑ መረጃዎችን በማጣቀስ ይከራከራሉ። የመንግስት (የትግራይም የፌደራሉንም መንግስት ይመለከታል) የመከራከሪያ ነጥብ ድግግሞሽ ይበዛዋ። የመከራከሪያ ነጥብን በማስረጃ ከማስደገፍ ይልቅም ጉዳዩን የማድበስበስ አማራጭ እየወሰደ ይገኛል። የሕወሓት አመራሮችንና ደጋፊዎች የመከራከሪያ ሃሳብን እንመልከት። የሕወሓት የቀድሞ ታጋይ መኮንን ዘለለውንና "ገላውዲወስ አርዓያ" በጉዳዩ ላይ መከራከሪያ የሚያቀርቡ ሲሆን ሁለቱም ሰዎች ወልቀይት የሚለው ስም የትግሬኛ ቋንቋ መሆኑ ወልቃይት የትግራይ መሆኑን የሚሳይ አንዱ ማስረጃ ነው ይላሉ። ከስያሜ ወጣ ባለ መልኩ ገላውዲዎስ የ17ኛው ክፍለዘመን የትግራይ ታሪክ በማጣቀስ የወልቃይትን ትግራዊነት ቢስረዱም የተጠቀሰው

መጽሃፉ ግን “የተከዜ ወዲህ የትግራይ አንዳልነበር የሚያስረዳ”[45] ነው። በሁለተኛነት ሌሎች በራካታ በአካባቢው ያሉ ቦታዎች ትግሬኛ ስያሜ የያዙ መሆናቸው ወልቃይት ለትግራይ እንደሚገባ ያሳል ይላሉ። ሆኖም የስሜ ጉዳይ ቦታዎችን የማን እንደሆኑ ለመወሰን የማያስችልበት ሁኔታ እጅግ ብዙ ነው። ለምሳሌ ወልቂጤ የምትባለው የጉራጌ ዞን ዋና ከተማ ስሟ የኦሮምኛ ቋንቋ በመሆኑ ላይ የጋራ መግባባት አለ። ነገር ግን ወልቂጤ በኦሮምኛ ስለተሰየመች ለኦሮሚያ ክልል ትሰጥ የሚል ምክንያታዊነት የልም። አንድ ቦታ በየትኛው አካባቢ ይካለል ለማለት በርካታ ኩነቶች ከግንዛቤ መግባት ያለባቸው በመሆኑ ስያሜን ብቻ መከራከሪያ ማድረግ ሊበሏት ያሰቧትን ....ምን ይላታል እንደሚባለው ነው።

ስርዓቱ ታሪካዊ ማስረጃዎችን ከማቅረብ ይልቅ ጥያቄውን ያነሱ ዜጎችን የተለያ የወንጀል በመስጥ ለእስር የመዳረግ ተግባር እየተፈጸመ መሆኑን በየጊዜው የሚወጡ መረጃዎች ሲኖሩ የሞቱ የተያዙ፣ የተወነጀሉ ግመሰቦችን ሙሉስ መግለጫ ኮሚቴው ይፋ አድርጓል። መንግስት በበኩሉ ከወልቃይት የአማራ ማንነት ኮሚቴ አባላት የወንጀል ድርጊት የተሳተፉ ስላሉ ለፍድ የማቅረብ ሃላፊነት አለብኝ በሚል በይፋ የማሰርና ክትትል የማድርግ ተግባር እንዳለ አረጋግጣል። የልማታዊ የመንግስት የመገናኛ ብዙሃኖች ይህኑ አጀንዳ በማስረጽ የወልቃይትን የማንነት ጥያቄ/የአማራ ብሄር ነን የሚል ጥያቄን/ እንዳይሰማ የማፈን ብሎም ከህገ-ወጥነት ጋር አስተሳስሮ የማስወራት ሚና እንደሚጫወቱ መጠነሰፊ ቅሬታ ይቀርባል። ኋላ ላይ የፌደራል መንግስት ሚዲያዎች ጉዳዩን ከመዘገብ የተቀጠቡበት አግባብም ይታያል። ግን ጥያቄውን በግምባርቀደምንት የሚመሩትንና ደጋፊውቻቸውን በተላያዩ ወንጀሎች ሰበብ ለእስርና ለሰብአዊ መብት ረገጣ የሚዳርጋቸው መንግስታዊ ስርዓት የፖሊሲ ለውጥ አላሳየም።

ካርታ1፡ የቀድሞውን የአስተዳደር አወቃቀር የሚያሳይ ካርታ

[45] በአንድ ወቅት “የታሪክ ዶክተር” ገላውዲዮስ አርኣያ ወልቃይት የትግራይ እንደነበር” ሲያስረዱ በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በElizabel Filleul በፖርቹጋል ቋንቋ የተጻፈውን “Tractatus tres historico-geographici (1634): A seventeenth century historical and geographical account of Tigray, Ethiopia (Aethiopistische Forschungen)” መጽሀፍ እንደጠቀሱ ይታወቃል። ይህ መጽሀፍ ወደ እንግሊዝኛ ተተርጉሟል። ዶክተር ገላውዲዮስ አርኣያ በጠቀሱት መጽሀፍ የመጀመሪያ ምዕራፍ የመጀመሪያ ገጽ ላይ ስለትግራይ ግዛት [ከሰሜን እስከ ደቡብ፤ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ] እንዲህ ተጽፎ እናገኛለን፤“Among all the kingdoms that the Emperor of Ethiopia possesses today one of the greatest if not the greatest and the most important is the kingdom Tigre. From north to south, that is from the limits of the Hamasen to Enderta, it covers an areas of from ninety to one hundred leagues (3.2 miles); and from the east, which is besides Dancali, located at the entrance to the Red sea to the southern end of the Red Sea, to the west bounded by the Tekezze River beside the Semen, it covers an area of similar size, so that the Kingdom has a nearly circular shape.(አቻምየልህ ታምሩ፣ በ2016)። እንግዲህ ተከዜን ያልዘነጋ ገለጻ ነው። የትግራይ ግዛት ከተከዜ ወንዝ በመለስ ነበር።



ካርታ 2፡ የቀድሞውን የአስተዳደር አወቃቀር የሚያሳይ ካርታ



ካርታ 3፡ ከ1983 ወዲህ ያለውን የአስተዳደር አወቃቀር የሚያሳይ ካርታ



የወልቃይት የማንነት ጥያቄ ታፍኖ ግጨውና ጎቤ ድርድር ለምን?

በተደጋጋሚ ለመግለጽ እንደተሞከረው የአማራ ህዝብ መሰረታዊ ችግር ከአሸናፊዎች ፍትህና፣ በመንዚት አስተዳደ ከመመራቱና ውክልና ከማጣት ጋር ጠብቅ ቁርኝት አለው። የኢትዮ-ኤርትራ ጦርንት ከመጀመሩና ከዚያ በፊት የባሶና ወረና ወረዳ (ደብረብርሃንና ዙሪያው ያሉ አካባቢዎችን የሚያጠቃልል ነው) አስተዳደር ከፍተኛ ባለስልጣን ከሰሜን ወሎ በህወሃት/ኢህአዴግ ተመልምሎ የተሾመው እሱና ማንነቱን የሚገልጹ ሰነዶች እንደሚያስረዱት የሰሜን ወሎ አማራ የማያውቀውን አካባቢ በማስተዳደር ለስርዓቱ የመረጃና የጥርነፋ መስመር ታማን ሆኖ ያገለግል እንደነበር አውቃለሁ። በዚያን ዘመን የሰሜን ሽዋ ወጣቶችን በመልመል በአስርሽዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን ላለቁበት ትርጉም አልባ ለሆነ ጦርነት ሲያስማሩ ከነበሩ ባለስልጣናትም አንዱ ነው። ይህ ሰው አሁን ላይ በ2010 የብርጌደር ጀነራልነት ማዕረግ የሚጠብቅና በተለያዩ የአለም አቀፍ የመረጃ ስለጠናዎችና ድርድሮች የመሳተፍ እድል የሚሰጠው ግለሰብ ነው። በ1998 ዓ.ም. እነብ/ጀነራል አሳምነው ጽጌ፣ ብ/ጀነራል ተፈራ ማሞና ሎሎች በመቶዎች የሚቆጠሩ የመከላከያና የፖሊስ ሰራዊት አባል የሆኑ የአማራ ልጆች በመፈንቅለ መንግስትና በአሸባሪነት ተወንጅለው ዘብጥያ ሲወርዱ ምንም አይነት ጥርጣሪ ከመንግስት ያልገጠመው መሆኑንና የማከላከያ መረጃ ዋና መምሪያ ሃላፊው የሜጀር ጀነራል ገብረ አድሃና (ገብረ ዲላ) አማካሪና የመምሪያው የአቅም ግንባታ ሃላፊ ሆኖ ተሸሞ እንደነበር አውቃለሁ። ዋናው ጉዳይ የሰሜ ሽዋ አማራ አስተዳዳሪ ከሰሞን ወሎ ሊሾምለት ለምን

አስፈለገ? ራሱን ሊያስተዳደር የሚያስችለው እንደመኩሪያ በረደድ (መኩሪያ፣ ለደህንነቱ ሲባል ስሙ የተቀየረ፡ ይህ ግለሰብ ያኔ ዲፕሎማም ያልነበረው ሰው ነው) አይነት የተማረና የአካባቢው ተወላጅ አልነበረም ወይ? የሚሉ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ፡፡ መልሱ ግን ቀላል ነው፡፡ በወቅቱ ለስርዓቱ ታማኝና የሚነግሩትን ብቻ የሚሰራ እንጂ ራስን በራስ የማስተዳደር ጉዳይና የአመራር ብቃት ከግምት የሚገባ አልነበረም የሚለው ነው፡፡ የስርዓቱ የትኩረት አቅጣጫ በታማኝ ሰው የመገዚት አስተዳዳር መመስረትና በአማራን ህዝብ ላይ ህወሃት/ኢህአዴግ የፈለገውን እንዲያደርግ መደላድል መፍጠር ነው፡፡

የጠገዴም ወረዳ ጉዳይ ከዚሁ ጋር የሚመሳሰል ማለትም አማራ ራሱን የሚያስተዳድርለት አካል በህውሃት/ኢህአዴግ እየተሾመ እንዲስተዳድር ከመደረጉ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ጸገዴና ጠገዴ ተብሎ የተከፈለው በግንቦት 20 ቀን 1984 ዓ.ም. የቀራቀር ወረዳ (የጠገዴ አካባቢዎች የሚገኝበት) አስተዳዳሪ/ሃላፊ/ በነበረው ኃይሌ በሚባል ሰው ነበር፡፡ ኃይሌ የህወሃት ክፍለ-ህዝብ አባል እንደነበር ከአካባቢው የሚወጡ ታማኝ ምንጮች የሚያስረዱ ሲሆን የጠገዴ አካባቢ የዳዳ-ሃሙስና ቀራቀር በሚል ተከፈለ፡፡ አንደ አካባቢው ምንጮች ጠገዴ በህወሃት የታላቋ ትግራይ ካርታ ላይ እንኳን ያልነበረ ነገር ግን ቀስ በቀስ የአማራ ክልል በአማራ ልጆች ባለመተዳደሩና በመገዚት የሚመራ በሆኑ ከቀድሞው የህወሃት እቅድ በተጨማሪ ጸገዴ የሚባል ቦታን ከአማራ ክልል ለመውሰድ የሚያስችል እድል ካላይ ስሙ በተጠቀሰው በአካባቢው አስተዳዳሪ አመካኝነት ተፈጠረ፡፡ በመሰረታዊነት የጸገዴምም የጠገዴም ህዝብ አማራ ነው፡፡ በመሆኑም በህዝቡ በኩል ብሄር ተኮር የድንበር ግጭት የለም ማለት ነው፡፡ የአማራና የትግራይ ህዝብም ቢሆን እንደህዝብ የጸብና የባላንጣነት ታሪክም እንደሌለው የሚታወቅ ነው፡፡

የ2009 ዓ.ም. የድርድር አወሳሰን በራሱ ግራ አጋቢ ነው፡፡ የጸገዴ ወይም የጠገዴ አካባቢዎች (ከፊል ግጨውና ጎቤ ለትግራይ የመስጠት አግባብ) ከወልቃይትና ጠለምት የማንነት ጥያቄ ተለይቶ የሚታይ አይደለም፡፡ የወልቃይት ጠለምት የማንነት ጥያቄ ከተመለሰ የግጨውና ጎቤ ጥያቄም መልስ የሚያገኝ ጉዳይ ነው፡፡ እናም የወልቃይት ጥያቄ መልስ ሳያገኝ የትግራይና የአማራ ክልል ፕሬዘዳንቶች ተስማምተው የድንበር ጉዳይ መልስ አገኘ መባሉ የህዝብ ጥያቄ እንደመናቅ ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ ይህ ቦታ በምንም አግባብ የአማራ እንጂ ከትግራይ ክልል ጋር የሚያስተሳስረው ታሪካዊም ሆነ ወቅታዊም ነገር የለም በሚል አቶ አያሌው ጎበዜ በ1998 አካባቢ (የአማራ ክልል ፕሬዘዳንት) የህወሃትን ፍላጎት እንደተቃወሙ ይነገራል፡፡ እስካሁን

በክርክር ቆይቶ መፍትሄ ሳያገኝ የቀረው አካባቢውን ወደትግራይ ለማሻገር ታሪካዊ መሰረት በመጥፋቱ እንደነበር መግለጽ የሚያስችሉ ማስረጃዎች አሉ፡፡

በተጨማሪም የ2009 ዓ.ም. የግጨው ድርድር አዋዛጋቢነት የወልቃይት ጥያቄ ሳይመለስ መፈጸሙ ብቻ ሳይሆን ግጨውና ጎቤ የተሰኘውን ቦታ ወደትግራይ ክልል የማስተላለፉ ጉዳይ የህወሃትና የብአዴን አመራሮች ውሳኔ መሆኑም ነው፡፡ ምክንያቱም ህዝቡ የራሱን ጉዳይ እንዲያስፈጽሙለት ይሁንታ ያልሰጣቸው የመንግስት አመራሮች ድርድር አደረጉ ተብሎ የድንበር ውል በመፈረሙ ነው፡፡ ብአዴን ህዝቡ እንደዳልተቀበለውና ህዝቡ በራሱ ድንበር ጠባቂ ሆኖ እንደቆየ ይታወቃል፡፡ ህዝቡ ባለጉዳይና መሬቱን የሚወድ (በርስትና ሚስት ቀልድ የለም የሚል) ነው ፡፡ በመሆኑም ለምን ህዝበ ውሳኔ አልተሞከረም? ለምን የህዝቡ የማንነት ጥያቄ አልተመለሰም? ብለን ብንጠይቅ መልሱ ግልጽ ነው፡፡ ይህም ስርዓቱ የህወሃት/ኢህአዴግ የመሬት ቅርምትና የተስፋፊነት ፍላጎት ማሳኪያ እንጂ የህዝብ በተለይም የአማራ ህዝብ ጉዳይ አይደለም የሚለው ነው፡፡ የህዝብ ጉዳይ አይደልም ሲባል የሰው ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት በጸገዴም ይሁን በጠገዴ ቀድሞም አሁንም የሚኖረው በስጋ ዝምድና ጭምር የተሳሰረ የአማራ ህዝብ ስለሆነ በወሰን ይገባኛል ጉዳይ የብሄር ጸብ የለም/አልነበረም፡፡ ቦታው በቀደምትነት የበጌምድር ግዛት የነበር ኋላ ላይ ከ1983 ዓ.ም. በሰሜን ጎንደር በዳባት ወረዳ ስር የሚተዳደርም ነበር፡፡ ሲጠቃለል መሰረታዊ የማንነት ጥያቄ ሳይመለስ (የማንነት ጥያቄ የሁሉም ጉዳዮች ግንድ ነው) የፓርቲዎች የግጨውን መሬት የመከፋፈል ድርድር አማራንም ሆነ የትግራይን ህዝብ ችግር የሚፈታ አይደለም፡፡

ከወልቃይት ባሻገር፡ የአማራ መሬት እጣ ፋንታ

ህወሃት/የኢህአዴግ ከመሰረቱ በአማራ ምድር ላይ የተስፋፊነት ብሎም የአማራንና የአማራ የሆነውን እሴትና ሃብት የማሳነስ ባህሪ የተላበሰ እንደነበር የህወሃት የመመስረቻ ሰነድ የሚያስረዳ እንደሆነ ምክንያታዊ ትችቶች ይሰነዘራሉ፡፡ ሰነዱ ማሻሻያ ከተደረገበት ወዲህ በተለይም የቀድሞው አማጺ የመንግስት ስልጣንን ከተቆጣጠሩ ወዲህ የቀድሞውን የተዛባ አመላካከት ከአመራሮቹ አዕምሮ ያልተፋቀ መሆኑን የሚያሳዩ ተግባራዊ የተስፋፊነትና የአማራን ህዝብ የነበረውንና ያለውን ሃብትና ማንነት የማቆርቆዝ ባስ ሲልም የማውደም አካሄዶች እንዳሉ አመላካች መረጃዎች አሉ፡፡ የአማራ ክልል ከሱዳን እንዳይዋሰን የማስድረግ አዝማሚያ፣ የአማራን ምድር ወደ ቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል የማካለል፣ በየራያና አላማጣ አካባቢዎችና ወደትግራይ ማካለል ተግባራቶች ከወልቃይት ባሸገር ያሉ የአማራን መሬትና

የህዝቡን የተፈጥሯዊ ሃብት የማኮሰስ ተግባራቶች ናቸው። ከእነዚህም የተወሰኑትን ብቻ እንመልከት።

የአማራ ክልል ከሱዳን ጋር እንዳይዋሰን መታለሙ። ኤርትራ ከኢትዮጵያ ከመገንጠሏ ቀደም ሲል ኤርትራ የሌለችበት የኢትዮጵያ ካርታ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ይታይ እንደነበር የወቅቱን ፖለቲካ ይከታተሉ የነበሩ ግለሰቦች ያስረዳሉ። እንደታዛቢዎች ገለጻ ቀድሞ የታለመውን የማስገንጠል አላማ የማስረትጽና ልመዱት እንደማለት ነበር። ቀደም ሲል በ1988 ዓ.ም. የቤኒሻንጉል ክልል ክልል ህገ-መንግስት አንቀጽ ሁለት (2)[46] መንግስቱ ተሻሽሎ የትግራይና የቤኒሽንጉል ክልሎች እንደማይዋሰኑ ከተደነገገ ወዲህም እ.ኤ.አ. የህወሃቱ መስራችና አባል ሃረጋዊ በርሄ በፍልስፍና ዲግሪው (ፒ.ኤች.ዲ) መመረቂያ ጽሁፉ በ1995 ዓ.ም. የተሻረው ህገ-መንግስት የሚደነግገውን ማለትም ከላይ የተጠቀሱት ክልሎች እንደሚዋሰኑ የሚያሳይ ካርታ አስፍሯል። ይህ ሳይታሰብበት ወይም በስህተት የተካተተ ካርታ ነው ለማለት የሚቻልበትን ምክንያት መገመት ያዳግታል። ምክንያቱም ጽሁፉ ምርምር ነው፤ በብዙ ምሁራን የሚተች የዶክትሬት ዲግሪ መመረቂያ። ሰውየው ደግሞ የህወሃት መስራች የታላቋ ትግራይ አቀንቃኝ የነበረ፣ ጥናቱ ደግሞ ለአንባቢያን በድ-ረገጽ ጭምር የተለቀቀ ነው። በመሆኑም ትግራይና ቤኒሻንጉል ጉሙዝን ክልሎችን አማሳኝነት የሚያሳይ ካርታ መካተት የአስተሳሰብ ውጤት ሆኑ የደርጅቱን የቀድሞ አላማ በየአቅጣጫው ተረባርቦ ለማሳካት ብሎም በአንባቢው ወስጥ ይህንኑ ማስረጽ አንደሚሆን ለመገመት የሚያስችል ነው። በ2009 ዓ.ም. የትግራይ ክልል በተፈጥሮ ሃብት አንክብካቤ በአለም ደረጃ ተሸላሚ ስለመሆኑ በሚዘገብ ዜና ተመሳሳይ ካርታ ለህዝብ ይፋ ሆኖ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ይቅርታ መጠየቁ ይታወቃል። ካርታውን ከድረ-ገጽ /ዌብ ሳይት/ ሲወሰድ የተፈጠረ ስህትት መሆኑን አስረድቷል። ግን ዜናው ኢዲተር የለውም?፣ በድረ-ገጽ ከሚስተዋሉ በርካታ አይነት የኢትዮጵያ ካርታዎች ይህኛው እንዴት ተመራጭ ሆኖ ለስህተት ዳረጋቸው? ብሎ ለሚጠይቅ ኢትዮጵያዊ መልሱ በአቶ ዘርዓይ አሰግዶም በሚመራው ተቋም ያለ ይመስለኛል።

አንቀጽ 46 (2)፡ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልል ወሰን፡1. በምስራቅ የኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት፣ 2. በምዕራብ ሱዳን፣3. በደቡብ የጋምቤላ ህዝቦች ክልል፣ 4. በሰሜን የትግራይ 5. በሰሜን ምስራቅ የአማራ ብሄራ ክልላዊ መንግስት (አዋጅ ቁጥር 1/1988 ዓ.ም. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የህገ-መንግስት አዋጅ).

ካርታ 4፡ የትግራይና ቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልሎችን መዋስን የሚያሳይና በሃረጋዊ በርሁ መጽሃፍ ላይ የተካከት



Map 2: Ethiopia since 1993 – Regions ('killil') and their capitals
Addis Ababa & Harar – City states
Dire-Dawa – Separate administrative region

Source: Information Section of the UNDP-Emergency Unit for Ethiopia, 1996.

የጎንደርና የአካባቢው መሬት ሱዳን ተሰጠ?፡ የአማራ ህዝብ በጎንደር መሬቱ በባዕድ ሃገር ሱዳን ተወሰደብኝ፣ የኢትዮጵያ መንግስት የእርሻ መሬታች ሲወሰድ ጥበቃ አልሰጠንም፡፡ ይባስ ብሎ የመንግስት ሰራዊ ለባዕድ ሃገር ወግኖ ጥቃት ያደርስብናል የሚል አቤቱታ ያቀርባል፡፡ ዛሬ ላይ ስለጉዳዩ የሰዎች ምስክርነትን አጣቅሶ መረጃ ማቅረብ ላመንኛውም የሰው የሚያዳግት አይመስለኝም፡፡ ተደፈርን የሚለው ስሜት በብዙው የጎንደርና በሌላው የአማራ ህዝብ አዕምሮ ውስጥ እየሰረጸ መጥቷል፡፡ ግን እውነት የኢትዮጵያ መሬቱ ለሱዳን ተሰጥቷል ወይ? ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚሰጥ በቂ ጥናቶች እንዳልተከናወኑ ቢገለጽም፣ ከሰብአዊ መብት ተከራካሪ

ሪፖርቶች፣ ከአካባው ማህበረሰብ፣ ከሱዳን መንግስት ባለስልጣናት መግለጫዎችና ከዜና ምንጮች ሱዳን ከኢትዮጵያ የእርሻ መሬት ስለማግኘቷ ይገለጻል። የሱዳን መንግስትን አቋም የሚያስገነዝቡ መግለጫዎችን የሚያበስረውና በታማኝነቱ ዝናን ያተረፈው ሱዳን ትሪቡን ሳያቋርጥ የሱዳን መንግስት በድርድር ከኢትዮጵያ መሬት እንዳገኘ ዘግቧል። ለአብነት ሱዳን እኤአ ሃምሌ 3 ቀን 2007 ባወጣው ዜና የምስራቅ ሱዳን ገበሬዎች አጨቃጫቂውን መሬት ከኢትዮጵያ አገኙ በሚል ርዕስ ስር "የኢት-ሱዳን የድንበር ግልግል ኮሚቴው በምስራቅ ተከዜ በኩል ከ17 በላይ ለሆኑ የሱዳን መንደሮች መሬት ሊያስረክባቸው ነው" ብሏል። በማከልም ድንበሩ ለመቶ (100) አመታትም ሲያወዛግብ እንደነበርም ይገልጻል። ሌሎችም ይህንኑ እየተቀባበሉት አስነብቧዋል። ይህ ውሳኔ እኤአ በ2004 ረጅሙን ድንበር ለማካለል የተፈረመው ውል ቀጣይ ነው።

ይህን ሃሳብ የሚደግፍ ጥናትም ያለ ሲሆን ሙላቱ ውብነህ (እኤአ 2015) የተሰኘ ጸሃፊ በአንድ አለም አቀፍ ጆርናል ላይ ባሳተሙት ጽኑፍ ከ1600 ኪሎ ሜትር በላይ የሚረዝም የጋራ ድንበር እንዳለቸውና በወጉ ያልተካለለ መሆን ገልጾ እ.ኤ.አ. በ2017 የኢህአዴግ መንግስት የሚስጥር የድንበር ድርድር ውስጥ ከሱዳን መንግስት ጋር እንደገባ አትቷል። እንደዚህ ጸሃፊ ገለጻ ድርድሩ ድንበሩን ማካለልና ማስተካከያን የሚመለከት ነበር።

ይህ ጉዳይ የመነጋገሪያ አጀንዳ መሆኑ በጦፈ ወቅት አውራምባ ታይምስት የተሰኘ የዜና ድርጅት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያምን በሁኔታው ላይ የጥናት ቡድን አባል ሆነው የሰሩ በመሆኑ አስተያየት እንዲያቀርቡ አድርጎ ነበር። እሳቸውም በቀድሞቹ ስርዓቶች የመሬት ይገባኛል ውዝግብ በሁለቱ ሃደራት መካከል እንደነበር አረጋግጠው የኢህአዴግ መንግስት ሰጠ ከተባለ ይህንኑ አካባቢ ስለሚሆን በቦታው ተገኝቶ ምርምር በማድረግ ማጣራት እንደሚያስፈልግ ምክር ለግሰዋል። የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ታዛቢዎች መሬት ተቀማን የሚለውን የህዝብ አስተያየት/ቅሬታ በመጋራት መንግስት ስለኢትዮጵያ የግዛት አንድነት ደንታ ቢስ ሆኗል በሚል ይተቻሉ። የኢትዮጵያ መንግስት ግን መሬት አልሰጠሁም የሚል መልስ ከመስጠት ወጪ ህዝቡን ሊያሳምን የሚችል ግልጽና ዝርዝር ማብራሪያ ለመስጠት አልሞከረም።

የወቅቱን የአካባቢ ፖለቲካ ከግምት ውስጥ በማስገባት የመረጃዎቹን እውነትነት ወይም አወዛጋቢ የድበር አካባቢ የእርሻ ቦታዎችን የኢትዮጵያ መንግስት ለሱዳን ሊያስረክብ የሚያስገድዱትን ምክንያቶችን ማቅረብ ይቻላል። <u>አንደኛ(1)</u> ከሰሜን ጎንደር (የድንበር ውዝግብ

የነበረበት አካባቢ ለማለት ነው) በኩል የኢትዮጵያን መንግስት የሚቃወሙ የትጥቅ ሃይሎች ወደ ኢትዮጵያ ሊሰርጉበት የሚያስችል ፖለቲካዊ ሁኔታና መልከ አምድራዊ አቀማመጥ አለው። የአካባቢው ነዋሪም በመንግስት ላይ የሚነሳውን ጥያቄ የመብት ጉዳይ ተደርጎ የሚወሰድ ሳይሆን የጸረ-ሰላም ሃይሎች አላማ አራማጅ ያስኛል፤ ያሳስራልም። ህዝቡ ከውጭ የሱዳን ሰራዊትና ገበሬዎች ይፋለማቸዋል፣ የሞትንም ጽዋ ይጎነጫሉ። ሀገሬ የሚላት ኢትዮጵያም አማጺውን አርበኞች ግንባር ታስጠጋላችሁ በሚል ለስር፣ ለድብደባና ለንብረት ውድመት የምትዳርጋቸው እንደሆነ የአካባቢው ነዋሪዎች ያስረዳሉ። ነዋሪዎቹ በተፈጥሮ ምክንያት (ተወልዶ-አድጎ-አርጅቶ መሞት) እየናፈቁ ያሉና ለጊዜውም ቢሆን ብቸኛ የህይወት ዋስተናቸው የመደበቂያ በርሃዎቻቸውና ጠብ-መንጃዎቻቸው ናቸው። በአጠቃላይ አካባቢው የመንግስት ስጋት ነው። መበመሆኑም የኢትዮጵያ መንግስት የስርዓቱን /የድርጅቱን ህልውና ለማረጋገጥ የኢትዮጵያን ጥቅም ወደጎን የማለት ባህሪ ያለው በመሆኑ ለመራቱን ለቀድሞ (በትጥቅ ትግል ዘመን) አጋሩ ዛሬም በተለይ የህወሃት የቅርብ ወዳጅ ለሆነው አማር ሃሰን አልበሽ መራቱን በመስጠት የህወሃት/ኢህአዴግን ስጋትን የመቀነስ እርምጃ ይወስዳል። ይህም ሁለት አላማ የሚያሳካ ሲሆን በአንድ በኩል ስጋት መቀነስ በሌላ በኩል ወዳጅን ማስደሰት ያስችላል። በተጨማሪም አዲሱ የድንበር ማካለል እየተከናወነም የኢትዮጵያ መንግስት የአማራ ገበሬዎችን እንቅስቃሴና የነፍጥ አማራጭን ከሚከተሉ ሃይሎች የተጋረጠበትን ስጋት ለመቀነስ ከሱዳን ጋር የጋራ ወታደራዊ ትብብር ተፈራርሟል(ሱዳን ትሪቡን ።

<u>ሁለተኛ(2)</u>፡ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስተርና ፓርቲው በትጥቅ ትግል ወቅት የሱዳን መሪና ሃገራቸው ሱዳን ላበረከቱለት ውለታ እጅ መንሻ ሊያስረክባቸው እንደሚችል ይታመናል። የሱዳን መንግስት ከ1983 ዓ.ም. መፈት ከነበረው አቋም በማፈንገጥ የኢትዮጵያን ተቃዋሚዎች ባለማስጠጋትም ለህወሃት/ኢህአዴግ ባለውለታነቱን አስቀጥሏል። በመሆኑም ህወሃት/ኢህአዴግም በንጉሱና በደርግ ዘመን የነበረውን የድንበር ይገባኛል ጥያቄ በማስቀጠል ከሱዳን ጋር ውዝግብ ውስጥ በመግባት የሁለቱን አካላት ወዳጅነት የሚያቀዛቅዝ ውሳኔ ለማሳለፍ ስለማይደፍር መራቱን ያስረክባል።

<u>ሶስተኛ(3)</u> ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ለማገኘት፡- ሱዳን በአለም አከፍ ደረጃ ብሎም በአፍሪካ ቀንድ ተጽኖ ፈጣሪ ሃገር ባትሆንም የግብጽ ቋሚ የዲፕሎማሲ አጋር ሆና መቀጠሏ ለኢትዮጵያ መንግስት እንደስጋት የሚወሰድ ነው። ይህም ለኢህአዴግ መንግስት ከአባይ ወንዝ ጋር (hydr-politics of Nile) ደካማ ተደራዳሪ እንዲሆን አስተዋጽዖ እንዳለው ይታወቃል። በመሆኑም

ሱዳን ይገባናል ያለውን መሬት ሰጥቶ በማሰደሰት ከግብጽ ለመነጠል መደለያ ይሆናል። ስለሆነም የጎንደር መሬት ለሱዳን ሊተላለፍ ይችላል ማለት ነው። በተግባርም እንደሚታየው በተያያዘ የሱዳን መንግስትም ከግብጽ ጋር የነበራውን የቆየ ዝምድና ወደጎን በመተው ኢትዮጵያና ግብጽን በሚያከራክረው የውሃ ፖለቲካው የኢትዮጵያን አቋም የመጋራት ብሎም በሃላይብ ትሪያንግል ከግብጽ ጋር ያለውን የድንበር ጥያቄ በማንሳትም ግብጽን እንደሚወቅስም ይታወቃል። በፖለቲካ የመተጋገዙ ጉደይ ከፍ ብሎ እንዲታይ የኢትዮጵያ መንግስትም በሃላይብን ትሪያንግል ጥያቄ የሱዳ አጋር መሆኑን አሳይቷል። የሱዳንም መንግስት የኢትዮጵያን መንግስት በዲፕሎማሲው የመደገፍ አዝማሚያ ማሳየት ለተሰጠው መሬትና ሌሎች የዲፕሎማሲ አጋርነት ውለታውን እየከደፈለ እንደሚሆን የሚታሰብ ነው።

ይህ ሃሳብ ሲጠቃልል የኢትዮጵያ መንግስት ለብዙ አመታት ኢትዮጵያና ሱዳን ሲያወዛግብ የቆየውን፣ የኢትዮጵያ ገበሬዎችም ሲጠብቁት፣ መሰዋዕትነት ሲከፍሉለትና ሲያጨቃጭቅ የቆየውን የጎንደር ህዝብ ሲያርው የነበረውን መሬት ለሱዳን ለመሰጠት ምክንያቶች አሉት። ውሳኔዎቹ በራሳቸው እደችግር ብሎም የችግር ምንጭ እየሆነ ያለው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው። ይህም የአፍሪካ ህብረት የድንበር አዋሳሰን መርህን በጥናት ላይ ተመስርቶ ካለመከተሉ፣ ብዙው ድርድር ሚስጥራዊና የህወሃት/አህአዴግ አመራሮች ውል መሆኑ፣ አወሳሰኑም የአካባቢውን የኢትዮጵያ ህዝብ ለአደጋ እያጋለጥ በመሆኑና በጥቅሉ ለስርዓቱ ህልውና ሲባል የሃገሪቱ ጥቅም ችላ መባሉ ነው።

ካርታ 5፡ የችግር ምጭ የሆነው የድንበር አካባቢ መሬት



ምንጭ፡ Borkena.com, Ethiopian News, 14 February 2017

የጠፋ ተራራ (ዳሸን)፡ ከመሬትና አከላለል ሳንወጣ ነገር ግን ከወልቃይት ጉዳይ ወጣ ብለን ተያያዥ ጉዳዮችን ስንመለከት የዳሸን ተራራ ከአማራ ክልል ካርታ ኮብልሎ ትግራይ ክልል ውስጥ መገኘቱ መንግስት በ2008 ዓ.ም. በይፋ ነግሮናል። በአማራ ክልልና ህዝቡ እየሆነ ካለው ነገር አንጻር ይህ ጉዳይ በጋጣሚና በቴክኒክ ስህተት ነው ለማለት አያስደፍርም። የማስተማሪያ መጽሃፎቹ ተመራምሮ ያስተምራል ተብሎ በሚታሰብ አስተማሪ እጅ የገቡ ናቸው። በመሆኑም ከ1996 ዓ.ም. ጀምሮ ጉዳዩ (በስህተት መታተሙ) ሳይታወቅ ቆይቷል ብሎ ለማሳመን መሞከር አመክኖዊነት የለውም። ከዚህም በላይ የምናውራው ስለአስተዳደራዊ ክልል አከላለልና የቦታዎች መገኛ ስለሚያሳይ ካርታ እንጂ በማስተማሪያ መጽሃፍ ውስጥ በአረፍተ ነገር መካከል ስለምትቀመጥ ነጥብ አይደለም። ካርታ በመጽሃፍ ውስጥ እንዳለች አንድ ቃል አድርገን የምንወስደው አይደለም። በመጽሃፍ ውስጥ ያለች አንድ ቃል እንኳን ከአርታኢው እይታ የመታለፍ አይደለችም። ቃላቶች ከአርታኢው አምልጠው ከተገኙ አስተማሪው ገና እጁ ሲገባ ያገኘዋል። ስለሆነም ስህተቱን ለመገንዘብ ጊዜ የሚፈጅ አይሆንም። ካርታ አይነግቡ ሆኑ የሚታይ ከመሆኑ ሌላ በጽሁፍ የሚብራራበትም ሁኔታ አለ። በጽሁፍ ሳይብራራ የተቀመጠ ካርታ ቢሆን እንኳን አስተማሪው በማብራሪያ እያጀበ የሚያስተምርበት ነው።

ካርታ ትልቅ፣ ግልጽና ገላጭ የሰነድ አካል ነው። በስህተት የተዛባ የአስተዳደር አከላለልን የሚያሰይ ከሆነ ከመምህሩ እይታ ስለማያመልጥ ምናልባትም መጽሃፉ በተሰራጨ በአንድ ወር ውስጥ ስህትት መሆኑ ለህዝብ ሊገለጽ ይገባው ነበር። ያም ግን አልተደረገም። ይህ ሁኔታ የተስፋፊነት አላማን የሚያሳይና ታስቦበት የተዘጋጀ የማስተማሪያ ሰነድ ይሆናል የሚል ጥርጣሬ ለማሳደር የሚጋብዝ ነው።

የወልቃይትና የአካባቢው የአማራ ችግር የመፍትሄ አማራጮች አሉትን?

የወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት መሰረታዊ ችግር ታውቋል፤ ችግሩ መታወቁ ደግሞ የመፍትሄውን መዳረሻን የሚያሳልጥ ነው። ስለሆነም የመፍትሄ አማራጮችም ይኖራሉ ማለት ነው። አሁን ባለው ስርዓት ላይ የአማራ ማንነት አደጋ ላይ ወድቋል የሚለው ሃሳብ ብዙዎች የሚስማሙበት ነው። ወልቃይት ጥያቄ የተነሳብት በምዕራብ ትግራይ ሲሆን የተጠራቀመው ግፍና ያልተቋጨው ዘር የማጽዳት እንቅስቃሴ ከተጠቀሰው ክልል ጋር ለመቆየት የሚያስችል እንጥፍጣፊ ተስፋ እንዲሚጠጥ በማድረጉ ብሎም አማራ በመሆናችን የአማራ ክልል አካል እንሁን የሚል ጥያቄ ነው እየተነሳ ያለው። በተለይ ጥያቄው የህዝባዊ እምቢተኝነት በማስነሳቱ የአካባበውንና በስፋትም የአማራ ክልልን የጸጥታ ሁኔታ አደጋ ላይ ከጣለው በኋላ የስርዓቱ አካላት ጉዳዩ "እንደትኩስ ድንች"[47] ሆኖባቸው ከአንዱ ወደ አንዱ ሲያንከባልሉት ተስተውለዋል። እስከሁን መልስ የለም። ይህን ጉዳይ እንደጥያቄ ማንሳት የማይቻልበት ህጋዊ መሰረት ባለመኖሩ የክልሉ መንግስት ሕወሓት ከዚህ ጥያቄ ሊያመልጥ የሚችለው የፌደራል አስተዳደሩ ብሄር ተኮር መሆኑ ካከተመ ብቻ ነው። ግን እንዴት? ጉዳዩ ቀላል አይደለም። የህገ-መንግስታዊ መሻሻልን፣ የገዢው ፓርቲውን አደረጃጀትንና መኒፌስቶ ለውጥ ጭምር የሚጠይቅ ነው። ሃገራዊ ፓርቲ መመስረትና ህገ-መንግስቱን በማሻሻል ቅይጥ (ማንነትንና የቦታዎችን አቀማመጥ ያማከለ የአስተዳደር አከላለል) ፌደራላዊ ስርዓት መመስረት ያስፈልጋል። ይህም ሆኖ የሁሉም ለውጦች ግብ ግን በወልቃይት የአማራ ማንነት ሳይሸራረፍ መከበሩና የህዝቡ እኩል ተጠቃሚነት መስፈኑ ነው። ሆኖም የሕወሃት/ኢህአዴግ ስሪት ለእዚህ አይነት ለውጥ የተዘጋጀ ያለመሆኑ ከ2009 ዓ.ም. ተሃድሶ ወዲህ እየወሰዳቸው ያሉ የፖለቲካ እርምጃዎችና ማሻሻያዎች አመላካች ናቸው። ከብዙዎች የመንግስት እንቅስቃሴዎች እንደመንረዳው ስርዓታዊ ማሻሻያ ያልተተኮረብትና በፓርቲዎች ላይ የተደረገው ግምገማ

[47] "...On the other hand, the question Welqait seems a "Hot Potato," still untouched. The question is direct to TPLF, a dominant party in EPRDF. However, optimistically, still there is time to give genuine strategic solution for the said identity question by the TPLF" (Damtew Tessema, 2017:189).

ሃገሪቱም ችግር አለባብሶ የሚያልፍ ነው። እንደፓርቲ የህወሃት የበላይነት አለ፤ በተጠቃሚነትም ደረጃ የህወሃት ሰዎችና ደጋፊዎቻቸው የበላይ ናቸው ብሎ መገምገም እንደኪራይ ሰብሳቢና አፈንጋጭ የሚያስቀጥር እንደነበረ ነው የማሰበው። ለዚህም ይመስለኛል የጥልቅ ተሃድሶው ግምገማ በጠቅላለው በመንግስት ላይ አተኩሮ ፈጻሚውን ሲያነታርክና ሲያናክስ የቆየው።

ወደ ወልቃይት ጉዳይ ልመለስና አሁን ባለው ሁኔታ የአማራ ማንነት ማጠንጠኛው የፖለቲካ ውሳኔ ነው። ይህም ህዝብን ማዕከል ያደረገ እስከሁን ህወሃት/ኢህአዴግ ሞክረውት በማያውቁት ደረጃ ከፍ ያለ የፖለቲካ ቁርጠኝነት የሚጠይቅ ነው። የፖለቲካ ቁርጠኝነቱ የህዝብን ዘላቂ ሰላም ለማምጣት የተሻለው አማራጭ ስለሚሆን በታሪክ ላይ ተመስርቶ መፍትሄ መዘየድ እንዲቻል የሚያደርግ ውሳኔን የሚያሳልፍ ሊሆን ይገባል። የሰሜን ኢትዮጵያን ቀድሞ አስተዳደራዊ ወሰን እንደሌሎች አካባቢዎች የቅርብ ጊዜ ክስተት አይደለም። በግልጽ በታሪክ የተመዘገበ መሆኑ የሚወቅ ነው። ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ ድንበር በመኖሩና አካባቢው ነገስታት በተለይም የትግራይ ነገስታት የታፈሩ ድንበራቸውን ጠብቀው የቆዩ በመሆኑ ለመፍትሄ የሚበጅ የታሪክ ጥናት የማድረግ ተግባርን ያቀለዋል። ከዚህም አልፎ የአካባቢው ታሪክ በሃገራዊና በአውሮፓ ቋንቋዎችና የታሪክ ተመራማሪዎች ተጽፎ የሚገኝ በመሆኑ ለውሳኔ ብዙም አስቸጋሪ አይሆንም። ዋናው የሕወሓት/ኢህአዴግ ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ነው።

የፌደሬሽን ምክር ቤት ችግሩ በትግራይ ክልል መንግስት ይፈታል የሚል እንድምታ ያለው ደብዳቤም ለወልቃይት የአማራ ማንነት ጥያቄ ኮሚቴ መላኩ እንዲሁም በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን የሃገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስተር የትግራይና የአማራ ክልል ከፍተኛ አመራሮች ችግሩን እንዲፈቱ ሲል ማሳሰቡ ይታወቃል። ካለው ነባራዊ ሁኔታ ብንነሳ የትግራይ ክልል /ሕወሓት/ ብቻውን ችግሩን እንዲፈታ መገመትም ሆነ ሃላፊነቱን መስጠት ሞኝነትን ወይም ታስቦበት የወልቃይትን ጥያቄ ጊዜ በመውሰድ ለማቀዝቀዝ/ለማክሰም/ መታሰቡን ከማሳብቅ ውጪ ሌላ ትርጉም አይሰጥም። እንዲያውም አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ የሚለው ተረት ስለማይገልጸው ጠዋት ቀማና ከሰዓት ዳኛ ቢባል ይመጠነዋል የሚል እምነት አለኝ። ሕወሓት ገና ከጠዋቱ የትግራይ ክልል ያደረገውን፣ ወልቃይትን፣ ጠገዴንና ጠለምትን ዛሬ ላይ ህዝቡ ጠይቋልና ይሰጠው ስለማይል እንደሃገር በሁሉም ኢትዮጵያዊ ባለድርሻ ተመክሮበት በገለልተና የታሪክ አጥኚዎች ውጤት መሰረት ውሳኔ ቢተላለፍ ተገቢነት አለው።

ታሪክን መሰረት አድረጉ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ፖለቲካዊ ቁርጠኝነቱን ባያመላክትም ጉዳዩ መንግስትን ፋታ የነሳው መሆኑ ግን ግልጽ ነው። በመሆኑም መንግስት በመስከረም 2008 ዓ.ም. በጠቅላላው በሃገሪቱ መምህራንን እንዲሁም ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን የማወየት ተግባር ሲያከናውን ወልቃይትን አልዘነጋትም። በዚሁ ወቅት በዩኒቨርሲቲዎች "የሩብ ምዕተ-አመታት የልማት የሰላምና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ጉዞ፡ የከፍተና ትምህርት ሚናና ተልዕኮ" በሚል ርዕስ የተለመደው ስኬትን የሚተርክ ጽሁፎች ተነበዋል። የፌደራሉ መንግስት የተወሰኑ ሃገራዊ የፖለቲካ ትኩሳቶች ላይ የሚነሱ ጥያቀዎችን በመተንበይም ጥያቄዎችን ከነማብራሪያው ለአወያዮች በማስያዝ አሰማርቶ እንደነበር አይን እማኝ ነበርኩ። የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን፣ የአማራና የኦሮሞ ህዝብ ህዝባዊ እምቢተኝነትም ከዋና የውይይት አጀንዳ የሚመደቡ ነበሩ። ወልቃይትን ትኩሳት በአንዱ ዩኒቨርሲቲ በተሳታፊነት ከተገኙ መምህራን አንዱ ካወያዩች "ወልቃይት በትግራይ የሚገኝ አካባቢ ነውና" "ህዝበ-ውሳኔ አማራጭ ሊሆን ይችላል" በሚል የተሰጠውን ሃሳብ በመቃቀውም አሁን ለተጋፈጥነው ችግር መፍትሄ የሚሆን አማራጭ ሲሰነዝር በውስጤ ሲንሸራሸር የነበረውን ሃሳብ አፈነዳልኝ። ሃሳቡ ሲጨመቅ እንደሚከተለው ነው፡-

አማራጭ አንድ፡ ቀጥታ ወደሪፈረንደም (ህዝበ ውሳኔ) መግባት የሚቻለው ህዝቦች የሚኖሩበት ምልክኣ-ምድራዊ አቀማመጥ የየትናው ህዝብ ነበር የሚል ማስጃ ከሌለ ብቻ ነው። ማለትም ቀድሞ ነባር ህዝብ ማን ነበርና በታሪክ በየትኛው ክልል ተሳሎ ነበር የሚለው ጥያቄ የሚመልስ ማስረጃ ከሌለ ለማለት ነው። ነገር ግን የመሬቱ የበስተኋላ ታሪክ ሲጠና የማንኛው ህዝብና ክልል እንደሆነ የሚያረጋግጥ ታሪካዊ ማስረጃ ከተገኘ የመጀመሪያ እርማጃ የሚሆነው መሬቱን ቀድሞ ወደነበረበት አካባቢ መልሶ ማካለል ይሆናል (ማካለሉ በሃሳብ ደረጃ ነው)። ከዚም ቀጣይ እርምጃ የሚሆነው የህዝቡን ጥያቄ ማስተዋልና መልስ መስጠት ሲሆን ይህም አማራ ነን ብለው የጠየቁት ህዝቦች በቁጥር የሚበልጡ ከሆነና በተደረገው ጥናት የመሬቱ ታሪክ ዛሬ የአማራ ክልል በተባለው አካባቢ ይተዳደር ከነበረና ይህም ከተረጋገጠ መሬቱም ህዝቡም የአማራ ክልል ይሆናል ማለት ነው። የትግራይ ህዝብ ደግሞ መብቱ ተከብሮለት እንዲኖር ይደረጋል ማለት ነው።

አማራጭ ሁለት፡ በሌላ በኩል አካባቢው እንደሚባለውና ከላይ የተጠቀሱት የታሪክ መዛግብቶች እንደሚያስረዱት የመሬቱ የኋላ ታሪክ የአማራ ክልል መሆኑ በጥናት ከተረጋገጠና በአካባቢው የትግራይ ህዝብ በቁጥር የሚበልጥ ከሆነ ወልቃይት በአማራ ክልል ተጠቃሉ በልዩ

ዞን ደረጃ የሚተዳደር ይሆናል። ይህም ሌሎች ለልዩ ዞን የሚበቁ መስፈርቶችን ካሟላ ብቻ የሚተገበር ነው። ይህ አገላለጽ ለትግራይም ለአማራም በተመሳሳይ እንደታሪኩ እውነታ የሚተገበር ነው።

በተጨማሪም ተናጋሪው ከመድረክ ህዝበ ውሳኔ እንደመፍትሄ ሊሆን ይችላል በሚል በተሰነዘረ ሃሳብ ለመስማማቱንና ስጋት እንዳለው ከመግለጽ በተጨማሪ ወልቃይትን በትግራይ ክልል ለማጸናት ቀደም ሲል ስራዎች መጠናቀቃቸውን ጠቁሟል። ይህን ሃሰብ የአካባቢውን ጉዳይ በውል መገንዘብ የሚችል ሰው የሚጋራው ነው። በመንግስታዊ የመረጃ ምንጮች መሰረት በወልቃይት ትግራዊ እንደሚበዛና የቀድሞ የሕወሓት ተቀናሽ ታጋዮች ዳንሻ አርሰው እንዲበሉ መሸኘታቸውን አስራት አብርሃ ጽፏል። ኋላም በሰፈራ መርሀ-ግብር ለድርቅ ተጋላጭና ለምነቱ ከተሟጠጡ የትግራይ አካባቢዎች ሰዎችን በማምጣት በወልቃይት መጠነሰፊ (massive) ሰፈራ ተከናውኗል።[48] ይህ ሽግሽግና ሰፈራ እንደችግር የሚታይ አይደለም፤ችግር ወይም ላለመግባባት ምንጭ የሚሆነው ሰፋሪው የነባሩን ወይም ነባሩ የሰፋሪውን መብት የተጋፋ ከሆነ ወይም ከደርግ መንግስት መገርሰስ በኋላ ወልቃይትን ከትግራይ ጋር ጠምሮ ያዋቀረው የኢህአዴግ ስርዓት የወልቃይት አማራዎችን መብት ከመጨፍለው ላይ ነው። በዚህ መሃል በልማት ሰበብ የተፈናቀሉ፣ንብረታቸው በመወረሱ የኢኮኖሚ ማንነታቸው በመነጠቃቸው በምሬ የጠፉ ወይም የቀድሞ ቅያቸውን በመልቀቅ ወደከተማ የፈለሱ እንዲሁም የማንነት ጥያቄ በማንሳታቸው በመገደላቸው የአማራ ማንነት ያላቸው ህዘቦች እንደተመናመኑ የወልቃይት ማንነት ኮሚቴ ሪፖርት ስረዳል። ይህ ሁኔታ ከኢንቨስትመንትና ከሰፈራው መርሃ-ግብር ጋር ተዳምሮ የትግራይ ተወላጆች የቁጥር የበላይነት እንዲኖራቸው የሚያስችል ነው። ለዚህም ነው ህዝበ ውሳኔ የኋላ ታሪክ ባልነበረበት ሁኔታ ብቻ እንደአማራጭ እንዲታሰብ የሚያስፈለገው።

አማራጭ ሶስት፡ ከብሄር ፖለቲካ ውዝግብ ተላቀን ኢትዮጵያን አንድንገነባ የሚያስችል ሰርዓት መገንባት በግሌ እንደአማራጭ የምወስደው ነው። እሱም ወልቃይት የአማራ ሆነ የትግራይ ያው የኢትዮጵያ ነው የሚል አስተሳሰብ እንድናዳብር የሚያስችል ፖለቲካዊ ለውጥ ነው።

[48] **Ethiopians move for food security**፡ some 95% of people live on the land, eking out a living on thin, rocky soil that has been over-farmed and yields barely a subsistence existence.The same is true of other highland areas of Ethiopia, on the central mountainous plateau... Against this background, the Ethiopian government has decided to **move** 2.2 million people off these barren, arid lands to more fertile lowland areas. After three days rattling along in the bus, Hadguy Mirutz has arrived at his new home from area arouds Mekele. He is greeted by some friends from his village who moved a year ago. He is encouraged to hear that their first 12 months have been relatively successful.Yields from the land near **Humera** close to the border with Sudan and Eritrea... his new land is huge compared with the land he left behind near Mekele. He crumbles the rich, black earth in his fingers. “This is virgin soil – ready for farming (Adam Mynott, 1 Maarch 2005).

ሃሳቤን ትርጉም የሚኖረው አማራ በትግራይ ክልልም ሆነ በአጠቃላይ ሃገራቱ ያለምንም በደል መኖር ሲችልና ሃገራቱ ከብሄር ፖለቲካ ጡዘት ተላቃ የአስተዳደሩም አከላለል ከቋንቋና ብሄር ወደ ቅይጥ ሲሻገር ነው። ሃገራዊ ራዕይ ላይ ለማተኮር፣ የአካባቢያዎነትና የጦዘ የብሄረተኝነት ስሜት እንዲቀዘቅዝ ከተመፈለገም ፓርቲ አደረጃጀትም ዘውግን ብቻ ያልተከተለ እንዲሆን የሚያስፈልግብት አግባብ አለ። ይህ ከሆነ ክልሎችና ብሄረሰቦች "የኔ"፣ "የኔ" የሚል የሸሚያን ፖለቲካን ማቀዝቀዝ ይቻላል።

አማራጭ አራት፡ ከላይ ላሉት አማራጮች መሳካት ሁኔታዎች ካልፈቀዱ የህወሃት/ኢህአዴግ ግትር አቋም ከቀጠለ የአማራ የማንነት ትግል ውጤታማ አስፋላጊነት እንዳለው ይታመላል። ማለትም አማራን ለዘርፈ ብዙ አደጋ የሚዳርግ የኢህአዴግ ስርዓት የፈጠረው ብሄር ተኮር ፖለቲካ እስካለ ድረስ በታክቲክ ደረጃ "አማራ አማራ" በመሆኑ ላይ ሳይደራደር ተባብሮ ስለወልቃይትም ሆነ ስለሌላው አካባቢ የአማራ ህዝብ ትጎሉን አጠናክሮ መቀጠሉ ከሁኔታዎች አስገዳጅነት አንጻር ተመራጭነት ያለው ስልት/አካሄድ ነው።

ምዕራፍ አምስት፡ መደምደሚያና ምክረ-ሃሳቦች

መደምደሚያ

ዛሬ ላይ የተንሰራፋውና ጽንፍ የያዘው የዘውግ ፖለቲካ፣ አማራን ከሌላው ማህበረሰብ የማቆራረጥ፣ በጨቋኝነት የመፈረጅና የማሰፈረጅ እንስቃሴ ብሎም በአማራ ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለው ግፍ ጥንስሱ ከ1983 ዓ.ም. የቀደመ ነው። ይህ ከ1950ዎቹ ወዲህ በኢትዮጵያ ስርዓት ጉድለቶች ላይ የሚሰጠው የችግር-መፍትሄ ትንተና የተዛባ ሆኖ ችግሮቹን ለመፍታት የሚዘየደው መፍትሄም ተደራራቢ ችግር እየፈጠረ ቆይቶ በ1974 ዓ.ም. የስርዓት ለውጥ ተደረገ። ለዚህም ሶሻሊስታዊ ተራማጆች የአንበሳውን ድርሻ ይይዛሉ። በዚህም የደርግ መንግስት ስልጣኑን እንደተቆጣጠረ ዜጎችን ደም ያለርህራሄ አፈሰሰ። ሲቀጥልም ስርዓቱን የሚፈታተኑ የከተማም የገጠርም እንቅስቃሴዎች የወታደራዊ እርምጃ ሰለባ ሆኑ። ስርዓቱ ለ17 አመታት ያህል የኢትዮጵያዊያን ህይወት በከንቱ ሲያጠፋ ቆይቶ በስተመጨረሻው ህዝቡና ስርዓቱ ሆድና ጀርባ ሆኑ። ህዝባዊ መሰረቱን ስላጣ ስርዓት በመክሰሙ ከአስርት አመታት በላይ የትጥቅ ትግል ሲያደርጉ የነበሩ በብሄር ፖለቲካ ጽንፈኝነታቸው የሚታወቁ ታጣቂዎች በ1983 ዓ.ም. የሚኒልክን ቤተ-መንግስት ተቀዳጁ። ከዚህ ለውጥ ወዲህ ጣሊያን ሲከተለው የነበረው በብሄር ከፋፍሎ የመግዛት፣ አማራን እንደጠላት የመፈረጅ አቅጣጫ፣ በብሄር መካከል

አለመግባባቶችና ግጭቶችን ማነሳሳት የስርዓቱ አቅጣጫ ሆነ፡፡ ስርዓቱ የበዳይ ተበዳይ የፖለቲካ ትረካዎች በስፋት እንዲጻፉና እንዲወሩ አደረገ፡፡ ታሪካዊ እውነታዎች ስሜትን በሚቀሰቅሱ የውሸት ማጣፈጫዎች እየተቀቡና በልብ ወለድ ጭምር እየተከሸኑ ለህዝብ የማሰራጨት ተግባርም የስርዓቱ የትኩረት አቅጣጫ ስለመሆኑም ይነገራል፡፡ በመፈረጅና የተዛባ ታሪክ ደጋግሞ በማስነገር በህዝብ ላይ በደል እንዲደርስ እንዲሁም በተለይም የኦሮሞና የአማራ ታሪካዊ ትስስሮችንና የጋራ የታሪካዊ እውነታዎችን በመሸፋፈንና በቀድሞ መሪዎች የተፈጸሙ ውስን በደሎችን የህዝብ ለህዝብ መበዳደል አስመስሎ ማሳየት የፖለቲካው ማጠንጠኛ ሆኖ ተወሰደ፡፡

እንደውነቱ ከሆነ በኢትዮጵያ በታሪክ አጋጣሚ ተከስተው የነበሩ የልዩነት ሽኩቻና ጦር የመማዘዝ ታሪኮች ነበሩ (ከተለያዩ ብሄሮች በሚገኙ ልዩነትን መካከል የሚፈጠር የመፋለም ታሪክ ለማለት ነው)፡፡ በእርስ በርስ ጦርነቶቹ የድል ፍሬዎችን የገፎነጠፉ እንዳሉ ሁሉ የጦርነትን አሰቃቂ ውጤት ስቃያቸውን ያበዛባቸው ተሸናፊዎች አሉ፡፡ እነዚህን ያለመግባባቶች የብሄር ግጭት በማስመሰል ፖለቲካ የሚሰሩ ገዢዎቻችን የወደፊት አንድነታችንን በሚያናጋ ሁኔታ ቅስቀሳ ማድረጋቸው የሞራል ሆነ የህግ መሰረት የለውም፡፡ የቀድሞው አገዛዝ የስኬትም ሆነ የጥፋቶች ሁሉ መሰረት የስርዓቱ ባለቤቶች የሆኑት መላ ኢትዮጵያዊያን መሆናቸው ቀርቶ ለአማራው ልዩነትን በመስጠት “አሁን የተፈጠረው ምቹ ሃገራዊ ሁኔታ” “የነፍጠኛው” ገዢ መደብ ከመፍረሱ ጋር የተሳሰረ መሆኑን መተንተን የወቅቱ አቢዮተኞች መገለጫ እየሆነ መጣ፡፡ ይህ አስተሳሰብ ሁሉም ኢትዮጵያዊያን በኢትዮጵያ አኩሪም ሆነ ጎስቋላ ታሪክ የነበራቸውን ድርሻና ለአሁኑ እኛነታችን ያበረከቱተን አስተዋጽኦ የሚያኮስስ መሆኑም እየተዘነጋም መጥቷል፡፡

የአማራንና የኦሮሞን ጉዳይን ነጥለን ብንመለከት በማርክሳዊ አስተሳሰብ እየተቃኙ በሚቀርቡ ብሄር ተኮር ቅስቀሳዎች ለአማራው ብሄር የበዳይነት ታሪክ የማላበስ በተቃራኒው የኦሮሞንና የሌሎች ብሄር ብሄረሰቦችን ከተጨቋኝ ጎራ የመመደብ ሂደት ለዛሬው የህወሃት /አህአዴግ አማራንና የኦሮሞን ልዩነትን በመከፋፈል የስልጣን ዘመኑን እንዲያራዝም አስችሎታል፡፡ ይህም የኦሮሞ ቡድኖች (በሻቢያ፣ የሱዳን መንግስትና በህወሃት እገዛና እቀነባባሪነት) በተለያዩ የኦሮሚያና የቤኒሻንጉል አካባቢዎች በንጹሃን አማራዎች ላይ ዘግናኝ ኢ-ሰብአዊ እርምጃዎችን አንዲወስዱ ምክንያት ሆኗል፡፡ አንዱን የስርዓቱን የመከፋፈያ ስልት የሆነውን የአኖሌን ሃውልት እንመልክት፡፡ ይህው የበዳጥ ተበዳይ ስሜት ሳይቀዘቅዝ እንዲቆይ የተጠቆረጠ ጡት

የሚሳይ ሃውልት በስርዓቱ ታንጾ ህዝብ እንዲጎበኘው ተደርጓል። ሃውልቱ የማነጹ አላማ እውን የህዝብን ሰቆቃ ለማሰብ ከሆነ የተቆረጠ የሰውነት አካል በአርማታ አንጾ ዘግናኝ ስሜትን መፍጠር ያስፈልግ ነበር ወይ? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው፡ ይህን ከማድረግ ፋንታ ሆስፒታል፣ ትምህርት ቤትና ኢንዱስትሪ በማቋቋም መታሰቢያነቱን ማጽናት ይቻል ነበር። ነገር ግን ለኢህአዴግ ይህን አይመስጠውም። ምክንያቱም ምኒልክን የአማራ ወገንና ጸረ-ኦሮሞ አስመስሎ ማሳየት የሚያስችል ብሎም ዘግናኝና ስሜት ቀስቃሽ ቋሚ የፖለቲካ ቅርስ የማስቀመጥ አላማን አያሳካምና።

ሆኖም ለፖለቲካ አላማ በስርዓቱና በደጋፊዎቹ ቆስቋሽነት የተወሰኑ መቻቻልን የሚሸሩ ተግባራት ተፈጽመው የአማራን ህዝብ ያነጣጠሩ ጥቃቶች ከመከሰታቸው ባሻገር በሁለቱ ህዝቦች መሃል ለወሬ የሚበቃ የባላንጣነት ታሪክ የለም። ቀድም ባሉት የመንግስት ስርዓቶች የተፈጸሙ ስህተቶች እንደነበሩ የማንዘነጋቸው ቢሆንም ጉዳዩን ከየትኛውም ብሄር ጋር በማያዝ የበዳይና ተበዳይ ብሄር አለ በሚል ልንከራከር የሚያስችል የታሪክ መነሻ የለንም። ዛሬ ላይ የስርዓቱ የመከፋፈያና የመግዛት ስልት በብዙሃኑ ማህበረሰብ እየታወቀና እየተጋለጠ መጥቷል። የሁለቱ ህዝቦች የፖለቲካ ልሂቃን በታሪክ አጋጣሚ የተፈጠሩ በደሎችን ከብሄር ጋር በማያያዝ ከመቆዘም የሚላቀቁበትና የጋራ ትግል የሚያደርጉበት እድል እየሰፋ መጥቷል። በተጨማሪም መልካምና አስቻይ የታሪክ መስተጋብሮች ሲኖሩ እነዚህም የአማራና የኦሮሞ ህዝቦች በአዲ አባባና በሁለቱም ክልሎች ተሰበጣጥሮ የመኖር ታሪክና አሁንም ቢሆን እየታየ ያለ ሁሉ-አቀፍ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት የጋራ ባህል፣ ልምድና ማንነትን ስላለ መቻቻልና ተከባብሮ መኖርን የሚያጠናክር ነው። የጋራ ታሪክን በተመለከተ በአመዛኙ እስከ 1983 ዓ.ም. ድረስ ያለው ታሪክ የሚያስረዳው ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን ጋር በመሆን የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት ለመጠበቅ ያልተተረከለት መሰዋዕትነት እንደከፈሉ ነው። የአማራና የኦሮሞ ህዝቦች በስትራቴጂክ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ማጭከል ላይ በመገኘታቸው ተጋግዞ በመስተዳደርና የሀገርን ደህንነት በመጠበቅ የላቀ ድርሻ አላቸው።

የአማራን ጉዳይ ብቻ በተመለከተ በ27 አመታት ውስጥ የኢ-ዲሞክራሲዊነት ባህሪው እየባሰ የመጣው ስርዓት ከሌው የኢትዮጵያ ህዝብ እጅግ በተለየ ሁኔታ የአማራውን ህዝብ መከራ አብዝቶት ቆጥቷል። ከማደህየት፣ ማፈናቀልና ዘር ማጽዳት እስከ የአደባባይ ግድያ የተፈጸመበት ህዝብ በመሆኑ የውልድት መጠኑም አጠቃላይ ቁጥሩ በማይታመን ሁኔታ እንደቀነሰ ስርዓቱ ራሱ መስክሯል። በሃገሪቱ ለረጅም ጊዜ የአማራን ህዝብ በወጉ የሚወክል

ድርጅት ካለመኖሩ በተጨማሪ የግንባሩ አባላት በእኩልነት ባለመታየታቸው የአማራ ህዝብ ተወካይ በማጣቱ የአማራን ክልል የሚያስተዳድረው ድርጅት የአማራን ህዝብ ጭቆና አስፈጻሚ ሆኖ እንዲቀጥል ተደርጓል። የአማራን ህዝብና ልሂቃኖቹን በተመለከተ ልሂቃኖቹ ከሃገር ውስጥ የሚመነጩ የጠላትነትና የማጥቃት ተግባራትን ችላ ብሎ በማለፍ የኢትዮጵን ህልውና የማስቀደም ባህል አለ። ህዝቡ በስርዓቱ ያላሰለሰ ድቆሳ እየተደረገበት ባለበት ሁኔታ ብዙዎቹ የአማራ ልሂቃን በህብረብሄራዊ አደረጃጀቶች ፍቅር መናወዝ ወይም የዘውግ አደረጃጀት ጠል የፖለቲካ ስልት በመከተሉ ስርዓቱ ለሚያደርሰው የዘር ማጽዳትና የማህበረ-ኢኮኖሚ ጉስቁልና መከታ ሳይሆኑ ቀርተዋል። ህዝቡ ተደራጅቶ ህልውናውን እንዲያስጠብቅ አቅጣጫ ባለማስያዝና የአማራን የትግል ኃይል በመከፋፈል ራሳቸውንም ህዝቡን በስርዓቱ ለሚሰነዘር ጥቃቱ ሲያጋልጡ ቆይተዋል። ይህ አሰላለፍ ስርዓቱ አማራን መደራጀት ካለመፈለጉና አማራ የለም የሚል ተዋስያ አቀንቃኞች ከሚፈጠሩት የአማራን ትግል የማዳከም ጫና ጋር ሲደመር የህዝቡን ከአደጋ ሊያተርፈው የሚችል ጠንካራ የፖለቲካ ወይም የሲቪል አደረጃጀት እንዳይኖር የሚያደርግ ሆኖ ታይቷል።

በሌላ በኩል ማቆራቆዙ፣ ከፋፍሎ ከመግዛቱና ነጥሎ ከማጥቃት በተጨማሪ አማራ ከሃገሪቱ ኢኮኖሚ በእኩልነት እንዳይጠቀም ባልተጻፈ ህግ የተከለከለ ህዝብ ሆነ። ማንነቱን የመደምሰስና ተፈጥሯዊ ሃብቱንም የሚያሳጡ ተግባራት ተጠናክረው በመቀጠላቸው የአማራ ህዝብና ስርዓቱ ሆድና ጀርባነት ጥግ ደረሰ። ማንነቱ ይከበር የሚል ጥያቄ ቢያነሳም የብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት ከወረቀት ያላለፈ ባለመሆኑና ሃገሪቱ የህወሃት/ኢህአዴግ አክሲዮን የመሆኗ ሃቅ በግልጽ በሚያሳይ መልኩ መልስ የመከልከልና ጥያቄውን ለማፈን ተሞከረ። ይህን ጊዜ አማራ ጨዋታ ቀየረ። የአማራ ህዝባዊ አመጽ ፈነዳና በሂደት ላይ ያለውን የኦሮሞ አመጽ ተቀላቀለው። የወልቃይት የአማራ የማንነት ጥያቄ ለአማራ እምቢተኝነት ፈር ቀዳጅ በመሆን በታሪክ ተመዘገበ።

እንደአጠቃላይ በ2006/07ና 2008 ዓ.ም. የተከሰተውን የህዝባዊ እምቢተኝነትንና ሃገራዊ ቀውሶችን ብንመለከት ከሁለት አስርት አመታት በላይ ያስቆጠረው አስከፊ የድህረ-1983 ዓ.ም. ስርዓት ውጤት መሆናችን እንረዳለን። ከላይ እንደተገለጸው የ1950ዎቹና ከዚያም በኋላም የችግር-መፍትሄ ትንተናዎች የሌላ ችግር መንስኤዎች ሆነው እንደቀጠሉት ሁሉ በእነዚህ ሃገራዊ ቀውሶችም የህወሀት/ኢህአዴግ ስርዓት የቀድሞውን ታሪክ የደገመ ሁነ። የችግር ትንተናው ተከትሎ የሚወስዳቸው እርምጃዎች ደግሞ በችግር ላይ ችግር እየደራረቡ ዛሬ

ላይደርሰናል፡፡ በ1997 ከምርጫ ጋር በተያያዘ በከተሞች አካባቢ በተከሰተ ነውጥ እንደችግር ተደርጎ በመንግስት የዱሮ ሰርዓት ናፋቂ የነፍጠኛና የትምኪተኛ ቡድኖች የፈጠሩት ሁከት ሲል ነበር፡፡ የተወሰኑትን የማህበረሰብ ክፍሎች በተለይም ለባላገሩ የተዛባ ግንዛቤ ማስጨበጥ ተችሏል፡፡ በዚያን ዘመንም ስርዓቱ የአማራን ልሂቃንን ጥላሸት በመቀባትና ጥቃት በመፈጸም ትግሉን ለማዳከም ችሏል፡፡

በመንግስት የችግር ትንተና የአማራ ህዝባዊ እምቢተኝትና አመጾች እንደስጋት በመውሰድ እንቅስቃሴው ጥያቄ እንዳልሆነ፣ የጸረ-ሰላም ኃይሎች እጅ ያለበት ተደርጎ ተወሰደ፡፡ በዚህም የተነሳ ምላሾቹ የተድበሰበሱና ውሸት የሚበዛባቸው እንደሆኑ ከየአቅጣቸው ሆኑ፡፡ የሚሱ ቀውሶችን እንደመልካም አጋጣሚ ወስዶ እውነተኛ ለውጥ ሳያደርግ ቀውስ በቀውስ ላይ ደራርቦ ቀጠለ፡፡ *ወልቃይት፡* ለአማራ ህዝብ መነሳሳትና ስርዓቱ በአማራ ህዝብ ላይ አደጋ የጣለና የሚጥል መሆኑን አብርቶ ያሳየን የወልቃይት የአማራ ማንነት ጥያቄ ምላሽ አላገኘም፡፡ በዚህም ረገድ ትውልዱ የትግል ስሜት እንደያዘ ለአማራ ብሄርተኝነት ፈር ቀዳጅ እንቅስቃሴውን ሳያቋርጥ ስርዓቱም የአማራን ማንነት የሚያከብር የፖሊሲ ለውጥ ሳያደርግ ብሶት እንደተዳፈነ ወደ 2010 ዓ.ም. ሽግግር ተደርጓል፡፡

በመጨረሻም ሁሉም የአማራ ልሂቃን የሚስማሙበት አንድ አንኳር ነጥቦች እንዳሉ እረዳለሁ፡፡ ይህም የአማራ ልሂቃንና የቀድሞ ነገስታቱ የኢትዮጵያዊያን የጋራ ማንነት እንዲገነባ፣ የሃገሪቱ ታላቅነት እንዲጎለብትና የግዛት አንድነት እንዲጠበቅ የማይተካ ህይወታቸውን የለገሱ መሆናቸው ነው፡፡ በአጭሩ የአማራ ብሄር መብትና ጥቅም በተናጠል የመተንተንና የማስፈጸም ተግባር የአጀንዳቸው አካል አልነበረም፡፡ ዛሬም ላይ ይህ አስተሳሰብ የሚያራምዱም ሆነ የዚህ አስተሳሰብ ነጸብራቅ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን የሚያደርጉ የአማራ ልሂቃን ስረመሰረቱና እድገቱ የብሄር ፖለቲካ ከሆነ ስርዓት ጋር የሚጣጣሙ ባለመሆኑ እጣ ፈንታቸው በስርዓቱ በጠላትነት መፈረጅና መደቆስ ሆኗል፡፡ በአማራ ብሄርተኝነት መስመር የተደራጀ ሃይልም በለመኖሩ የአማራ ህዝብ ህልናና ማንነት በቀጥታና በእጅ አዙር በሚደረግ ጥቃት አደጋ ላይ እየወደቀም በጋራ መመከት ሳይቻል ቀርቷል፡፡

ምክረ ሃሳብ

የኢትዮጵያ ታሪክ ህዝቦቿን አስተሳስሮ የጋራ ራዕይ ሰንቆ የሃገሪቱን ብልጽግና የማያስችል በማስመሰልና ልዩነቶችን በማጉላት አንድነትን የማኮሰስ እርምጃ በስርዓቱ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ለሃገሪቱ ፖለቲካዊ ቀውሶች የሚሰጠው የችግር-መንስዔ ትንተና የተዛባ ሆኖም ቀጥሏል፡፡ ይህ የታሪክ እይታ ዝንፈትና የችግር ትንተና የስርዓቱ ተግባራዊ እርምጃዎችና የፖሊሲ አቅጣጫዎች መነሻም ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ስርዓቱ የበዳይ ተበዳይ ታሪክ ነጋሪነት ስራው በመላቀቅ ያኮረፉ ኢትዮጵያዊያን ለእርቅ በመጋበዝ ስልጣን አጋርቶ ህዝቡ ለረጅም አመታት የተጫነበትን የጨቆና ስርዓት ይላቀቅ የሚል ምክረ-ሃሳብ ሲሰጥ ቆይቷ፡፡ የ2006/07 ዓ.ም. ቀውስም ተጋግሎ ሲቀጥል ተመሳሳይ አስተያየት ቀርቧል፡፡ ሆኖም ስርዓቱ ይህን ምክር ሳይቀበል ቀውሱም ሳይበርድ 2010 ዓ.ም ገብቷል፡፡ ቀውስ በቀው ላይ እየተደራረበም ነው፡፡ ዛሬ ላይ ያለው ቀውስ ከመቼውም በላይ የገዘፈ በመሆኑ የጉዳዩ ባለቤቶች የሚከተሉትን የመፍትሄ አማራጮች እንዲያጤኗቸው ሁኔታው ስለሚያስገድድ ማመላከቱ አስፈልጓል፡፡

- በሃገሪቱ ያለው ፖለቲካ ቀውስ በኢህአዴግ ብቻ የመፈታት እድሉ እየመነመነ መጥቷ፡፡ በመሆኑም ቀጣይ ምርጫ እስኪከናወን ድረስ የትጥቅ ትግል የመረጡ ኃይሎችን ጭምር በመጋበዝ ቢያንስ እኩሌታውን የመንግስት ስልጣን በድርድር በማካፈል የዲሞክራሲ ምህዳሩን የሚያሰፉ የህግ ማዕቀፎችን ማጽደቅ ያስፈልጋል፡፡ በተጓዳኝ በየብሄራቸው የተደራጁና የህብረ-ብሄር ሃይሎች ያለ-ኢህአዴግ ጣልቃገብነት እንዲሰባሰቡና የጋራ መድረክ ያሻል፡፡ በዋናነት ስርዓቱ የችግሮቹን ስርዓታዊ መሆኑን በማመን በችግሮቹ ላይ ተገቢውን ትንተና በማድረግ የመፍትሄ አቅጣጫ እንዲነድፍና ከጥግንግን ለውጥ በመላቀቅ ስልጣን በማጋራት አሳታፊ ስርዓት ቢዘረጋ ሃገሪቱ ከተጋረጠባትን አደጋ መታደግ የሚቻልበት እድል አለ፡፡
- ህወሃት/ኢህአዴግ ከላይ የተገለጸውን እጁ ላይ ያለውን እድል መጠቀም ካቻለና ሀገሪቱን በወታደራዊ እዝ ውስጥ ማውጣት ካልቻለ የአማራ ህዝብ፣ የኦሮሞ ህዝብና ሌሎች የስርዓቱ በድል ያንገሸገሻቸው ኢትየጵያዊያን ግንባር ፈጥረው እንዲታገሉ ሁኔታው ያስገድዳል፡፡ በዚህ ሂደት በተለይ የአማራና የኦሮሞ ምሁራን የተጀመረውን የአንድነት ጉዞ በማጠናከር በኩል በትብብር ከሰሩ የስርዓቱን አወዳደቅ ማሳመርም፣ ማፋጠንም የሚችልበት አቅም አለ፡፡ ከጋራ ትግሉ ጎን ለጎብ ስርዓቱ በአማራና ኦሮሞ ህዝብ መሃል

ቁርሾን ለማግነን ይጠቅሙኛል በሚል የገነባቸው ቁሳዊም ሆነ ስነ-ልቦናዊ አድረጃጀቶች የሚፈርሱበት አግባብም ሊታሰብበት የሚገባ ነው።

- በአማራ በህዝብ በኩል አማራ ተወክሎ በሀገሩ የሚገባውን የመወሰን ድርሻ አስካላገኘ አሁን ያለው ቡድን የአማራን ማንነት ከማኮሰስ፣ የማንነት ጥያቄ ከማዳፈን፣ በኢኮኖሚ ከማደህየት፣ ከመፈረጅና ዘር ከማጽዳት ተግባራት የሚቆጠብ ባለመሆኑ በአማራ ትውልድ የአማራ ብሄርተኝነት መግነንና መደራጀት አማራጭ የሌለው ራስን የመከላከል ስልት ነው። የአማራ ወጣት የአባቶቹን ትዕግስት፣ ምክርና ወኔ እንደስንቅ በመያዝ ከአጋጣሚ ይልቅ በመርህ ላይ የተመሰረት የረጅም ጊዜ የትግል ስልት በመንደፍ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ በየመተባብርን መንፈስ አጎልብቶ ህልውናን በማዳን ስራ ላይ እንዲያተኩር ጊዜው ያስገድደዋል። ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር በትብብር ለሚደረግም ሆነ በተናጠል ለሚቀጣጠል ትግሎች የተጠናከረና ተቋማዊ ይዘት ያለው የአማራ ብሄርተኝነትን የመገንባት ስራ ችላ የማይባል የሁላችንም የቤት ስራ ነው።
- በአማራ ህዝብ ላይ የተፈጸመውን ገደብ የለሽና በማንነት ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ማንም የሚክደው ጉዳይ አይደለም። በመሆኑ በአንድነት ሃይሎች ስር የተሳባበሰቡና ትግሉን የሚመሩ ፣ የአማራ ሪፐብሊክ መመስረትን በአጀንዳነት ያስቀመጡ፣ በቅድሚያ የአማራን ህልውናን በመታደግ የኢትዮጵን አንድነት ለማጽናት ያለሙና በአካባቢ የተደራጁ (ጎጃም፣ ጎንደ፣ወሎ፣ ሸዋ፣ ሃረር ወዘተ... ህብረት የመሰረቱ) የአማራ ልሂቃን በአማራ ህዝብ ላይ ስርዓታዊ ጥቃትን መቃወማቸውና የህዝቡ ማንነት መከበርና ቀጣይ ብልጽግናውን የሚናፍቁ መሆናቸው አንድ የሚያደርግቸው የጋራ እሴት ነው። ስለሆነም ጥቃቅን ልዩነቶች የወለዷቸው የጎንዮሽ መጎነታተልና መፈራረጆች በትግሉ ጥንካሬና በዋናው ግብ ላይ ጫና በማሳደር ትግሉን ስለሚያራዝሙት እስከድል ቀን ድረስ የሚከፈለውን መስዋዕትነት እንዲበዛ የሚያደርጉ በመሆኑ የግቡን ትልቅ ስዕል ታሳቢ በማደርግ ተቀራርበው በትብብር ሊሰሩ ይገባል። መዋሃድ ወይም የጋራ ግንባር መመስረት ካልተቻለም ሰብአዊነትና ህዝባዊ ወገንተኝነት ሁሉም ሃይሎች የሚታገሉነት የጋራ አላማ በመሆኑ በየተሰለፉበት መስመር ሆነው የጎንዮሽ መገፋፋትንና ጉንተላን የሚስቀር ድንጋጌን ያያዙ መርሆችን በጋራ በማስቀመጥ የትግል ሃይል እንዳይበታተን ማድረግ ይቻላል።
- ወልቃይትን በተመለከተ ጉዳዩ ቁርጠኛ ፖለቲካዊ መፍትሄ ይጠበቃል። የነገሮች ፈጣሪ፣ የቁልፍ ስልጣኖች ባለቤት የሆነው ሕወሓት የአማራነት ማንነት አለን በሚል ጥያቄ

ያነሱት አማራዎችን መብት በተሟላ መልኩ በማክብርና እካሁን ለደረሰባቸው ግፍ ካሳ በመክፈል ለችግሩ መፍትሄ መስጠት ይገባዋል። በዚህም በታሪክ ጥናት ላይ ተመስርቶ እንደሁኔታው ወልቃይትን በልዩ ዞንነት ወይም በአማራ ክልል (ጎንደር) እንዲተዳደር በማድረግ ለችግሩ አፋጣኝና ቀጣይነት ያለው ሰላም ሊያመጣ የሚችል ውሳኔ ከህወሃት/ኢህአዴግ ይጠበቃል።

- በሌላ በኩል በአማራ ህዝብ ላይ የተደቀነውን አደጋ ብዙው የሃገሩቱ ልሂቃንና ማህበረሰቦች የሚውቁት ሃቅ ነው። በአማራ ላይ የሚደረግ ያልተቋረጠ ስርዓታዊ የጥፋት ዘመቻ መቀጠሉ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ህልውና ወይም የሃገሪቱ እንደሃገር እየተንገዳደች እንድትቀጥል እንኳን እድል የሚሰጥ አይደለም። በመሆኑ ሁሉም የሃገሩቱ ህዝቦች የአማራን ራስን የመታደግ እንቅስቃሴ ሊደግፉ ያስፈልጋል። ይህ ከሆነ የሃገሪቱን የገነነ የፖለቲካና ታሪክ ባለቤትነትን እንደአስቻይ የጋራ ሃይል በመጠቀም ለኢትዮጵያ የመጪ ዘመን ከፍታ መሰረት መጣል ይቻላል።

ዋቢ መጸህፍቶች

ኃይሌ ላሬቦ (መስከረም 2008 ዓም.)። ከታሪክ መድረክ- ለመሆኑ የብሄር ብሄረሰቦች ጭቆና ነበር ወይ? በወልቀይት ዶት ኮም ላይ የሚገኝ።

ኃይለመለኮት አግዘው (ጥቅምት 19 ቀን 2009 ዓ.ም)። ኢትዮጵያ በአንድ ጀንበር አልተፈጠረችም። አዲስ አባባ።አዲስ አድማስ፣ቅፅ 16 ቁጥር 876።

መስፍን ወልደማሪያም። (2004 ዓ.ም.) ። አደጋ ያንጣበበበት የአፍሪካ ቀንድ።

መስፍን ወልደማሪያም (2007 ዓም) አዳፍኔ፡ ፍሃትና መክሸፍ፡ አዲስ አበባ።

መሬራ ጉዲና (2008 ዓም)። የኢትዮጵያ የታሪክ ፈተናዎች እናየሚጋጩ ህልሞች። የኢህአዴግ ቆርጦ ቀጥል ፖለቲካ.

ሙሉቀን ተስፋው (ጥር 2009 ዓ.ም.)(አራተኛ እትም)። የጥፋት ዘመን፡ ከ1983 እስከ 2007 ዓ.ም. በአማራ ህዝብ ላይ የተፈጸመ የዘር ማጽዳት።

ቤ.ጉ.ክ.መ ህግ-መንግስት (1995)። የተሸሻለው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ህግ-መንግስት፣ አሶሳ።

ቤ.ጉ.ክ.መ ህግ-መንግስት (1988)። የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ህግ-መንግስት፣ አሶሳ።

ነአምን አሸናፊ (ነሐሴ 26 ቀን 2008 ዓ.ም.)። የወቅቱን ሁኔታ ብዙም ያልዳሰሰው የጠቅላይ ሚኒስትሩና የወጣቶች ውይይት. አዲስ አበባ፡ ሪፖርተር ጋዜጣ።

አሰፋ ጫቦ (ሃምሌ 30 ቀን 2008 ዓ.ም.)። ሶስቱ መንግስታት በንጽጽር (ንጉሱ-ደርግ-ኢህአዴግ)። ሪፖረተር ጋዜጣ ሃምሌ 30 2008 ዓም.።

አበባው መሃሪ (መስከረም 13 ቀን 2009ዓ.ም.)። መከፋፈል አያዋጣም አንድ መሆን አለብን። አዲስ አድማስ ጋዜጣ።

ጌታቸው ኃይሉ(እኤአ 2015)። ያልመከተ ተፈነከተ፤ ያልተደራጀ ተፈጀ። ሳተናው ደረ-ገጽ።

የኢትዮጵያ የሽግግር ቻርተር፣ 1983 ዓ.ም. አዋጅ ቁጥር 1፣ አዲስ አባባ

ዮናስ አባይ (2008 ዓ.ም.)፡፡ በአማራ ክልል የተቀሰቀሰው ህዝባዊ ተቃዎሞ ተጨማሪ ቦታዎችን እዳረሰ ነው፡፡ ሪፖ`ርተር፡፡

ጋሻው መርሻ (2008 ዓ.ም.) አንጸባራቂው ኮከብ፡ ጽሮፈሰር አስራት ወልደየስ፡፡ አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ፡፡ ኔባዳን ፕብሊኬሽን፡

ጌታቸው ረዳ (2006 ዓ.ም.)፡፡ የትግራይ ብሔረተኞች በአማራ ላይ ያላቸው ጥላቻ ከምን የመነጨ ነው?" (ጥናታዊ ጽሑፍ)፡፡ ካልኒፎርኒያ፡፡ መረሽ ወገኔ (ተቆርቋሪደ ድርጀት)፡፡

ተስፋ ገብረዓብ (2006)፡፡ የስደተኛው ማስታወሻ፡፡ ኔዘርላንድስ

አልቤርቲ ስባኪ (2002)፡፡ ኢትዮጵያ በኢጣሊያን ፋሽስት የወረራ አመታት፡ 1928-1933 ዓ.ም. አዲስ አበባ፡፡ ትርጉም በእምሻው አለማየሁ፡፡

ባቢሌ ቶላ (1989 ዓ.ም.)፡፡ የትውልድ እልቂት፡ ቀይ ሽብር በኢትዮጵያ፡፡ ኢምፕረስ ማተሚያ ቤት፡፡ አዲስ አበባ፡

ዳኛቸው አሰፋ (ቅዳሜ መስከረም 21 ቀን 2009 ዓ.ም.)፡፡ኹለቱ ታራሚዎች፡፡ አዲስ አድማስ ጋዜጣ ቅፅ 16 ቁጥር 872. አዲስ አባባ፡፡

Aaron Maasho (Augest 8/2016) At least 90 protesters killed in Ethiopia- residents-Opposition.Addis Ababa, Reuters.

Abasa Genemo (1014). Conquest and resistance in the Ethiopian empire, 1880-1974- The Case of Arsi Oromo: African Social Science Series, Neilsen Book Vol.32.

Abinet Hunegnaw (January 2017**).** Mistaken Identity of the Amhara People and the Quest for Organized Resistance Against TPLF Atrocities.

Achamyeleh Tamiru (2016). Forceful Annexation, Violation of Human Rights and Silent genocide: A Quest for Identity and Geographic Restoration of Wolkait-Tegede, Gondar, Amhara, Ethiopia.

Al- Jazeera (29 Sebtember 2014). Al- Jazeera- Amhara Region; not only the poorest in Ethiopia but the world. Available at https://m. www.youtube.com, accessed on 10 Sebtember 2016.

Andargachew Tiruneh (1993).The Ethiopian revolution 1974-1987 A transformation from an Aristocratic to a Totalitarian autocracy. Cambridge: Cambridge University Press.

Assefa Negash (18th of April 2012). Why Have the Amaras Once Again Become Victims of Ethnic Cleansing by TPLF? Amstelveen, the Netherlands.

Assefa Negash (April 2012). Why Have the Amaras Once Again Become Victims of Ethnic Cleansing by TPLF? Amstelveen, the Netherlands.

Berhanu, Girma. (2017).Ethiopia: Intellectual Genocidein the making? The Strong and Pervasive Evidence of Ethnic Inequalities. Advances in Social Sciences Research Journal, 4(13) 133-165.

Dametew Tessema (2017). Crisis Leadership in Ethiopia: A Comparative Analysis on the 1989 Coup D'état and the Post-2016 Protracted Political Instability. International Journal of Scientific and Research Publications, Volume 7, Issue 9. Pp. 180-190.

Ghelawdewos Araia (2016) Beyond Ethnocentric Ideology and Paradigm Shift for a Greater Ethiopian Unity, Tigrai Online, Ethiopian News, April 21, 2016.

Hailemariam Teklu, Alula Sebhatu and Tesfayi Gebreselassie. (2013). Components of Fertility Change in Ethiopia. Further analysis of the 2000, 2005 and 2011 Demographic and Health Surveys. DHS Further Analysis Reports No.80.Calverton, Maryland, USA: ICF International

Henry Aaron Stern (1868) Wanderings among Falashas in Abyssinia: together with a description of the country and its various inhabitants, p. 137.

Joseph-Émile Coulbeaux (1929) Histoire politique et religieuse d'Abyssinie: depuis les temps les plus recules jusqu'a l'avenement de Menelick II p. 11.

Kinfe Abrham (2001) Ethiopia from Empire to Federation

Mekonnon Zelelew, Interview by Kassahun Seboqa, SBS Amharic, News and Features, Australia: 22 APR 2016, Radio.

Mulatu Wubneh (2015). This land is my land: the Ethio-Sudan boundary and the need to rectify arbitrary colonial boundaries. Journal of Contemporary African Studies Vol. 33 , Iss. 4.

Paulos Chanie (2001).The Challenges of the Civil Service Reform in Ethiopia: initial observations.

Paulos Milkias (2011). African in Focus: Ethiopia. Santa Barbara and California: ABC-CLIO, LLC..

Plato (1999). The Republic: The Introduction Book II. Translated by Benjamin Jowett available at http://www.processtext.com/abclit.html.

Prime_minister_Meles_Zenawi_and_Professor_Mesfin_Woldemariam,_About_Amhara_-_YouTube 1990.

Sudan Tribune ((January 17, 2016). Sudan, Ethiopia to complete border demarcation this year. Khartoum.

Sudan Tribune (February 14, 2017).Ethiopia-Sudan border development conference kicks off on Thursday. Khartoum.

Walter Chichele Plowden (1848) Travels in Abyssinia and the Galla Country: With an Account of a Mission to Ras Ali p.39.